የእስር ቤቱ አበሳ

በታላቁ ቤተመንግሥት
(1966 - 1974)

ከአበራ ጅምበራ



ከአበራ ጀምበሬ

የእስር ቤቱ አበሳ

በታላቁ ቤተ መንግሥት

(1966–1974 ዓ.ም)

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የሽፋን ሥዕል፡- ወሰኔ አባይ

1985

በረከት

ለልጆቼ ፡-
ለተመስገን
ለኑርልኝ

ርዕሰ አቅርቦት

1· ተቀላቀሉ 9
2· ያዳቆን ሠይጣን ሳያቀስ አይተውም 13
3· ከድጡ ወደ ማጡ 21
4· የተዳፈነ እሳት 32
5· ሕጋዊ ምላሽ ለሕዝብ ጥያቄ 39
6· እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን 44
7· የሰው ፊት ግርፋት 47
8· ተዘከር እንደኮምፒውተር 52
9· ፀለምት ቅዳሚት 59
10· የዕለት ውሎ 63
11· የእልፍኙ ምሥጢር 81
12· ትውስት 96
13· ቶማስ ወልድ 107
14· ረትዖ መታሰር 137
15· ይቅር በሉኝ 141
16· ሰሙነ ሕማቱት 151
17· መማቀቅ 156
18· ዕድል ፈንታ 169
19· የማይታወቅ የተሰወረ የለም 174
20· አዘክሮት 179
21· የእስረኞች ዝርዝር 180

ማቅረቢያ

በዚህ መጽሐፍ የተካተተው ጸሐፊው በታላቁ ቤተ መንግሥት አስር ቤት ለስምንት ዓመታት ያህል ባሳለፈው ሕይወት የተዘከረው ዕውነተኛ ታሪክ ነው ። በደርግ ዘመነ መንግሥት በየአስር ቤቱ ከደረሰው አበሳ ይህ መጽሐፍ የሚያቀርበው በተጠቀሰው አስር ቤት የተፈፀመው ብቻ ነው ። የሌሎቹም አስር ቤቶች አበሳ ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረው ይችላል ።

በታላቁ ቤተ መንግሥት የዙፋን አዳራሽ የምድር ቤት ዋሻ (ደይን) ውስጥ የተፈጸመውንም ቢሆን በዝርዝር ሳይሆን በጥቅል ነው ለማቅረብ የተሞከረው ። ይህም የሆነበት ምክንያት የዕለት ተዕለቱን ሁኔታ በማስታወሻ ለመያዝ ፍተሻው የማያስችል በመሆኑ ነው ። ስለዚህ ጠቅላላ ትውስቱንና ድርጊቱን ብቻ በአጭሩ በማቅረቡ መወሰኑ የግዴታ ሁኖአል ።

ያንን ዘመን ደግሞ አያምጣውና ያለፈው ለወደፊቱ የመታረሚያ ትምህርት እንደሚሰጥ ተስፋ ይደረጋል ።

ደራሲው

አዲስ አበባ መጋቢት 27 ቀን 1985 ዓ.ም

ብዕሬ ተዘከሪ!

1· ብዕሬ ተዘከሪ ፡ ይገለጥ ምሥጢሩ
ደፋ ቀና እያሉ ፡ ለሀገር በሠሩ
እነማን ተገድለው ፡ እነማን ታሠሩ? ።

2· አይንጠፍ ቀለምሽ ብዕሬ አትሁኝ ብቡ
የእልፍኙ ሰቆቃ ይመዝገብ ባግባቡ
የእስር ቤቱ አበሳም ይገለጥ ለሕዝቡ ።

3· አንች የሐምሌ ሳምንት ሥቃይ የታየብሽ
የሕዝብ ደም እንደጐርፍ በግፍ ፈሰሰብሽ
እንደ እስስት በገመድ አቡን ታነቁብሽ ።

4· በኛስ ባገራችን ልማድ ሆነ ደገል
መንግሥት ተገልብጦ ፡ ሥልጣን ሲደለደል
ሥርዓተ ሕግ ሆነ ፡ ሰው ማሰር ሰው መግደል ።

5· ባገራችን ታሪክ ከጥቁሩ ነጥብ እንዱ
ዘመነ ደርግ ነው አሲቃቂው ጋዱ
ምሁራንም ጠፉ ፡ ወጣቶች ታረዱ ።

6· ለገድለ ሰማዕታት ይሄ ነው መቅድሙ
የታሪክ ጸሐፍትም የጐደለ አርሙ
ለቀጣዩ ትውልድ ታሪኩን አሰሙ ።

7· አሳታሚ ካለ ይወጣል በተራ
ያምሐ ገብርኤል የስርቤቱ ሥራ
ካምሮ ማህፀን ተወልዶ በአበራ ።

ደገል ፡ ቂም ፡ ቂም በቀል ፡ መበቀል

፩

ተቀላቀሉ

ለአካባቢው ባይተዋር ያልሆኑ ሰዎች በታላቁ ቤተ መንግሥት ተሰባስበዋል ። የቤተ መንግሥት ኑሮአቸው ግን አልተመቻቸላቸውም ። ለማረፊያ የተመረጠላቸው በታላቁ ቤተ መንግሥት በዙፋን አዳራሽ ስር የሚገኝ ለወይን ጠጅ ማቀዝቀዣ የተዘጋጀው ዋሻ ነው ። ክረምት ተበጋ እንደበረዶ ይቀዘቅዛል ። አካላቸው በብርድ ተኮማትሮአል ። በቁጭት እንፋሎት ደምስሮቻቸው ተሣተርትረዋል ። መንፈሳቸው ተጨንቋል ። በቁጥጥር ስር የዋሉት ፡ ጊዜ ፊቷን ያዞረችባቸው እነዚህ ሰዎች ንፁህ አየር ለማግኘት ፡ በፀሐይ አካላቸውን ለማሞቅ ፡ የተሳሰሩ እግሮቻቸውን ለማፍታታት በዙፋን አዳራሽ አጠገብ በሚገኝ ፡ በሽቦ በታጠረ ፡ 17 ሜትር በ25 ሜትር በሆነ ጠባብ ክልል ውስጥ ይንከላወሳሉ ። ሁሉም ከሚቀርቧቸው ጓደኞቻቸው ጋር ሁነው ከላይ እታች ይላሉ ። በጭንቀት የተወጠረ ፡ በችግር የተቆራመደ ሕይወታቸው ያሳደረባቸውን ጭንቀትና ምሬት ለመርሳት የቆጥ የባጡን ያወጋሉ ። ያለፈውንና የወደፊቱን ሁኔታ ሲቃኙ ፡ አንዳንዴ ተስፋ ከመቁረጥ ፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከመጽናናት ላይ ይደርሳሉ ።

የአሳብ ቁራኛ ሁነው በዚያች ጠባብ ግቢ ሲንከላወሱ ነበር በመጋቢት 3 ቀን 1968 ዓ·ም ከእኩለ ቀን በኋላ ታላቁ መንፈሳዊ አባት ሁለት እጆቻቸው በአንድ ላይ በሰንሰለት ታስረው እየተገፈተሩ ፡ ያለመጫሚያ በባዶ እግራቸው ሲመጡ የተመለከቱትና ባሉበት ክው ብለው የቀሩት ። በዚህ ወቅት ነበር አንዱ እስረኛ ልቡ ተነክቶ "አዲዮስ የኢትዮጵያውያን ሰብዓዊነትና መንፈሳዊነት !" ያለው ፡ እኒያ የተከበሩና የታፈሩ መንፈሳዊ አባት እንዲያ ሲጉላሉና የኢትዮጵያዊ የጨዋነት ባህሪ

እንዲህ ተሟመ በማየቱ አስፈሪ ጊዜ መምጣቱ ተሰምቶት ።

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብረ ገብነትና መንፈሳዊነት በእነዚህ ጋጠወ ጮች አይለካም" አለ ሴላው ፣ በድርጊቱ መብገኑን ሁኔታው እየነገረበት ።

"ካህኑን እንደ ፖለቲከኛ ፣ መንፈሳዊ አባቱን እንደወንጀለኛ የሚመ ለከት ወታደራዊ ቡድን በዚች ቅድስት ሀገር መነሳቱ ያሳዝናል ! መንፈሳዊ አባት በማፍ ሲንገላታ ከማየት ሞት ይመረጣል !" አለ ሴላው በመበሳጨት ።

የአደፈ ቹሮአማ ቀሚስ እንደለበሱ ፣ ከቀኝም ከግራም ፣ ከኋላም ሳንጃ የተሰነዘበት ጠበንጃ ተደግኖባቸው ወደዚያች የፖለቲካ አስረኞች መቀየጃ ቅጥር ግቢ ሲገቡ መንፈሳዊ አባቱ "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት ግፍ ለሚፈጽሙባቸው የሚጸልዩ እንጂ የተበሳ ጩና የተሸበሩ አይመስሉም ነበር ።

አስረኛው ከድንጋጤው ገና ሳይላቀቅ ፣ ምን እንደሚልና እንደሚያ ደርግ አሰላስሎ ሳይጨርስ ፣ ከቆመበት ሳይላወስ ነበር ከእንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ አስገብተው የቆለፉባቸውና እግራቸውን በእግረ ሙቅ ፣ እጃቸውን በሰንሰለት ጠፍረው ያሰሩዋቸው ።

"ይህን አዚመኛ ቂስ ተጠንቅቃችሁ ጠብቁ" በማለት ለወታደሮቹ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶ የዘቡ አዛዥ ከአጥሩ እንደወጣ ነበር አስረኞቹ ሰእታቸውን አይተው ለዐሐይ መሞቂያና ለአየር መቀበያ የተወሰነው ጊዜ ማብቃቱን የተረዱትና ወደ ጉርፍእሙ ማዝገም የጀመሩት ። የእግዜ ሩም አየርና ዐሐይ በሰው የሚቆጠብ ፣ በስለትም የማይገኝ ሆነባቸው። የማንኛውም ንገር ዋጋ የሚታወቀው በመታጣቱ ፣ እንዲያም ሲል ተቆጥቦ በመሰጠቱ መሆኑ ለእስረኞቹ ከታወቃቸው ውሎ እድሮአል ። ያች የሚሳሱላት የዐሐይ መሞቂያ ጊዜ ፣ ያች በኢንተርናሽናል ቀይ መስቀል ኮሚቴ አሳሳቢነት በቀን ከግማሽ ሰዓት ወደ አንድ ሰዓት ተኩል የተራዘመችው ጊዜ ተገባዳ እስረኞቹ ወደ መቀየጃ ዋሻቸው የገቡት በዓዩት አዝነው ፣ በጊዜው ሁኔታ ፈጽሞ ተስፋ ቆርጠው ነበር ።

በዚያች ዕለት ማምሻውን አስረኛው ሁላ በየክፍሉ የአደረገው የማኅበርና የማል ፀሎት ከወትሮ በበለጠ እንባ የታከለበት ፣ ትሁት ልቡና የተሰበረበት ነበር ። በመንግሥት ሰዎች ሳይሆን በመንፈሳዊ አባትም ላይ የግፍ ግፍ ሲፈጸም በመታየቱ ዘዘኑ ተበራከተ ። የባሰ እታምጣ ከማለት ሴላ አማራጭ ልመና የሚቀርብበት ወቅት መስሎ የታየው ሰው

አልነበረም ።

መንፈሳዊ አባቱ የታሰሩባት ክፍል በግማሽ የአሳሪዎች ምልልስ ታየባት ። ሹማምንት በመፈራረቅ ጉበኟት ። ፈንጠር ፣ ፈንጠር ፣ ቀበጥበጥ ብለው እንዳልገቡ ፣ ተስፋ ቆርጠው ሲወጡ ተስተዋሉ ። ይህ ሁሉ ምልልስ ፣ ይህ ሁሉ ጋጋታ የተከሰተው በእንድ ክፍል ውስጥ እግር እጃቸው ከአልጋ እግር ጋር የታሰረው መንፈሳዊ አባት "ምግብ አልበ ላም" ብለው በመወሰናቸው ነበር ። ሻለቃ ዳንኤል አስፋው እና ሴሎቹ የእስር ቤቱ ኃላፊዎች የሚመጣላቸውን ምግብ እንዲመገቡ ለማድረግ ቢሞክሩም ቆራጡ አባት አልተበገሩም ። ከዚህ በኋላ ነበር ምግብ አልበላም በማለት ማስቸገራቸውን በመግለጽ ሻለቃ ዳንኤል ለደርግ የፀጥታ ጥበቃ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ባቀረበው ማስታወሻ ግርጌ ላይ "ምግብ እንዲገባላቸው አድርጉ እንጂ ፣ ባይበሉ የራሳቸው ጉዳይ ነው" ሲል ሻለቃ ተካ ቱሉ ምልክት ያደረገው ።

የእስረኛ ላለመመገብ መወሰን ለሰብዓዊ መብት መከበር በሚታገል ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ሁካታ ያስነሳል ። በዓለም አቀፍ መድረክ ብርቱ ንቅፌታ ያስከትላል ። ስለዚህም ኃላፊነት የሚሰማው መንግሥት በጣም የሚሰጋበት ጉዳይ ይሆናል ። ሻለቃው "ባይበሉ የራሳቸው ጉዳይ ነው" ያለው ይህን አጥቶት ይሆን ወይስ እርሱም ሆነ ሌሎቹ ግብረ አበሮቹ ለሕዝብ አስተያየት ምንም ዓይነት ከበሬታ የማይሰጡና ደንታም የሌላቸው በመሆናቸው ?

እኒያ አዛውንት በዚያች መስኩት በሌላት ጠባብ ክፍል ምግብ ብቻ ሳይሆን ንፁህ አየርም ሳያገኙ ሰባት ቀን ጠማቸውን ሙለው እደሩ ። ከዚያ በኋላ ነበር ሌሎቹ እስረኞች አማባብተው ምግብ እንዲበሉ እንዲያደርጉ ለእንድ ቁጥር ክፍል ኃላፊ ትእዛዝ በመስጠት አሳሪዎቻቸው ከሰው እንዲቀላቀሉ ያደረጉት ። እግር እጃቸው ከብረት ተላቆ ከመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ጋር ተቀላቀሉ ። ለፀሎት እንዲያመቻቸውም ወደ ሁፋን አዳራሽ በመግቢያው ዋና በር ደረጃ ስር የሚገኘው ጉረና ለእርሳቸው መኝታ ተለቀቀላቸው ። በእንድ ቁጥር ክፍል ውስጥ የሚገኙት አስረኞች በተለይም ብ ጄኔራል ሳሙኤል በየነ አትማቸው በፈቀደ መጠን የሚጉድ ለውን እሚልተውና አንጥፈው ተቀበሉዋቸው ። ምግብ ሲያቀርቡላቸው ግን "እግዚአብሔር ይስጣችሁ ፣ አልበላም" የሚል ሆነ መልሳቸው ። የደረቀ ጉሮሮአቸውን በውሃ እየተጉመጠመጠ በመትፋት ብቻ ምግብ

ሳይበሉ ፡ ውሀ ሳይጠጡ መጾሙን ቀጠሉ ። ጠንካራነታቸውን አስመሰከሩ። የመንፈስ ብቻ ሳይሆን አካላዊ ምግባቸውም ጾም ፡ ጸሎት ሆነ ። የዕለት ተዕለት ሁኔታቸውም ለሌሎቹ አስረኞች መንፈሳዊ ፅናት ሰጠ ። ወራቱም የአቢይ ጾም ወቅት በመሆኑ ሱባኤው በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ በእግዚአብ ተጠናከረ ። ለፍትህ ፡ ለሰብዓዊ መብት መከበር ተፀለየ ። የሁሉም ምኞት ፍጻሜውን ያሳምርልን የሚል ሆነ ።

፱

ያዳቆነ ሠይጣን ሳያቀስ አይተውም

ታላቁ ቤተ መንግሥት ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የሥልጣን ማዕከል ሁኖ አገልግሎአል ። በኢትዮጵያ ታሪክ በመጀመሪያ የስልክ መስመር የተዘረጋው ፡ የኤሌክትሪክ ብርሃን የገባው ፡ ሙሀ በቧንቧ ከምንጭ የተሳበው ፡ የከተማዋ ዋና ዋና መንገዶች ያመሩት ወደዚሁ ቤተ መንግሥት ነበር ። ንጋሪት የሚጐሰመው ፡ አዋጅ የሚነገረው ፡ ሹም ሽር የሚደረገው ፡ የመጨረሻ ፍርድም የሚሰጠው ፡ የተንበሸበሸ ግብር የሚበላው በዚሁ ቤተ መንግሥት ነበር ።

የዚህ ቤተ መንግሥት ግርማ ሞገስ የተቀነሰበት ዘመን ቢኖር ፡ በጠላት የወረራ ዘመናትና ከነፃነትም በኋላ የግብር አዳራሹ ከመጋዘንነት እስኪፀዳ ድረስ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ብቻ ነበር ። ከነፃነት በኋላ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በመጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ·ም በክብር ስፍራዋ እንደገና እንድትውለበለብ የተደረገው በዚሁ በታላቁ ቤተ መንግሥት ነበር ። ይህ ቤተ መንግሥት የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ግቢ በመባልም ይታወቃል ።

ታላቁ ቤተ መንግሥት የታነፀበት ስፍራ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ አዳጋ ቦታዎች ሁሉ ይበልጥ ከፍ ፡ ላት ፡ ኮራ ብሎ የሚታይ ነው። ስለዚህ ከቤተ መንግሥቱ ምድረ ግቢ ሁኖ በአራቱም ማዕዘን ቢመለከቱ የከተማዋን የየትኛውንም ክፍል በውል ማየት ይቻላል ። አዲስ አበባ በተቆረቆረችበት ዘመን የከተማዋ እምብርት ይኸው ቤተ መንግሥት ነበር ። መኳንንቱና ወይዛዝርቱ ፡ ዲፕሎማቱ ፡ ነፍጠኛው (ወታደሩ) እና ነገረተኛው ፡ ሥራ ቤቱና ባለሟሉ ፡ ልጅና አዋቂው ይርመሰመስበት በነበረው ምድረ ግቢ መካከል የሚገኘው ሕንፃ የዙፋን አዳራሽ ተብሎ

የተሰየመው ነው ። የንጉሠ ነገሥቱም ዙፋን የተዘረጋው በዚሁ አዳራሽ መካከለኛው ክፍል ውስጥ ነው ። የቤተ መንግሥት ታላላቅ ሥነ ሥርዓቶች የሚከናወኑት በዚሁ አዳራሽ ውስጥ ነበር ።

ይህ የዙፋን አዳራሽ ነበር በዘመነ ደርግ ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው ።በርቱ ላይ ከሚገኙት ክፍሎች ዋናው የዙፋን ክፍሉ ነበር የደርግ አባሎች መሰብሰቢያ የሆነው ፣ ክቡም ሆነ በጉ የሚመክርበት ፣ ሲያሰኝም የፖለቲካ ውሳኔ ወይም የፖለቲካ እርምጃ ትእዛዝ የሚሰጥበት። የዚሁ ሕንፃ አንደኛው ክንፍ ነበር የውጊያ እዝ የሚመነጭበት የካርታ ክፍል የሆነው ። ሌላው ክንፍ ደግሞ ሻልዩ ጦር ፍርድ ቤት ማስቻያነት ነበር የተመደበው ። የዚህ አዳራሽ ምድር ቤት ነው ለእስር ቤትነት የተመረጠው ።

ከዙፋን አዳራሽ ሕንፃ ወደ ደቡብ ጥቂት ወረድ ብሎ ቀድሞ ግብር ይበላበት የነበረው ትልቁ አዳራሽ ይገኛል ። በቤተ መንግሥቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኙት ሕንፃዎች ሁሉ ብዙ የሚወራለት ፣ ብዙዎች በልዩ ትዝታ የሚያስታውሱት ፣ እስከ ሶስት ሺህ ሰው የሚይዘው ሞላላው አዳራሽ ነው ። በዚያ አዳራሽ ከጠላት ወረራ በፊት ግብር የሚበላው በአዘቦቱ ቀን በቀን አንድ ጊዜ ፣ በበዓላት ዕለት ደግሞ ከአንደኛ እስከ ሶስትኛ ዙር ነበር። ግብር የሚገቡትም መኳንንቱ ብቻ ሳይሆኑ ፣ ጭፍሮቻቸውና ደጅ ጠኚዎችም ነበሩ ። ጥሩ ከመናኛ ምግብ ለመብላት ፣ ጠጅና ጠላ ለመጐንጨት ፣ ጮማ ከጉላንጅ ለመቁረጥ ፣ ጋራ ከነጩ አቀላቅሎ ፣ ሙዳ ሥጋ ጨምሮ በለበሱት ነጠላ ቋጥሮ ለመውጣት ወራዊቱና ደጀጠኝው ወደ አዳራሹ ለመግባት ቀደም ብሎ ይኮለኮላል ። የመግቢያው ሰዓት ሲደርስ ደግሞ ቀድሞ ለመግባት መጋፋት ፣ ከአጋፋሪ ምቹ ልምጭ ለማምለጥ መሽሎክሎክ ፣ ጣትን በጥላሎት አውዝቶ ፣ እስትንፋስንና ልብስን በጠጅ ሽታ እያወዱ ለመውጣት መጣጣር የዘወትር ትዕይንት ነበር ። ስለዚሁ የተሳትፎ ግዕድ የሰማ ፣ ከወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የመጣ አንድ ሰው ለግብር ከአሰፈሰፈው ሰው መካከል ገብቶ ሲኮለኰልና ሲጋፋ ቆይቶ ከአዳራሹ ደፍ አጠገብ ሲደርስ አጋፋሪው በእርጩሜ ሽንቆጥ ሲያደርገው ነበር “ኤ ! ኮሰቶ አቤራቲር?” ብሎ የዘበተው ፣ “ይህ አፕሬቲቭ መሆኑ ነው እንዴ?” ለማለት ።

በዙፋን አዳራሽ ምዕራብ በኩል ለዓይን የሚጋርድ ነገር ባለመኖሩ አሻግሮ ሲመለከቱ ቆርቆሮ ክዳናቸው የዛገ ቤቶችና አልፎ ፣ አልፎ

ዘመናዊ ሕንፃዎች ይታያሉ ። በዙፋን አዳራሽ በስተሰሜን የቀድሞው የጽሕፈት ሚኒስቴር ቅጥልጥል ሕንፃዎች ፣ በስተምሥራቅ ደግሞ የእንቁላል ቤትና የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ እልፍኝ የሚባለው ሕንፃ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛሉ ።

የእንቁላል ቅርፅ ያለው ፣ በጥንታዊ የቀለም ቅብ ፣ በሐረግ ያጌጠው የእንቁላል ቤት የሚባለው ባለእንድ ደርብ (ፎቅ) አንስተኛ ሕንፃ በዚሁ ግቢ ከፍተኛ ቦታ ላይ ጉብ ብሎ ይታያል ። በዘመነ ምኒልክ ሕንፃው ያገለግል የነበረው በስልክ ቤትነት ነበር ። አጼ ምኒልክ በየከፍለ ሀገሩ ከሚገኙ እንደራሴዎቻቸው ጋር “እገር እንዴት አደረ ፣ ሕዝብ ምን አለ ፣ እረኛ ምን ዘፈነ?” እያሉ የሚጠይቁትና ሌላም ፣ ሌላም በስልክ ይነጋገሩ የነበረው ከዚህ ሕንፃ ነበር ። በሕንፃው ሰገነት ላይ ቁሞ በየትኛውም አቅጣጫ ሲመለከቱ ፣ ሁሉንም ቁልቁ አድርጉ ስለሚያሳይ ፣ አጼ ምኒልክ ነፋስ ለመቀበልና በየመኳንንቱ ግቢ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለመመልከት ፣ በዕየለቱ ብቅ ማለትን ያዘወትሩ ነበር ። ጋሻ ከጓዝ ፣ መስቀል ከሰላጤ እያደረጉ የከተማ ቦታ በሰፈው የመሩዋቸው ፣ ግዛት ከሁዳድ አቀናብረው የሰጡዋቸው ሰዎች ጭፍሮቻቸውን ግብር ያበሉ እንደሆነና እንዳልሆነ የሚያጣሩት ከመኳንቶቻቸው ማዕድ ቤት የሚወጣውን ጪስ በመመልከት ነበር ። ሠራዊቱ የማይሰበሰብበትንና ጪስ ያለማቋረጥ የማይተንበትን ግቢ ባለቤት በንፉግነት ይታዘቡት ፣ ብቻውን በመብላቱ ከሹመቱም ይሽሩት እንደነበረም ይነገራል ።

ከእንቁላል ቤት አጠገብ የንግሥት ዘውዲቱ አልፍኝ የሚባለው ሕንፃ ይገኛል ። ያ ሕንፃ ነበር ስመ ሚመታቸው “የነገደ ይሁዳ አንበሳ አሸነፈ” በሚል ትዕምርተ ጥቅስ የአሸበረቀው ፣ የዕድሜ ባለፀጋው አዛውንት የመቆያና የመጨረሻ ማረፊያ የሆነው ። ሕንፃው ከመካከል አንድ ሰፊ ክፍልና ሁሪያውን ደግሞ ሌሎች አነስተኛ ክፍሎች አሉት ። ግንቡ የመድፍ ካልሆነ በቀር የጠበንጃ ጥይት የማይደፍረው ወፍራም ግድግዳ ነው ። ምንጊዜም የሚቀዘቅዝ ክፍል ነው ። በቂ ብርሃንም የለውም ። እስከ 1967 ዓ·ም· ድረስ ይህ ሕንፃ ለዓመታት የግቢ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ነበር ።

በ1967 ዓ·ም ነበር ይህ ሕንፃ ሌት ተቀን በጥብቅ የሚጠበቅ ፣ ግቢ ውጭዎቹም ቁጥራቸው የተወሰነ ፣ በነጋ በጠባም የሚፈተሹ የሆነው ። እንደልብ የሚገቡ ፣ የሚወጡ ቢኖሩ የዕለት ሁኔታ የሚከታተሉ ፣ በልዩ

ልዩ ዘዴ ንገር ለማውጣጣት የሚጥሩ የዘመኑ ባለሥልጣኖችና ታማኞቻቸው ብቻ ነበሩ ።

በዚህ ሕንፃ አጠገብ የሚገኘው ሌላው ቤት "ሳንቃ ቤት" የሚባለው አነስተኛ ቤት ነው ። ይህ ቤት ቀድሞ ልዑል ራስ ተፈሪ መኩንን ከላይኛው ግቢ (ከገነተ ልዑል) ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሲመጡ ያርፉበት የነበረ ሲሆን ፡ የግድግዳው እንጨት በሽክም ከጫር እገር መጥቶ የተሠራ ፡ ለዘመናት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውኖ ያገለገለ ነው ። ይህ ቤት ብዙ ተመክሮበታል ፡ ተዘክሮበታልም ። በ1967 ዓ·ም ግን በመጀመሪያ ለልዩ የጦር ፍርድ ቤት የአቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤትንት ፡ በኋላ ደግሞ ለዘመኑ ባለሥልጣኖች የኮሚቴዎች መሰብሰቢያ እንዲውል ተደርጓል ።

ከዚህ ቤት ጥቂት ወረድ ብሎ "ቶጆ" የሚባለው እንበሳ ከሚታሰር በት አጠገብ ፡ ቀድሞ የንጉሠ ነገሥቱ የእፄ ኃይለ ሥላሴ ጽሕፈት ቤት የነበረው ፡ በአንድ በኩል ምድር ቤት ያለው ፡ ከግድግዳው ከፊሉ በሞታ የተመረገ ፡ ከፊሉ ሸክላው በእሸዋ የተገረፈ ቤት ይገኛል ። ይህ ቤት ነው በ1967 ዓ·ም የአዲሱ ርዕሰ ብሔርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ጽሕፈት ቤት ውኖ ፡ ጦር ይንቀሳቀስ ፡ እገሌ በቁጥጥር ስር ይዋል ፡ እገሌ ይገደል የሚለው ትእዛዝ ይመነጭበተ የነበር ። ምን ይህ ብቻ ! በዘመነ ደርግ እንድ ክንፉ የመቃብር ቤትም ውኖ ነበር ፡ ያልታወቀ መቃብር !!

በ1967 ዓ·ም በጥቢያው ወራት ነበር እነዚህ በቤተ መንግሥቱ ምድረ ግቢ ውስጥ የሚገኙት ሕንፃዎች ለተለያየ አገልግሎት በደርግ የተደለደሉትና ግቢውም ደርግ የመሸገበት የጦር ሠፈርና የፖሊቲካ አስረኞች የሚሰቃዩበት የሆነው ።

መንግሥታዊ ሥልጣንን ሙሉ በሙሉ ከመያዙ በፊት ነበር ደርግ ሥራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁት የካቢኔ አባሎችና ሌሎች የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ እንዲደረግ የተጠየቀውና በሥልጣን ላይ ከሚገኘውም አዲሱ ካቢኔ አባሎች የሚበዙት ጥያቄውን ለመቀበል የተስማሙት ። የመክላከያ ሚኒስትሩ ሌ ጀኔራል ዓቢይ አበበ ነበሩ የቀድሞዎቹ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችና ሌሎች ባለሥልጣኖች በአንድ ስፍራ እንዲጠበቁ የሚደረግ ከሆነ ተስማሚ ቦታ ተመርጠ ፡ ምግብ ከኢትዮጵያ ሆቴል በመንግሥት ሂሳብ እየተመላለሰላቸው ለጊዜው በአንድ የተወሰነ ስፍራ እንዲቆዩ

ይደረግ ዘንድ አሳብ ያቀረቡት ። የእርሳቸውም አሳብ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረው "የጥያቄ አቅራቢዎቹን አዝማሚያ እንደተመለከትኩት ከሆቴል በመንግሥት ሂሳብ ምግብ ይመላለስላቸው ቢባል ነገሩ ይባባሳል" ሲሉ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹመ፡ በሰነዘሩት አስተያየት ምክንያት ነበር ። የቀድሞዎቹ ሚኒስትሮች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ የቀረበውን አሳብ ወደመቀበሉ ካቢኔው ያዘነበለውም ከቀድሞዎቹ ሚኒስትሮች አንዳንዶቹ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር በመቃወም በሚያሰሙት ነቀፌታ በመገፋፋት ጭምር ነበር ።

ንጉሠ ነገሥቱም ነገር የሚበርድ መስሎአቸው በቀረበላቸው አሳብ መሠረት ከቀድሞዎቹ ሚኒስትሮች በየቤታቸው የተገኙትን አስጠርተው እጃቸውን ለጦሩ እንዲሰጡ ሚያዝያ 18 ቀን 1966 ዓ·ም አዘዙ ። የቀድሞዎቹ ሚኒስትሮችም የንጉሠ ነገሥቱን ጥያቄ በፀጋ እንዲቀበሉ ሲያግባቡ "ውሻ ሲሥሀ አጥንት ይጥሉለታል" ሲሉ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ፡ አዲሱ የግቢ ሚኒስትር በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ተረቱ ። በዚያ ቅፅበት ነበር ተናግረው ማንንም የማያስቀይሙት አቶ ጌታሁን ተሰማ "ለውሻ እንደሚጣል አጥንት እምንቆጠረው እኛ ነን እንዴ!?" በማለት ከፍ ዝቅ አድርገው ደጃዝማቹን የገረመሙት ።

"ጃንሆይ ፡ እኛን አሳልፎ በመስጠት በሥልጣን ላይ ለመቆየት አስበው እንደሆነ ተሳስተዋል" በማለት አይን አፋሩ ጸሐፈ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ የቀናገሩትና ይህን ንዴት የተመላበት ኃይለ ቃል በመናገር ፡ ንጉሠ ነገሥቱን ከፈታኝ ሁኔታ ላይ የጣሉት በዚሁ ወቅት ነበር ።

ተቃውሞአቸውን ከገለጹ በኋላ የሚከላከልላቸው በማጣታቸው በሥልጣን ላይ ያለው የልጅ እንዳልካቸው መኩንን ካቢኔ አባል ከሆኑት በቀር ሌሎቹ ሚኒስትሮች አብዛኛዎቹ በዚያው ዕለት ነበር እጃቸውን የሰጡትና ከየቤታቸው በወታደር እየተለቀሙ ጉፋ ሠፈር በእሥራ ሰባተኛ ሻለቃ ጦር የመኰንኖች ክበብ ውስጥ የታሰሩት ።

ደርግ የመጀመሪያው ሙከራው ሲቃናለት የንጉሠ ነገሥቱ የልጅ ልጅ የሆኑት ራር አድሚራል እስክንድር ደስታ ከኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት እጃቸውን እንዲሰጠው ጠየቀ ። በዚያን ወቅት ደርግ "ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም ፡ አቆርቋዥዋ ይውደም" የሚል መዝሙር በመገናኛ ብዙሃን ባሰማ ቁጥር ማንም ከምልከታችን ውጭ

አይሆንም ለማለት ፣ ከሶማሊያ የቀዳውን ፣ የአንድ የአተኮረ ዓይነ ምልከት በቴሌቪዥን ያሳይ ነበር ። በዚያው ሰሞን ነበር የንጉሠ ነገሥቱን የልጅ ልጅ ከጉያቸው ፈልቅቆ ለመውሰድ ሲጠይቅ "እንደሚያሳየው እርግ ደርግ አውንስ ዓይን አወጣ" ሲሉ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ በጨዋታ መካከል ለዚህ ጸሐፊ የነገሩት ። ከምራቸው ይውን ወይም ለቀልድ የተናገሩት እንደሆነ ግን አይታወቅም ።

የደርግ እንቅስቃሴ አሳምር እያለ በመሄዱ በአዲሱ ካቢኔና በደርግ መካከል የሥራ መግባባት ለመፍጠር ካቢኔው በጋራ ኮሚቴ አባልነት በሰየማቸው ሚኒስትሮች አማካይነት የአድሚራሉን መታሰር ለማስቀረት ተሞክረ ። ደርግ ግን አሻፈረኝ አለ ። በማስከተልም የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ አገልጋይ የሆኑትን ፣ የልዩ ግምጃ ቤታቸውን ሹም ብላታ አድማሱ ረታንና ዋናውን የልፍኝ አስከልካይ ሌ/ጀኔራል አሰፋ ደምሴን ከቤተ መንግሥት አስገድዶ ወሰደ ። በተከታታይም እንደዚሁ የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን ፣ የሌሎችንም የመንግሥት ሹማምንት ስም እየጠራ እጃቸውን በፈቃዳቸው እንዲሰጡ ፣ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ባይሰጡ ግን ንብረታቸው እንደሚወረስ በራዲዮና በቴሌቪዥን ማስታወቁን ተያያዘው ። በዚያን ሰሞን የእጅህን ስጥ ማስታወቂያ በጋዜጣ ተከታትሎ ስለወጣ በፍርድ እንወጣለን በሚል እምነት በጥሬው መሠረት ብዙዎች እጃቸውን ሰጡ ።

እጁን አልሰጥም በማለት ከነወንድማቸው ተታኩሰው የሞቱት በ1953 ዓ·ም የኩ ደኤታ ሙከራ ጊዜ ሬሳቸው በአራተኛ ክፍለ ጦር በራፍ ላይ ተዘርሮ እንዲታይ እንደተደረገው እንደ ብርጋዴር ጀኔራል ጽጌ ዲቡ ሬሳ ሁሉ በዚሁ ስፍራ ሬሳቸው በደርግ ለትዕይንት የቀረበው ደጃዝማች ፀሐዩ እንቆሥላሴ ነበሩ ። ደርግ በማስታወቂያ በመጥራት ብቻ አልተወሰነም ። ሊታፈርና ሊከበር የሚገባውን ፓርላማ በታኅከ አስከብቦ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ፣ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወትን በማስገደድ ሰኔ 24 ቀን 1966 ዓ·ም ከምክር ቤት ሲወሰድ ደርግ ለሕግ ልዕልና ምንም ከበሬታ እንደሌለው ተረጋገጠ ።

የሕገ መንግሥታዊ መንግሥቱን ሥልጣን ቀስ በቀስ በመቦርቦር ላይ እያለም ደርግ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ እንደሆነ ለማስመሰል ያምታታና ከካቢኔውም ጋር አብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ መስሎ በመታየት በጋራ ኮሚቴው አማካይነት ይደራደር ነበር ። የልጅ እንዳልካቸው

ካቢኔ በእንግሊዝ አገሩ አጠራር "ጓይት ፔፐር" ማለትም "ንጭ ወረቀት" በሚል ርዕስ ባዘጋጀው የመንግሥቱ ፖሊሲ አቅጣጫ አመልካች ሰነድ ይዘት ላይ ደርግ ተወካዮቹን እየላከ ይነጋገር ነበር ። በመንግሥት በኩል የኮሚቴው አባሎች ቋሚ ሲሆኑ ፣ የደርግ ተወካዮች ግን በየስብሰባው ይለዋወጡ ነበር ። በካቢኔው በኩል የተወከሉት ፣

1/ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ
2/ አቶ በለጠ ገብረ ጻድቅ
3/ አቶ ተካልኝ ኀዲሙ
4/ አቶ ጌታቸው በቀለ
5/ ፊታውራሪ (በኋላ አቶ) ደምሴ ተፈራ ሲሆኑ ፣

በደርግ በኩል በጋራ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ አብዛኛውን ጊዜ ይገኙ የነበሩት ፦

1 ሻለቃ ናደው ዘካርያስ
2/ ሻምበል ሚሳይ ሀብቴ
3 ሻምበል ደምሴ ዱሬሳ
4 ጢቲ አፈሰር ታምራት ፈረደ
5 ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል
6 የመቶ አለቃ ዓለማየሁ ታይሌ ነበሩ ።

በመጨረሻም በተደረገው የጋራ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ከካቢኔው ለደርግ የቀረበው አማራጭ በተዘጋጀው የፖሊሲ መመሪያ መሠረት ካቢኔው አስፈላጊውን መሻሻል እንዲያደርግ ፋታና ዕድል ተሰጥቶት ፣ ጦሩ ፀጥታ በማስከበር ብቻ እንዲወሰን ፣ ወይም የደርግ አባሎች የተወሰኑ ሚኒስቴሮችን ፖርትፎልዮ ይዘው (ሚኒስትር ሁነው) በጣምራ በመሥራት የታቀደው ከግቡ እንዲደርስ በማድረግ ሽግግሩ እንዲሰምር እንዲስማማ ነበር ። ዓላማው ሌላ በመሆኑ ደርግ የትኛውንም አማራጭ አልተቀበለም ፣ ወይም ሌላ ማማረጫ አሳብ አላቀረበም ። በየጊዜው ተለዋዋጭ አሳብ ወይም ጥያቄ ይዞ በመቅረብ ግን ሚኒስትሮቹን ግራ ሲያጋባ ቆየ ። በመጨረሻ በመዘጋጀት ላይ ያለውን የሕገ መንግሥት ረቂቅ ሳያፀድቁ የፓርላማው አባሎች ለእረፍት እንዳይሰናበቱ እንዲደረግና በመሰ ጠቅላይ ግዛት የደረሰውን ሪሀብ በመረባረብ ለመቋቋም ይቻል ዘንድ ግዛቱን በወታደራዊ አስተዳደር ስር የሚያደርግ አዋጅ እንዲታወጅ ጠየቀ ። በጥያቄውም መሠረት ፓርላማው በሥራ ላይ እንዲቆይ ተደረገ ።

በዚሁም ወቅት አዲሱ ሕገ መንግሥት በሚፀድቅበት ጊዜ በቶሎ ተፈጻሚ ለማድረግ መንገድ ለመጥረግ ሲባል ፣ ፀንቶ ባለው የ1948 ዓ·ም ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 131 "ይህ ሕገ መንግሥት በሁለት ጊዜ የስብሰባ ወራቶች ውስጥ የፓርላሜንቱ የያንዳንዱ ምክር ቤት አባሎች ከአራት እጅ ሦስቱ እጅ ተስማምተውበት በሚወስኑት በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድና ሥልጣን በሚታወጀው ባንድ ዐይነት ውሳኔ ሊሻሻል ይቻላል" የሚለው በእዋጅ ተሻሻለ ። የወሎ ጠቅላይ ግዛትም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀበት ክልል ሁኖ በወታደራዊ ሹማምንት እንዲተዳደር ተደረገ ። በሰላማዊ (ሲቪል) ሹማምንት ፈንታ ወታደራዊ መኰንኖች ከጠቅላይ ግዛቱ እስከወረዳ ግዛቶቹ ድረስ ተሾመበት ።

ስንዝር ሲሰሙት ክንድ የሚጠይቀው ደርግ በተደረገው ሁሉ አልረካም ። የንጉሠ ነገሥቱንና የመንግሥቱን የኃይል ጥንካሬ ሲፈታተን ቆይቶ በነሐሴ ወር 1966 ዓ·ም እንደ ጽሕፈት ሚኒስቴር ፣ የዘውድ ምክር ቤት ፣ የሁፋን ችሎት ፍርድ አጣሪ ያሉትን መሥሪያ ቤቶች አፈረሰ ፣ መሠሪ ፕሮፓጋንዳውን በመቀጠል ንጉሠ ነገሥቱን ተፈታተኑ ፣ ያዳቆን ሠይጣን ሳያቀስ አይተውም እንዲሉ ።

፫
ከድጡ ወደ ማጡ

የመስከረም ደመና በኢትዮጵያ ሕዋ ላይ አንጎባሏል ። የንጉሥነት ድምፅ በየስፍራው ይሰማል ። የተፈጥሮ ሕግን ተከትሎ አደይ አበባው በየመስኩና በየተራራው ፈንድቶ ቢጫ ሥጋጃ የተነጠፈበት አስመስሎታል ።

ለዘመን መለወጫ ሁሉም እንደየአቅሙ ደግሷል ። በዋዜማው ችቦ በየቤቱ ተበርቶ "እዮሀ አበባዬ ፣ መስከረም ጠባዬ" ተብሎ ተዘምሮአል ። "የጉመን ምንቸት ውጣ ! የነገር ምንቸት ግባ !" ተብሎም ተመርቋል ። ልባዊ ባይሆንም አፍአዊ ደስታ በየቤቱ ይሰማል ፣ አዲሱን ዓመት በፍስሐ ለመቀበል ሁሉም ጥረት ያደርጋል ። በዚያን ዕለት ደመና ያጠላበት ፣ በታንክ የተከበበውም የኢዩቤልዩ ቤተ መንግሥት ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱን "እንኳን ለአዲሱ ዓመት በደህና አደረሰዎት" ለማለት ወደ ቤተ መንግሥቱ ጉራ ያሉት ፓትርያርኩ ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ብቻ ነበሩ ።

በመስከረም ፩ ቀን 1967 ዓ·ም ማታ ነበር "ለአዲሱ ዓመት ገጸ በረከት የወሎን እልቂት ፊልም እንዲያዩ ንጉሠ ነገሥቱን ጋብዘናቸዋል" ሲል ደርግ ድምፁን በቃለ አዋዲው አማካይነት ያሰማውና የተቀነባበረ ሐተታውን ያቀርንዶደንዶው ። በማግሥቱም ከሥልጣን እንዲወርዱ መወሰኑን ለመግለፅ ሻሊቃ ደበላ ዲንሳ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት በመቅረብ በደርግ ስም ንግግር አደረገ ። ሰንግግሩ መልስ ሲሰጡ ነበር ፦

"በየጊዜው የሚለዋወጠው ነገር ደግሞ ለሀገር የሚጠቅም ነገር እስካለበት የአገርን ጥቅም በበላይነት ለመለወጥ አይቻልም" ያሉት ንጉሠ ነገሥቱ ። ከዚያም በሁዋላ በታሳቢነት በስፍራው በተገኙት

በልውል ራብ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ላይ ዓይናቸውን ጣል አድርገው ወደ ተፈለጉበት ቦታ ለመሄድ ከኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ወጡ ። በእንድ ትንሽ አሳቻ ቮልስዋገን አቶሞቢል ውስጥ ገብተው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ሠፈር ተወሰዱ ። በየመንገዱም ለዚሁ ተብሎ በቅድሚያ በተኮለኮሉ ሰዎች በተወረወሩ አስጠያፊ ቃላት ተወረፉ ።

ከዚህ ቀደም ብሎ በ1966 ዓ·ም በሐምሌ ወር እኩሌታ ላይ ለቦስት ወራት ደርግ በጉፋ ሠፈር ፡ በእርሚ እቭዬሽን ፡ እንዲሁም በጃንሜዳ የፈረስ እሽቅድድም ከበብ አስሮ ያቆያቸውን የቀድሞ ባለሥልጣኖች ወደ አራተኛው ክፍለ ጦር መምሪያ ግቢ አዛወራቸው ። አያብሩልኝም የሚላቸውንም ሁሉ እስከ ጳጉሜን መጨረሻ ማሰሩን ቀጠለ ። ደርግ በመስከረም 2 ቀን 1967 ዓ·ም ሥልጣን ከያዘ በኋላ ለቦስት ሳምንታት ያህል ፋታ ሰጥቶ ካዘንጋ በኋላ እንደገና የፍየል ወጠጤ ማፈን ጀመረ ።

በዚህ ወቅት ንበር ደርግ አምሐ ገብርኤልን በሥራው ዓለም አብሯቸው ከነበሩት ጋር በአራተኛ ክፍለ ጦር ያቀላቀለውና በማከታተል ልም ሌሎች 18 ወንዶችና 2 ሴቶች ያሰረው ። በሰላም እጁን የሰጠ ሰው በአሰረ ቁጥር ለሚያወጣው ሀተታ መግቢያ አድርጉ የሚያቀርበውን "የፍየል ወጠጤ" የተባለውን የግብዝነት ዘፈን ያሰማ ጀመረ ። በመስከረም 30 ቀን 1967 ዓ·ም ፍሬው ከገለባው የማይለይ ፡ በሀሰት የተመላ መግለጫ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አወጣ ።

በመስከረም ወር አራተኛ ሳምንት ውስጥ ከአሠራቸው መካከል ወንዶቹን ብቻ በራተኛ ክፍለ ጦር አጎራቸው ። "በጥበቃ ስር የዋሉ የቀድሞ ባለሥልጣኖች" እየተባሉ ሲጠሩ የቆዩት በአራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ግቢ ወስጥ ቁጥር 5 ፡ 6 እና 7 በሚል መለያ በሚታወቁ ዛኒጋባዎች ንበር የተከረቸሙት ። አምሐ ገብርኤልም በ7 ቁጥር ካሉት እስረኞች ጋር ንበር የተደመረው ።

በመስከረም 27 ቀን 1967 ዓ·ም በዕለተ ሰንዴ ፡ ከቀኑ በአስር ሰዓት ላይ አምሐ ገብርኤል በቀድሞው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ውስጥ ለሥራ ጉዳይ ወደ ሥራ ጓደኛው ቢሮ ወደ ፎቅ መጥቶ ወደ ራሱ የሥራ ገበታ ለመመለስ የፎቁን ደረጀ ሲወርድ ስማቸውን የማያውቃቸው ሁለት የሲቪል ልብስ የለበሱ ቀያይ ሰዎች "እገሌ ናት ወይ ?" ሲሉ የተፀውኦ ስሙን በመጥራት እሱ መሆኑን ጠየቁት ። "እዎን ነኝ" ሲላቸው "ለሥራ ጉዳይ አራተኛ ክፍለ ጦር ይፈለጋሉና አብረን

እንሒድ" አሉተ ። የተፈለገው ለሥራ ጉዳይ ከሆነ መልእክቱ በሰልክ ሊነገረው ሲችል ሁለት ሰዎች መላካቸው እንደ ዓይነት ጥርጣሬ ቢያሳድርበትም ፡ ትክክለኛውን ሁኔታ ለማጣራት ከተፈለገበት ስፍራ ለመሄድ መንገድ ሲቀጥል "እንደ ጊዜ ከቢሮዬ ልድረስና ማስታወሻ ደብተር ልያዝ" አላቸው ፡ ያደረበት ሥጋት ያለውደ፣ታው በገጽታው እየተከሰተበት ። "አሁን ስለሚመሰሉ በቀጥታ እንሂድ" በማለት ጥያቄውን ሳይቀበሉት ቀሩ ፡ እንደጣረ ሞት አጣዳፊዎቹ መልእክተኞች ። ከሕንፃው ወጥተው ወደ አውቶሞቢል ማቆሚያው ሲያመሩ "በራሴ አውቶሞቢል ልከተላችሁ" ቢላቸው "እኛው ስለምንመልስዎ መኪና መያዝ አያስፈልግም" አሉት ቆፍጠን ብለው ።

ፈታ ሳይሰጡ አዋክበው እንዱ ነጂ ፡ ሌላው ከኋላ ተቀማጭ ሁነው ፡ እርሱን ከነጂው ጐን አሳፍረውት በቮልስዋገን አውቶሞቢል ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ከነፉ ። የቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤትን አለፍ እንዳሉ "መሣሪያ ይዘዋል ወይ?" ብለው ጠየቁት ። እርሱም አለመያዙን አረጋገጠላቸው ። ያክፍለ ጦሩ በራፍ ሲደርሱ ዘቡ አላስገባም በማለቱ እንደኛው ወረዶ የዘቡን አለቃ ካነጋገረ በኋላ በሩ ተከፍቶ ወደ ውስጥ ገቡ። ከዚያም ሻለቃ ዳንኤል አስፋው ወደሚባለው የደርግ የዘመቻ መኰንን ጽሕፈት ቤት ተወሰደ ። እንደኛው ጠሪ ከእርሱ ጋር ለሁለት ሠዓት ያህል እውጭ ሲጠብቅ ፡ ሁለተኛው ቀድሞ ገብቶ መኰንኑን ከአነጋገረ በኋላ አምሐ ገብርኤል እንዲገባ ተጋበዘ ። መኰንኑም ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አንድ ማኅደር አውጥቶ በውስጡ የሰፈረውን መልክት አደረገና በቁጥጥር ስር እንዲቆይ መታዘዙን ገለጸለት ። በእንድ ብጣቂ ወረቀት ላይ ሜር ሜር አድርጉ ሻምበል ጥበበ ሙሉ ለሚባለው በመስጠት ወደ ማረፊያ ክፍል እንዲያደርሰው ነገረው ።

ይህን ሲሰማ አምሐ ገብርኤል ምድር ሰማዩ በላዩ ላይ የተደፋ መሰለው ። በተሰባበረ እነጋገርም ያለበትን ለማስታወቅ ወደ ቤቱ ስልክ ለመደወል እንዲፈቀድለት ጠየቀው ። ብስጭት የገዛ ምራቁን በእንድ እፍታ ከግራዋ የመረረ አደረገበት ። መራራው ምራቁ እያንገፈገፈው ንበር አስደንጋጭ የሆነውን ዜና ለንፍሰጡር ባለቤቱ የነለጸላት ። እንደአጋጣሚ እርሱ እዚያው እንዳለ የመጀመሪያው የደርግ ሊቀ መንበር የሌ ጀኔራል አማን እንዶም ልዩ ረዳት የነበረው ሻለቃ ወንዳየን ምሕረቱ ለሻለቃ ዳንኤል ስልክ ደውሎ ሲነጋገሩ ስም በመስማቱ ለማነጋገር

ጠይቆ፡ ስልኩ ስለተሰጠው የተባለውን ገልጾ ፡ በዚሁ ምክንያት ከሥራ ገበታው መለየቱን አስታወቀ ።

ለማረፊያው ከተወሰነለት 7 ቁጥር ክፍል ከመግባቱ በፊት በእንድ ድንኳን ውስጥ የያዘውን ለማወቅ መጠነኛ ፍተሻ ተደረገለት ። ወደተባለው ክፍል ሲገባ የክፍሉ ተጠሪ (ጎላፊ) አቶ አበበ ወርቁ በትሕትና ተቀበሉት ። ወዲያውም አልጋና ፍራሽ መታደሮች እምጥተው ሰጡት ። በክፍሉም ውስጥ የሚያውቃቸውንና የማያውቃቸውን ሰዎች ሲያገኝ ፡ እግሩ ከደፋ እንደገባ አስረኞች ከበው የከተማው ወሬ ይጠይቁት ጀመር ። የእስረኛውም ዕድል ምን እንደሚሆን ሊያውጣጡት ሞከሩ ። የሚያረካቸው መልስ ሊሰጣቸው ግን አልቻለም ፡ ከስጋት ገና አልተላቀቀም ነበርና።

መታሰር ካልቀረለት የተያዘው ከቤተሰቡ መካከል ፡ በተለይ ከሕፃን ልጁና የመውለጃ ጊዜዋ ከተቃረበው ባለቤቱ ፊት ሰይሆን ፡ ከመሥሪያ ቤቱ ውኖ ፡ ቤተሰቡ ከድንጋጤ በመዳኑ አምሐ ገብርኤል ፈጣሪውን አመሰገነ ። ሆኖም በትካዜ የተዋጠባት የዚያች ዕለት ሌሊት ርዝመት የእንድ ተራ ሌሊት – የአሥራ ሁለት ሰዓት ጊዜ – ሳይሆን ፡ እጥፍ ፡ የእጥፍም እጥፍ ሆነበት ። የአሳብና የጭንቀት ማኅደር ሆኖ ከአደረው ከአምሐ ገብርኤል ላዕላይ ገላ – የእራስ ቅል – ላይ በማግሥቱ ረፋዱ ላይ ጠጉሩን ሲላጩት የራስ ቅሉ ብቻ ሳይሆን የሰራ አካላቱ ሥሮች (ነርቮች) ሟምር የኤሌክትሪክ ኃይል እንደነዘረው ሁሉ እርር ፡ ኩምትር አሉ ። በዚህ ወቅት ነበር መንፈሱ የታወከው ፡ ዓይኑ እንባ ያቀረረው ፡ የተፈጠረበትን ዕለት መርገም ፡ በእትዮጵያዊነቱ ማማረር ፡ በእጋጣ ሚው ሁሉ መብከንከን የጀመረው ። በምግብ ማቅረቢያ ሰዓት ባለቤቱ ምግብ ይዛለት በዛኢጋው አጠገብ ወደ ማስፈተሻው ድንኳን ስትመራ ወጉሩ ተላጭቶ ፡ መንፈሱ ዝቅ ብሎ ስትየው የበለጠ ድንጋጤና እሳብ እንዲያድርባት ላለማድረግ ከጓደኛው ከአቶ ካሣ በየነ በተዋሰው ቆብ ራሱን ሸፍኖ ውስጡ በሀዘን የተሸማቀቀ ገጽታውን በፈገግታ ለመሸሸግና ለማስመሰል ሞከረ ። እልህና ቁጭት ስለተናነቀው ግን ያልሆነውን ለመሆን ያደርግ የነበረው ሁሉ ሳይሰምርለት ቀረ ።

በአራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ አምሐ ገብርኤል አዲስ ሕይወቱን አሐዱ ያለው በዚህ የጭንቀት መንፈስ ነበር ። አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ በጦር ሰፈርነት ብቻ ሳይወሰን ፡ ከንጉሠ ነገሥት እስከ ጭቃ ሹም ማሠሪያ



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሆነ ። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ነበር ደርግ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው ሰዎች ሰቆቃ የጀመረው ፡ ለአገራቸው ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱት ባለሥልጣኖች ውርደት የተቀበሉት ፡ ለአገር ውሀደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት አዛውንት ንቡረ ዕድ ዲሚጥሮስ ገብረ ማርያም አልጋ ተሸከመው ወደ መቆያ ክፍል እንዲሄዱ በማድረግ ስሜታቸውን ለመንካት የተሞከረውና የሌሎችም ልብ የቆሰለው ።

የአራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ የሚገኘው በደቡብ አዲስ አበባ ከደብረ ዘይት መንገድ ፡ የባቡሩን ሐዲድ ሻገር እንዳሉ ፡ ከመኧለኪያው አጠገብ ነው ። ይህ ግቢ እንደስሙ ሁሉ በዚያን ወቅት ደንበኛው የጦር ሠፈር ሆኖ ነበር ። በ1967 ዓ·ም የደርግ አባሎች የሚሰበሰቡበት ፡ የቀድሞ ባለሥልጣኖች–ንጉሠ ነገሥቱ ጭምር – የታሠሩበት በዚሁ ሠፈር ምድረ ግቢ ውስጥ በመሆኑና የጦር እዝ መስጫም ስለነበረ በጥብቅ ይጠበቅ ነበር ። በግቢ ወጭውም ላይ ቁጥጥሩና ፍተሻው እጅግ የጠነከረ ነበር ። የጊዜው የኢትዮጵያ የእዝ ማዕከልም ይኸው ግቢ በመሆኑ የብዙዎች ህሊና ያተኮረውም ወደዚሁ ነበር ። የፍየል ወጠጤ እንዲዘፈን የሚታዘዘው ከዚሁ በመሆኑ የሕዝብ ዓይንም ሆነ ጆሮ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የሚነገረውን መግለጫ የሚጠብቀው ከአራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ሁኖአል ። ደርግ እስረኞችን ከለላ በማድረግ የከረቸመበት ይህ ምድረ ግቢ መሰብሰቢያውና እስር ቤትም በመሆኑ በሰው ተጨናንቀ ። በጐ መካሪ መስለው በቀረቡ ሰዎች መርመስመስም ተጣበበ ።

ይህ ግቢ የሕዝብ አትኩሮት ያጣው ደርግ መሰብሰቢያውን በጥቅምት 12 ቀን 1967 ዓ·ም ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ካዛወረበት ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ወደዚያው ከተወሰዱበት ከጥቅምት 13 ቀን 1967 ዓ·ም ጀምሮ ነው ። ይኸውም ሁኖ የመንግሥት ማዕከልነቱ እንጂ እስር ቤትነቱ ሙሉ በሙሉ አልቀረበትም ነበር ። የተዳፈነው እሳት መቀጣጠል የታሪካዊ ስፍራነት ደረጃ የሰጠው የአራተኛ ክፍል ጦር ሠፈር ሌላው የሚዘከርበት የጥፋት እሳት በ1966 ዓ·ም የተጫረበት ቦታ መሆኑ ነው ።

በዚሁ ስፍራ ነበር በነሀሴ 3 ቀን 1966 ዓ·ም "በእስረኞች ደንብ መሠረት ራሳችሁን እንድትላጩ ፡ ሰውነታችሁን በወር አንድ ጊዜ ብቻ እንድትታጠቡ ፡ መለወጫ ልብስ በወር አንድ ጊዜ ብቻ እንዲገባ ፡ የዐሐደ መሞቂያ ጊዜ በቀን ግማሽ ቀን ብቻ እንዲሆን ተወስኖአል" የሚል የደርግ ትእዛዝ የወጣውና "በጥበቃ ስር የዋሉ የቀድሞ ባልሥልጣኖች"

የሚለውም ሐረግ "እስረኞች" በሚል አንድ ቃል ተተክቶ ፡ በነጋታውም ትእዛዙ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ የዋለው ። በነሐሴ 27 ቀን 1966 ዓ ም ደግሞ ከወህኒ ቤት የሚመጣ ምግብ እንዲመገቡ ተመሰን ።

እንዲራብ የተፈለገውም የእስረኞቹ ሥጋዊ እካል ብቻ ሳይሆን አእምሮአቸውም ሞምር በመሆኑ ፡ የሚነበቡ መጽሔቶችና መጻሕፍት (የሃይማኖት መጻሕፍት ሞምር) እንዳይገቡላቸው ፡ የገቡትም እንዲወጡ ተደረገ ። የእስረኞቹ ይዞታ እየተካበደ ፡ የተያዝንበት ጉዳይ በሕግ አግባብ ተጣርቶ እንለቀቃለን የሚለውም ተስፋ እየጨለመ ሄደ ።

በዚያን ዘመን ክረምቱ በጣም ከባድ ፡ ቀዝቃዛም ሆኖ ነበርና በደረት ጻቦ የሚውለውን እስረኛ ጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ ረፈረፈው ። በመድኃኒትና በምግብ ሕመሙን ይከላከል የነበረውን እውን ተጻክሞና ተበሳጭቶ ሲያገኘው አስም ገዘገዘው ፡ አሰቃየው ። እላውንቱ ሁሉ ከእስር ቤት የመጣ የዕለት ድርጉ ለመቀበል ተኮለኩለ ። ራስ መስፍን ስለሺ ነበሩ ድርጉውን ለመቀበል ቀዳሚ ሆነው የቀረቡት ። ያንን ተቀብለው ሲመለሱ የተመለከተ ሁሉ እዘን ፡ ወታደሩ ሞምር ። ጣም የሌለውን የእሸር ባሸር ብጥብጥ ፡ የማይቆረሰውን ደረቅ ሞፎና ሻይ ተቀብሎ ከእስረኛው ከፊሉ ለመብላት ቢሞክር አንጀቱ አልቀበል አለው ። ሰም ውሉ ማይሩን መረጠ ። ሌሎቹ ለቁመተ ሥጋ የተገኘውን ለመብላት ቢሞክሩም ውለው አድረው በድርቀት ተሰቃዩ ። በምግቡ አለመስማማት የብዙዎች ጤና ታወከ ። ከጤንኛው የታማሚው ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየበረከተ ሄደ ። በሐኪሞች ጉትጉታ በመጨረሻው ጥብቁ ትእዛዝ ተሻሽሎ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ቤተሰብ ምግብ እንዲያስገባላቸው ተፈቀደ።

በአዲሱ ዓመት ደግሞ አዲስ ትእዛዝ መጣ ። በጥቅምት 12 ቀን 1967 ዓ·ም ምሽት ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺና ሌሎች ጥቂት የደርግ አባሎች ወደ ሶስቱም ክፍሎች ተራ በተራ እየገቡ ፡ "ስማችሁ እውን የሚጠራው እዚሁ ትቆያላችሁ ፡ ሌሎቻችሁ ወደ ሌላ ስፍራ ትዛወራላችሁ ፡ ስለዚህ ዕቃችሁን ሌሊቱን አዘጋጅታችሁ ተጠባበቁ" ብለው አዘዙ ። በዚህ ጊዜ ነበር በ7 ቁጥር ውስጥ ሻለቃ ጌታቸው ከቀድሞ ጓደኛው ከሻለቃ ተፈራ ተክለ አብ (በየካቲት 21 ቀን 1966 ዓ·ም የአዲስ አበባ ራዲዮ ጣቢያን ከያዘው መኰንን) ጋር የተገናኘውና ሻለቃ ተፈራ "ሲጋራ ስጠኝ" ብሎ ጓደኛውን የጠየቀው ። ሻለቃ ጌታቸው ሲጋራውን ተኪሱ አውጥቶ

ሲሰጠው ጉንበስ ሲል በጉኑ ወሸቅ እድርጉት የነበረው ሽጉጡ ወደቀበት። ከእስረኞች መካከል ሽጉጥ ይዞ በመግባቱ ሻለቃ ተፈራ በንቀት ዓይነት አንጋጥጦ ተመለከተው ።

የመያዛቸው መግለጫ በአንድ ላይ የወጣባቸው ሰዎች እዚያው እንዲቆዩ ስማቸው ሲጠራ የአምሐ ገብርኤል ስም አልተጠራም ነበር ። ስለዚህም ስሜ ሲጠራ ባላዳምጥ እንጂ ሌሎቹ ሲቀሩ እኔ ለምን ተለይቼ እንድሄድ ይደረጋል የሚል ጥርጣሬ አደረበት ። ሻለቃ ጌታቸው በደረሰበት አጋጣሚ በሲጨት በማለቱ "የእኔ እጣ ምንድነው?" ብሎ ሊጠይቀው ግን አልፈለገም ። ጫት ከሂያጆች ጋር ስሜ ከተጠራ እሄዳለሁ፡ ካልተጠራም እዚው እቆያለሁ ፡ ቢሆንም የሚሆነው አያታወቅምና ዕቃዬን ላሰናዳ ብሎ ሌሊት ተነስቶ እንደሌሎቹ ያለችውን ቁሳቁስና ልብስ ጠቀለለ ። ማለዳ ወፍ ሞሞ ፡ ሞሞ ፡ ሲል የሚሄዱት ሰዎች ስም እየተጠራ በማክ መኪና ከነዕቃቸው ሲሳፈሩ ሞት ይርሳውና ስሙ አውንም ሳይጠራ ቀረ ። ከማታውም ከጪቱም የስም ዝርዝር ውስጥ ስሙ ስላልተጠራ በመቸገሩ ፡ በመኪና እንዲሳፈሩ የሚያዘውን ፡ ከአውን በፊትም በቁጥጥር ስር እንዲውል መወሰኑን ነግሮት የነበረውን ሻለቃ ጻንኤል የሚባለውን መኰንን "ቀሪ ነኝ ወይስ ሂያጅ?" ሲል ጠየቀው ። ሻለቃው ዝርዝሩን አገላብጦ ቢፈልግ ከዝርዝሩ ውስጥ የእርሱን ስም ስላጣ ጠብቀኝ ብሎ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ሔዶ ሲመለስ "በመጨረሻው መኪና ላይ ዩሳፈሩ" አለው ፡ የፈረደበትን እስረኛ ለማሳፈር እየተጣደፈ።

አብረው በአንድ ሰሞን ከተያዙት መካከል ሌሎቹ እዚያው ሲቀሩ እርሱ ብቻ ከታሳላቆቹ ሰዎች ጋር እንዲሄድ መታዘዙን የሰሙት ሌሎቹ እስረኞች በጣም አዘኑለት ፡ የራሳቸውን እጣ እንዳወቁ ሁሉ ። አነጋጋራቸው አምሐ ገብርኤልን አባባው ። ከጥቂት ቀናት በፊት ቅማል እንዳለበት ሁሉ ወጉሩን በማድ ሲላጨት የተሰማው መራራ ስሜት እንደገና ከውስጡ ገንፍሎ ከፊቱ ስለመጣበት በዕድሉ አማረረ ።

መቼስ ምን ያደረጋል ፡ የጠቀለለውን ቅራቅንቦ ይዞ እንደታዘዘው በሽራ ተሸፍነው ከተደረደሩት መኪናዎች በኋለኛው ላይ ተሳፈረ ። ጉዞው ተጀመረ ። መኪናዎቹን መትረየስ የተጠመደባቸው ጂፖች እጅበዋቸዋል ። አፍራካ አዳራሽ አጠገብ ሲደርስ ነበር እጀባው ከፊትም ከኋላም የተጠናከረ መሆኑን የተመለከተው ። መድረሻውን አያውቅምና በዚሁም ልቡ እጅግ ተሸበረ ። ከደጉ ይልቅ ክፉ ክፉው ታሰበው ። ፍቅሩን

ያልጠገበው የስለት ልጁ ፡ የነፍስሙር ባለቤቱና የእሮጊት እናቱ ገጽታና ትዝታ ከፊቱ መጥቶ ተጋረጠ ። ይህም የበለጠ እሽበረው ፡ ከባሰ አሳብ ላይ ጣለው ። እንዴን እንስቶ ሌላውን እንደጣለ ፡ እንደተጨነቀ ነበር ካልጠበቀው ከታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ የደረሰው ።

እስረኞቹ ከታላቁ ቤተ መንግሥት ከዙፋን አዳራሽ አጠገብ ደርሰው መኪናው ሲቆም ሶስት መኰንኖች አፋፍ ላይ ቁመው በትረ መኰንን ከእጃቸው ላይ እየጠፉ በመንጠባረር ሲመለከቱዋቸው አስተዋለ። በፈቃደኛነት እጃቸውን የሰጡ ሰዎችን በመኪና አሳፍሮ ማምጣትን እንደትልቅ የጦር ሜዳ ጀብዱ በመቁጠር ተኩራርተዋል መኰንኖቹ። በእግራችን እርግጥ ፡ በእጃችን ጭብጥ አድርገን ይዘናቸዋል በማለት ታብየዋል ።

ከሶስቱ መኰንኖች አንዱ ማለዳ "በኋለኛው መኪና ተሳፈር" ያለው ሻለቃ ዳንኤል ሲሆን ፡ ሁለተኛው በሐምሌ 30 ቀን 1966 ዓ·ም በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በዚያ ወቅት ተቋቁሞ በነበረው የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ረቂቅ በደርግ ተወካይነት ሲቀበል ያየው ሻለቃ አጥናፉ አባተ ነበር ። ሶስተኛው መኰንን ማን እንደሆነ ግን አላወቀም ነበር ፡ ማንነቱን የሚያውቀው አንድ የእስር ቤት ጓደኛው "ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ማለት ይህ ነው" ብሎ እስካመለከተው ድረስ ።

ከመኪና እንደወረዱና ዕቃቸው እንደተራገፈ ስማቸውን እየጠሩ እነሌ ከዚህኛው ክፍል ፡ እነሌ ከዚያኛው ክፍል ግባ በማለት እስረኞቹን በዙፋን አዳራሽ ስር ከሚገኘው ደይን ውስጥ አጎሩዋቸው ። ተቀባዮቻቸው በወቅቱ ራሱን "ርዕሰ ብሔር" ብሎ የሰየመው ደርግ የሚባለው አካል ምክትል ሊቀን መናብርት ቢሆኑም ፡ መስተንግዶው ግን በወግ አልነበረም ።

በዙፋን አዳራሽ ስር በስተደቡብ በኩል በሚገኙ ፡ እቀማመጣቸው በእንድ በኩል ከሠሀ ልክ በታች በሆኑ መጠነኛ ስፋት ባላቸው ሁለት ክፍሎች ውስጥ ነበር እስረኞቹ የታጉሩት ። እነዚህ ክፍሎች የውስጥ መካፈያ ግድግዳቸው ሳንታ ሆኖ ፡ አንድ ቁጥርና ሁለት ቁጥር የሚል መለያ ተሰጥቷቸዋል ። እንዳንድ በርና ጥቂት መስኩቶች ብቻ ያላቸው ናቸው ። የሁለቱም ክፍሎች በስተሰሜን በኩል ያለው ግድግዳ ጎመቱን

ሙሉ የሚያኀ ፡ በስሩ የሚገኘውም ወለሉ የሚወረዛ ነው ። በስተምስራቅም ሆነ በስተምዕራብ በኩል ክፍሎቹ መስኩት ስለሌላቸው የዉ.ትም ሆነ የማታ የፀሐይ ብርሃንና ሙቀት አያገኙም ። ብርሃን ብቻ ሳይሆን በቂ አየርም አይገባባቸውም ። እስረኞቹ ብርሃን የሚያገኙት ሰው በዋይት ለመልቀም ከሚያስችሉት ባውዛዎች በስተደቡብ በኩል በሚገኙት በሮች ከሚገባው ዓይን የሚያጠፋ መጋገንና በክፍሎቹ ውስጥ አልፎ አልፎ በተንጠለጠሉ ጥቂት የፍሎሬሰንት መብራቶች ነው ።

ከእነዚህ ክፍሎች ከኢንደኛው ክፍል ጋር የተያያዘ በግድግዳ የተከለለ አንድ በረንዳ አለ ። እንደዚሁም ግድግዳው ከሌላው ክፍል ግለትም ከሠሰት ቁጥር ጋር የተያያዘ ፡ በሩ ግን ለብቻው የሆነ አንድ ጠባብ ክፍል ይገኛል ። ይህም ክፍል ቁጥር ሶስት በመባል ይታወቃል ። በዚህ ክፍል ውስጥ ነበር አቡኑ ለጥቂት ቀናት ብቻቸውን የታሰሩት ።

እነዚህ ክፍሎች ተዋክበው ለመጡት ፡ ለምን ያህል ጊዜ በዚያ እንደሚቆዩ ላላወቁት ለደርግ አስረኞች ማስተናገጃነት ተመረጡ ። የወለሉ ሲሚንቶና ጥርብ ድንጋይ ንጣፉ የታጠበበት ሙሀ ባልደረቀ ፡ የግድግዳው መወርዛት ባልተወገደ ፡ ንፁሕ አየርና የተፈጥሮ ብርሃን በማይገባቸው እንደመቃብር ክምድር በታች በሆኑት በእነዚህ ክፍሎች ግለትም በእውነተኞዎቹ ደይኖች ነበር እስረኞቹ የተቀየዱት ። በእንድ ወቅት በእንድ ቁጥር 69 ፡ በሁለት ቁጥር 8፣ ሰዎች ነበሩ እጅግ ተጣበው የታሰሩት ። በተለምዶ የሚበርድ ክፍል የሚሞቀው በእሳት ሲሆን ፡ የእነዚህ ክፍሎች ወለል እርጥበት የደረቀው ግን "ኑሮ ካለት የመቃብር ቤትም ይሞቃል" እንዲሉ ፡ በሰው እስትንፋስ ሙቀት ነበር ። የመጀመሪያ ያምቹ ጥቂት ቀናት በሰው ብዛት ፡ በትንፋሹ ሙቀት ባይሆን ኑሮ ብርዱ የሚቻል አልነበረም ። በቅዝቃዜና በብርድ እካላቸው በጊዜ ብዛት በድን እንዲሆን የተፈለገው እስረኞች ሞቃት ልብስ ከቤታቸው እስኪመጣላቸው ድረስ ተፈጥሮ ፀጋዋን ስለለገሰቻቸው በገዛ ትንፋሻቸው ለጊዜው ብርዱን ተከላከሉ ። እያደር ግን የብርድ በሽታ የማይለቅ ቁራኛቸው የሆኑት ብዙዎች ነበሩ ።

በዚህም ሁሉ ምክንያት የእስረኞቹ ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ ተሸጋገረ። የመንፈስም ፡ የአካልም መቆራመድ ደረሰባቸው ። የሕይወት ሂደት እስከሚያቆምበት ማዝገሙ ስለማይቀር እስከጊዜው ከባዱን ሕይወት ያለሙድ ተያያዙት ።

* የአንድ ሰው መኝታና እቃ ማስቀመጫ ከሁለት ካፊ ሜትር አይበልጥም ነበር ።

፬

የተዳፈነ እሳት

በያዝነው ምዕተ ዓመት በሁለተኛው አጋማሽ ውስጥ በምድረ ኢትዮጵያ ሁለት ተቃራኒ ሁኔታዎች ፡ ማለትም ለልማት የተነቃቃ ፍላጎትና የብሶት ስሜት መፈታተግ ከመቼውም በበለጠ ጉልቶ መታየት ጀመረ ። ለልማት የተነሳሱት ጥቂቶች አልነበሩም ። ሩቅ ሔዶ ዱር ለመመንጠር ፡ ከባንክ ተበድሮ ትራክተር በማሰማራት ለማረስ የተነሳሱት እንደ እንጉዳይ ነበር በየትም ብቅ ፡ ብቅ ያሉት ። ጥጥና ቡና ለመትከል ፡ ቦሎቄና ሌላም ዓይነት ሰብል ለመዝራት የተሰማሩት ወንዶች ብቻ አልነበሩም ፡ ሴቶችም ጭምር እንጂ ።

በምዕተ ዓመቱ እኩሌታ የመጀመሪያዎቹ አሠርት ዓመታት ወንዶች እጀጠባባቸውንና ሽሚዛቸውን ሰብሰብ ፡ በአጭር ታጠቅ ማድረግ ፡ ሴቶች ደግሞ ቀሚሳቸውን በጂንስ ሱሪ ፡ ነጠላቸውን በጃኬት መተካት ጀመሩ ። ሁለቱም ጾታዎች መሬትን በትራክተር ማገላበጡን ተያያዙት ። "የሳምንት መጨረሻ ገበሬዎችም" ለእርሻ ሲሯሯጡ በብዛት ታዩ ።

ኢትዮጵያ እንድትለማ ፡ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ፍላጎት ያላቸው ወዳጅ መንግሥታትም ለእርሻ ማስፋፊያ የሚሰጡት እርዳታና ብድር በሞተር ኃይል ለሚካሄድ እርሻ (ሜካናይዝድ ፋርሚንግ) መስፋፋት አጋዥ ኃይል ፡ እንቀሳቃሽ ሞተር ሆኑ ። እህል በሽበሽ ፡ ዋጋው ርካሽ የሆነበት ጊዜ ሆነ ። በደፈናው ሲመለከቱት ልማቱ የአገር ኢኮኖሚን የሚያዳብር በመሆኑ የሚደገፍ ፡ አቦ በርቱ ! የሚያሰኝ ነበር ።

ነገር ግን በትራክተር ሰፋፊ እርሻዎች የማረሱ ስምሪት ለልማት ከመበጀቱ አንፃር የሌሎችን ብሶት በማስከተሉ የሁለቱን ወገኖች የጥቅም ግጭት አስከተለ ። ጥቂት ማሳዎች አገላብጠው የሚያድሩ ገበሬዎች

ይዞታ በትራክተር አራሾች ተገፋ ። ባለሰፋፊ እርሻዎች ቀስ በቀስ የጭሰኞቻቸውን ይዞታ አጣበቡ ። ይህም እያደር ጭሰኞችን ከተፈናቃይነት ደረጃ አደረሳቸው ። በበሬ መለስ ፡ ቀለስ ፡ በገበሬው መውደቅ ፡ መነሳት ፡ በጅራፍ ጩኸት ፡ በማረሻው ሰርዶ ነቃይነትና ጉቶ ፈንቃይነት ታርሶ ለዕለት ጉርስ ፡ ለዓመት ልብሰ ብቻ ይገኝ የነበረው ሰብል ይብሱን ተመናመነ ። ከዘመናዊ እርሻ መስፋፋት በፊት ከእጅ ወደ አፍ የነበረው የአርሶ አደሩ ኑሮ ይበልጥ እንዲያዘቀዝቅ ምክንያት ሆነ ። የኑሮ መቆርቆዝም ለሕዝብ የብሶት ነዲድ መቀጣጠል ምክንያት ሆነ ።

በሕዝብ ብሶት በማሳበብ በ1953 ዓ.ም መኰንናዊ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደረገ ። ሙከራውም "ይህም አለ ለካ !" የሚለውን መንፈስ አነሳሳ ። አስቀድሞ ያሰበውንም ፡ ያላሰበውንም በብሶት አብገነገነው ። የምሬት እሳት ጫረ ፡ ቁጭት አሳደረ ። በተለይ የአንዳንዶችን የብስጭት ሙቀት አጋጋለው ። ዛቻ ፡ ድንፋታ አስከተለ ። በአንፃሩም ሙከራውን ይበጅ ፡ የተቃና ያድርገው የሚሉትን አደባባይና አውራ ጉዳና አስወጣቸው ። በደረሰው የመደሰት ቅጽበታዊ ስሜት ከሌላው ጭንቀት ጋር ተፋጠጠ ። ከሕዝቡ በአንደኛው ክፍል ፡ በተለይም በከተሜው ላይ ሁለት ዓይነት ገጽታ ፡ ማለትም በብሶተኛውና በወጣቱ ዘንድ የመፈንደቅ ፡ በሀብታሙና በአዛውንቱ ዘንድ ደግሞ የመከፋት ስሜት ተንፀባረቀ ። የዚህ የተቃራኒዎች ስሜቶች መከሰት ነበር በወታደራዊ አንጃዎች መካከል ያልተጠበቀ መከፋፈልንና መፋጠጥን ያስከተለው ። በመፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፍ ምክንያት ነበር በ1953 ዓ.ም የተጫረው እሳት የተዳፈነው ።

የተዳፈነው እሳት ውስጥ ውስጡን ሲጋጋም ቆይቶ አገርሽቶበት በ1965 ዓ.ም እንደገና መቀጣጠል ጀመረ ። በዚህ ዓመተ ምሕረት ወታደሩና መምህሩ ፡ ሰላማዊው የመንግሥት ሠራተኛና ዳኛው የደመወዝ ጭማሪ ጠየቀ ። የኢንዱስትሪና የንግድ ተቋማት ሠራተኛውም በደመወዝ ማነስና በሥራ ሁኔታዎች አለመሟላት ብሶቱን ፡ አርሶ አደሩ ደግሞ በባለርስቶች አያያዝ እሮሮውን አሰማ ።

የአስተዳደር ሹማምንት በዳኝነት ሥራ እንዳይገቡ በማድረግ የፍትሔ አካል (ፍርድ ቤቱ) ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ ሁኖ እንዲሠራ የሚያስችል የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 323 65 በመታወጁ ፡ ሥልጣናችን ተቀነሰ በማለት ጠቅላይ ገዥዎችና እንደራሴዎችም በሚኒስትሮች

ላይ ተታውሞ ማሰማት ጀመሩ ። ከብሶት ሳይሆን መንግሥታዊ ሥልጣንን በሶስቱ የመንግሥት አካላት የመከፋፈልን መሠረታዊ አስተሳሰብ ካለመገንዘብና ለምን ሥልጣናችን ይቀንሳል ከሚል የግትርነት ስሜት የመነጨ ክርክር ነበር ያቀረቡት ።

የ1965 ዓ·ም የተታውሞ ስሜት ፈርጁ እጅግ የተለያየ ነበር ። ከተሜው ዋጋ ናረ ፡ ኑሮ ተወደደ ብሎ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲጨፈጨፍ ፡ ተማሪዎችና መምህራን ደግሞ የወደፊቱ የትምህርት አቅጣጫ ትልም (ኤጁኬሽናል ሴክተር ሪቪው) የተባለውን ጥናት አጥብቀው ተታወሙ ። በዓለም ላይ የንዳጅ ድፍድፍ ዋጋ በመጨመሩ የአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ ድርጅትን ወጭ ለማካካስ በነዳጅ ላይ መጠነኛ ዋጋ በመጨመሩ የነዳጅ ዋጋ ተጨመረ በማለት ባለታክሲዎች አድማ መቱ ። መናንያንና ባህታው ያን ሳይቀሩ ሁሉም በየፈናው ብሶቱን በይፋ መግለጹን ዕለታዊ ተግባሩ ያደረገውም በዚያው ወቅት ነበር ።

ተዳፍኖ የነበረው እሳት እንደገና ሲቀጣጠል ለማጥፋት በ1966 ዓ·ም ያልተበጠሰ ቅጠል ፡ ያልፈሰሰ ውሀ ፡ ያልተደረገ መረባረብ አልነበረም ። ለዚህም ሲባል ለመታደሮች ፡ ለመምህራን ፡ ለዳኞች ፡ ለሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ተጨመረ ። ጭማሪው ከአራት ወራት በኋላ ቢቋረጥም ፡ ለከፍተኛ የመንግሥት ሹማምንትም የሹመት ቦታ ጭማሪ ተደረገ ። ለኢንዱስትሪና ለንግድ ተቋማት ሠራተኞች ጥያቄ ምላሽ ለመስጠትም የተሻሻለ የአሠራና የሠራተኛ ግንኙነት አዋጅ ረቂቅ ለፓርላማ ቀረበ ። የተማሪውንና የመምህራኑን ተታውሞ ለማብረድ የሴክተር ሪቪው ጥናት ተፈጸሚነት ታገደ ። የፍርድ ቤቶችን የአሰራር ነፃነት የሚያስቀር ባይሆንም ፡ የአገረ ገዥዎችን ስም·ታ ለማብረድ በታወጀው ሕግ ላይ መጠነኛ መሻሻል እስከማድረግ ተደረሰ ። በሚካናይዝድ እርሻ መስፋፋት ምክንያት ጭሰኛው ከይዞታው በቀላሉ እንዳይነቀል ለማድረግ የባለርስትንና የጭሰኛን ግንኙነት የሚመሰገን የአዋጅ ረቂቅ እንዲመከርበት ለፓርላማ ተላለፈ ። በነዳጅ ላይ የተደረገው የዋጋ ጭማሪ ተነሳ ።

የዚህ ሁሉ መደረግ ግን የተዳፈነውን እሳት መጫጫስ አልገታውም ፡ የሕዝቡንም የስሜት መገንፈል አላስከነውም ። እንደ ጊዜ በአዲስ አበባ ፡ ሌላ ጊዜ በጎንደር ቦረና ፡ እንዲሁም ሌላ ጊዜ በአስመራ ከመጫጫስ አልፎ ነበልባል ማሳየት ጀመረ ። በ1966 ዓ·ም የተከሰተው የመሬ የረሀብ

አልቂት አስቀድሞ የተቀጣጠለውን እሳት አግለበለበው ። ነበልባሉንም ከመጋረፍ ወደ ግቃጠል አሸጋገረው ። ጉምጉምታና መብሰልሰል ወደ ሰላማዊ ሰልፍና የተታውሞ ድምፅ ወደማሰማት ተለወጠ ። ዴሞታ ፡ የታታውሞ ጽሑፎች መበተን የዕለት ፡ ተዕለት ተግባር ሆነ ። በመንግሥት ከፍተኛ ባለ ሥልጣናች መካከል መተማማት ፡ እንዴ በሌላው ላይ ማመካኘት ፡ የአሳብ ልዩነት ስንጥቅን ማሳፋት የዘመኑ ልዩ ክስተት ባይሆንም ይበልጥ ተባባሰ ።

ከመሸበር የተነሳም ከየአቅጣጫው የሚመጣው መልእክት ፡ የሚቀርበው የአሳብ መጋጨት ንጉሠ ነገሥቱን ግራ አጋባ ። የዕድሜ መግፋት ፡ የሚቀርቡት አሳቦች እርስ በርስ መቃረን ፡ የሕዝቡ ፍላጎት መብዛት ፡ የወዳጅ መንግሥታት እመለካከት መቀዝቀዝ የይሁዳ አንበሳ የተባሉትን ንጉሠ ነገሥት በወጥመድ ውስጥ የገባ ነብር እደረጋቸው ፡ የሚይዙትን ፡ የሚጨብጡትን አላጣቸው ።

የቅርብ ረዳቶቻቸው የሆኑት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎች ከወዲያ ወዲህ በሚዘምተው ወሬ ተወናብደው በየካቲት 20 ቀን 1966 ዓ·ም የሥራ ስንብት ጥያቄ አቀረቡላቸው ። በስንብቱ ጥያቄ ወቅት ያልነበሩት ሚኒስትሮች ልጅ እንዳልካቸው መኮንን አቶ ማለሀ ሔኒትና ፡ አቶ ከተማ አበበ ነበሩ ። ከማቅማማት በኋላም የሚኒስትሮቹን ስንብት ንጉሠ ነገሥቱ ተቀበሉት ። የሚወጣው መግለጫ ይዘት ግን በብዙ ማወዛገቡ አልቀረም ። በሚኒስትሮቹ በኩል "ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን የሥራ መልቀቅ ስንብት ተቀብለውታል" የሚል ረቂቅ ሲቀርብ "በእገራችን ልማድ ከሥራ አሰናብተዋቸዋል እንጂ ስንብታቸውን ተቀብለዋል አይባልም" ሲሉ በምክሩ ላይ የነበሩት ልዑል ራስ አሥራተ ካሳ አሳብ አቀረቡ ።

"በጥፋት ሳይሆን ከአንዳንድ አቅጣጫ የሚሰማው ቅሬታ በሚኒስትሮች ላይ ነው በመባሉ የእኛ መልቀቅ ሁኔታውን የሚያረጋጋው ከሆነ ለአገራችን ደህንነት ስንል ሥራ እንለቃለን አልን እንጂ በጥፋተኛነት ሰለማንለት አሰናብተዋቸዋል ሊባልብን አይገባም ፡ አሰናብተዋቸዋል ከተባለ ፡ ምክንያቱን በውል ያላወቀ ወገን እንዲነሳሳብን መጋበዝ ነው" በማለት ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ተታወሙ ። በሥራ መልቀቂያቸው ዕለት እንደዚህ ያለ አሳብ ከአንድ መስፍን መሰንዘሩ

በቦታው የነበሩትን ሚኒስትሮች ሁሉ ልብ አቆሰለው ። ንጉሠ ነገሥቱ ነገሩን ተረድተው "የሥራ ስንብት ጥያቄአቸውን ተቀብለውታል" በሚለው ባይስማሙ ኑሮ አጋ ለይቶ ውስጥ ውስጡን የሚደረገው ሽኩቻ የሚፈነዳው ከውጭ ሳይሆን በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ውስጥ ይሆናል ተብሎ አስግቶ ነበር ።

ይህ ክርክር እልባት አግኝቶ በየካቲት 20 ቀን 1966 ዓ.ም ማታ በመገናኛ ብዙሃን መግለጫው ከተነገረ በኋላ በጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ አሳሳቢነት የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የነበሩትን ፡ በጦሩም ዘንድ ተሰሚነት አላቸው ተብሎ የሚገመተውን ሌ ጀኔራል አቢይ አበበን ጠርተው ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ሊሾሟቸው ማሰባቸውን ንጉሠ ነገሥቱ ገለጹላቸው ። ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የታጩት የሹመት መቀበያ ንግግራቸውን ለማዘጋጀት ከጓደኛቸው ከደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ጋር ከታላቁ ቤተ መንግሥት ወደ ፓርላማ ከተመለሱ በኋላ የጦሩ ፍላጎት የቀድሞው ካቢኔ አባል የነበሩት ልጅ እንዳልካቸው መኰንን እንዲሾሙ መሆኑ ለንጉሠ ነገሥቱ በጎን ተነገራቸው ። በዚህ ምክንያት አሳባቸውን ለውጠው ልጅ እንዳልካቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር፡ ሌ ጀኔራል አቢይን የመከላከያ ሚኒስትር አድርገው ሾሙ ።

አምስት ወር ስንኳ ሳይሞላ ደርግ የጠቅላይ ሚኒስትር ለውጥ እንዲደረግ ጠየቀ ። አቶ ሀዲስ ዓለማየሁና ልጅ ሚካኤል እምሩ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሁነው አልተገኙም በማለት ደርግ ከአሳጣቸው በኋላ ጀኔቫ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጽሕፈት ቤት ዘንድ የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክትኛ (አምባሳደር) የሆኑት ልጅ ሚካኤል እምሩ በአባታቸው ማግባባት ሹመቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ሁነው ስለተገኙ ሐምሌ 15 ቀን 1966 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ሁነው በንጉሠ ነገሥቱ ተሾሙ ።

ተዳፍኖ ውስጥ ውስጡን ሲጋጋም ቆይቶ በ1966 ዓ.ም በወርሀ የካቲት እንደእሳተ ጎሞራ የፈነዳው የእምቢታ ረመጥ ግን በሹም ሽር አልጠፋም ፡ ይበልጥ የሚያሰጋ እየሆነ ሄደ እንጂ ።



የጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ካቢኔ አባሎች በከፊል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ.

፭

ሕጋዊ ምላሽ ለሕዝብ ጥያቄ

በ1966ዓ·ም በዚህው ወራት የአየሩ ሙቀት ተጋግሞአል። አየሩ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም ስሜት ተጋግሎአል ። የአዲስ አበባና የየጠቅላይ ግዛቱ አውራ ጎዳናዎችና ፡ አደባባዮች በሰላማዊ ሰልፍ ተጨናንቀዋል ። ሕዝባዊ ጥያቄዎች ከየአቅጣጫው መጉረፍና የብሶት መግለጫና የተቃውሞ ጽሑፎች በየቦታው መረጨት በባለሥልጣኖች ላይ ሥጋቀትን አሳድሮአል። ስለዚህም ለሕዝባዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የምርመራ ኮሚሽንና የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን በተለያየ ጊዜ ተቋቋሙ።

በየካቲት 26 ቀን 1966 ዓ·ም ማታ በራዲዮና በቴሌቪዥን ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ ለደረሰችበት ውኔታ ተስማሚ የሆነ፡ ለሕዝብ ጥያቄ ሕጋዊ ምላሽ የሚሰጥ ሕገ መንግሥት አርቅቆ የሚያቀርብ፡ ከልዩ ልዩ የሞያ መስክ የተውጣጡና የሕዝብ አመኔታ ያላቸው ሰዎች በአባልነት የሚገኙበት አንድ የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን እንዲቋቋም መፍቀዳቸውን አስታወቁ። በዚህ መሠረት ንበር ከመንግሥት፡ ከሃይማኖት ድርጅቶች፡ ከግለሰቦች የተውጣጡ 30 ሰዎች በአባልነት የሚገኙበት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን በመጋቢት 13 ቀን 1966 ዓ·ም በማዘጋገ የተቋቋመው። ኮሚሽኑ በእቶ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ሊቀ መንበርነት፡ በእቶ አማኑኤል አምደ ሚካኤል ምክትል ሊቀ መንበርነት ሥራውን ጀመረ። ከኢትዮጵያ ነባራዊ ውኔታ በመነሳት አዲስ ሕገ መንግሥት ለማርቀቅ በማሰብም ኮሚሽኑ ጥናት ሲያደርግና ከሕዝብና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የቀረቡለትን አሳቦች

ሲያጠና ቆይቶ፡ በመሠረታዊ ጉዳዮችና በሕገ መንግሥቱ ይዘት ላይ በሰፊው ተከራክሮ በሞብጠች ላይ በአንድ ቃልም ሆነ በድምፅ ብልጫ ከስምምነት ከደረሰ በኋላ እንደየአርዕስቱ በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ተከፋፍሎ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህራንና በፍርድ ሚኒስቴር በሚሠሩ ባለሙያዎች በመታገዝ በየኮሚቴው በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ ተራ በተራ ከተመከረበትና አስፈላጊው መሻሻል ከተደረገም በኋላ የሕገ መንግሥቱ ረቂቅ በአንድ ወጥነት ተዘጋጅቶ ቀረበ። አንቀጽ በአንቅጽ እየተነበበ ጽምዕ ከተሰጠበት በኋላም ረቂቁ በመጨረሻ በኮምሽኑ ፀድቆ በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ በማድረግ ለሕዝብ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ረቂቅ ተጠናቆ ለበላይ በሚቀርብበት ዕለት በዚያን ጊዜ የደርግ አንደኛ ምክትል ሊቀ መንበር ኻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምና ሌሎች የደርግ አባሎች ኮሚሽኑ በሚሠራበት በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የስብሰባ አዳራሽ ድረስ ሄደው ረቂቁ ለንጉሥ ነገሥቱ ሳይሆን ለደርግ እንዲቀርብ ጠየቁ። የኮሚሽኑ አባሎች "እኛ የተሰየምነው በደርግ ሳይሆን በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትእዛዝ ስለሆነ የጥናታችንን ውጤት ማቅረብ የሚገባን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንጂ ለደርግ መሆን አይገባውም" ሲሉ አጥብቀው ተከራከሩ። ከብዙ ክርክር በኋላ ነበር በመጨረሻው እንደታቀደው በዚሁ ዕለት ከእኩለ ቀን በኋላ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለደርግ ተወካይ በእንድ ጊዜ እንዳንድ ቅጂ እንዲሰጥ ከስምምነት የተደረሰው።

ስለ ሕገ መንግሥቱ ረቂቅ አቀራረብ በተደረገው ስምምነት መሠረት በኮሚሽኑ መሰብሰቢያ አዳራሽ ሙስጥ በሐምሌ 30 ቀን 1966 ዓ.ም በተደረገው ሥነ ሥርዓት ላይ የረቂቁ እንዳንድ ጥራዝ ለአፄ ጠቅላይ ሚኒስትር ለልጅ ሚካኤል እምሩና ለደርግ ምክትል ሊቀ መንበር ለሻለቃ አጥናፍ አባተ ተሰጠ። ጠቅላይ ሚኒስትሩና አግባብ ያላቸው ሌሎች ሚኒስትሮች፡ የኮሚሽኑ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀ መንበር በመድረኩ ላይ ተቀምጠው የርክክቡ ስነ ስርዓት ሲፈጸም ፡ ፎቶግራፍ ላለመነሳትና ማንነቱ እንዳይታወቅ ሲል ሻለቃ አጥናፉ የተቀመጠው ከመድረኩ በታች፡ ከኮሚሽኑ አባሎች በስተጀርባ ከጋዜጠኞች መካከል ነበር።

ዕለቱን እንድ ቅጂ ለንጉሠ ነገሥቱ ወደ ቤተ መንግሥት ሲልኩ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ የሕግና የፓርላማ ጉዳይ ኃላፊ ለሆነው ለአምሐ ገብርኤል ረቂቁን አንብቦ ፀንቶ ካለው ሕገ መንግሥት ጋር ያለውን መሠረታዊ ልዩነት አውጥቶ በማሳሰቡ እንዲገለጽላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዋናውን ቅጂ ሰጡት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሠረታዊ ለውጡን እንደተረዱም የሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ለሚንስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲመከርበት አደረጉ። የሚኒስትሮች ምክር ቤትም በመሠረተ አሳቡ ላይ ከተነጋገረበት በኋላ በፍርድ ሚኒስትሩ በአቶ በላቸው አሥራት ሰብሳቢነት፡ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መሀመድ አብዱራህማን ፡ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ኮ/በላቸው ጀማነህና አምሐ ገብርኤል በአባልነት በሚገኙበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ኮሚቴ በአስቸኳይ ተጠንቶ እንዲቀርብለት አዘዘ። ኮሚቴውም በፍርድ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ሌት ተቀን እየተሰበሰበ አስተያየቱን ምዕራፍ በምዕራፍ እያቀረበ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጉዳዩ በመምከር ላይ ሳለ ደርግ አሳቡን ለውጦ ወደ ሌላ እርምጃ አመራ።

ለሕዝብ ጥያቄ ሕጋዊ ምላሽ ለመስጠት የተደረገው ሌላው ሙከራ የምርመራ ኮሚሽን ማቋቋም ነበር። የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች የአስተዳደር በደልና የዳኝነት ጉድለት ፈጽመዋል፣ ያለግባብ ሀብት አካብተዋል በመባሉ ሁኔታውን የሚያጣራ ኮሚሽን የሚያቋቁም፣ ሥልጣኑንና ተግባሩንም የሚወስን የአዋጅ ረቂቅ በልጅ እንዳልካቸው ካቢኔ ለፓርላማ ቀረበ።

በሕጉ ረቂቅ ላይ ፓርላማው በሚመክርበት ወቅት በእንዳንድ አንቀጾች ሕገ መንግሥታዊነት ቅር መሰኘታቸውን ለሚቀርቡላቸው ጥቃቄዎች ይሰጡት ከነበረው መልስና ከገጽታቸው በመረዳት ይመስላል በስብሰባው ላይ የተገኘ አንድ ጋዜጠኛ "በሕጉ ይዘት ቅር የተሰኙ ቢኖሩ በወቅቱ የፍርድ ሚኒስትር የነበሩትና በፓርላማ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ወኪል ብቻ ናቸው" ሲል በጋዜጣ የጻፈው። የአስረጂዎቹ ቅሬታ ደርሷል የሚባለው በደል በመጣራቱ ላይ ሳይሆን ፡ ሕጉ ወደኋላ ተመልሶ (ሬትሮአክቲቪሊ) ክ1933 ዓ.ም ጀምሮ ላለው ጊዜ ጭምር ተፈጻሚ እንዲሆን በመደረጉ ሕገ መንግሥታዊ ካለመሆኑ ላይ ነበር። የሆነው ሆኖ በነበረው ግፊት ሕጉ ታወጀ፣ የቀድሞ ባለሥልጣኖችም ወደኋላ ተመልሶ

በሚሠራ ሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደረገ። የኮሚሽኑም አባሎች ከልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ተመርጠው ሥራ ጀመሩ። የኮሚሽኑ አባሎች የተመረጡት በፓርላማ፣ በጦር ኃይሎች፣ በፖሊስ ሠራዊት፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲና በዋናው አዲተር መሥሪያ ቤት ነበር። ለኮሚሽኑ አባልነት ከአገር ውጭ በፓርላማ ከተመረጡት መካከል አቶ ዘነበ ኃይሌ ምረጫውን ተቀብለው ከአምባሳደርነት ሥራቸው ላይ ተነስተው ለመም ጣት ፈቃዳኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ፣ ዶክተር በረከተ አብ ሀብተሥላሴ በዓለም ባንክ ካላቸው ሥራቸው ተሰናብተው የመጡት በመጣደፍ ነበር።

በቁጥጥር ስር ከዋሉት የቀድሞ ባለሥልጣኖች ምርመራው ተጣ ርቶ፣ ለፍርድ ቤት ቀርቦ በእጥፊነት ሳይፈረድባቸው ነበር እንደወንጀለኛ እጃቸውን በሰንሰለት እያታሰሩ ወደ ኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ተወስደው በኮሚሽኑ የተመረመሩት። እጃቸው በሰንሰለት እንዲታሰረም ወደ ኮሚ ሽኑ መሰብሰቢያ አዳራሽ ሲገቡና ሲወጡ ኃላፊነት የማይሰማቸው ሰዎች እንዲሰድቡአቸውና እንዲያፈዙባቸው የተደረገው ። በአገለገሉዋት አገራ ቸው እንደዚህ ያለ ውርደት ስለደረሰባቸው መሪር ሀዘን ያዘኑ፣ በብስጭ ትም ለጊዜው ሕሊናቸውን እስከማሳት የደረሱም ነበሩ።

በዚህ ወቅት በፓሪስ ከኢትዮጵያ ሌጋስዮን ጸሐፊነት እስከ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ለአገራቸው ያገለገሉትን፣ ክልጅነት እስከ ዕውቀት የነበራ ቸውን ምግባር በመዘርዘር የሕግ ባለሙያውና ታላቁ ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማትና የፖለቲካ ሰው /ስቴትስማን/ ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ በጽሁፍ መካላከያቸውን ለኮሚሽኑ አቀረቡ። ደርግ ፀጉራቸውን ላጭቶ፣ ከቤተሰብ የሚላክላቸውን ምግብ በመከልከል ከእስር ቤት በሚመጣ፣ አጣጥመው ሊመገቡት ባልቻሉት ምግብ ምክንያት ሰውነታ ቸው ተጎድቶ፣ ቅስማቸው ተሰብሮ ስለነበረ በጉንፋን በተዘጋ ድምፃቸው ከኮሚሽኑ አባሎች ለቀረቡላቸው አፋጣጭ ጥያቄዎች ሁሉ መስከረም 10 ቀን 1966 ዓ.ም መልስ ሰጡ ።

በምርመራው ወቅት ለተመርማሪዎች የቀረቡት ጥያቄዎችና መል ሶች ከሞላ ጎደል በራዲዮ ይሰሙ ስለነበረ፣ በቁጥጥር ስር የዋሉትን ሰዎች የመንፈስ ጭንቀት የሰማ አንድ አስተዋይ፡—

"ለነዚህ ሰዎች የሚፈርድላቸው የዘመኑ የሕግ ባለሙያ አይደለም፣ ታሪክ ነው እንጂ" ሲል በሚፈጽምባቸው ሁሉ ቅሬታውን ገለጸ።

ከኮሚሽኑ ምርመራ በሀዳር 12 ቀን 1967 ዓ.ም ቢጋዜጣ ታትሞ የወጣው ስለ ወሎ እልቂት ያደረገው ምርመራ ውጤት ብቻ ነበር። ኮሚሽኑ ሥራውን እንዲያቋርጥ ሲደረግ በ1969 ዓ.ም የመጨረሻ ሪፖርቱን ለመንግሥት አቅርቦአል።

የምርመራ ኮሚሽን ስለወሎ ምርመራ ውጤት በሀዳር 5 ቀን 1967 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት "በሕግ ያስጠይቃቸዋል" ያለው ሀዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም በግብታዊነት ደርግ ላደረገው የፖለቲካ ውሳኔ ግብዓት ኑሮት ይሆን?

፮

እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን

ንፁህ አየር ለመሳብ ፡ የተቃጠለውን ለማስወጣት በ1967 ዓ.ም. በጥቢው ወራት ከታላቁ ቤተ መንግሥት የዙፋን አዳራሽ አጠገብ ወደሚገኘው ሚዳ አስረኞች ከጉሮናአቸው ብቅ ብለው ፖናርድ የተባለ ታንክ መሰል ተሽከርካሪ ላይ የተጠመደ መትረየስ ተኩማጥሮባቸው ይንከላወሳሉ ። ብርድ የሚያሰቃያቸው ደግሞ ከሳሩ ላይ በደረታቸው ለሽ ብለው ሕመም በሚሰማቸው በኩል አካላቸውን የወሐይ ጨረር ያስመ ታሉ ። ዕለቱ ቅዳሚት ሀዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ግዚያቱም ከእኩለ ቀን በኋላ በ9 ሰዓት ነው ። ፀሐይ ለመሞቅና አየር ለመቀበል ሁሉም የወጣው በመጣደፍና ጊዜ በመሻማት ነበር ። የውጭው ሁኔታ ከመቆያ ክፍላቸው እጅግ የሚመረጥ በመሆኑ የመውጫው ሰዓት የሚጠበቀው በጉጉት ነበር።

በዚያች ዕለት ማለዳ ልዩ ልዩ ሕመም የሚሰማቸው ወደ ጦር ኃይሎች ሆስፒታልና ፖሊስ ሆስፒታል ተልከው ምርመራና የሕመም ማስታገሻ ተሰጥቶአቸው ተመልሰዋል ። ጥርሳቸውን ታክመው ከሆስፒ ታል ከተመለሱት መካከል ፈገግታ የማይለያቸው ፡ ገርጋዳው ልጅ እንዳልካቸው መኩንን የቀድሞ ፍሱህ ገጽታቸው ተለውጦ ነበር የተመለሱት ። ምክንያቱን የገለጹት ለቅርብ ወዳጆቻቸው ብቻ በመሆኑ ሌሎቹ እስረኞች አያውቁትም ። ሆኖም ደስ የማይል ቢሰሙ ይሆናል የሚል ግምት ሁሉም ወስጂል ። ጠጋ ብሎ ለማውጣጣት ግን ጊዜ አልነበረም ። ከእኩለ ቀን በኋላ ካለው የመንሸራሸሪያው ጊዜ በፊት ያለውን ጊዜ ያላለፉት ከጥቂቶቹ ጋር በመንሾካሾክ ነበር ። ያወያዩአቸ ውም ልውል ራስ አሥራት ካሣና ሌ/ጂኤራል አቢይ አበበ ናቸው ። እነርሱንም ጠይቆ ትክክለኛውን ሁኔታ ለማወቅ አልተቻለም ።

በዚያች ዕለት በዙፋን አዳራሽ ውስጥ ሁካታ ይሰማል ። የውካታው

ርዕስና የቃላት ልውውጡ ግን በግልጽ አይሰማም ። እስረኞቹ የእኩለ ቀን በኋላ የመንከላወሻ ጊዜአቸውን ጨርሰው ወደየጉሮኖአቸው ሲመለሱም ሁካታው አላቋረጠም ። መሸትሸት ፡ ደንገዝገዝ ሲል ሁሪያቸውን የተሸፈኑ ሁለት መኪናዎች መጥተው ከሽቦው አጥር ውጭ ከሁለት ቁጥር ክፍል በር ትይዩ ቆሙ ። ለእንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ከበሩ ሦር በሉ የሚል ትእዛዝ ከጠባቂዎቹ ተሰጠ ። ወዲያው የደርግ አባሎች ፡ የጥበቃው ኃላፊዎችና ወታደሮች ወደ ሁለት ቁጥር ጉራ ብለው ሻለቃ ጌታቸው ሺበሺና አንድ ሌላ የደርግ አባል ስም መጥራት ጀመሩ ። ከሁለት ቁጥር ስማቸው እየተጠራ ሀያ ሰባት እስረኞች እንደወጡ ፡ የአንዱን እጅ ከሌላው ሰው እጅ ጋር በሰንሰለት አቆራኙ ። አንዳንዶቹ በገጀማ ላይ ጋውን ወይም ጋቢ ደረብ አድርገዋል እንጂ የውጭ ልብስ አለበሱም ። እንደጣሪ ሞት እያጣደፉ ስለሚያስወጡዋቸው ልብስ ወይም የቤት ውስጥ ጫማቸውን ስንኳ ለመለወጥ አልተቻላቸውም። በአንድ ቁጥር የሚገኙት ግን የደረሰውን በሳንቃው በኩል ከሁለት ቁጥር ስለተነገራቸው በገጀማና በጋቢ ብቻ የነበሩት ልብስ ለመለወጥ ፡ ጫማ ለማጥለቅ ችለዋል ።

ከሁለት ቁጥር የሚፈልጉዋቸውን ሰዎች ስም ጠርተው እንዳስወጡ የብረት ፍርግርግ የሆነውን በሩን ዘግተው በባና ሸፈኑት ። ከዚያም ወደ አንድ ቁጥር አምርተው የሃያ ሰዎች ስም እየጠሩ አስወጡ ። ከዚህ ክፍል የሚደርስባቸውን ባያውቁም ከወንድማቸው ባለመለየታቸው ብቻ ሲጠሩ ፈገግታ ያሳዩትና "እንደዚህ ነው አሁን ደህና" ያሉት አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ ነበሩ ። ከአንድ ቁጥር እየጠሩ ያስወጡዋቸውንም እያቆራኙ ከአጥር ውጭ ወደቆሙት መኪናዎች ወሰዱአቸው ። ከአንድ ቁጥር ውስጥ የተጠሩት ጓደኞቻቸው ከበር ከወጡ በኋላ የቀሩት በክፍሉ አቀማመጥ የተነሳ የሆነውን ለማየት አልቻሉም ። በሁለት ቁጥር ያሉት ግን የተጠሩት ሰዎች የሚያልፉት በክፍላቸው በር አጠገብ በመሆኑ ፡ ምንም በሩ በባና ቢሸፈንም ከወለሉ ላይ በመንጠፍ በበሩ ደፍ የሚሆነውን ሁሉ አቶ ሀብተ ሥላሴ ታፈሰ ይመለከቱ ነበርና ከአስረኞቹ እያንዱ የተሰመረ ነገር አልነበረም ። ሌላው ቀርቶ ታመው በሆስፒታል በሙታ ከም ላይ የነበሩት ሌ ጂኤራል ኢሳያስ ገብረ ሥላሴና ያክተር ተስፋዬ ገብረ እግዚዕ እጆቻቸው በሰንሰለት እንደታሰሩ ከአንድ ላንድሮቨር ላይ መርደው ወደ እስር ቤቱ መኪና ሲዛወሩ ታይተዋል ። ዶክተር ተስፋዬ በምርመራ ሲያንገላቱዋቸው በደረሰባቸው ጉዳት ሆስፒታል አስገብተዋ

ቸው ስለነበረ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት አስቀድሞ አላመጡዋቸውም ነበር ። ሌ ጂኤራል ኢሳያስ ግን በአንድ ቁጥር ታስረው ሳለ ከቤቱ ከልክ ያለፈ ቀዝቃዛነት የተነሳ በብርድ በሽታ ይሰቃዩ ስለነበረ ፡ በብዙ ውትወታ ወደ ሆስፒታል ወስደዋቸው ነበር ። ለሁለቱም ከሕመማቸው እስኪድኑና እስኪያገግሙ ድረስ ስንኳ ጊዜ አልሰጡዋቸውም ። ከሆስፒታል አልጋ ላይ እስኑስተው እያዋከቡ አምጥተው ከእስር ቤቱ መኪና ውስጥ ከሌሎቹ እስረኞች ጋር ቀላቀሉዋቸው ።

በስም ጥሪው ጊዜ አንደኛው መኩንን በያዘው ሲስት መሠረት ስም ሲጠራ ፡ ሌላው መኩንን ይዞት ከመጣው መካከለኛ መዝገብ ጋር ያመሳክር ነበር ። በሁለቱ መካከል ልዩነት የተፈጠረው በደጃዝማች ሐረጉት አባይ ስም ብቻ ሲሆን ፡ በዚያን ወቅት አንደኛው ለሌላው የተናገረው "የእርሳቸው ቅርቷል" የሚል ነበር ። ከዚህም የተነሳ እርሳቸው አልተወሰዱም ። እስረኞቹን እያጣደፉ ሲወስዱዋቸው ከቀሪዎቹ አንዱ ከበራፉ ላይ ቆሞ የጥቂቶቹን ኃላፊ "እገሌ መድኃኒቶቹን አልወሰዱምና እባክህ ይዘችን የመድኃኒት ብልቃጥ ስጥልኝ" ብሎ ሲጠይቀው ፡ "አውን ስለሚመለሱ መስጠት አያስፈልግም" የሚል መልስ ሰጠው ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የደርግ አባሎች ከርቀቱ ላይ ያመኑ ስለነበረ ፡ በትርምስ መካከል ጠርሙስ ሲንቃጨል ይሰማ ነበር ። የተጠሰኑ የደርግ አባሎችና ጠባቂዎቹ ግን በእስር ቤቱ አካባቢ ይንቆራጠጡ እንደነበር በሞላንሞል ታይተዋል ። መደናገጥም ይታይባቸው ነበር ። የፈሩት እጃቸውን በሰንሰለት የታሰሩትን ወይም በክፍል ውስጥ ቀርቅረው የዘገባቸውንና ዓይን የሚያጠፋ ኃይለኛ የባውሃ ብርሃን የጠመዱባቸ ጐን ቀረምቹን እስረኞች እንደሆነ ያወቀ የለም ። የገዛ ሕሊናቸውን አለመ ቦኑ ግን እያጠያይቅም ።

ተጠርተው ሲወጡ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን በመገመትም እንደሆነ እንጂ በአጠገባቸው የሚገኙትን ንቡረ ዕድ ገብረ ሥላሴ ወሐዙን "ይፍቱኝ" ብለው ፡ መስቀል ተሳልመው የወጡት ሌ ጂኤራል ደበብ ኃይለ ማርያም ናቸው ። በተረፈ ሐያጆቹም ፡ ቀሪዎቹም በድንጋጤ ተውጠው ፡ በሞንቀት ተጠምደው ሳሉ ፡ የተለዋወጡዋቸው ታላት "እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን" የሚሉ ነበሩ ፡ እስከመጨረሻው እምነታቸው በፈጣሪያቸው ነበርና ።

፯
የሰው ፊት ግርፋት

እስረኞች ከአራተኛ ክፍለ ጦር ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት እስከተዛወሩበት ጊዜ ድረስ ቤተሰብ በተቻለው ስንቅ ለማቅረብ ተግደረደረ ። የወር ገቢ በመቋረጡ ፡ ንብረት በመከበሩ ፡ ከባንክ ሂሳብ ያላቸውም ስንኳ እንዳያወጡ በመታገዱ ሁሉም ብርቱ ችግረኛ ሆነ ። ችግር ጓዙን ጠቅልሎ ከእስረኞች ቤት ገባ ። የቤተሰብ መተዳደርያ አስገኝ የሆነው አባወራ ሲታሰር ቤተሰቡም ጦም አዳሪ ፡ የሰው እጅ ተመልካች መሆን የግድ ሆነበት ።

በ1967 ዓ·ም በወርሀ ጥቅምት በዕለተ ቅዱስ ሩፋኤል ነበር የፖሊቲካ እስረኞች ከአራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት የተዛወሩት ። በተዛወሩበት ስፍራ እስረኞቹ እንዲተኙ የተደረገው እንደበፊቱ መንግሥት ባዘጋጀው አልጋና ፍራሽ ላይ ነበር ። ከጥቅምት 1 ቀን 1967 ዓ·ም ጀምሮ ለቀለብ ማቅረቢያ በወር አንድ መቶ ሀያ ብር የተወሰነላቸው መሆኑ የተገለጸላቸውም ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት በተዛወሩ በሶስተኛው ቀን ነበር ። በወኪላቸው አማካይነት እስከ የካቲት 30 ቀን 1969 ዓ·ም ይኸው ገንዘብ ሲከፈላቸው ቆይቷል ።

ከመጋቢት 1 ቀን 1969 ዓ·ም ጀምሮ ግን ይኸውም በዛ ተብሎ ለቀለብ ማቅረቢያ እየተባለ እምላ ብር ብቻ እንዲከፈላቸው ተደረገ ። የደርግ ርኅራኄ ቁልቁል የሚያዘቅጥ ሆነና ይኸውም ከመጋቢት 30 ቀን 1970 ዓ·ም ጀምሮ ከነአካቴው ተቋረጠ ። ይህ ክፍያ የቀጠለው በጣት ለሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ነበር ። ደርግ የሚራራለትም በመገኘቱ ያልተደነቀ አልነበረም ፡ ከደርግ እምብዛም በጉ ነገር አይጠበቅም ነበርና ።

ይህ ገንዘብ ለስንቅ ማቅረቢያ ቀርቶ ስንቅ ለማቅረብ ለመመላለሻም

ስንኳ የማይበቃ መሆኑ ሲታወቅ ፣ መቋረጡ እስረኞቹ ለጤና እጠባበቅ በጣም የሚያስፈልጋቸውን እንደላሙናና የመፀዳጃ ወረቀት /ሶፍት/ ያሉትን ስንኳ ከቤተሰብ ከመጠየቅ በተቻለ መጠን እንዲታቀቡ አደረጋ ቸው ።

ቤተሰብ ጠሙን ውሎና አድሮ ለእነርሱ ቁመተ ሥጋ ምግብ ሲልክ እንዴት እንደዚህ ያለውን እንጠይቃለን የሚል ሥጋት አሳደረባቸው ። በዚህም ምክንያት የሚላክላቸውን ምግብ ቆርሰው ሲጐርሱ የቤተሰባ ቸው መቸግር ፣ መራብ ፣ መታረዝ ፣ የሰው ፊት ማየት ፣ መቆራመድ እየታሰባቸው ምግቡ የሚያንታቸው ሆነ ። ምግብ ሳይሆን የቤተሰባቸውን ሥጋ ቆርሰው እርም እንደሚበሉ መስሎ ተሰማቸው ፣ ስለዚህም በምግብ ሰዓት ሰውነታቸውን ይሰቀጥጣቸው ጀመር ።

የቀለብ ማቅረቢያ ተብሎ የተወሰነው እጅግ አነስተኛ አበል ገንዘብነቱ ሳይሆን አለኝታነቱ ነበር ዋጋ የነበረው ። ይኸውም የማያወላዳ ገንዘብ ተመናምና በመጨረሻ መቋረጡ እስረኞቹን ያሳጣቸው ይህንኑ አለኝታነቱን ብቻ ሳይሆን ፣ በረሀብ እንዲያልቁ እንደተወሰነባቸው ስለቆጠሩት የመኖር ተስፋንም ጭምር ነበር ። ቀቢፀ ተስፋ በሰው ላይ ምንን እንደሚያሳድር የሚያውቀው የደረሰበት ብቻ ነው ።

ቋሚ ገቢ ከተቋረጠ ፣ በረጅም ጊዜ የተፈራ ቅርስ ስንኳ ቢኖር ያልቃል ፣ ያውስ ስንቱ ነው የሚያወላዳ ቅርስ ያለው ። ጌጥም የቤት ዕቃም፣ ልብስም ቢሸጥ ለብዙ ጊዜ አያቆይም ፣ ያልቃል ። በዘመናችን ከሰማይ መና አይወርድም ። ታዲያ ለዘመናት በምን ይኖራል? ለጎብረተ ሰብዓዊነት ቆሜአለሁ የሚል መንግሥት ላለራቸው ፣ ንብረታቸውን ለወረሳቸው ሰዎች ምግብ ስንኳ ሲነሳ ምን ይባላል?።

ስለዚህ ያ ሕይወት ሲያስቡት ይዘገንናል ስንኳስ ሲኖሩት ። ወዳጅ ዘመድ ፣ ለጋሽም ይሰለቻል ሲበዛበት ። በዚያ ላይ የደርግ የኢኮኖሚ መመሪያ በሕዝቡ ላይ ያደረሰው ሚና ሁሉንም አርገድግዶታል ። ቀንበሩን ሕዝቡ ለመሸከም ተስኖታል ።

እስረኛን በዚያን ወቅት የሚያስጨንቀው ፣ ተስፋ የሚያስቆርጠው የእስራቱ ክብደት ብቻ ሳይሆን ፣ እንደዚህ ያለውን ሁኔታ ሌት-ተቀን ማሰላሰል የሕይወቱ ተጓዳኝ መሆኑ ነው ። ከዕለት ወደ ዕለት እየተካበደ የሄደው ፣ ዘወትር የማይለየው ጭንቀት የእስረኛውን ብቻ ሕሊና አይደለም የሚፈታተነው ፣ የቤተሰቡንም ጭምር እንጂ ። ''ልጅ ታመመ፣

ለትምህርት ቤት የሚከፈል ታጣ'' የሚል ደብዳቤ ከቤተሰብ ሲደርስ የሚሰማው እንጀት ኩምትር የሚያደርግ ፣ ቆሽት የሚያሳርር ሁኔታ የደብዳቤውን ተቀባይ ብቻ ሳይሆን የጻፈውንም ሰው ልቡና እንደሚቦረ ቡር አያጠያይቅም ።

ቤተሰብ ከቤት የተገኘውን ምግብ ለእስረኛ የሚያቀርበው ጦም ውሎና አድሮ ፣ ለምኖና ተለቅቶ ፣ የሰውም ፊት ገርፎት ነው ። በዚህ ላይ ምግብ ይዞ ሲመጣ ያለው መገልመጥ ፣ ማዋከብ ፣ የፍተሻው ጋጋታ እጅግ የሚያስመርር በመሆኑ ጦም ውሎ ባደረ እንጀት የሚቻል አልነበረም ።

ለእስረኞቹ የቀለብ ማቅረቢያ ገንዘብ መወሰንና በአልጋ ላይ እንዲተኙ ማድረግ በሰብዓዊ ርኅራኄ ሳይሆን ለፖለቲካ ዓላማ የተደረገ ሳይሆን አልቀረም ። የእስረኞቹን ይዞታ ለማየትና የሰብዓዊ መብት መከበርን ለማረጋገጥ የኢንተርናሽናል ቀይ መስቀል ኮሚቴ እስረኞቹን ለመጐብኘት ጥያቄ አቅርቦ ስለነበረ በሚገባ ይዘዋቸዋል ይሉናል በማለት ይምሰላል በአልጋ ላይ እንዲተኙ የተደረገው ። የቀይ መስቀል ልውካን ከብዙ ጉትጐታ በኋላ እስረኞቹ ያሉበትን ሁኔታ በታህሣሥ 8 ቀን 1967 ዓ·ም ጉብኝተው ከሄዱ በኋላ ነበር አልጋ ወጥቶ እስረኞቹ መሬት ላይ እንዲተኙ የተወሰነው ። ከቤተሰባቸው ዘንድ ሽራ አልጋ ስንኳ እንዲገባላቸው ባለመፈቀዱ ከህዳር 15 ቀን 1970 ዓ·ም ጀምሮ በቀዝቃ ዛው መሬል ላይ የደቀቀ እሮጌ ፍራሽ አንጥፎ መተኛት የግድ ሆነ ። በቁስል ላይ ጥዝጣዜ ተጨመረ ።

ሌላው የእስረኛውን ሕሊና የሚገዘግዘው የቤተሰቡን ሁኔታና ጤንነት ለማወቅ በየጊዜው ለመገናኘት አለመቻሉ ነበር ። ከቤተሰብ ጋር ለመተያየትና ለመነጋገር የተወሰነው በዓመት ሶስት ቀን /የዘመን መለወጫ ፣ የገናና የትንሣኤ/ ዕለት ብቻ ነው ። በሌላ ጊዜ ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት ሲያስፈልግ የእስር ቤቱን ሹማምንት ማስፈቀድ ያሻል ። ፈቃዱ የሚሰጠውም እነርሱ የሚያምኑበት ምክንያት ሁኖ ሲገኝና ያውም የእስር ቤት ኮሚቴ ሲቀበለው ብቻ ነው ። ይኸውም ሁኖ በብዙ ልመና የሚገኘው የቤተሰብ መገናኛ ጊዜ በጣም ውሱን በመሆኑ በሰፊው ተጠያይቆ ናፍቆትን ለመወጣትና ቁም ነገር ለመነጋገር አይበቃም ። መሣሪያ ባንገበ ወታደር ተከቦ የሚነጋገሩት ፣ ለወታደሮቹ እንዲሰማ ተደርጐ የሚለዋወጡት አሳብ ወይም ሰላምታ ድሮስ ምን ሊያረካ!! መተያየቱ ለእፍታ የማስደሰቱን ያህል ሲለያዩ የሚቀሰቅሰው ስቅቀን ፣

ሊናገሩት ያሰቡትን ሳይጨርሱ ተገዶ መለያየቱ የበለጠ ቁጭት ያሳድራል።

በ1967 ዓ.ም በትንሣኤ ዕለት የእምሐ ገብርኤል ቤተሰቦች እንደሌሎቹ ሁሉ ሊጠይቁት ሲመጡ ፡ የአራት ዓመቱ የበኩር ልጁ ተሾመስገን በእግሩ ድክድክ እያለ ፡ የሶስት ወሩ ሁለተኛው ልጁ ኑርልኝ በእቅፍ ተይዞ ከባለቤቱ ከወይዘሮ ንግሥት ዘውዱና ከሰባት ቤተሰብ ጋር ከመጮብኛው ስፍራ ደረሱ ። እስረኛው ከሽቦ አጥሩ ውስጥ ቤተሰብ ከሽቦው ውጭ በሶስት ሜትር ርቀት ከተዘረጋ ገመድ በስተኋላ ሁኖ ፡ ጮክ ብለው ነበር የሚነጋገሩት ። ከሌላው ሰው ንግግር መካከል በሚገባ መስማማት አይችሉም ነበር ። በዚያን ሰሞን "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚል በደረት ላይ የሚደረግ ምልክት ደርግ በቆርቆሮ አሠርቶ ለሕዝብ ይሸጥ ነበር ። ምንም ስንኳ "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" ከሚለው መፈክር "ያለምንም ደም" የሚለውን መንደርደሪያ ሐረግ ደርግ እጁን በሰው ደም በመታጠቡ በግብሩ ገና ድሮ ያስቀረው ቢሆንም "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን ኃይለ ቃል የያዘውን ምልክት /ባጅ/ አስረኞችም ጭምር እንዲገዙ አድርጉ ነበር ። ይህንኑ ምልክት አመሐ ገብርኤል ከቤተሰብ መገናኛው ዕለት ከደረቱ ላይ ለጥፎት ነበርና ከወራት መለያየት በኋላ የበኩር ልጁ አባቱን በሩቅም ቢሆን ሲያገኘው ልጁ ስጦታ ወይም ያማረውን መጫኖቁ የነበር በመሆኑ ፡ ያችን ምልክት እንዲሰጠው አባቱን ጠየቀው ። ከደረቱ እንስቶ ሊሰጠው እጁን ተንጠራርቶ ሲዘረጋ ንግግር ለመቆጣጠር በመካከላቸው የቆመው የዘብ አለቃ ሕግኑን በጣም በሚያስደንግጥ ድምፅ "እይቻልም ወደኋላ ተመለስ" ሲል አምባረቀበት ። ልጁ ደንግጦ የዘረጋውን እጁን ሳያጥፍ ወደኋላው ሲመለስ ፡ እምሐ ገብርኤል በጣም በማዘን እንባና እልህ ስለተናነቀው ቆሞ ለማነጋገር አላስችል ብሎት ናፍቆእቸው የነበሩትን ቤተቦቹን ለተወሰነውም ጊዜ ስንኳ ሳያነጋግር ወደ ጉሮኖው ተመለሰ ። ቀደም ብሎ "አባቴ ምነው አይመጣ? ወዴት ሄደ?" እያለ ተመስገን ለሚያቀርበው ጥያቄ "ለሥራ ወደ ውጭ አገር ሄዶ ነው ፡ በቅርቡ ይመጣል" እየተባለ የሚነገረውን በማመን የአባቱን ወደ ቤቱ መመለሻ ቀን በጉጉት ሲጠባበቅ ሳለ አባቱ በጦር መሣሪያ ተከቦና ሊሰጠው ያሰበውንም ሲከለከል በማየቱ የሚነገረው ሁሉ መደለያ እንጂ እውነት አለመሆኑን ተረዳ ። በወታደሩ ቁጣና በእያረገው ማስፈራራት መደንገጥ

ብቻ ሳይሆን የወታደር ጥላቻም እደረበት ። ይህም የሚቆዝም ፡ ደስታ ያጣ ልጅ እደረገው ። የታላቁ ቤተ መንግሥት ትዝታው እያደር ምሬትን ፡ የቤተሰብ መለያየት ጉዳትን ፡ ወገን በወገኑ ላይ የሚፈጽመውን ጭካኔን ሁልጊዜ የሚያዘክረው ሆነ ። በራዲዮና በቴሌቪዥን በየዕለቱ ስለሚሰማው የእኅ መፍቻ ያደረገውን "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ፡ አቆርቋሂ ይውደም" የሚለውን በጉ ምኞትን ከእርግማን ጋር ያጣመረውን መዝሙር መዘመሩን እርግፍ አድርጉ አቆመ ።

እርሱ በሕግንነቱ ምክንያት ሲዘምረው ይቆይ እንጂ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው ከቀድሞው የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ የተወሰደው ትዕምርተ ጥቅስ ደርግ በየጊዜው በወሰደው እምርጃ ከፊትም ከኋላም እጃቢ አጥቶ እርቃኑን የቆረ ፡ በኢትዮጵያ ምድር ደም እንደጉርፍ የፈሰሰበት ፡ አገር የቆረቆዘበት ፡ ሕዝብ የደኸየበት በመሆኑ በአዋቂ መዘመሩ ከተቋረጠ ወራት አልፎአል ። ሕግኑ ተመስገንና መሰሎቹ ነበሩ የደርግ እካሄድ እየገባቸው እስኪሄድ የዘመሩት ። ምኞቱ በደርግ አመራር እውን እንደማይሆን ሲረዱትና ዐነርሱና በሌላው ቤተሰባቸው ላይ በሚደርሰው የሰው ፊት ግርፋት ሲጠበሱ ነበር የደርግን መፈክር ከራሱ ከደርግ ጋር አንቅረው እነርሱም የተፉት ።

፰

ተዘከር እንደ ኮምፒዩተር

በኢትዮጵያ ሕዋ ላይ የሥጋት ደመና ማንገሥበብ ፡ የለውጥ አየርም መንፈስ ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል ። ለውጡ ለበጐ ፡ ሽግግሩ ደግሞ ሰላማዊ እንዲሆን ሁሉም ይመኝ ፡ ለዚህም ይጥር ነበር ። ለአንድ መንፈቅ ጊዜ የለየለት ሁኔታ ባለመታየቱ አሳብ የገባው ግን ጥቂት አልነበረም ። የአገር ተወላጁ ብቻ ሳይሆን ፡ ባዕዱም ፡ ባሕር ማዶ ያለውም በሁኔታው ግራ ተጋብቷል ። መፍትሔ እንዲፈልጉም ንጉሠ ነገሥቱን ጐትጓቹ በዝቷል ።

ያንገበገበውን የሥጋት ደመና የሚገልጥ መስሎአቸው ነበር አልጋ ወራሻቸው ወራሲ መንግሥት መሆናቸውንና የአልጋ ወራሹም ወንድ ልጅ ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ አስፋ ወሰን ተክታዩ አልጋ ወራሽ መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ በ1966 ዓ·ም የትንሳኤ ዕለት በአደረጉት ንግግር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገለጹት ። በውጭ አገር በሕክምና ላይ የሚገኙት የአልጋ ወራሹም ልጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈቅዱ ከሆነ የተጣለበትን ኃላፊነት በደስታ እንደሚቀበል ጀኔቫ ላይ የጋዜጣ ጉባኤ ጠርቶ ለዓለም ያስታወቀው ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነበር ። ይሁን እንጂ ይህም የነበረውን ሥጋት አላስወገደውም ።

ከየካቲት 21 ቀን 1966 ዓ·ም· ጀምሮ ብቅ ጥልቅ ሲል ፡ ከሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ·ም ጀምሮ ደግሞ እንደ ኤሊ ጉሦ ሲያዘግም ፡ እንዴ እንጉቱን ሲያወጣ ፡ እንዴ ሲቀብር ከቆየ በኋላ ነበር ወታደራዊው ደርግ በመስከረም 2 ቀን 1967 ዓ·ም በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ፈጠጥ ያለው ።

"ንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋን ወርደው በአልጋ ወራሹ ተተክተዋል ።

አልጋ ወራሹ ወደ ኢትዮጵያ እስኪመለሱ ድረስ የጦር ኃይሎች ፡ የፖሊስ ሥራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ደርግ የመንግሥቱን ሥራ ይመራል" በማለት እታሞ እየመታ ለሕዝብ ያወጀው ።

ለማዘናጊያ ነበር ደርግ "አልጋ ወራሹ ለሕክምና ከሄዱበት አገር እስኪመለሱ ሥልጣን ይጎለሁ" ብሎ ያሳወቀው ። የሕዝብ ተቀባይነት ንም ለማግኘት ሲል ታዋቂውን ሌ/ጄኔራል አማን አንዶምን የደርግ ሊቀ መንበር አድርገናል ያለው ። ዕውቁኝ ፡ እቀፉኝ ፡ ሲል ደርግ ተማጠን ፡ በእንድ ንጉሠ ነገሥት ፈንታ 120 መስመራዊ መኰንኖችና ባለሌላ ማዕረጐች ነግሠው አንከሰስም ፡ አንወቀስም አሉ ።

በጥቅምት 10 ቀን 1967 ዓ·ም· ልዩ የጦር ፍርድ ቤት ተቋቋመ ። ሲቪሉም በጦር ፍርድ ቤት እንዲዳኝ ማድረጉን ደርግ አወጀ ። ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ አሳግባብ በእስተዳደር ባለሥልጣን የታሰረ ሰው ከፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚያስደርገውን (ሄቢየስ ኮርፐስ) አንቀጽን ነጠቅሶ ለፍርድ ቤት የማመልከትንና በዋስ ተለቆ የመከራከርን መብት የሚነፍግ ፡ የቅጣት መጠንንም የሚያካብድና ፀንቶ ባለው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ የሌለ አዲስ ቅጣት የሚደነግግ ፡ ወደኋላም ሄዶ ተፈጻሚ የሚሆን ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግና ልዩ የሥነ ሥርዓት ሕግ በማከታተል አወጣ ።

ይህ ሁሉ ሕገ መንግሥታዊ አለመሆኑን በቁጥጥር ስር ያዋሉዋቸው የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች ቢያውቁም ፡ "ሁሉም ነገር የሚፈጸመው በሕግ አግባብ ነው ፡ ጥሬው ከገለባው ይበጠራል ፡ ጥፋተኛው ከንፁሁ ተጣርቶ ይለያል" እያሉ የደርግ አባሎች ይምሉ ፡ ይገዘቱ ፡ እያከታተሉም መግለጫ ያወጡ ስለነበረ በዚሁ ቃል በመተማመን ፡ ሲሆን ጉዳያቸው ተጣርቶ ለመለቀቅ ፡ አለበለዚያም ከፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከር በተስፋ ሲጠባበቁ በምርመራ ኮሚሽን በኩል የሚሞሉት የመጠይቅ ቅጽ (ፎርም) እስር ቤት ድረስ ተላከላቸው ።

ከ1933 ዓ·ም ጀምሮ እያንዳንዱ እስረኛ በውርስ በግዢ ወይም በስጦታ ያገኘውን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቱን ዝርዝርና ዋጋ በውርስ ወይም በስጦታ ወይም በሽያጭ ለሌላ ያስተላለፈውን ፡ የገቢ ምንጩንና የወር ወጭውን እንደዚሁም ጌጥ የገዛበትን ወጭውን ጭምር በ34 ገጽ ፎርም ሞልቶ ለትክክለኛነቱ ቢቃለ መሐላ እንዲያቀርብ የሚጠይቅ ነበር ። በጠቅላላው ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በቁጥጥር

ስር እስከዋለበት ዕለት ድረስ የንቢና የወጭ ሂሳብ ሚዛን ፡ ከወጭ ቀረውን፡ የባንክ ሂሳብ ቁጥሩንና ያለውን ገንዘብ መጠን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ማቅረብ እንደሚያስፈልግም ቅጹ ይገልጻል ። በእጭሩ ጥያቄው ተዘክር እንደ ኮምፒዩተር የሚል ነበር ። ኮምፒዩተር ገና በኢትዮጵያ ሳይገባ ለአባሻ ለማይ ቅርቡ ነው እንደሚባለው ኮሚሽኑ በመዝገብ ያልተያዘ የዘመናት ንቢና ወጭ ሂሳብህን አስረዳ የሚል ጥያቄ አቀረበ ።

የወር ወጭን ለተለያዩ ዘመናት ለመተመን ፡ የቤት ሠራተኛን ደመወዝ ልክ ተጠያይቆ ለማወቅ ፡ እንደዚሁም ሌሎች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት ፈቃድ ሲጠየቅ እንደአስፈላጊነቱ ለማግኘት የደርግ ባለሥልጣኖች ፈቃደኛ አልነበሩም ። አንዳንዶቹ ጥያቄዎች ግልጽ ስለአልሆኑ ከኮሚሽኑ አባሎች ጠይቆ ለመረዳት ይቻል ዘንድ መጥተው እንዲያነጋግሯቸው እንዲደረግ ለሚቀርበው ጥያቄ አጥጋቢ መልስም አይገኝም ነበር ። ከምርመራ ኮሚሽን አባሎች ጥቂቶቹ እስረኞቹ ወደሚገኙበት መጥተው ያነጋገሩዋቸው ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር ። በመጀመሪያ ቅጹን ለማይል ፡ በሁለተኛው ጊዜ ለጥያቄ ነበር ። በሁለተኛው ጊዜ አንዳንድ መረጃዎችን ለማጠያየትና ለማጣራት ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት ጠባቂዎቻቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በተሟላ አኳኋን ፎርሙን ለማቅረብ መቸገራቸውን አስረዮቹ ገልፀው ፡ የማቅረቢያው ጊዜ እንዲራዘምላቸውና ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት እንዲፈቀድላቸው እንዲያደርጉላቸው ጠየቁዋቸው ። እነርሱም ይህን ለማስፈቀድ እንደሚሞክሩ ቃል ገብተው ነበር ። ሆኖም እንድም የተፈፀመ ነገር አልነበረም ፡ ማን ሰሚ ተገኝቶ !

ምርመራው ተጠናቆ ለመፈታት ወይም በፍርድ ቤት በመከራከር ፍትሕ ለማግኘት ተስፋ በማድረግ አስረኞቹ ሊያስታውሱ በሚችሉት መጠን ቅጹን ሞልተው በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ ተጣጣሩ ። በቃለ መህላ የሚሰጡት ማስረጃ በመሆኑ ግን መረጃ ለማቅረብ ያሉበት ሁኔታ ችግር ለእንጠመቁዋቸው ርዕሶች ወይም በጠቅላላው በቅጹ ላይ በቃልአባይነት ተጠያቂ ከመሆን ለመዳን "ሬዘርቬሽን" አስፍረው ለምርመራ ኮሚሽኑ የሞሉትን ቅጽ አስረከቡ ። ፍትሕ ለማግኘት ካላቸው ጉጉት የተነሳ ከታላቁ ቤተ መንግሥት በህዳር 14 ቀን 1967 ዓ·ም ከተወሰዱት አስረኞች አንዳንዶቹ ቅጹን በመጣደፍ ሞልተው በህዳር 10 እና 13 ቀን 1967 ዓ·ም አቅርበው ነበር ።

የአስረኞቹ ምርመራ የሚካሄደው በአንድ ማምባር ብቻ አልነበረም፡ በሁለት ፈት እንጂ ። ከአስረኞቹ አንዳንዶቹ በምርመራ ኮሚሽን እየተጠሩ ሲመረመሩ ፡ ከትጽ መሙላት በቀር ሌሎቹ በኮሚሽኑ አልተጠየቁም ። ቢሆንም ድርግ በታላቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ ባቋቋመው የምርመራ ቡድን ፊት እየቀረቡ ለሚተርብላቸው ጥያቄ ሁሉ መልስ መስጠት ነበረባቸው ። መሠረታዊው ጥያቄ ስም ፡ የአባትና ያያት ስም የሠራባቸው መሥሪያ ቤቶች ዝርዝርና ዘመን ፡ ያፈራውን ሀብትና የትውልድ ሀረግ ፡ በምርመራው ወቅት ያለውን ንብረት ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ፡ ከስ ወይም ስሞታ የቀረበበት ከሆነ ለዚሁም መልስ እንዲሰጥ እያንዳንዱ አሰረኛ ይጠየቃል ። የእንዳንዶቹ እስረኞች ምርመራ በአንድ ቀን ሲያበቃ ፡ የሌሎቹ ብዙ አመላልሷል ።

አምሐ ገብርኤል ከምርመራ ቡድኑ በንድ የቀረበው በጥር 19 ቀን 1967 ዓ·ም ብቻ ሲሆን ፡ የቀረበለት ጥያቄ መሠረታዊው ጥያቄ ብቻ ስለሆነ ለዚሁ መልስ ሰጥቶና በምርመራው ስንድ ላይ ወዲያው ፈርሞ ከተመለሰ በኋላ በድጋሚ አልተጣራም ።

ከምርመራ ኮሚሽን ፊት የቀረበው በተከሳሽነት ሳይሆን በምስክርነት ፡ ከመታሰሩ በፊት በጳጉሜን 3 ቀን 1966 ዓ·ም ነበር ። የቀረበለትም ጥያቄ ከወሎ ጠቅላይ ግዛት የተመረጡ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባሎች ስለደረሰው ረሀብ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ያቀረቡት አቤቱታ ስለአገኘው ውሳኔ የሚያውቀውን በምስክርነት እንዲያስረዳ ነበር ። ለዚህም ጥያቄ አምሐ ገብርኤል የሰጠው መልስ በአጭሩ እንደሚከተለው ነበር ።

በጥቅምት 29 ቀን 1966 ዓ·ም የወሎ ጠቅላይ ግዛት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባሎች በወሎ በድርቅ ምክንያት በሕዝቡ ላይ ችግር በመድረሱ የግብር ምህረት እንዲደረግለት በማሳሰብ የጻፉትን ማመል ከቻ ይዘው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ከእርሱ ቢሮ ድረስ መጥተው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድ እንዲያቀርባቸው በፓርላማ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተወካይ በመሆኑ በእላቸው የሥራ ግንኙነት ምክንያት ጠየቁት ። እርሱም ወዲያው ለማገናኘት ሞክሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰጊዜው ከእንግዳ ጋር በመሆናቸው ሳይቻል ቀረ ። በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ይህን የመሰለውን ጉዳይ የሚከታተለው አምሐ ገብርኤል ኃላፊ የሆነበት ቆሕግና የፓርላማ ጉዳዮች ዋና መምሪያ ሁኖ

ሳይሆን ፡ በሥራው ጠባይ ምክንያት ከፓርላማ አባሎች ጋር ቅርብ የሥራ ግንኙነት ያለው ከመሆኑ የተነሳ ፡ እንግዳው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድ እንደወጡ ማመልከቻውን በማቅረብ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀጠሮ እንደሚጠይቅላቸው ነግሮአቸው አባሎች ተመልሰው ሄዱ ። እንግዳው እስኪ ወጡ ጠብቆ የፓርላማ አባሎች የጻፉትን ማመልከቻ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቦ በማንበብ ስለዚሁ ጉዳይ ሊያነጋግሩዋቸው መጥተው እንደነበር ገለጸላቸው ። እርሳቸውም ወዲያው ለአገር ግዛት ሚኒስትሩ ለአቶ ጌታሁን ተሰማ ስልክ በመደወል ሰሞኑን ንጉሠ ነገሥቱ ለጉብኝት ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደሚሄዱና የወሎ እንደራሴዎች የጻፉት ማመልከቻ እንደሚላክላቸው ገልፀው የተጠየቀውን የምሀረት ጉዳይ በአዋጁ መሠረት እርሳቸውና የገንዘብ ሚኒስትሩ በቶሎ አጥንተው እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጡ ። መጥተው ለነበሩት የፓርላማ አባሎችም ይህንኑ እንዲያስታውቃቸው ለእምሐ ገብርኤል ነገሩት ።

ድኋላ ሥራ ጉዳይ እምሐ ገብርኤል በጠቅላይ ሚኒስትሩና በልዩ ጸሐፊያቸው ቢሮ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ወደቢሮው ሲመለስ ፡ አቶ ጌታሁን ተሰማ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲመጡ በር ላይ ስለአገኛቸው "ቅድም በስልክ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ስለተነጋገራችሁበት ጉዳይ የተጻፈው ማመልከቻ ይህ ነው" ብሎ በእጅ ሰጣቸው ።

አቶ ጌታሁንም እንደትእዛዙ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ከአቶ ሚሞ ታደሰ ጋር በመመካከር ቀደም ብሎ ከጠቅላይ ግዛቱ የቀረበውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ የምሀረቱን ጉዳይ አጥንተው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ወሎ ሲሄዱ የሚነገረውን አዋጅ ቃል አዘጋጅተው ናር ፡ በሀዳር ወር መጀመሪያ ሳምንት ውስጥ የተባለው አዋጅ ደሴ ላይ ለሕዝብ ተነገረ ። በጋዜጣም ታትሞ ወጣ ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ጥቂት የወሎ ጠቅላይ ግዛት የሕዝብ እንደራሴዎች ከፓርላማው መግቢያ በር ላይ አምሐ ገብርኤልን አግኝተውት ፡ በችግሩ ምክንያት ከወሎ ወደ ሸዋ የሚመጡት ሰዎች ካራ ቆሬ እጠገብ ከጃራ ወንዝ እንዳይሻገሩ ተከልክለው በብርቱ ችግር ላይ መሆናቸውን ስለነገሩት አባሎቹ ባሉበት ወደ አገር ግዛት ሚኒስቴር ስልክ ሲደውል ሚኒስትሩ ለሥራ ጉዳይ ወደ ውጭ አገር መሄዳቸው ተነገረው ። ከእርሳቸው ቀጥሎ ላሉት ባለሥልጣን (ለሚኒስትር ደኤታው) ለአቶ* ለገሠ በዙ የአባሎቹን ቃል በመግለጽ ተቀብለው እንዲያነጋግሩዋቸውና

* በኋላ ደጃዝማች

ደርቧል ለተባለውም ችግር በቶሎ መፍትሔ እንዲፈልጉለት አሳሰበ ። በዚያው ዕለት ከእኩለ ቀን በኋላ የአገር ግዛት ሚኒስትር ደኤታው ሊያነጋግሩዋቸው ቀጠሮ መስጠታቸውንም ለአባሎቹ ገለጸላቸው ። ጉዳዩ በቶሎ እንዲያልቅላቸው ለመርዳት እሱም በቀጠሮው ሰዓት ከአገር ግዛት ሚኒስቴር እንደሚገኝ አረጋገጠላቸው ።

በቀጠሮው ሰዓት ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ተገኝቶ የሕዝብ እንደራሴዎቹ ደርቧል የተባለውን ችግር ለአቶ ለገሠ በዙ ሲያስረዱና ሚኒስትር ደኤታውም በበኩላቸው ደርቧል ስለተባለው ችግር ጊት በስልክ እንደተነጋገራቸው ከወሎ ወደ ሸዋ ግዛት እንዳያልፉ የታገዱ ሰዎች አለመኖራቸውንና የወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃ በወሎ ረሀብ መኖሩን እንደማያውቁ እንዳረጋገጡላቸው ለአባሎቹ ሲገልጹ አላምጪል። በዚሁም ጊዜ የሕዝብ እንደራሴዎች ከግዛቱ እንደራሴ ተሰጠ የተባለውን ቃል በማስተባበል በሕዝቡ ላይ ችግር መድረሱን በመረረ እንጋገር ስለገለጹ አቶ ለገሠ በዙ ሁኔታውን የሚያጣራ ቡድን ወደ ስፍራው ስለሚልኩ የስምንት ቀን ጊዜ እንዲሰጧቸው ጠየቁ ። የሕዝብ እንደራሴዎቹ በዚሁ ስለተስማሙ በቀጠሮ ተለያዩ ።

ከዋቂት ቀናት በኋላ የወሎ የረሀብ ጉዳይ ለሕግ መምሪያ ምክር ቤት ቀርቦ የወሎ እንደራሴዎች ማመልከቻ ከተሰማ በኋላ አስረጂዎች እንዲቀርቡ ለመወሰኑ ከፓርላማ በመጻፉ አምሐ ገብርኤል በቀን ቀጠሮው አስረጂዎች እንዲቀርቡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ለአገር ግዛት ሚኒስቴርና ለሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ደብዳቤ ጻፈ ። በቀጠሮውም ቀን የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ሙላቱ ደበበ ፡ የአገር ግዛት ሚኒስትር ደኤታ አቶ ለገሠ በዙ በአስረጂነት ቀርበው አምሐ ገብርኤል በአለበት የጥያቄና መልስ ልውውጥ በሕግ መምሪያ ምክር ቤት ጉባኤ ላይ ተደረገ ።

በዚህ ጊዜ ነበር አቶ ለገሠ በዙ ከወሎ እንደራሴዎች በቀረበው ጥያቄ መነሻነት ደርቧል የተባለውን ሁኔታ ለማጣራት በቀኛዝማች ማሞ ወልዴ ሰንበት መሪነት አንድ ቡድን ልከው እንዲጣራ ማድረጋቸውንና ብዙ ሰው ስለተራበ እህል በቶሎ እንዲላክ ቡድኑ በቴሌግራም መጠየቁን ለምክር ቤቱ ጉባኤ የገለጹትና አቶ ሙላቱ ደበበም የሚያስፈልገው እርዳታ በቶሎ እንደሚላክ ያረጋገጡት ። የሕግ መምሪያ ምክር ቤትም በጉዳዩ ሰሰፈው ከተነጋገረና ከተከራከረ በኋላ ለተራበው ሕዝብ አስፈላ

ጊው እርዳት በአስቸኳይ እንዲላክ ወሰነ ።

ይህን ነበር አምሐ ገብርኤል ለምርመራ ኮሚሽን ጉባኤ የገለጸው ። ይኸው ቃሉም ነበር በመስከረም ወር 1967 ዓ·ም በራዲዮ ለሕዝብ የተነገረው ።

ከምርመራ ኮሚሽንም ሆነ ከደርግ ልዩ የምርመራ ቡድን ለቀረቡለት ጥያቄዎች አምሐ ገብርኤል በሚገባ መልስ የሰጠ ቢሆንም "ጥፋተኛ ውና ንፁሁ በምርመራ ይጣራና ጥፋተኛ ያልሆነው ይፈታል ፣ ጥፋተኛ ውኖ የተገኘውም ለፍርድ ቤት ይቀርባል" ሲል ደርግ አስቀድሞ እንደሰጠው ቃል አልተፈጸመም ። ተዘክር እንደነም·ፑፑተር የሚለውንም የምርመራ ኮሚሽን ቅጽ ሞልቶ በጊዜው ቢያቀርብም የደርግን ቃል አውሶ ነፍስ ከሰማይ ሳይ ያዙት በመጥፋቱ መፈታቱ የሕልም ሩጫ ውኖበት ቀረ ። ይህም መጥፎ እድል የአምሐ ገብርኤል ብቻ ሳይሆን የሌሎችም ነበር ።

፱
ፀለምት ቅዳሚት

በታላቁ ቤተ በመንግሥት የዙፋን አዳራሽ አካባቢ ትርምስምስ በተፈጠረበት በ1967 ዓ·ም ህዳር 14 በዕለተ ቅዳሚት ምሽት፡ መትረየስ የተጠመደባቸው ጂፖችና፡ ሳንጃ የወደሩ የደርግ ወታደሮች የከበቡዋቸው ሁለት የእስር ቤት መኪናዎች ወደ ዙፋን ቤት ምድር ቤት መግቢያ ቀረቡ። የደርግ አባሎች ወሳኞች ብቻ ሳይሆኑ ፡ ውሳኔ አስፈጻሚዎችም ሁነው ሽር ጉዱን ካሳመሩበት ምሽት ቀደም ብሎ በቀኑ፡ በቀድሞው አውሮፕላን ማረፊያ የልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ይባል ከነበረውና አሁን የጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተብሎ ከተሰየመው ቤተ ሕክምና አጠገብ "እጅ ስጥ፡ አልሰጥም" በማለት ግብ ግብ ተፈጠረ። ታንክ በጦር ሜዳ ሳይሆን በመኖሪያ ቤት አካባቢ ተርመሰመሰ። እንደቡልዶዘር ቤት ሊያፈርስ ሰው ሊድጥ ተሰማራ። ወንዱ የመሸጉበት መኖሪያ ቤት ተመጣጣኝ ባልሆነ የጦር መሣሪያ ተደበደበ። ከአቅራቢያው የሚኖሩ ሰዎችና የሆስፒታሉ ሕመማን በተኩሱ ልውውጥ ተሸበሩ፡ ሰላም አጡ።

ተታኩሰው ጉዳት ካደረሱ በኋላ የሚፋጅ እጃቸውን ሳይሆን በታንክ የተጻጠ፡ በጨካኝ ጥይት እንደወንፊት የተበሳሳ አካላቸውን ጥለውላቸው አለፉ፡ ወደማይቀርበት ዓለም በክብር ተሸጋገሩ።

የዚህ ጽዋ ቀማሽ የሆኑት "ኮዳ ትራሱ ፡ቆራጡ ጀግና፡ የኢጋዴኑ አንበሳ አዛዥ" እያሉ የደርግ አባሎች ሞምር ያቆላምጡዋቸው የነበሩት፡ በሠራዊቱም ሆነ በሲቪሉ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲል ደርግ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ·ም የደርግ ሊቀ መንበር ብሎ የሾማቸው

ከፍተኛ መኰንን፣ ሌ/ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ነበሩ። ይህ ከመሆኑ ከጥቂት ቀናት በፊት በደርግ አባሎችና በጀኔራል አማን መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ የሊቀ መንበርነት ቢሮአቸውን ለቀው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ሄደው መሸጉ። የእርሳቸው ራስን ማግለል ከተሰማ በሐረርጌ የሚገኘው የሶስተኛው ክፍለ ጦር ባልደረቦች ከእርሳቸው ጋር በማበር በደርግ ላይ ይነሳሉ በማለት ነበር የደርግ አባሎች እጅግ የተደናገጡት።

ጀኔራሉ ተላልከው ጦር እስኪያስመጡ ድረስ ጊዜ ሊሰጡ አልፈለ ጉም። ይህም የሚያስከትለው መዘዝ (ሪስክ) ሊቋቋሙት የሚቻላቸው መስሎ አልታያቸውም። ለፍትህ መጠበቅም አክብሮት አልነበራቸውም። ዓላማቸው እርሳቸውን ገድሎ ከተፈራው ሥጋት መዳን ብቻ ነበር። ስለዚህ በጦር ኃይል ቢቻል ጀኔራል አማንን ከነሕይወታቸው ለመያዝ፣ ካልተቻለ ደግሞ በመኖሪያ ቤታቸው እንዳሉ በኃይል ለመደምሰስ ወሰኑ። የራሳቸው ጀግና አርገው ይመኩባቸው የነበሩትን፣ እውነተኛ ሳይሆን የይስሙላ የደርግ መሪ አድርገው ለሕዝብ ያቀረቡዋቸውን ከፍተኛ መኰንን ይመሰሉ።

ለዚህ እድራጎታቸው ማደናገሪያ ወይም ጀኔራሉን ከሚደግፈው ጦር የሚነሳውን ተቃውሞ ለማብረጃ ይበጃል በሚል እጉል እስተሳሰብ፣ ያለፍርድ ቤት ብያኔ ሰው መግደል በሕግና በታሪክ የሚያስወቅስ መሆኑን በመዘንጋት፣ ግብታዊ የመግደል ጥማታቸውን ለማርካት ሲሉ ፊታቸውን በታላቁ ቤተ በመንግሥት የዙፋን አዳራሽ ስር ወደሚገኘው ዋሻ አዞሩ።

በታላቁ ቤተ መንግሥት ዙፋን አዳራሽ ስር በሚገኝ ደይን ውስጥ በእስር ላይ ከሚገኙት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የቀድሞ ባለሥልጠኖች መካከል አርባ ሰባቱን በስም እየጠሩ በማስወጣት እጃቸውን በሰንሰለት አስሩ፣ በመገፍተር ከአጥር ውጭ በማስወጣት ዙሪያቸውን በተሸፈኑ የእስር ቤት መኪናዎች እያጉሩ አጓዟቸው። በደርግ አመራር ባለመደሰት ተቃውሞ ያሳዩትን የከብር ዘበኛ የንዑስ ደርግ አባሎችና የምድር ጦር የመሀንዲስ መምሪያ ባልደረቦች የሆኑ ጥቂት መስመራዊ መኰንኖችና ፣ የበታች ሹማምንት፣ ሌሎችንም በድምሩ አሥራ ሶስት ሰዎች ከሌሎች የደርግ የማሠሪያ ቦታዎች አሰባስበው የዚሁ ጉዞ ተጓዳኝ እንዲሆኑ አደረጉ።

በዚህ ወቅት የደርግ አባሎችና ታጣቂዎቻቸው ለእነዚህ ቀን ለጣላቸው ፣ ጊዜው ለመሸባቸው ምስኪን ሰዎች የሚያሳዩዋቸው ከንፈር መንከስ፣ ግንባር ማኮማተር፣ ክፉ እመለካከት ወደ አልታወቀ መዳረሻ የሚያደርጉትን ጉዞ ስቃይ የተካበደ እደረገው። የጠለቀችውን ጀምበር መልሶ የማየት ተስፋ አሳጣቸው። እንዳንዶቹ ቢማጠኑም ነማ ጆሮ፣ የሚራራ ልቡና ሳያገኙ ቀሩ።

የቀድሞዎቹ ባለሥልጣናች የሽግግሩ ዘመን ሰላማዊ እንዲሆን በማሰብና የአገራቸው ሕዝብ ለዳኝነት ባለው ስሜት በመተማመን ነበር ከሚያዝያ 18 ቀን 1966 ዓ.ም ጀምሮ እጃቸውን የሰጡት፣ በእስቀመጡዋ ቸውም ስፍራ ሥነ ሥርዓት ጠብቀው የቆዩት። ደርግ ግን ለአሳዩት በጎ ፈቃድ፣ ለሽግግሩ ሂደትም ሰላማዊ መሆን ዋጋ ባለመስጠት፣ ደጉን በክፉ ለመለወጥ የታጠቀ ሆኖ ያልተጠበቀ እርምጃ መውሰድን መረጠ። ''አባቱ ደኛ ልጁ ቀማኛ'' እንዲሉ ራሱ ባቋቋመው ልዩ የጦር ፍርድ ቤት ስንኳ ባለመተማመን፣ ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ ዳኛ ሁኖ በማን አለብኝነት ቁጥጥር ስር በአዋለው በያንዳንዱ እስረኛ ላይ የሀሰት ክስ አዘጋጅቶ ለጉባኤው በማቅረብ የይሙት በቃ ፍርድ ራሱ ፈረደ ። ይህ ሲፈጸም ነበር በዙፋን አዳራሽ ሮቅ ላይ ሁካታ ይሰማ የነበረው፣ የማፋ ጽናት ስቅቆት ሕንፃው በገዛ ቋንቋው ድምፅ ያሰማውና፣ ከማዕዘን ማዕዘን ያስተጋባው። የፈጠራ ክሱ እየተነበበ እገሌ ይሙት፣ አይሙት የሚለው ድምፅ እጅ በማውጣት የተሰጠው በሕግ አግባብ ተከሳሹ ቀርቦ መከላከያውን አሰምቶ ሳይሆን፣ በሌለበት፣ የመፍረድ ሥልጣንና የሕግ ሙያም ባልነበራቸው ወታደሮች ነበር። ሌላው ቀርቶ የቀድሞ ባለሥልጣናቹ ያጠፉት ነገር ቢኖር እንዲያጣራ የተቋቋመው የምርመራ ኮሚሽን ምርመራውን ፈጽሞ የመጨረሻ ሪፖርቱን ሳያቀርብ የፖለቲካ ውሳኔ ተደረገ።

ከታላቁ ቤተ መንግሥትና ከሌሎች የማሰሪያ ስፍራዎች የአስባሰቡ ዋቸውን ሰዎች እጆቻቸውን በሰንሰለት አቆራኝተው በሽፋን መኪና ወደ ዓለም በታኝ እስር ቤት ወስደው ግድግዳ በማስደገፍ በጥይት በግፍ ደበደቡዋቸው። ሬሳቸው ሜዳ ላይ እንደተጣለ እድሮ በማግሥቱ በታላቁ ወህኒ ቤት የሚገኙ እስረኞች በሌሌከትሪክ መግደያው ክፍል እንዲያሳር ፉና ጉድጓድ እንዲቆፍሩ ተደረገ። በእስረኛ ጉልበት ለስድሳ ሰው መቅበሪያ የሚበቃ ጉድጓድ ተቆፍሮ ከጊዜ በኋላ አጽማቸው ተለይቶ እንዳይታወቅም ኖራ አርከፍክፈውባቸው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንደ

አልባሌ ነገር ጣሉአቸው።

ለሀገራቸው በጀግንነት የደሙላትንና የቆሰሉላትን አርበኞችና በስደት የተንገላቱትን ሰዎች፣ በዲፕሎማሲው መድረክ ተሟግተው የረቱላትን የፖለቲካ ሰዎች (ስቴትስሜን) የዓለም ኅብረተሰብ አባልነቱ ማዕቀቡን በብቃት እንድትወጣ በሰላም አስከባሪነት ተሰልፈው ክፍተኛ አድናቆት ያተረፉላትንና የሀገር ድንበር ያስከበሩትን መኰንኖች፣ ዝጠቅ ላላውም ለአንድነቷና ለዕድገቷ ሌት ተቀን የደከሙላትን ልጆቿን ነበር ኢትዮጵያን በአንድ ቅጽበት ያሳጡዋት።

በዚያች ዐለምቲቱ ቅዳሚት ነበር ''ያለምንም ደም'' የሚለው የደርግ መፈክር በደም የተለወሰው። ይህም እርምጃ ነበር በኢትዮጵያ ምድር የማያቋርጥ የዋይታና የለቅሶ ድምፅ መጀሪያው የሆነው። በመስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ''የሠለማው ዘመን አከተመ፡ የብርሃን ዘመን ፈነጠቀ'' ብሎ ባወጀ ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ደርግ ያለዳኘነት ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም የስድሳ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ቀሰፈ። ጥሩ ሥራ እንደሠራ ሁሉ በትምክህተኛነት መግለጫ አወጣ።

ለሚቀርብላቸው ክስ መልስ ለመስጠት እንደማይችሉ እርግጠኛ ሲሆን ሙት ወቃሽ በመሆን በሕያውነታቸው ሳይሆን በፈሳቸው ላይ ደርግ ክስ አቀረበባቸው። በማግሥቱ ማለዳ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን በመሰብሰብ የደርግ አንደኛ ምክትል ሊቀ መንበር ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ''ከፍተኛ መፈንቅለ መንግሥት ሊፈጽሙብን ሲዘጋጁ ቀደምናቸው'' ብሎ በትምክህት ተናገረ።

ያች ደርግ መቅሰፍት ያወረደባት ቅዳሚት፡ ያች ጨለማ ሴሊት፡ ያች የዋይታ ዕለት አዝጋሚው አብዮት የተሰኘው የደርግ እንቅስቃሴ እውነተኛው ገጽታው ገሐድ የወጣባት፡ የመከራ ዘመን የተጀመረባት ነበረች። በኢትዮጵያ ታሪክ ''ጥቁሪቷ ቅዳሚት'' ተብላ ትታወቃለች። በኢትዮጵያ ምድር የጨለማ መጋረጃ የተጋረደባት ቀንም ሁና ትታወሳለች።

፲

የዕለት ውሎ

ነፍስ ካለ መንቀሳቀስ ፡ መንቀሳቀስ ካለ ደግሞ እኗኗርን መወሰን አስፈላጊ ይሆናል ። የአስር ቤት ሕይወትን በሥርዓት ለመምራት አስረኞች የተቻላቸውን ለማድረግ ማሰላሰል ከጀመሩ ውለው አድረዋል ። ከዚህም የተነሳ ከአራተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ትጥር ግቢ በተዛወሩ በአምስተኛው ቀን አስረኞቹ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ አውጥተው ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ጀመሩ ። ተወካዮቻቸውን መረጡ ። በተወካዮቻቸው አማካይነት በክፍሉ ውስጥ ሥርዓት ለማስከበር ፡ በአስረኛውና በጠባቂዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት የሰመረ እንዲሆን አቀዱ ።

በተመራጮቹም የሥራ ክፍል አንዱ የክፍል ኃላፊ ፡ አንዱ ምክትል ኃላፊ ፡ አንዱ ጸሐፊ ፡ አንዱ ገንዘብ ያዥ ፡ አንዱ የዕዳት ኃላፊ ፡ አንዱ የፖስታ ኃላፊ ፡ አንዱ ዐጥቃ አስከባሪ ሁነው ነበር የሚሠሩት ። በወል ደግሞ በኮሚቴ ደረጃ እየመከሩ የአስረኞቹ ጤንነት ፡ የክፍሉ ጽዳትና ዐጥቃ እንዲጠበቅ ጥረት ያደርጉ ጀመር ። የውስጥ አስተዳደሩ በነዚሁ የኮሚቴ አባሎች አማካይነት ይካሄድ ስለነበረ ለፍተሻ ካልሆነ በቀር ጠባቂዎቹ ከክፍሉ ውስጥ ገብተው ይህን እድርጉ ፡ ይህን አታድርጉ አይሉም ነበር ።

ስለ አስረኞች አኗኗር በጠቅላላ ስብሰባ በአንድ ቋጥርና በሁለት ቋጥር ክፍሎች የወጀቀው የዕለት ፕሮግራም ይዘት ይብዛም ይንስ እንደሚከተለው ነበር ።

1 ተቆልፎ ያደረው በር ከንጉቱ በ12 ሰዓት በጠባቂዎቹ ሲከፈት ፡ አስረኞቹ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደው ይዐዳላሉ ፡ ጂምናስቲክ

የሚሠሩትም አካላዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ፡ ገላ የመታጠብ ተራ ያላቸው አካላቸውን ይታጠባሉ ።

2/ ከጧቱ ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ድረስ በክፍሉ ውስጥ የፀጥታ ጊዜ ስለሆነ ፡ ይዝው ተከብሮ እኩለ ሌሊት ላይ የጠፋው የኤሌትሪክ መብራት ከጧቱ በ12 ሰዓት ተሩብ ይበራል ። ቀድሞ የተነሳውም ሰው እንደልቡ ሊዘዋወር ይችላል ።

3/ ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ የክፍሉ ጽዳት ተጀምሮ ፡ ሁሉም እስረኛ (ከሽማግሌዎቹ በቀር) በግሉ ወይም ከሌሎቹ ጋር ተራ ገብቶ በመጣመር መኝታውንና አካባቢውን በመወልወያ (ሞፕ) በመወልወል ያፀዳል ። የግል ጸሎቱንም ያደርሳል ። ፀሐይ ለማስመታትና ልብስ ለማራገፍ የሚፈልጉም ፍራሽና ልብስ እውጥተው ያሰጣሉ ። በሳምንት አንድ ቀን ፍራሽና ልብስ ማራገፍና ቦታውን መወልወል የተለመደ ነው ።

4/ ከጧቱ በሁለት ሰዓት በአዳራሹ ውስጥ በዘወትሩ ቀን አጭር ጸሎት ፡ በሰንበትና በበዓላት ቀን ደግሞ ኪዳን ወይም የሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎት ይደረጋል ። ከእስረኞቹ መካከል ፈቃደኛ የሆኑት በካህኑ ተመርጠ በመንፈሳዊ ፕሮግራም አስተባባሪው አማካይነት የሚታደለውን አንድ ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተራ ያነባሉ ። በኪዳን ወይም በሥርዓተ ቅዳሴው ጸሎት ላይ ደግሞ ፈቃደኛ የሆኑት በዲቁና ሙያ ሰልጥነው ምስባክ በመስበክና የዲያቆን ፈንታ የሆነውን ዝማሬ በማዜም በዲያቆንነት ሲያገለግሉ ፡ የተቀሩት እስረኞች ተሰጥዎ ይቀበላሉ ። የዕለቱ የመዐዳጃና የገላ መታጠቢያ ቤት ተረኞች ግን ወደ ማጽዳቱ ተግባር ይሰማራሉ ። ከመጀመሪያው ጀምሮ የሁለት ቁጥር ቋሚ ካህን የሆኑት ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ* ቀደም ሲል ከንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደና ከንቡረ ዕድ ገብረ ሥላሴ ፀሐዩ ጋር በመተባበር ፡ በኋላም ብቻቸውን ጸሎቱን

*አውን አቡን መልከ ጸዲቅ

ከመሩ በኋላ በጸሎቱ ፍጻሜ ላይ አጭር ስብከት ሰብከው ያሳርጋሉ ። በእንድ ቁጥር ደግሞ ጸሎቱ የሚመራው በመጀመሪያ ሽንቡረ ዕድ ዲሜጥሮስ ገብረ ማርያም በኋላ ደግሞ በንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ነው ።

5/ በዘወትሩ ቀን ጸሎቱ ከጧቱ በሁለት ሰዓት ተሩብ ፡ በበዓላት ቀን ደግሞ ከሁለት ሰዓት ተኩል እስከ ሶስት ሰዓት ተሩብ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚፈጸመው የማኅበር ጸሎት እንዳበቃ ቁርስ ይበላል ።

6/ ከቁርስ በኋላ እስከ አራት ሰዓት ተሩብ ባለው ጊዜ ውስጥ መጽሐፍ የሚያነበው ንባቡን ፡ የሚጽፍው ድርሰቱን ፡ የቤት ውስጥ ሴዋታ የሚሄወተው ሴዋታውን* ፡ የሚማረው ትምህርቱን ይቀጥላል ። የልብስ እጠባና ሌላም ተግባር ያለበት ደግሞ በየሥራው ይሰማራል ።

7/ አራት ሰዓት ተሩብ ሲሆን ፀሐይ ለመሞቅና ለመንሸራሸር እስረኛው ሁሉ ከክፍሉ ወጥቶ የተወሰነለትን ክልል ሳይተላለፍ በምድረ ግቢው ውስጥ በንድ ፡ በንድ እየሆነ ይንከላወሳል ፡ ይጫወታል ፡ ለጧት ፀሐይ መሞቂያ የተወሰነው የአርባ አምስት ደቂቃ ጊዜ ሲያልቅ ወደ ጉርና መልስ ይሆናል ።

8/ ከአምስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት ተኩል ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በየዕለቱ ተረኞች ምግብ ከመኪና እያወረዱ ለባለስንቁ ሲያደርሱ ፡ በዚህን ሰዓት ገላ የመታጠብ ተራ ያላቸው ይታጠባሉ ። ልብስ የሚያጥቡም ያጥባሉ ። ማንበብ የሚሹም ያነባሉ ። የሚማሩትም ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ ።

9/ ባመጣጡ እንደመቅደሙና መዘማየቱ ከስድስት እስከ ሰባት ሰዓት ተኩል ድረስ ባለው ጊዜ እስረኞቹ ምሳ በልተው የምግብ ዕቃቸውን ያጥባሉ ።

10/ ከሰባት ሰዓት ተኩል እስከ ጠዘኝ ሰዓት ተኩል ባለው ጊዜ በልዩ ፈቃድ ካልሆነ በቀር እስረኞች እንደልብ ከክፍላቸው ውጭ የማይዘዋወሩ ስለሆነ ፡ በየክፍላቸው ይከተታሉ ። በስምንት ሰዓት ደወል ተደውሎ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ የፀጥታ ጊዜ ስለሚሆን ለማሸለብ የፈለገ ይተኛል ። ያልፈለገም በፀጥታ ያነባል ወይም ይጽፋል ።

*የቤት ውስጥ ሴዋታዎቹ ካርታ ፡ ቼዝና ዳማ ናቸው ።

11/ ከዘጠኝ ሰዓት ተኩል እስከ አስር ተሩብ ድረስ ለመፀዳዳት ወደመታጠቢያ ቤት ጉራ ለማለት ወይም ከአንደኛው ክፍል ወደ ሌላው ክፍል ለመሄድ የሚፈልግ እንደልብ ይዘዋወራል ።

12/ ከአስር ሰዓት ተሩብ እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ያለው ጊዜ የእኩለ ቀን በኋላ ፀሐይ መሞቂያና የሽርሽር ጊዜ ስለሆነ ፡ እንደጢቱ ሁሉ እስረኞቹ ሽርሽሩን ይቀጥላሉ ።

13/ ከአሥራ አንድ ሰዓት እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ እስረኛው ሁሉ ተጠናቆና ከውጭ የሚፈጽመውን ተግባር ፈጽሞ በክፍሉ ይከተታል ።

14/ በአሥራ ሁለት ሰዓት ጠባቂዎች በሩን በስተውጭ ይቆልፉታል።

15/ በር እንደተቆለፈ የማታ የማጎበር ጸሎት ይደርሳል ። በጸሎቱም ጊዜ ካህኑ አጭር የመክፈቻ ጸሎት ካደረጉ በኋላ አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል በጎብረት ይፀለይና በአዘቦቱ ቀን በመፈራረቅ እግዚአታ ወይም አኩቴት በመቀባበል ይባላል ። በሁዳዴና በፍልሰታ ሰሞን ፡ እንደዚሁም ቅዳሜና እሑድ የሠርክ ኪዳን ይከናወናል ። በማንኛውም ዓይነት ጸሎት ፍጻሜ ላይ ካህኑ ያሳርጋሉ ።

16/ ከጸሎት በኋላ ራት ተበልቶ ፡ ዕቃ ማጠቡ ይቀጥላል ።

17/ ከምሽቱ ከአንድ እስከ ሁለት ሰዓት የአንድ ቁጥር ክፍል ፡ ከሁለት እስከ ሶስት ሰዓት የሁለት ቁጥር ክፍል በር ይከፈትና ለመፀዳዳት ወደ መታጠቢያ ቤት ይሄዳሉ ።

18/ ከዚያ በኋላ ከሌሊቱ እስከ አምስት ሰዓት ድረስ ንባብና ጽሕፈት፡ ልዩ ልዩ ዓይነት ጨዋታ ፡ ውይይት በየፈናው ይቀጥላል ።

19/ በአምስት ሰዓት ፀጥታ እንዲከበር ለማሳሰብ ደወል ይደወልና ለመኝታ መብራት እስከሚጠፋበት እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ድረስ ሁሉም በፀጥታ የግል ሥራውን ይሰራል ።

20/ ከሌሊቱ በስድስት ሰዓት መብራት ስለሚጠፋ የግል ጸሎቱን አድርሶ ሁሉም ይተኛል ። ሁሉም የየራሱ የሆነ የግል ጸሎት አለው ። የአምሐ ገብርኤል የጧትና የማታ የግል ጸሎት የሚከተለው ነበር ።

"ቸሩ ፈጣሪዬ ሆይ!!

ኃጢያቴን ይቅር በለኝ፡ ዕድሜና ጤና ስጠኝ። በደሀና እንዳሳደርከኝ በደሀና አውለኝ*። ደጉን አስመልክተኝ። ክፉውን ከኔ አርቅ። ጠባቂ መልአክህን አዘዝልኝ፡ ከተናግሮ አናጋሪም አንተ ጠብቀኝ። ይህችም ቀን ቸር እምሰማባት፡ ምህረትህን አማንኝባት፡ ከዚህ የምወጣባት ትሁንልኝ። አማዝን፡ እምተከዝባት፡ የምከሰስ፡ የምወቀስባት አትሁንብኝ። ሊከሱኝ፡ ሊወቅሱኝ ሊፈርዱብኝም የሚያስቡ ቢኖሩ አንተ አሳባቸውን አስተዋቸው።

በቸርነትህ የሰጠኸኝንም ልጆቼን አምሐ ሥላሴንና አካለ ወልድንም አንተ ጠብቅልኝ፡ ከክፉ ሰውርልኝ፡ ዕድሜና ጤና ስጣቸው። ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው፡ የሰው መውደድ ያላቸው፡ ለሰው የሚያስቡ የተባረኩ ልጆች አድርግልኝ። ዕውቀትን ግለጽላቸው፡ በደሀና ውለው እንዲገቡም አድርግልኝ። ተምረው፡ አድገው፡ ተድረው፡ የጥቂት ብዙ ለመሆን፡ እኛ ወላጆቻቸውንም ለመጦር አብቃቸው፡ አንተ ጠብቅልኝ።

እንደዚሁም ረዳቴ፡ ደጋፊዬ፡ አሳቢዬ፡ መካሪዬ አድርገህ የሰጠኸኝን ባለቤቴን አንተ ጠብቅልኝ፡ ከክፉ ሰውርልኝ፡ ዕድሜና ጤና ስጣት፡ ችግሩዋንም አቃልላት፡ የሚረዱዋትን አንተ አብዛላት። በደሉዋንም ይቅር በላት። የጀመረችውንም ሥራ አንተ ባርክላት፡ በቂ መተዳደሪያም የምታገኝበት አድርግላት። ግራ በሚገባት ነገር ሁሉ አንተ ብልሀቱን፡ ጥበቡን ግለጽላት። የሱዋንም ጸሎት፡ የኔንም ልመና ተቀብለህ፡ የልጆቼን ናፍቆት የቤተሰቦቼንም መላቀቅ አይተህ ከቤተሰቦቼ ጋር ለመቀላቀል አብቃኝ፡ አንተ ተለመነኝ። ቸሩ ፈጣሪዬ ሆይ እኔ አለሁልህ በለኝ።

እናቴን፡ አህቶቼን፡ ልጆቻቸውን፡ ወንድሞቼን፡ የኔንም የባለቤቴንም ዘመዶች ሁሉ፡ ቤተሰቦቼንም አንተ ጠብቅልኝ፡ ከክፉ ሰውርልኝ፡ ዕድሜና ጤና ስጣቸው። የታመሙትን ፈውስ፡ የተወለዱትንም አሳድግ። ችግራቸውንም አቃል፡ የሚረዱዋቸውንም አብዛ። እኔን ባሪያህንም በዛሬይቱ ዕለት ከዚች ቦታ እውጥተህ ወርቶ ለማደር አብቃኝ።

በችግሬ፡ በእሥራቴ፡ በማጣቴ ጊዜ ቤተሰቦቼን በገንዘብ፡ በጉልበት፡ በሃሳብ፡ በምክር የሚረዱትን ሁሉ አንተ አርዳቸው፡ ዋጋቸውን አንተ ክፈላቸው። ዕድሜና ጤና ስጣቸው። ለጋስ እጃቸውም ከቤተሰቦቼ እንዳይታጠፍ አድርግ።

*ግታ ሊሆን በደሀና እንዳሳልከኝ በደሀና አሳድረኝ

አገራቱንም የሰላም አገር አድርግ፡ ሕዝቡንም ባርክ፡ ከረሀብ ከቸነፈር፡ ከእልቂት፡ ከመቅሰፍት፡ ከጦርነት፡ ከእርስ በርስ ግጭትም አንተ አድነው። በሥልጣን ላይ የሚገኙት የሚሠሩትም ግፍ እንዲያቢት፡ የንፁሃን ደም በከንቱ እንዳይፈስ አድርግ፡ እነርሱ ያሰሩዋቸውንም አንተ ፍታ፡ ፅኑ አገዛዝንም ከሚንቃቸው አውርድ፡ የሚቀጀውንም አስተዳደር አንተ መሥርት።

ስለእግዝዕትን ማርያም ብለህ ተለመነኝ። እመቤቴ ማርያም የዘወትር ጸሎቴን እንዲፈጽምልኝ እንቺ አማልጂኝ።''

ከዚህ አሞር የግል ጸሎት በኋላ አምሐ ገብርኤል ዘወትር አቡነ ዘበሰማያትንና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤልን ይደግማል። በተጨማሪም የዕለቱን ሙዳሴ አምላክ፡ የዘወትር ጸሎት፡ የንግሀ ኪዳን፡ ሴጦን፡ ሙዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃን ፀ.ት ፀ.ት፡ የሌሊትና የሠርክ ኪዳን፡ ጸሎተ ሃይማኖትንና ይቄድስዋን ፡ በእነቱ ቅዱሳትንና በሰማይ የሚለውን ጸሎት ማታ፡ ማታ ከመጽሐፈ ጸሎት በአማርኛ ይደግማል። ከዳዊት መዝሙርም ሁለት ወይም ሶስት መዝሙር ከማታ ጸሎቱ በኋላ ያነባል። ሌሊቱም ድብን ባለ እንቅልፍ ወይም ቅዠት ተቀላቅሎበት ያልፋል። በነጋታውም የተለመደው ሕይወት ይቀጥላል።

በእስር ቤቱ እንደሰው ፍላጎት ፡ ዝንባሌና የትምህርት ዓይነት ምርጫ ቀንና ማታ የትምህርት ፕሮግራም ይካሄዳል። ትምህርቱንም የሚያስተምሩት ከእስረኞቹ መካከል በሙያው የበሰሉት ሲሆኑ፡ እንዱ የሚያውቀውን ለሌላው ለማካፈል፡ ለመማር የሚፈልገው ደግሞ ዕውቀትን ለመገብየት የሚያደርገው ጥረት በጣም የሚደነቅ ነበር።

በተለያየ ጊዜ ቁጥራቸው ለተወሰነ ሰዎች ያስተምሩ ከነበሩት መካከል የሚከተሉት ሰዎች ስም ሳይጠቀስ ሊታለፍ አይገባም። የሚያስተምሩትም የትምህርት ዓይነት የሚከተለው ነው።

1. አቶ አበበ ረታ
   ግዕዝ
2. አቶ ይልማ ደሬሳ
   አርምኛ
3. አቶ ጌታሁን ተሰማ
   የአርበኝነት ታሪክ

4. ቢትወደድ ዘሙዴ ገብረ ሕይወት
   የኢጣልያን ጦርነት ታሪክ
5. ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተማርያም ወርቅነህ
   ግዕዝ ፡ ቅዳሴ ፡ ዜማ ፡ የሃይማኖት ትምህርት ፡ የግዕዝ ሰዋሰውና ግሪክኛ
6. ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ
   ኤሌክትሪሲቲና የሬዲዮ መሠረታዊ ትምህርት፡
7. አቶ ማሞ ታደሰ
   ፈረንሳይኛና እስፓኒሽ ቋንቋ
8. አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ
   ሚካኒክ፡ እርሻ፡ ከብትና ዶሮ እርባታ፡ የህንፃ ንድፍ አሠራር
9. አቶ ሠይፉ ማኅተመ ሥላሴ
   ኤሌክትሪሲቲ
10. አቶ ሀብተ ሥላሴ ታፈሰ
    የጣልያንኛ፡ የመስኩብኛና የግሪክ ቋንቋ
11. አቶ በትሩ አድማሴ
    እንግሊዝኛና ሳይንስ
12. ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ
    ሥሌት አልጀብራ፡ ማቴማቲክስ፡ ካልኩለስ እና ፊዚክስ
13. አቶ ማለህ ሂኒት
    አረብኛ
14. አቶ ምናሴ ለማ
    የአረብኛና የፈረንሳይኛ ቋንቋ
15. አቶ አሐዱ ሳቡሬ
    ፈረንሳይኛ ቋንቋ
16. ደጀዝማች ተስፋ ዮሐንስ በረሄ
    ትግርኛና ጣልያንኛ ቋንቋ
17. አቶ ታደሰ ያዕቆብ
    እብራይስጥና የኢትዮጵያ ታሪክ
18. አቶ አባሻውል ወልደ ማርያም
    ማቴማቲክስና ሰርቬይንግ

19· አቶ ኃይሉ ሰብስቤ
የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና እርዳታ አሰጣጥና ጠቅላላ የጤና አጠባበቅ ትምህርት፡
20· አቶ ጎርፉ ገብረ መድህን
ኢኮኖሚክስና የሂሳብ አያያዝ (ቡክ ኪፒንግ ኤንድ አካውንቲንግ)
21· ዶክተር ሥዩም ሐረጎት
ሕግና የእንግሊዝኛ ቋንቋ
22· አቶ እስናቀ ጌታቸው
ኢኮኖሚክስ
23· አቶ ንጉሤ ሀብቱ ወልድ
እንግሊዝኛና የርዕዮተ ዓለም ትምህርት
24· ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም
እንግሊዝኛ ቋንቋ
25· አቶ አብርሃም ወርቅነህ
እንግሊዝኛ ቋንቋና ማኔጅሜንት
26· አቶ ተፈራ ሻውል
ጀርመንኛ
27· ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ
ሃይማኖትና ዜማ
28· አቶ ወርቁ መካሻ
እንግሊዝኛ ቋንቋ
29· ፊታውራሪ አላሚን እንዲራስ
አረብኛ
30· ኮሎኔል ፀጋዬ መሸሻ
ማቴማቲክስ

እነዚህ ትምህርቶች ይሰጡ የነበረው በተለያየ ቀንና ጊዜ ስለነበረ፡ አንድ ሰው እንደፍላጎቱና እንደጊዜው ተስማሚነት ብዙ ዓይነት ትምህርት ለመከታተል ይችላል። ከነዚህም የትምህርት ዓይነቶች አብዛኛዎቹ ለረጂም ጊዜ፡ ጥቂቶቹ ደግሞ ለአጭር ጊዜ የተሰጡ ሲሆኑ፡ ብዙዎች ተጠቅመውባቸዋል። አምሐ ገብርኤልም ለአውኑም ሆነ ለተከታዩ ትውልድ እንደሚጠቅሙ በሚታመንባቸው፡ አገርንና ጠቅላላ ዕውቀትን

በሚመለከቱ ጉዳዮች የምርምር ጽሑፍና ድርሰት ለሕዝብ ለማበርከት በማሰብ፡ የእስራት ዘመኑን ያዋለው ለምርምርና ለድርሰት ተግባር በመሆኑ፡ በትምህርት ረገድ ይከታተል የነበረው ለአጭር ጊዜ የፈረንሳይኛና ስለጤና አጠባበቅ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ብቻ ነበር። በዚሁም ጊዜ ውስጥ መጻሕፍትን በመመርመርና የጥንቱን የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ለአገር ይበጃል፡ ለሕዝብ ይጠቅማል በሚላቸው ርዕሰ ጉዳዮች የልዩ ልዩ መጻሕፍት ረቂቅ ሌት ተቀን በመሥራት ከመጻፉም በላይ በስመ ጥሩው ደራሲና የታሪክ ጸሐፊ በፕሮፌሰር እርፍልድ ቶይንቢ "ኢትዮጵያና ኢጣልያ" በሚል ርዕስ የተጻፈውን የኢትዮጵያን የታሪክ መጽሐፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉሞ ሲጨርስ አንድ የማዕከለ—በሐሙርት (ኢንተርናሽናል) ሕግ መጽሐፍ ትርጉም ጀምሮ ሩቡን ያህል ሠርቷል። በዚሁ ጊዜ የመጀመሪያ ረቂቃቸው ከሞላ ጎደል የተጠናቀቀላቸው መጻሕፍት

1·ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሕግ
ምንጮች፡ ታሪክና የፍትሕ አፈጻጸም
2·ሕይወት
3·ብቸኛው ሰው
4·አባኮስትር (ገመድ ማተቡ)

የሚሉ ነበሩ። "አባገስጥ" በሚል ርዕስ ለሚጽፈውም መጽሐፍ ምርምሩን ጀምሮ ነበር።

ዘወትር መጻሕፍት ከመመርመርና ጽሑፍ ከመጫጫር አለመለየቱን የተመለከቱ ጓደኞቹ ለጊዜ ማሳለፊያ ከሚጫወቱት የቤት ውስጥ ጨዋታዎች ቢያንስ ለአንደኛው ልምምድ እንዲያደርግ በየጊዜው ይጠይቁት ነበር። ስለአላስመለከተው ጥያቄአቸውን አልተቀበለውም። "ቤሎት" በሚባለው የካርታ ጨዋታ ከተደረገው ውድድሮች በአንደኛው ጊዜ ተመልካቾች ማን እንደሚያሸንፍ በመተንበይ ግጥም እንዲጽፉ ሲጠየቁ፡ አምሐ ገብርኤልም እንዲገጥም የውድድሩ አዘጋጅ ዎች እጥብቀው ስለጠየቁት " ታተርፋለች ትዕግሥት ሕይወትና ፍቅር" በሚል ርዕስ አንድ አጭር ግጥም ጽፎ ነበር። የውድድሩ አዘጋጅዎች ግጥሙ የተወዳዳሪ ቡድኖችንና የሚወዳደሩትን ግለሰቦች ስም በማውሳት ማን እንደሚያሸንፍ የሚተነብይ መሆን እንዳለበት ስለገለጹለት በዚሁ መመሪያ መሰረት ሌላ ግጥም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመግጠም ተገድዶ ነበር። ሁለቱም ግጥሞች ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙት ናቸው።

ታተርፉለች ትዕግሥት ሕይወትና ፍቅር

ከጎረቤታቻን የሚመጣው ጥሪ
"በተሰቀለው ሰው፡ ለመድኃኔ ዓለም ኀኝና አዝካሪ፡
ለጸሎት ኑልኝ፡ ምስጋና እናቅርብ ለፈጣሪ"
የሚል በመሆኑ አይደለም አስቸጋሪ።
ስለዚህ እሄዳለሁ ለጸሎት፡ ጠበል ጠዲቅ ለመቅመስ
ፈጣሪንም ለማለት፡ ሥሉስ ወቅዱስ፡
እንዲበጀኝ ብዬ ለቁመተ ሥጋ ፡ ለድህነተ ነፍስ ።
የኛስ ቤት ሆኖአል የደብተራ
ግጠም፡ ተቀኝ የሚል በፈጠራ።
እንዴት ይባላል ሰው፡ ቅኔ ውለድ
ሙያኮ ይጠይቃል፡ አይበቃም በጎ ፈቃድ።
በዚህስ ዋያቄ ተጨነቀች ነፍሴ
ስለሚታጣት ፍቅር፡ አብሮ የመኖር ዋሴ።
ከሰምና ወርቁ ምን አለኝ እኔ
ጎብር ምርምሩ ከሆነልኝ ቅኔ።
ወርቁ ገደደ እንጂ መች ታጣ ሰሙ
ይዘረፍ የለም ወይ ሲከሰት ቀለሙ።
አላበረክትም ለሰው መወድስ
አለህ፡ አለህ ሲሉት ቶሎ ለሚፈርስ፡
ሳለም ለመከራ፡ ለችግር ላይደርስ።
ቢሆንም እሻለሁ ላካፍለው ምክር
የተረዳሁትን መጽሐፍ ስመረምር፡
አገባሪ አምላክ የሚሉትን ፍቅር
ቢያዝ ይበጀዋል፡ ለሰብዓዊ ፍጡር።
እኩሉ ሲጫወት ራሚና ቤሎት



አብራ ጀምበሬ (ሥራቢሙ) በቤተ መጻሕፍት

እኩለ ሲያስላሰል የሰንጠረዝ ሥሌት፡
ምንው እንዳንዶቹ ተበሻ ሆኑ የመጻሕፍት።
ትኔ ቤት ባልገባም ባልደርስም ዋሸራ
እኔስ መርጫለሁ መጻፍ፡ የማይክድ ባልንጀራ
ስለሚመክረኝ ከሰው እንዳልጋጭ፡ እንዳላፈራ ባላጋራ።
ለመገብየት ዕውቀት፡ ለመክላት ትካዜ
መጽሐፍ አነባለሁ፡ ሳላሰልስ ሁልጊዜ።
ማንበብ ብቻ አይበቃም ይደርሷል ይቀኟል
ዳሩ ምን ይሆናል፡ ችግሩ እየበዛ አሳብ ይባዝናል።
አሳቤ ተቀመጥ ከልቤ፡ ተሰብሰብ ከዋሻው
መሰብሰብ እንጂ፡ መባዘን አይበጀውም ለሰው።
መግንባት ማነጥ ተስኖኝ በውነት
ቤት ኑሮዬን በማዘን ብቻ ባሳብ አቆምኩት።
አሳቤ አትገስግስ፡ አትሂድ ከቤት
ሰውና አሳብ እብሮ ሲሄድነው የሚፈጸም ምኞት።
ሰው መላክ አይሆንም፡ ስላልተፈቀደ በተፈጥሮ ሕግ
ለመርዳት ካልሆኑ፡ ለመሥራትም ደግ።
መከራን በመቻል ቀን ማለፉ ላይቀር
ያስተዛዝብ ጀመር የወዳጅስ ነገር።
ሁሉንም መቻል ነው፡ አለማማረር
ታተርፋለች ትዕግሥት ሕይወትና ፍቅር ።

ድል ለባለዕድል

ከክርስቶስ በፊት በአርባ ዘጠኝ ዓመት*
ቄሳሩ ጁሊዩስ ፈረንሳይን ለማስገበር ሲዘምት

"ጠጠሩ ስለተማለ ሩቢኮንንም" ስለተሻገርን በፍጥነት
ወደኋላ አንመልከት እንገስግስ ወደፊት
ደርሰናልና ዒላማ ሳይመቱ ከማይመለሱበት"
ሲል አውጆ ነበር ለሮማ ሠራዊት ።
እንደዚሁም በቤሎት ጨዋታ ውድድር
ደንቡ ይጠይቃል ሩቢኮንን መሻገር
ብልጫ ለማምጣት ፡ ነጥብ ለማስቆጠር ።
የበረቱትማ አለፉ ገደቡን በፈተና
ያልታደሉት ቀሩ በመሐል ጉዳና ።
ውጣ ውረድ በመሆኑ የጨዋታ ወጉ
ያስቀነሱ ነበሩ ፡ ለማስቆጠር ሲጓጉ ።
በተቻለ መጠን ሁሉም ተወዳድሮ
ኃያላኑ ተለዩ ጨዋታውም ሰምሮ ።
እራቱ ኃያላን የድል ዝና ቀማሽ
ዛፉና ሽልጌ ፡ ሰላምና ደራሽ ...
መልካሙ ዕድላቸው ያራቱ ቡድኖች
የተለዩ ስሜት ሰጥቷል ለተመልካች ።
ጨዋታ እማላውቀው እኔ ስንኳ ሳልቀር
ትንቢት እንድናገር ተጠይቄ ነበር ።

*እንደኤውሮጳ አቆጣጠር
**ሩቢኮን በስሜን ኢጣሊያ የሚገኝ የወንዝ ስም ነው
***በሙድድሩ ብልጫ ያሳዩ ቡድኖች ስሞች ነበሩ

ትንቢት ለመናገር ባይኖረኝ ተውህቦ ፡
የጠቆምኩት ግምት ሆነብኝ እምህበለቦ ፡
ኩራት ተሰምቶታል ሻውል ጂኤራሉ
ተሰልፎ ሲገኝ ወታደሩ ኃይሉ*
የቡድኑንም ስም ደራሽ አለው አሉ ።
አጣማጁ ሻውል ቢመጣም በወዶ ዘማችነት
ኃይሉ እኮነው ኩክቡ ተጨዋች ከሁለት ቁጥር ቤት ።
ጨዋታው ተሟሙቆ ፡ ትንቢቱም ተነግሮ
ሁሉም ሲጠባበቅ ውጤቱን በአንክሮ
ደራሽ አሸነፈ ፡ ጥሮ ተጣጥሮ ።
ይደልም አላለሁ ላሸናፊው ቡድን
ሽልማት እንዲያገኝ የታሰበለትን ።
ሌሎችም እንዲሁ እንዲቀናቸው
በትጋት መጫወት ይሁን ዓላማቸው ።
በርትቶ ተጫዉቶ ነጋጠመው ዕድል
ተሸናፊው ደግሞ ይሆናል ባለድል ።
ስለዚህ አትዘኑ የተሸንፋችሁ
እናንተም ወደፊት ታሸንፋላችሁ ።
የቁመቱ መርዘም** ከበደው መሰለኝ
የተነበይኩለት ዛፉ*** ዝቅ አለብኝ ።
ባልታደል ነወይ ፡ ለመንገር ትንቢት
እሙን ያልሆነው ፡ የኔውስ ግምት
ኃይሉና ተስፋዬ ከዛፉ ሰቅለውት ። ****

*ጂኤራል ሻውል ዘለቀና ወታደር ኃይሉ እሸቴ ለእንድ ቡድን የተሰለፉ ሲሆን ፡ ጂኤራሉ ከእንድ ቁጥር ፡ ወታደሩ ከሁለት ቁጥር ክፍል ነበሩ ።
**የቡድኑ አባሎች ቀሣ ኃይሉ መሳይና አቶ ተስፋዬ ታደሰ ረዣዥም በመሆናቸው ።
***ዛፉ የቡድኑ ስም ነበር ። አባላቱ ረዣዥም ስለሆኑ ቡድኑ ዛፉ ተባለ ።
****አምሐ ንብርኤል በጨዋታው እኩሌታ ላይ ያሸንፋል ብሎ የተንበየለት ቡድን ።

እንደእመለከተው የጨዋታው ሥልት
ባልተገታም ነበር ዛፉ በሁለተኛነት ።
የትንበር ሽሽጉ ፡ ሂዶ የነበረው
ለመሰናዳት ነው ለካስ ያደፈጠው ።
ሶስተኛ የሆነው ባክሊሉና ባስፋው*
አበጅተዋል ለቡድናቸው ስም ሰላምን መምረጣቸው
ድልን በሰላም ለመቀዳጀት የተጣጣሩት ለገሠና ጌታቸው**
አሁን ቢሆንም አራተኛ ፡ ሰላምኮ ነበር የቀድሞው ሁለተኛ
እኔስ የምመኘው ሰላም እንዲሆን ነው ሁልጊዜም እንደኛ ።
የሁላችን ምኞት ይተርጉም በሥራ
ጨዋታውም ይደርጅ የሁሉ ዕድል ይብራ ።

*አቶ አክሊሉ ቤተግርያምና አቶ አስፋው መኩንን እንድ ቡድን ነበሩ ።
**አቶ ለገሠ ንብረሐና እና አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ አንድ ቡድን ነበሩ ።

በእስር ቤት ሕይወት የባለሙያ እርዳታ የሚጠይቁ ልዩ ልዩ ችግሮች በየጊዜው ያጋጥማሉ ። ችግሮቹንም ለማቃለል ሲሉ የሰፋ ልብስ በማጥበብ ፡ የተቀደደውን በመጥቀም ፡ እንደዚሁም የተበላሸን ዕቃ በመጠገን ፡ ሴላም ልዩ ልዩ ዓይነት የእጅ ሥራ በመሥራት ፡ በየበዓላቱ ለቤተሰብ የሚላኩ ካርዶች በማዘጋጀት ፡-

1 ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ
2/ ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም
3/ ብ/ጀኔራል ሴንጫ መለሰ
4/ አቶ አሸናፊ ሽፈራው
5/ አቶ ኃይሉ ሰብስቤ
6 ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ
7 ሻምበል መንግሥተአብ ባሕሩ
8 አቶ ዘውዴ በዳዳ
9 አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ
10/ አቶ አበበ ከበደ
11 አቶ አስናቀ ጌታቸው
12/ አቶ ጉርፋ ገብረ መድህን
13/ አቶ ሀብተሥላሴ ታፈሰ
14/ አቶ ተፈራ ሻውል

በበጎ ፈቃድ ይፈጽሙት የነበረው ማኅበራዊ አገልግሎት በጣም የሚደነቅ ነበር ። በተጨማሪም አቶ ኃይሉ ሰብስቤ የታመመውን ሁሉ በመርዳትና መንፈሳዊ ፕሮግራምን በማስተባበር ፡ ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ፡ አቶ አክሊሉ ቤተ ማርያምና አቶ ሀብተሥላሴ ታፈሰ ደግሞ በጉር በመቁረጥ ሕሙማንንና ሽማግሌዎችን በመርዳት በእስራቱ ዘመን በበጎ ፈቃድ የፈጸሙት በሁሉም ሕሊና ሲታወስ የሚኖር ምግባር ነው ። ከመንግሥት ክሊኒክና ሆስፒታል የሚገኘው መድኃኒት እጅግ መጠነኛ በመሆኑ የእስረኞችን ችግር ለማቃለል ዶክተር ዊዳድ ኪዳነ ማርያምና ሲስተር ጥሩ ወርቅ አስፋው ልዩ ልዩ ዓይነት መድኃኒት ከበጎ አድራጊዎች በመሰብሰብ ለሁለቱም ክፍሎች በየጊዜው በመላካቸው ፡ ዶክተር ዮሐንስ ወርቅነህ ደግሞ በመጀመሪያ በሳምንት ሶስት ቀን ፡ በመካከሉ በሳምንት አንድ ቀን ፡ በመጨረሻ በሁለት ሳምንት አንድ ቀን

እስረኞቹ እሚታከሙበት ክሊኒክ ድረስ ያለማቋረጥ እየተመላለሱ በግ ከም ያደረጉት እርዳታ በታላቁ ቤተ መንግሥት የነበሩትን እስረኞች የማይከፈለው ውለታቸው ባለዕዳ አድርጓቸዋል ።

እንደዚሁም ሲስተር ጥሩወርቅ አስፋው ፡ ወይዘሮ ጽጌ ሻረው ፡ ወይዘሮ ዘውዲቱ ድልነሣሁ ፡ ወይዘሮ ስለሺ ወንድወሰንና ወይዘሮ ሳባ ተምትም በተለያየ ጊዜ የእስረኞች ቤተሰብ አስተባባሪ በመሆን ያደረጉት እርዳታ ምን ጊዜም የሚዘነጋ አይደለም ። በተጨማሪም ለእስረኞቹ የማኅበር አገልግሎት የሚያስፈልጉትን የጽዳት ዕቃዎች በየወሩ በሚዋጣው የማኅበሩ ገንዘብ በመግዛት ያቀርቡ የነበሩት አቶ ቦጋለ ሻውልና ከተፈቱ በኋላ አቶ ታደሰ ሚሜ እቃ በማቅረብ ያደረጉት ውለታቸው የሚረሳ አይደለም ።

የእስረኞችን ችግር ለማቃለል ያልተቆጠበ ጥረት የዳረጉት እነዚህ ብቻ ስለአልሆኑ ፡ በግልጽም ሆነ በስውር የእስረኞችን ቤተሰቦች በመርዳት ፡ በመጠየቅ ፡ በማዕናናት የመንፈስና የቁሳቁስ እርዳታ ላበረከቱት ሁሉ ፡ ከነዚህም መካከል ለወይዘሮ ትርሲት እበበ እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይክፈላችሁ ከማለት በቀር ሌላ ምን ወሮታ ይከፈላቸዋል ?

፲፩

የእልፍኙ ምስጢር

ሕንፃው የንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ እልፍኝ ነበር ። በዘመነ መይዛዝርት የተሞናደሱበት ፡ አልጋ ወራሹ እጅ የነሱበት ፡ በመሶብ የእልፍኝ ግብር የተበላበት ፡ ምርጥ ወጣቶች የጣት ሙሀ ያቀረቡበት ፡ ሜማ አውልቆ ፡ ድግድጋት አሳምሮ የተገባበት ፡ ያውም በንጉሱልኝና በጥሪ ብቻ ። ሕንፃው የነበረ ክብሩን ካጣ ግን አርባ አምስት ዓመት ሁኖታል ። ሁሉም ነገር ከንግሥት ዘውዲቱ ጋር አልፎበታል ። ስለዚህ ከሌላው በአካባቢው ከሚገኝ ከማንኛውም ሕንፃ የበለጠ የክብር ስፍራ አይሰጠውም ነበር ።

በ1967 ዓ·ም· በጥቢው ወራት ነበር ክፍሉ ለተለየ አገልግሎት የታጨው ። ያሳጨውም ሊመለጥት ከማይቻልበት አካባቢ የሚገኝ መሆኑ ሳይሆን አይቀርም ። ዋናው ክፍል ዙሪያውን በሌሎች ክፍሎች የተከበበ መሆኑ ፡ ዙሪያውን ጠባቂ ለማስቀመጥ ፡ እንቅስቃሴ ለማዳመጥ አመቺ መሆኑም ሌላው የተመረጠበት ምክንያት ሊሆን ይችላል ። መቼስ ለአንበሳ ማሰሪያ ጠንካራ ግንብ መፈለግ በአስተማማኝ ሁኔታ በሩን መቆለፍ የተለመደ አይደል !!

"ቆጆ" የሚባለው እርጌ አንበሳ ከታሰረበት ስፍራ ከሁለት ሙቶ ሜትር በማይበልጥ ርቀት ላይ የሚገኝ ይህ ሕንፃ የተመጠረው ክናዱ ለሚያደቅ ፡ ግርማው ለሚያስፈራ ጉልማሳ አንበሳ ሳይሆን ፡ በዕድሜ ለገፋ ፡ በሰው እጅ ለወደቀ ፡ ጊዜ ፊቷን ላዞረችበት በጊዜው ግን የበለጠ ተፈሪ ለነበረ የኢትዮጵያ አንበሳ ነበር ። የግቢ ሚኒስትሩ መሥሪያ ጠረጴዛ ወጥቶ በመካከለኛው ክፍል ነጠላ አልጋ ተዘረጋበት ።

ያንን አንበሳ ለማሰር እጅ የተንቀጠቀጠው ፡ ወኔ የራደው ይህ ሕንፃ ለአንበሳ ማሰሪያነት በተመረጠበት ወቅት አልነበረም ። አንበሳውን ከወጥመድ ውስጥ ለማስገባት በዓመቱ መጀመሪያ ዕለት የበዓል መዋያ

ተብሎ የተለየ ገጸ በረከት በቀረበበት ዕለት ነበር እንጂ ። ተፈሪና ተከባሪ የነበሩትን ንጉሠ ነገሥት ደርግ ከዙፋን ገርስሶ የቅርብ ጠባቂዎቻቸው አዚም እንደዞረበት እፍጠው እየተመለከቱ ፡ የወጥ ቤት ኃላፊያቸው ሚስ ትሪንክለር ግን እንባ እየተናነቃቸው አንድ ጥይት ሳይተኮስ በቮልስዋገን አውቶሞቢል ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ደርግ የከነፈው በቅዱስ ዮሐንስ ማግሥት ነበር ። በዚያው ዕለት የማታ ማታ ነበር ደርግ ሽለላውን ያቀለጠው ፡ ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን ስለማውረዱ መግለጫውን ያሾርንደንደው ።

ለአገር ከበጀ ግድ የለም በማለት የሞቀ ቤተ መንግሥታቸውን ፡ የተደላደለ ዙፋናቸውን ለቀው ውርደትን በፀጋ ለተቀበሉ አባውንት ከሥልጣን መውረድ ነበር ቁማታ የተመታው ፡ ጉሮ ወሸባዬ የተደለቀው ።

በአራተኛ ክፍለ ጦር በአዛዥ ጽሕፈት ቤት በተቆለፈባቸው ግዜያት በውጭ አገር ባንክ አስራ አንድ ሚሊዮን ሳይሆን አስራ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያስቀመጡበትን ባንክ እንዲገልጹና ለአዲሱ መንግሥት እንዲያስረክቡ በደርግ በተደጋጋሚ ተጠየቁ ።

"ለመሆኑ ሥሌቱን ታውቁታላችሁ?" የሚል የምፀት ጥያቄ ነበር ንጉሠ ነገሥቱ ያቀረቡት ። ከኢትዮጵያ መንግሥት የብዙ ዓመታት በጀት የበለጠ ገቢ አጠራቅመው በውጭ አገር እንዳስቀመጡ ብመታሰቡ ግምታቸው እጅግ የተሳሳተ መሆኑን ሲያስገነዝቡ ነበር የሥላች ሰይፋ ጣል ያደረጉባቸው ። የደርግ ሊቀመንበር በተባሉት በሌ/ጀኔራል አማን እንዶም እንደዚሁም አብሮ አደግ ጓደኛቸው በሆኑት በልውል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ አማካይነት አላቸው የተባለውን ገንዘብ እንዲያምኑና ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ እንዲያደርጉ ለማግባባትና ማስረጃ ለማግኘትም ወተወቷቸው ። ጽሕፈት ቤታቸውና መኝታ ቤታቸው ተበረበረ ። በጣታቸውም ቀለበት ውስጥ የሚገኘው ቁልፍ ተወስዶ የሰነድ መያዣ የቆጻ ቦርሳቸውም ተጎረጎረ ። ለሕዝብ የተገለጸው ግን በቦርሳቸውና በአውቶሞቢላቸው ውስጥ 979,506 የኢት ብር መገኘቱ ብቻ ነው ። ከዚህ በኋላ ነበር "የቅርብ ጓደኞቸው አማላጅ ቢላኩባቸውም በውጭ አገር ያስቀመጡትን ገንዘብ ለማስመጣት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል" በማለት በመንናኛ ብዙሃን አማካይነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሳሙት ።

የተባለው ገንዘብ መምጣት ጉዳይ አልባት ሳያገኝ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት እንዲገወሩ ተደረገ ። ንጉሠ ነገሥቱ ወደዚህ ቤተ መንግሥት ለመጨረሻ ጊዜ ጉራ ብለው የነበሩት በሐምሌ 16 ቀን 1966 ዓ·ም 82ኛው የልደት በዓላቸው በዙፋን አዳራሽ በተከበረበት ዕለት ነበር ። ሥነ ሥርዓቱ የተከበረው በዋዜማው ልጅ እንዳልካቸው መኩንን ተሸረው በደርግ ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብለው የተሾሙት ልጅ ሚካኤል እምሩ በአምባሳደርነት ያገለግሉ ከነበረበት ከጂኔቫ ገና ሳይ መጡ ፡ ጥቂት የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ብቻ በተገኙበት ፡ በጣም በቀዘቀዘ ሁኔታ ነበር ። "እንኳን አደረሰም" በማለት የተናገሩት ጨግምንት ንግግርም ሆነ የንጉሠ ነገሥቱ መልስ እንደቀድሞው ሞቅ ያለ አልነበረም ። ሆኖም ኬክ መቆረሱ ፡ ሻምፓኝ መከፈቱ አልቀረም ። የቀድሞ አቀራረቡን ያላሳነሰ ቢናር ፡ የኢትዮጵያ የሀገር ፍቅር ማኅበር የኪነት ቡድን ብቻ ነበር ። በተረፈ ከዚያን ዕለት ድርጊት ታዋቅ "ግራኝ መሐመድ" በሚል ርዕስ በአቶ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ የተደረሰው መጽሐፍ የመጀመሪያ ቅጂ ለንጉሠ ነገሥቱ በሥነ በዓሉ ላይ መበርከቱ ነበር ።

የንጉሠ ነገሥቱ ከአራተኛ ክፍለ ጦር ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት መዛወር እንደወትሮው በሌላ ክብረ በዓል ላይ ለመገኘት ሳይሆን ፡ የንግሥት ዘውዲቱ እልፍኝ በነበረው ሕንፃ ውስጥ በአራት ግድግዳ ውስጥ ተወስነው እንዲቀመጡ ለማድረግ ነበር ። ከዚያ በእስራት በቆዩበት ጊዜ በአራፊ ጨርቅ የተሸፈን ምግብ ከኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ከአሳላፊዎቻቸው በእንዱ እማካይነት ይመላለስላቸው ነበር።

በዚውም ጊዜ የደርግ ምክትል ሊቃነ መናብርትና ሌሎችም አባሎች እየተመላለሱ ገንዘብ ያስቀመጡበትን ፍንጭ እንዲያወጡ ጫት ማታ ይንዘንዟቸው ስለነበር በመሶበ ወርቅ ብጤ የሚመጣውን ምግብ ቢመገቡ ትም ከሰውነታቸው አይጠጋም ነበር ። በውትወታ ብዛት ሕሊናቸውን እንዲስቱ ከማድረግም አልተቆጠቡም ።

ከእነርሱ ምርመራና ጥያቄ ፋታ ሲያገኙ በስተምሥራቅ በኩል ባለው መስኮት በቤተ መንግሥቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ወደሚገኘው የኪዳነ ምሕረት ፡ የበዓታ ማርያምና የቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት እየተመለከቱ የመጨረሻ ሕይወታቸውን እንዲያሳምርላቸው ይፀልዩ ነበር ። ፀሎታቸው በማወቅ ወይም ባለማወቅ በፈጸሙት ፈጣሪያቸው

ይቅር እንዲላቸው ፣ ሽግግሩ ሰላማዊ እንዲሆን ፣ በኢትዮጵያ ምድር ደም እንዳይፈስ ፈጣሪያቸውን መማፀን እንደሚሆን መገመት ይቻላል ። እንደ ደም መፋሰስ የሚጠሉት ነገር ባለመኖሩ ነበር የቀድሞው የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ሌ ጂኔራል አበበ ገመዳ የደርግ አባሎች ገና በመደራጀት ላይ እንዳሉ ለማፈን አቅደው ፈቃድ ሲጠይቁ አይሆንም በማለት የከለከሉዋቸውና የመጨረሻው የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ሜ/ጂኔራል ታፈሰ ለማ እርሳቸውን ለመጠበቅና ቤተ መንግሥቱንም ለማስከበር በታንክ ባሳጠሩበት ወቅትም ምንም እርምጃ እንዳይወሰድ ያስጠነቀቁት ።

ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል ኢትዮጵያን ከአስተዳደሩ በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይል ሥላሴ ሥልጣናቸውን ለወታደር አስረከቡ ። የማኪያቬሊ የአስተዳደር ፈሊጥ እንግዳ የማይሆንባቸው ፣ ማንኛውንም ነገር የማይንቁ ፣ እህ ? ማለትን የሚያዘወትሩት ፣ ከልዩ ልዩ ተከታታዮች የሚቀርቡት መረጃዎችንና የባለሥልጣኖችን የሥራ መግለጫ ያለመሰልቸት የሚያነቡት እኒህ ብልህ ሰው ምኑ ተስኖአቸው ይሆን በዚህ ወቅት መበለጣቸው ?

በዕድሜ በመግፋት ፣ ደም ለማፍሰስ ባለመፈለግ ፣ መካር በማጣት ፣ ወይም ምክር ባለመስማት ወይስ በንግርት በማመን ይሆን ፣ የዕድሜም ሆነ የሥራ ተመክሮ ብልጫ ለሌላቸው ፣ ለበቀል ለተነሳሱ ፣ የሌሎችን ውጥን ነጥቀው እኛ አለንልህ የሚል ብልጣ ብልጥ ተሰፋ ለሕዝብ በመስጠት ከሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመውጣት ለቀረቡ የወታደራዊ ቡድን አባሎች እጅ የሰጡት ?

መልሱ የሁሉም ምክንያቶች ድምር ውጤት ሳይሆን አይቀርም የሚል ይሆናል ። እርግጥ ዕድሜያቸው ገፍቶአል ። ንጉሥ ዳዊት "የሰው ዕድሜው ቢበዛ ሰባ ወይም ሰማኒያ ዓመት ነው ፣ ከዚያ በላይ ያለው ድካም ነው" አይደል ያለው ? እንደ ኢትዮጵያ ባለ ብዙ ችግር በሚበዛበት አገር ከሰማንያ ዓመት ዕድሜ በኋላ አገር ለማስተዳደር መሞከር እድካሚም አስቸጋሪም ነው ። የሰማኒያኛውን የልደት በዓላቸውን በአከበሩበት ጊዜ ነበር የለውጥ ምሥራች ከእርሳቸው የተጠበቀው ። ተሰሚ መካር በማጣት ይሆን የወደፊቱን የኢትዮጵያ ዕድል ፈንታ ሳያቃኑ የቀሩት ? ። እርሳቸው ከልብ ያዳምጡ የነበረው የልዑል ራስ ካሳ ኃይሉን ፣ የግርማዊት እቴጌ መነንንና የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስን ምክር ነበር ። ምክራቸው ከእነርሱ ጋር ስላለፈ አሁን ከየት ተገኝቶ !! ሌሎቹን የሚመለከቱት

በእጅጉት ደረጃ ባለመሆኑ የበታች አባላ አድርገው ነው የሚያዳምጡት ። በተፈጥሮ ተጠራጣሪ በመሆናቸው የሥነንም ምክር ያለ ጥርጣሬ ወይም ያለማመንታት ስመቀበል ያዳግታቸዋል ።

ጥርጣሬ ካለ ፣ ለሥልጣን ቀናኢ ከተሆነ እንደዚሁ ያለው ሁኔታ ግጋጠሙ አይቀርም ። ንግርት እየተባለ ከየአቅጣጫው የሚመጣው አሳብም ቁርጠኛ እርምጃ ከመውሰድ ያግዳል ። በዚህ ዕድሜ ለሥልጣን በመታገል ደም ለማፍሰስ አለመፈለግ ደግሞ ደምሳሹ ምክንያት መስሎ ይታያል ። ይህ ባይሆን ኑሮ "ከሥልጣን ወርደዋል" ሲባሉ በአጠገባቸው የሚገኙትን ስንኳ በለው ቢሉ ለማስደንገጥ ያህልም ቢሆን ስንኳ ጥይት ሳይተኮስ አይቀርም ነበር ። እርሳቸው የሠጉበት የደም መፍሰስ ለወራት ስንኳ ሳይቆይ ሥልጣን በነጠቁዋቸው ሰዎች በጠብታ ሳይሆን እንደጎርፍ ነው የፈሰሰው ። ስህተቱ ደም እንዳይፈስ ለማድረግ ሥልጣናቸውን ያለምንም ማንገራገር በመልቀቃቸው ላይ ሳይሆን ፣ ለኢትዮጵያ በዘላቂነት የሚተላለፍ የፖለቲካ ጉዳዳና ቀደም አድርገው ሳይቀይሱ በመቅረታቸው ላይ ነው ። ቀደም ብሎ ያልተደራጀ ነገር ሁኔታዎች አቅጣጫ ከለወጡ በኋላ ለማቃናት መሞከር ውጤቱ "ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" ከሚባለው ተረት የተለየ አይሆንም ። ለነገሩማ ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ፣ የአልጋ አወራረሱ በተከታታይነት እንዲታወቅ አድርገው አልነበር፣ የዘገየ ውሳኔ ፣ ጊዜው ያለፈበት እርምጃ ሁኖ ቀረ እንጂ ! ። በዚህ ላይ ለሥልጣን ያቆበቆበው ቡድን ለእርሳቸው ታማኝ መስሎ መቅረቡ ሌላው ሊያግልላቸው የቻለ ጉዳይ ነበር ። የተቆርቋሪዎቻቸውን ምክር ባለመስማታቸው "አያያዙን አይተህ ጭብጦውን ቀማው" የሚባለው የአበው ፈሊጣዊ አነጋገር ተፈጻሚ ሊሆን ቻለ ። በዕድሜያቸው መግፋት ምክንያት ልጅ የሚያቀርበው ልምምጥ የአባቱን ልብ እንደሚሰብር የደርግ የሕሳዊ መሲህ አነጋገር በቀድሞ አስተዋይነታቸው ላይ ጫና አሳደረበት ። ይሁን ያለው ሆነና አጅራም ተበለጡ ፣ ተቀደሙ ።

ሕይወታቸውን በሥርዓት ፣ በፕሮግራም የሚመሩ ለጸሎት ፣ ለሥራ ፣ ለምግብ ፣ ለመኝታ ጊዜያቸውን የመደቡ ፣ የዕለት ፕሮግራም ተከትለው የሚኖሩ ነበሩ ። ከመኝታ የሚነቁት ሲነጋጋ በ12 ሰዓት ሲሆን፣ የ45 ደቂቃ የንጋት ፀሎት ያደርሳሉ ። በበዓላት ቀናትና በተለይም ወር በገባ ከ1—7 ባሉት ቀናት ጾም ካልሆነ ማለዳ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ካስቀደሱ በኋላ ነበር ወደ መኖሪያ ቤተ መንግሥታቸው የሚመለሱት ።

በፍስክ ቀን ቁርስ በልተው ፡ ጾም ከሆነ ምንም ላይቀምሱ ልክ በሦስት ሰዓት በታላቁ ቤተ መንግሥት ከሚገኘው ጽሕፈት ቤታቸው ገብተው በአቅቤ ሰዓት ሹማምንቶቻቸውንና ባለጉዳዮችን በማነጋገር ነበር ሥራ የሚጀምሩት ። ጾም በሚሆንበት ጊዜ ልክ በሰባት ሰዓት ከጽሕፈት ቤታቸው ተነስተው በበዓላትና በየወሩ ከ1—7 ባሉት ቀናት ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ያስቀድሳሉ ። ከቅዳሴ በኋላም ወደመኖሪያቸው ቤተ መንግሥት (ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት) ሄደው ምሳ በልተው ከ8—10 ሰዓት ለዕረፍት ይተኛሉ ። ልክ በ10 ሰዓት ፡ ከሻይ በኋላ ደግሞ በኢዮቤልዩ ቤተመንግሥት ከጽ/ቤታቸው ገብተው የቀረቡላቸውን ጽሑፎች ይመረምራሉ ወይም በአቅቤ ሰዓት ባለሥልጣኖችንና ቀጠሮ የተሰጣቸውን ሰዎች እስከ 11 ሰዓት ሲያነጋግሩ ይቆያሉ ። ከ11 ሰዓት በኋላ ደግሞ እስከ 12 ሰዓት በየሆስፒታሉ ተኝተው የሚታከሙ የሚያውቋቸውን ሰዎች ይጎበኛሉ ወይም በቤተ መንግሥት ምድረ ግቢ በእግራቸው ይንሸራሸራሉ ። ከምሽቱ በ2 ሰዓት ተኩል ራት በልተው እንደጨረሱ ታላቅ ፊልም ያያሉ ። ፊልሙ እንዳበቃ ወደመኝታ ክፍላቸው ገብተው የሚያነቡዋቸውን ጽሑፎች እንብበው ሲጨርሱ ለአርባ አምስት ደቂቃ የምሽት ፀሎታቸውን አድርሰው ይተኛሉ ። ሲነጋጋ እንደነቁ የቀን ፕሮግራማቸውን ይቀጥላሉ ። የቀጠሮ ሰዓት አክባሪ በመሆናቸው ፡ በተለይ ከውጭ አገር ሰዎች ጋር ያላቸው ቀጠሮ ዝንፍ አይልባቸውም ። ለውጭ አገር ሰዎች በተለይም ለዲፕሎማቶች ያላቸው አስተያየት ከፍተኛ በመሆኑ በክብር ተቀበለው ነው የሚያነጋግሩዋቸው ። የውጭ አገር ሰዎችን የሚያነጋግሩትም በእንግሊዝኛ ሲሆን ቀደም ሲል ልዩ ጸሐፊያቸው በነበሩትና በኋላም በተለያየ ጊዜ የጽሕፈት ሚኒስትርና የግቢ ሚኒስትር በሆኑት በእቶ ተፈራ ወርቅ ኪዳን ወልድ ወይም በልዩ ረዳቶቻቸው በዶክተር ምናሴ ኃይሌና በእቶ ዮሐንስ ኪዳን ማርያም ፡ በፈረንሳይኛ ሲሆን ደግሞ በልዩ የፕሬስ ክፍላቸው ኃላፊ በእቶ መብሃ ሥላሴ ዓለሙ አስተርጓሚነት ነበር ።

ጠንቃቃነታቸው በሥራና በዕለት የዕረፍት ጊዜያቸው ብቻ ሳይሆን በአመጋገባቸው ልክና ዓይነትም ጭምር ነበር ። የሚመርጡትም ምግብ ሥጋ በመጠኑና ከአትክልት የሚሠራውን ሲሆን ፡ ፍራፍሬም ያዘወትራሉ ። ጤናቸውንም የሚጠብቁት በአመጋገብና በእኗኗርም ጥንቃቄ ነው ። ከሐኪም ምክርም አይወጡም ። በሕይወታቸው በዕኑ ታመው

* በኋላ ጸሐፊ ትእዛዝ

የነበረው ዓይናቸውን ነበር ። ስለዚህም ለዕውራን ያላቸው በጐ አመለካከትና ርህራሄ በጣም ከፍተኛ ነበር ። ለእንስሳት ያላቸውም ርኅራኄ በጣም የሚደንቅ ነበር ። ውሾችን ፡ ለማዳ እንስሳትንና አዕዋፍን በእጃቸው መመገብ የዕረፍት ጊዜያቸውን ከሚያሳልፉበትና ከሚደሰቱበት ተግባር አንዱ ነበር ።

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕይወት ከኢትዮጵያ ዕድገትና ውድቀት ጋር የተሳሰረ ውኖ ይገኛል ። ኢትዮጵያ ከባላባታዊ (ፊውዳል) አስተዳደር ወደ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መንግሥት አቅጣጫ ያመራችው በዘመነ መንግሥታቸው ነው ። በኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፈ ሕገ መንግሥት የታወጀው ፡ ዕድገትን ተከትሎ የተሻሻለው ፡ በመጨረሻም በሕዝብ ጥያቄ ሌላ ሕገ መንግሥት የተረቀቀው ፡ ዘመናዊ የማዕከላዊ መንግሥት አውታርም በየክልሉ የተዘረጋው ፡ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ተቋሞች ያቆጠቆጡት ፡ የበቀሉትና ለፍሬ የበቁትም በዚሁ ዘመነ መንግሥት ነው ። ኤርትራ ከእናትዋ ከኢትዮጵያ ጋር የተቀላቀለችው ፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን በኢትዮጵያ ዋትጧዋ·ት በአርሳቸው ጥረትና የአፍሪካ አባት ሁነው በመታየታቸው ። ኢትዮጵያ የቀድሞው የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሀ ነችው ፡ የአሁኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥራች አባል ኅመሆን የበቃችው ፡ በገለልተኛ አኳሮች ንቅናቄም ተሳታፊ የሆነችው በእርሳቸው የአርቆ አስተዋይነት ዘመን ነው ። ዘመናዊ አበይት ሕግጋት (ኮድስ) መታወጅም የዚሁ ዘመነ መንግሥት የሥራ ፍሬ ነው ።

በአንፃሩ ደግሞ በኢጣልያ ወረራ ምክንያት የኢትዮጵያ ነፃነት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የታጣው ፡ ከአምስት ዓመታት የቅኝ ግዛት አስተዳደር በኋላ ሀገሪቱ እንደገና ነፃነቷን የዋጀችው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው ። በመጨረሻም ደርግ በኢትዮጵያ መድረክ ላይ ብቀ ብሎ አገሪቱ ካልተጠበቀ አዘቅት ውስጥ መውደቅ የጀመረችው በዚሁ ዘመነ ንጉሠ ነገሥት ማክተሚያ ላይ ነው ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ገናና በመሆናቸው በዚህ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በመፈንቅለ መንግሥት ከዙፋን መውረዳቸው እንደተሰማ በጣም የሚያከብሩዋቸው ፡ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም አለኝታ እድርገው የሚመለከቱዋቸው የአንዳንድ አገሮች መሪዎች ከኢትዮጵያ በሰላም ወጥተው ወደ እነርሱ እንዲላኩላቸው ሥልጣን

ለያዘው ለደርግ ጥያቄ አቅርበው ነበር ። ከኢጣልያን ወረራ በኋላ በድል አድራጊነት ከስደት መምጣታቸውን ፡ በ1953 ዓ.ም ደግሞ የመፈንቅለ መንግሥቱን ሙከራ አክሽፈው ወደ ዙፋናቸው መመለሳቸውን በማስታወስ ደርግ የመንግሥታቱ መሪዎች ላቀረቡት ጥያቄ አዎንታዊ መልስ አልሰጣቸውም ። እንዲያውም ከእጁ እንዳያመልጡት ሙጭጭ ብሎ መጠበቅ ፡ አኗኗራቸውን ማካበድ ጀመረ ። የዕድሜያቸውን መግፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት አስተያየት ለማድረግ አልፈለገም ። ስለዚህም የለመዱትን ስደተኛነትንም ነፈጋቸው ። በዓለም ላይ ባላቸው ገናና ዝና የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ያልተቋረጠ ጥረት ምክንያት የእነርሱ ጥቅም የተነካባቸው የመሰላቸው የአንዳንድ መንግሥታት ባለሥልጣኖች ግን ከሥልጣን በመውረዳቸው መደሰታቸውን የገለጹት በመልእክተኛ አማካይነት ነበር ። ልዑካኖቻቸውም ፡ ከወፍ ፈጣን የሆነ ሚራጅ ተሳፍረው ወደ አዲስ አበባ በመክነፍ መጥተው ለውጡን የሚደግፉና ሥልጣን ከያዘውም አካል ጋር አብሮ ለመስራት ፈቃደኛ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ።

ንጉሠ ነገሥቱን ከደርግ እጅ ለማውጣት አለመቻሉ ከታወቀ በኋላ የተከተለው ልምምጥ ፡ በአያያዛቸው ሰብዓዊ ርኅራኄ እንዲደረግላቸው ፡ ለክብራቸው የሚገባው አያያዝ እንዳይቀነስባቸው ነበር ። ይህም ሰሚ አላገኘም ።

በዕድሜ መግፋት ፡ በአያያዝ መጐሳቆል ፡ በምርመራ መብዛት ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ሕመም ተጫጫናቸው። አካላቸውም፤ መንፈሳቸውም እየተዳከመ ሄደ። እንደቀድሞው የሐኪም ክትትልም አልተደረገላቸውም። የሽንት መከልከል (ፕሮስቴት) ሕመም አሰቃያቸው። ከብዙ ውትወታ በኋላ ነበር ስመ ጥሩ የቀዶ ጥገና ሐኪም ዶክተር* አስራት ወልደ ኢየሱስ እንዲመረምሩዋቸው የተደረገው። ሐኪሙም ተገቢውን ሕክምና ለማግኘት እንዲችሉ ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ ሀሳብ አቀረቡ። ግን ማን ቢፈቅድ? ከዚህ በኋላ ነበር በሐኪም ቤት ሳይሆን በታሰሩበት ስፍራ የቀዶ ጥገና ሕክምና እንዲያደርጉላቸው ሐኪሙ በደርግ ባለሥልጣኖች የተጠየቁት። በአገር ውስጥ ኦፕራሲዮን እንዲረግላቸው ከተፈለገ በማረፊያ ቤት ሳይሆን፡ ድርጅት ባለበት በሐኪም ቤት መሆን እንዳለበት ሐኪሙ የገለጹት በቀረበላቸው ጥያቄ በመገረም ነበር።

* በኋላ ፕሮፌሰር

የደርግ ባለሥልጣኖች ወደው ሳይሆን ሌላ አማራጭ መንገድ በማጣታቸው ምክንያት ከሆስፒታሉ ገብተው ኦፕራሲዮን እንዲሆኑ የቀረበውን አሳብ ሲቀበሉ፡ በሆስፒታል ምርጫ ላይ ደግሞ ሌላ ችግር ተፈጠረ። ዶክተሩ ራሳቸው ኦፕራሲዮን እንዲያርጉላቸው ከተፈለገ በሚሠሩበትና በአንፃራዊ ሁኔታ የተሟላ መሣሪያ በሚገኝበት በልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ተኝተው ኦፕራሲዮን እንዲያደርጉላቸው ሲጠይቁ፡ ደርግ ድግሞ ወታደራዊ ሆስፒታል በሆነው በቀድሞው የክብር ዘበኛ ሆስፒታል ኦፕራሲዮን ይደረግላቸው በማለት የሐኪሙን ምርጫ አጥብቆ ተቃወመ። እንደፍላጐታቸው ሳይሆን የአዛውንቱን ሕይወት ለማዳን ሲሉ ሐኪሙ በዚሁ ተስማምተው ግንቦት 23 ቀን 1967 ዓ.ም በዚሁ ቤተ ሕክምና ኦፕራሲዮን ተደረገላቸው። ትረፍ ብሎአቸው ሕይወታቸው ዳነ። ከሕመሙ ስቃይ ተፈወሱ። ነገር ግን በቂ የማገገሚያ ጊዜ ሳይሰጣቸው የሐኪሙን ተቃውሞ በመጋፋት ደርግ ወደ እስር ቤት መለሳቸው።

ሴት ልጃቸው ልዕልት ተናኜ ወርቅ ኃይለ ሥላሴም እታሰሩበት ቦታ ድረስ ሄደው እንዲጐበኙዋቸው ተደረገ። ያ ኮሳሳ ሰውነታቸው ተጐሳቁሎ፡ ጠጉራቸው ተንጨባሮ ነበር ያገኙዋቸው። ሆኖም በደረሰባቸው ማዘናቸውን በሕይወታቸው መትረፍ በመደሰት ነበር የለወጡት። የተመኙትን ቢያጡ የጠሉትን ይመርጡ ሆነባቸው። ከኦፕራሲዮን ጠረጴዛ ላይ በሕይወት መውረዳቸው ግን የደርግ ምኞት አልነበረም፡ የያዛቸውም ሕመም፡ የቢላዋው ሥለት ወዲያውኑ ቢገላግላቸው ነበር የሚመርጡት።

ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ ኦፕራሲዮን ያደረጉዋቸው ሐኪም ከእስር ቤት ድረስ ገብተው እንዲጐበኙዋቸው የተፈቀደው አንድ ጊዜ ብቻ ነበር፡ ያውም ከብዙ ጉትጐታ በኋላ። ከሐኪም ቤት ከወጡ በኋላ "የግል ሐኪማቸው ተፈልገው ታጡ፡ ንጉሠ ነገሥቱ በድንገት ታመው ነሐሴ 21 ቀን 1967 ዓ.ም አረፉ" ተብሎ በደርግ መርዶው ለሕዝብ ተነገረው። በተባለው ቀን ግን ዶክተር አስራት ከሶደሬ ተመልሰው ከቤታቸው እንደነበሩና ማንም አንዳልጠራቸው በሌላ ጊዜ አረጋግጠዋል።

በቅርብ ያገለግላቸው የነበረው የቤት አሽከር አቶ እሸቱ ተክለ ማርያም ንጉሠ ነገሥቱ የሞቱት በሕመም ሳይሆን፡ ታፍነው መሆኑን በመገናኛ ብዙሃን ገልጽዋል።

የእልፍኙ ሌላው ምሥጢር አሟሟታቸው ብቻ ሳይሆን የት እንደተተበሩ ሳይታወቅ መቅረቱ ጭምር ነበር።

ንጉሡ ነገሥቱ የሞትን ጽዋ የቀመሱት በዓመቱ መጨረሻ ላይ ይሁን እንጂ ደርግ በማስገደድ የንብረት ውርስ ሰነድ ያስፈረማቸው ቀደም ብሎ በጥቅምት 7 ቀን 1967 ዓ.ም ነው። ንጉሡ ነገሥቱ በደርግ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ የፈረሙት በመገደድ መሆኑን በዕለቱ የተነሳው ፎቶግራፍ ይገልጻል። ይህ ባይሆን ኑሮ " በሙሉ አገር በስሜ፣ በእቴጌ፣ በልጆቼና በልጅ ልጆቼ ስም በየባንኩ የሚገኘውን ገንዘብ በኢትዮጵያ ለደረሰው ድርቅ ማቃለያ እንዲውል ፈቅጃለሁ" በማለት ከራሳቸው አልፎ በሌሎች ስም የተመዘገበው ሁሉ (የተመዘገበ ካለ) አውርሻለሁ ባላሉም ነበር ። ይህ ሰነድ ምን ሕጋዊ ዋስትና ይኖረዋል ብለው ይሆን ያስፈረሙዋቸው፣ በማስገደድ የተፈረመ ሰነድ በሕግ ፊት ዋጋ እንደሌለው የሚያማክር ባለሙያ በመካከላቸው የለም ይሆን? በልጅ ልጆቻቸው ስም በውጭ አገር የሚገኘው መጠነኛ የሆነ ገንዘብ ለመንግሥት የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ገንዘቡ ለመንግሥት እንዲከፈል በማዘዝ ደርግ ባሰናዳው ሰነድ ላይ በመገደድ የፈረሙት በታላቁ ቤተ መንግሥት በእስር ላይ ያሉበሩት ቀደም ሲል የልዑል መኮንን ልጆችን ሐሳብ ያንቀሳቅሱ የነበሩት ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነወልድና አቶ ዮሐንስ ኪዳን ማርያም ነበሩ።

ንጉሠ ነገሥቱ ሰነዱን በፈረሙበት ወቅት በስፍራው የተገኙትና ሌላ ሰነድ የፈረሙት የእነዚህ የቀድሞ ልዩ ጸሐፊዎቻቸው ገጽታቸው ብቻ ሳይሆን አለባበሳቸውም ጭምር በመገደድ የፈረሙ መሆኑን ያስረዳል ። ይኸውም ሆኖ ገንዘቡን መገኘቱን ፣ ከተገኘስ ደግሞ ደርግ ለምን እንደአዋለው የተገለጸ ነገር የለም ። የእልፍኙ ምሥጢር ግዳጅ ፣ ሞትና የመቃብር መሰወርን ያካተተ ነው ። "ተሸፋፍነው ቢቀጉ ገልጠ የሚያይ አምላክ አለ" እንደሚባለው የደርግ አባሎች ለዓመታት የሸፈኑት ጉድ ገሀድ ሳይወጣ አይቀርም ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ዓለም የሚያውቀው ይሆናል ።

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስም ምን ጊዜም ከመቃብር በላይ የመዋሉን ያህል ተክለ ሰውነታቸውና ገጽታቸው ልዩ ትዝታ የሚያሳድር ነበር። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተክለ ሰውነት በእጭር ቁመት፣ በሰፊ ደረት፣ በትልቅ ራስ ቅል፣ ሰፋ ባለ ፊት የተገነባ ሲሆን፣ ጫፉ ቆልመም ያለ ስልካካ አፍንጫ፣ በዓይን ጉድጓድ ውስጥ የተቀበሩ ቢሆኑም፣ አትኪሪ የሆኑ ዓይኖች፣ ጭቅጭቅ ያሉ ንጫጭ ጥርሶች ያሏቸው ፣ ከርዳዳ ጠጉራቸውን የሚያጉፍሩ፣ ፈታቸው በረዝ የተሸፈነ ብስል ቀይ ናቸው። የፈልድ ማርሻል ምልክት ያለበት የነበርዲን የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) የሚያዘወትሩ፣ በዚሁ ላይ ካባ የሚደርቡ፣ የሚጸያዩና የኒሻን ሪበን ምልክቶች የዩኒፎርማቸውን የግራ ደረት የሸፈኑ፣ ከቡሽ የተሠራ ካሰክ (መለዮ) በአጉፈረው ወጉራቸው ላይ የሚያጠልቁ፣ ተረከዘ ረጅም ጫማ የሚጫሙ፣ በትረ መኰንናቸውን ከእጃቸው የማይለዩ ቆፍጣና ሰው ናቸው። ጠቆር ያለ የሲቪል ልብስ የሚለብሱት አልፎ አልፎ ሲሆን፣ የአገር ልብስ የሚለብሱት ግን ለዘመን መለወጫ፣ ለልደትና ለትንሣኤ ብቻ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብርቅዬ ልጅ በመሆናቸው በልጅነታቸው በቂ የፀሐይ ሙቀት ቅልጥማቸውን ስለአልመታው ወርሀነት ያለባቸው ሲሆኑ፣ ጸገት ቁልቁሉቱን ሲወጡና ሲወርዱ ግን የማይዘነጣቸው ናቸው። ተከታዮቻቸው በላብ እንዲደፈቁ ያደርጋሉ እንጂ፣ እርሳቸው ድካም አይሰማቸውም። በአገር ሲጓዙ እርምጃቸውም ከሌላው እጥፍ ነው። ተፈጥሮን አድናቂ፣ ለሥልጣኔ ከፍተኛ አስተያየት ያላቸው፣ በውጭ አገር ጉዞአቸው ብዙ ቁምነገሮችን የቀሰሙ መሪ ናቸው። ድምፃቸው ጉርናና፣ የአንጋገር ዘዬአቸው ለየት ያለ ነው። ለምሳሌ " ታላት ሲሉ "ትላት" እንደዚሁም " ጀምበር" ሲሉ "ዝምበር" የሚሉ፣ ንግግር በሚያዳምጡበት ጊዜ በሁለት እጆቻቸው ጣቶች የልብ ቅርጽ ያለው ክብ የሚሠሩ፣ የውጭ አገር እንግዳ ካልሆነ በቀር ሌላውን ሁሉ በጽሕፈት ቤታቸው ውስጥ አብዛኛውን እየተንጐራደዱ የሚያነጋግሩ፣ ደከመኝን የማያውቁ ሰው ናቸው። ሕሙማንን መጐብኘት፣ ተማሪዎችን ማበረታታት፣ ለነዳያን መዘከር፣ ለሕፃናት መራራት፣ ለመንፈሳዊ አባቶች የላቀ ክብር መስጠት፣ ቁሞ ዳኝነት መስማት፣ በወታደራዊ ሰልፍ ጉብኝት ወቅት ንቃትና ጠንቃቃነትን ማሳየት፣ የንበታ ሥርዓት(ኢቲኬት) መጠበቅ፣ ቀጠሮ ማክበር የመለያ ባሕሪዎቻቸው ናቸው። የዕድሜ ሙግፋት

በአእምሮአቸው ላይ ተፅዕኖ ማድረግ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ የማስታወስ ችሎታቸው በቀላሉ ተወዳዳሪ የሚቀርብለት አልነበረም።

በዚህ ሁሉ እንግዳ አንያ ከተጣሉ ያቀረቡትን ሲያርቁ፣ ተቀናቃኛቸውን ሲደቁሱ፣ የሚሞግታቸውን ሲገስፁ፣ የሚጠራጠሩትን ሲከታተሉ ማየት የብርቅ አልነበረም። ከዚህም የተነሳ ነበር ከአክብሮቱ ሌላ ሁሉም ወጥ ለጥ፣ ለጠቅ ብሎ የሚተዳደርላቸው፣ የጠየቁትን የሚያመጣላቸው፣ ያዘዙትን የሚፈጽምላቸው።

በፖለቲካ የገበጣ ጨዋታ በቀላሉ የማይበለጡ፣ የተነሱበትን ከግቡ ሳያደርሱ የማያርፉ፣ የባለሙያ ምክርና አሳብ የሚያዳምጡ በመሆናቸው ነበር በዘመነ መንግሥታቸው ብዙ ታሪካዊ ሥራዎች በመፈጸም፣ ለወደፊት ዓላማ ተገቢ መሠረት ለመጣል የቻሉት። አላቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የማሰባሰብ ፣ የማመሳከርና ቁርጠኛ እርምጃ የመውሰድ ችሎታም ነበራቸው።

ከመንግሥታዊ ተግባራቸው ጉን ለጉን ችግረኞችን እና አካለ ስንኩላንን ለመርዳት፣ ባለሙያዎችን ለማበረታታት በማሰብ በገዛ ገንዘባቸውና በመንግሥትም ድጐማ በስሚቸው የተሰየመ እንድ የበጐ አድራጐት ድርጅትና* እንድ የሽልማት ድርጅት** ማቋቋማቸው፣ የሁለቱንም ሥራ በቅርብ መከታተላቸው የላቀ ዝናንና አድናቆትን በእገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ሊያተርፍላቸው ችሏል።

ሌላው በታሪክ ሞገስን የሚያሰጣቸው ዘመናዊ አዘያት ሕግጋት በስመ ጥር የሕግ ባለሙያዎች እንዲረቀቁ ማድረጋቸው ሲሆን ፣ በቁመት መሰላቸው ከሆነው ከፈረንሳዩ ናፖሊዮን ጋር በተግባርም ተወዳዳሪ አድርጓቸዋል። ከነዚህም ሕግጋት ዋናዎቹ በኢትዮጵያ እስከአሁን የሚሠራባቸው የወንጀል ሕግ፣ የፍትሐብሔር ሕግ፣ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጎች ፣ የንግድና የባሕር ሕጎች ናቸው ።

በዲፕሎማሲውም መስክ ኢትዮጵያ የሁሉም ወዳጅ እንጂ የማንም

---

* "የቀኃሥ በጐ አድራጐት ድርጅት መመሥረት" በሚል ርዕስ በዚህ ጸሐፊ ተዘጋጅቶ በ1952 ዓ.ም የታተመውን መጽሐፍ ይመልከቷል።

** "የቀኃሥ የሽልማት ድርጅት አስረኛ ዓመት" በሚል ርዕስ በ1963ዓ.ም የታተመውን መጽሔት ይመልከቷል።



አጼ ኃይለ ሥላሴ በመታጀራቸው የደንብ ልብስ

ጠላት አንዳልሆነች ለማሳወቅ መጣጣራቸው፡ አማካሪዎቻቸውን ከአንድ አገር ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ አገሮች እንዲሆኑ ማድረጋቸው፡ በዓለም አቀፍ መድረክ ኢትዮጵያ ተደማጭነት ያላት አገር እንድትሆን ለማድረግ በመቻላቸው ታሪካዊ ስፍራዎን ይዛ እንድትቆይ አድርጓታል። ይህ ሁሉ ነበር በአፍሪካ መሪዎች ዘንድ አንጋፋ፡ ጠቢብ ሽማግሌ፡ መልካም መካሪ፡ አስታራቂ ሰው ሊያሰኛቸው የቻለው የእነዚህ ሁሉ ሀብተ ተሰጥዎ ባለቤት የሆኑት የሰማኒያ ሦስት ዓመቱ አዛውንት ነበሩ የአልፍኝ ምሥጢር ሰለባ የሆኑት።

፲፪

ትውስት

ከእስር ቤት ትውስት የማይዘነጋው ክፉው ነው ። የታላቁ ቤተ መንግሥት ትውስት የማይዘነጋውም በዘግናኝነቱ ነው ። ዘግናኝነቱ ንጉሠ ነገሥቱና ባለሥልጣኖቻቸው ለአሰቃቂ አሟሟት በመደረጋቸው ብቻ አይደለም ፡ አብዮት መጣላችሁ ተብለው ለሚሸነገሉትም ጭምር ለስቃይ ፡ በመጨረሻም ለሞት የሚዳረጉበት ሁኔታ በዚሁ ቤተ መንግሥት በመፈጸሙ ጭምር እንጂ ። ገና ከእስር ቤት ሲገቡ ለሞት የተጻፉ የመገደያ ሁኔታ እስኪመቻችላቸው ድረስ እንዲያርፉ የሚደረገው በዙፋን አዳራሹ ምድር ቤት ሶስት ቁጥር ተብሎ በተሰየመው ጠባብ ክፍል ውስጥ ነው ።

በታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት ሴት የታሰረችው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። የእርሷም እስር ለአንድ ቀን ቢሆንም ፡ አንድ ፡ ሁለትና ሶስት ቁጥሮች በወንዶች በመያዛቸው ያደረችው ከዘብ መቆሚያ ዛኒጋባ ውስጥ ነበር ። ከዚያ ወደ ሌላ እስር ቤት ተዛውራ ነው በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደለችው ። በአገራችን ወግና ልምድ "የትሙት በቃ ፍርድ" ከተፈረደባትም በኋላ ቢሆን ሴት ዕርጉዝ መሆንዋ ከታወቀ እስክትወልድ ድረስ ጊዜ ይሰጣት ነበር ። የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ የነበረችው ወይዘሮ ዳሮ ነጋሽ ግን ልጅዋን እስክትገላገል ድረስ ስንኳ ጊዜ አልተሰጣትም ፡ በደርግ ባለሟሎች በጭካኔ ስትገደል ። ፍትህ ሠርቻለሁ ለማለት ይመስላል ደርግ የነፃ እርምጃ ሥልጣን ለካድሬዎቹ ከሰጠ በኋላ በመካከላቸው በተፈጠረ ቅራኔ ምክንያት አቶ ግርማ ከበደ እነ ወ/ሮ ዳሮን በመግደሉ የሞትን ጽዋ እንዲቀምስ ሲያደርግ ነበር እርሷ በግፍ መገደሏን የገለጸው ። ልትወልድ የተቃረበች እርጉዝ መሆኑዋ ጎልቶ ይታይ የነበረችው ወይዘሮ በማሰቃየት መገደልዋን ሲሰማ በእስረኛው ሕሊና

ዘግናኝ ስሜት ነበር ያሳደረው ።

ሌሎችም እንደዚሁ ለግድያ እስከሚወሰዱ ሶስት ቁጥር በመባል በሚታወቀው ገደ ቢስ ክፍል ለጥቂት ቀናት በጥብቅ እስራት ከቆዩ በኋላ መገደላቸውን ደርግ በመገናኛ ብዙሃን ሲገልጽ የሌሎች እስረኞች ልቡና በሀዘን ይቆራመዳል ። ይህ መጥፎ ዕድል ከደረሰባቸው መካከል ታላቁ አርበኛ ደጃዝማች ይልማ በሺ ፡ ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩና ደርግ ያቋቋመው ልዩ የጦር ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩት ኩ/ኃይሉ ረጋሳ ይገኙበታል ። ኩሎኔሉ የተገደሉት በወንጀል እሳቸው ራሳቸው ያስችሉበት በነበረው ፍርድ ቤት በተሰጠ ፍርድ ሲሆን ፡ ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ ግን የደርግን ዓላማ በመቃወም በምዕራብ ሸዋ ውስጥ ከደርግ ሠራዊት ጋር ተታኩሰው በመማረካቸው ለተባለው ፍርድ ቤት ቀርበው በተሰጠው ፍርድ ነው ። ደጃዝማች ይልማ በሺ ደግሞ በሰላሌ በሰላም ተቀምጠው ሳለ ደርግ እጅ እንዲሰጡ ሲጠይቃቸው አዛውንቱ አርበኛ "አምስት ዓመት ሙሉ ለጠላት ያልሰጠሁትን እጄን አንዱን ወንድሜን ፊታውራሪ ማሞ በሺን ለአሰረ ሌሎች ባለሥልጣኖችን ስገደለ አምባገነን አልሰጥም በማለት ከሁለት ወንድሞቻቸው ከደጃዝማች ሸዋረገድና ከኩሎኔል አማረ በሺ ጋር ሁነው ከደርግ ጦር ጋር ተታኩሰው ፡ ወንድሞቻቸው ሲሞቱ እርሳቸው ስለተማረኩ ፡ በጦር ፍርድ ቤት ቀርበው ሞት ስለተፈረደባቸው መሆኑን ደርግ ገልጿል ። እኒህን ዕድሜያቸው በጣም የገፉ ፡ በሽምግልናና በሕመም ምክንያት ዓይናችው በደንብ የማያይ ፡ በአርበኝነት አገራቸውን ያገለገሉ ሰው ለሞት ተቃርበው ሳለ ሁኔታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በመማር ፋንታ ለመግደል መቻኮሉ ለደርግ ምን እርካታ እንደሰጠው አይታወቅም። የታላቁ ቤተ መንግሥት እስረኞች ከፊታውራሪ ማሞ በሺ ጋር ሀዘን በመቀመጥ ነበር ምህረት የለሹን ደርግ ያማረሩት ፡ ልባዊ ሀዘናቸውን የገለጹት ።

የተማረከን ሰው በዓይን የማየት አምሮት ያደረባቸው የደርግ ም/ሊቀመናብርት ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ ተማርከው ሲመጡ ብቻ አልነበረም በአጥር ስር ቆመው ምርኮኛውን በማነጋገር አምሮታቸውን የተወጡት ፡ እነ ደጃዝማች አሉላ በቀለ ቆስለው በወሳንሳ ወደ ክሊኒክ ሲወሰዱም ጭምር አሰፍስፈው ተመልክተዋል ።

እስረኞችን በ"ዙ" ውስጥ እንደሚገኝ እንስሳ እየተዘዋወሩ ማየት ፡

እንዳንዶችንም በንቀት ማነጋገር ፣ የደርግ አባሎችና በየክፍለ ጦሩ የተቋቋሙት የንዑስ ደርግ አባሎች አልፎ አልፎ ከሚፈጽሙት ተግባር እንዱ ነበር ። መቼስ በሰው እጅ ያለ ሰው የዘወትር ምኞቱ መፈታት በመሆኑ እንዲፈቱ ፣ እስከዚያውም እያያዛቸው እንዲሻሻል እንዲያደርጉ በጉብኝታቸው ወቅት ሲጠይቋቸው ብዙዎቹ የሚሰጡት መልስ ተስፋ የሚያስቆርጥ እንጂ ተስፋ የሚያሳድር አልነበረም ። ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ባለማድረጋቸው የእነርሱ ጉብኝት በእስረኛው ላይ ያሳደረው ስሜት የደርግ አባሎች ብቻ ሳይሆኑ ፣ ሠራዊቱም ጭምር ርህራሄ እንደሚጎድለው አድርጎ የመመልከት ነበር ።

አንዱን ክፍለ ጦር የሚወክሉ የንዑስ ደርግ አባሎች የእስረኞችን ሁኔታ በመጎብኘት ላይ ሳሉ "በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፣ መንግሥት ለመገልበጥ አሲረሀል በሚል ወንጀል በቀረበብኝ ክስ ተፈርዶብኝ ለአምስት ዓመታት ታስሬአለሁ ፣ የታሰርኩት ለፍርድ ቤት ቀርቤ በሚገባ ተከራክሬ በተሰጠ ፍርድ ከመሆኑም በላይ የነበርኩበት ሁኔታ ለሰው ልጅ መብት ቆሜአለሁ ከሚለው ደርግ እያያዝ በጣም የተሻለ ነበር" በማለት ሌተና ኩ/እምሩ ወንዴ በድፍረት ለደርግ የጻፉትን ደብዳቤ ቅጂ በማንበብ የደርግን ይዞታ በማጣራር ፣ አቶ ተገኝ የተሻ ወርቅ በኃይል መናገራቸው የጎበኝዎችን ሕሊና የሚመታ ቢሆንም ፣ በጦሩ ስም የሚፈጸመውን ግፍ ለማስለቀስ መልእክተኞች ያደረጉት ነገር አልነበረም። በሌላ ጊዜ ደግሞ ፊታውራሪ አበበ ገብሬ ፣ አቶ ዘውዴ በጻጻና ኩ/ማሩ ጋረድ መረር ባለእንጋገር የሚፈጸመውን ኢሰብዓዊ ድርጊት በመቃወም ለጎብኝዎቹና ለደርግ አባሎች ያደረጉት ንግግር ከሶስት ቁጥር ውስጥ ብቻቸውን እንዲዘጋባቸውና በኋላም ወደ ማዕከላዊ ምርመራ ተወስደው እንዲሰቃዩ መደረግን አስከትሎባቸዋል ።

በሶስት ቁጥር ለብቻ በመታሰር የባሰ ሰቆቃ የደረሰባቸው እነዚህ ብቻ አልነበሩም ። አቶ ታደሰ ያዕቆብ ከቤት በተላከላቸው አንሶላ ላይ በውጭ አገር ቋንቋ(በእብራይስጥ) የተጻፈ ቃል አለበት በማለት ፣ አቶ አሐዱ ሳቡሬ ደግሞ ከቤት ልብስ በተላከበት ሻንጣ ውስጥ ሳይታወቅ ተሸጉጣ የገባች እንዲት ጥይት ተገኝታለች በማለትና በውጭ አገር አምባሳደር ሳሉ በውጭ ባንክ ስለአስቀመጡት ገንዘብ ከባለቤትዎ ጋር ተጻጽፈዋል በሚል ምክንያት ፣ ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም ደግሞ ከቤት በተላከ ሱሪ የግርጌ እጥፋት ውስጥ የከተማ ወሬ የሚገልጽ እህትዎ

የጻፉልዎት ወረቀት ተገኝቷል በሚል ሰበብ በዚሁ ክፍል የፀሐይ ብርሃን ሳያገኙ ተቆልፎባቸው ከሰው ተለይተው ብቻቸውን ታስረው እጅግ ተሰቃይተዋል ።

ይህ ሁሉ ከህዳር 14 ቀን 1967 ዓ·ም እልቂት ጋር ተደምሮ ነበር የእስረኞችን አእምሮ የመራራ ትውስት ማጎደር ያደረገው ። ይህም ነበር ከደርግ አባሎች የሚሰጠውን ማንኛውንም ተስፋ በሙሉ ልብ ለመቀበል እስረኛውን እምነት ያሳጣው ። በህዳር 16 ቀን 1967 ዓ·ም ነበር ሻለቃ ጌታቸው ቪበቪ ወደ እስረኞቹ መጥቶ "ጉዳያችሁ እየተጣራ ትፈታላችሁ፣ የምትከሰሱት ለፍርድ ቤት ትቀርባላችሁ እንጂ በሌሎች ላይ የተወሰደው ዓይነት የፖለቲካ እርምጃ እንደማይወሰድባችሁ በስመ እግዚአብሔር አረጋግጥላችኋለሁ ፣ ስለዚህ ይህንኑ በመግለጽ ለቤተሰቦቻችሁ የማረጋጊያ ደብዳቤ አሁንኑ ጻፉ" በማለት የተጣጠነው ። ይህ በደርግ አባሎች የተሰጠ ቃል ተፈጻሚ ያልሆነ ስለነበረ እስረኞቹ በየጊዜው ለፍርድ ቤት አቅርቡን ወይም ፍቱን የሚለውን ጥያቄ ያላቀረቡበት ዘመን አልነበረም። እስረኞቹ ያለፈ የእንፈታ ጥያቄያቸውን በማደስ ባለሥልጣን ያነጋገረን በማለት በጻፉት ማመልከቻ መነሻነት ሻምበል ካሣዬ አረጋው የሚባለው የደርግ አባል ከእስር ቤት ጠባቂዎች ጋር መጥቶ በእነጋገሩበት ጊዜ "መጣሪያ እንስተው የወጉዋቸውን በምህረት ስትለቁ ፣ ጥፋት ያለባችሁ ክስ ይቀርብባችኋል ፣ ሌሎቻችሁ ትፈታላችሁ የሚል ቃል ሰጥታችሁ ሳለ ከሁለቱ እንደኛውም ሳይፈጸም ይህን ያህል ጊዜ እቆያችሁን ። በዚህ መካከል ብዙዎቻችን በበሽታ ላይ ወደቅን ፣ ቤተሰባችንም በችግር ተፈታ ፣ ስለዚህ ፍቱን" በማለት ነበር በእስረኛ አፈ ጉባኤነት አቶ ክተማ ይፍሩ የተናገሩት ።

"ጠበንጃ አንስቶ የወጋንን ገበሬ ብንምርም ፣ በዓለም ታዋቂ የሆናችሁን ፣ ለምላሌ እርስዎን አቶ ክተማ ይፍሩን ብንፈታ ፖለቲካ ሠርተው ሥጋት ላይ ስለሚጥሉን እርስዎንና ተራውን ገበሬ በእኩል ኀይለ አናይም ፣ ስለዚህ ነው ባትወጉንም እናንተን የማንፈታው" በማለት ነበር ተስፋ የሚያስቆርጥ መልስ ሻምበሉ የሰጠው ። ጥፋት ሳይይሆን መፈራት ነበር ለእስረኞች መጥፎ ጻፋ የሆነው ። ምክንያቱም ማወቅ ፣ መታወቅ ለሰው ልጅ ለእበሳ መጋለጥ ምክንያት የሆኑበት ዘመን ነበርና ።

እስረኞቹ በመፈታት ረገድ ያላቸው ተስፋ ቢሟጠጥም ፣ እግዚአብሔር የሚያደርገው አይታወቅም በማለት ራሳቸውን ማጽናናታቸውን ፣ የመኝታ ክፍላቸውን ፣ የመጸዳጃ ቤቱንና የቁሻሻ ማፍሰሻ ጋሪውን ሳይቀር

በየዕለቱ በመጥረግ ፣ በማጠብና በማጽዳት ፣ የጽዳት መሣሪያና የሚረጩ መድኃኒት በሚያዋሉት ንጉዘብ በማጎበር በማስገዛት በተቻለ መጠን ጤናቸውን መጠበቃቸውን ቀጠሉ ።

አልጋ ወጥቶ እስረኞች መሬት ላይ በሚተኙበት ጊዜ ቀድሞ በአልጋ ስር ይተመጥ የነበረው የልብስ ሻንጣና የምግብ ዕቃ ፣ የሽንት መክፈያ (ፖፖ) እና የውሃ መቅጃ በእጠገባቸው ማስቀመጥ ስለነበረባቸው በቦታ መጣበብ ተጨማሪ ችግር ተፈጠረ ። ንፋሽኝ ፣ ወሰን ተላለፍክ በመባባል መናቆር ተጀመረ ። እንዳንድ እስረኞች ዕቃና መኝታቸውን ከሌላው ለመለየት በማሰብ ፣ ይልቁንም በአኗኗር ልምዳቸው ግለኛነት ፣ ማለትም በክፍል ፣ በቤት ፣ በአጥር ተለይቶ መኖርን በመልመዳቸው ፣ ይሽው ክባይ የማይለቃቸው ሁኖ በሙቅ በተነባበረ ጋዜጣ የወረቀት ግርዶሽ እየሠሩ እየሩ በነፃ እንዳይተላለፍ በማድረጋቸው ለብዙዎች ጤና መታወክና ለጭትጭት ምክንያት ሆኑ ። ሌሎችም መተላለፊያ መንገድ, አጥቶ አቅጣጫ በመለወጥ ያለወግ ከሚመጣው የንፋስ ጉዳት ራስን ለመከላከል ተመሳሳይ ግርዶሽ ሰለእበጁ በቤት ውስጥ ቤት ተሠርቶ የእስር ቤቱን ሕይወት እስቸጋሪ አደረገው ። የቅዠት መብዛት ፣ የራስ ምታት የሰውን አእምሮ በጠበጠው ። እርስ በርስ መጨቃጨቅና ከዚያም አልፎ እንዳንዶች የተጣሉትን ለበላይ መወንጀል ከእስር ቤቱ መዋፎ ትዝታ ሌላው ነበር ።

ከእስር ቤቱ ጥሩ ትውስቶች ደግሞ የምሥራች የተሰማባቸውም ዕለታት ነበሩ ። በዋቅምት 18 ቀን 1967 ዓ·ም ነበር ለዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ ቤት ልጅ የተወለደችላቸው የመሆኑ ምስራች የደረሳቸውና የጠይሙ ዶክተር ገጽታ በደስታ የበራው ። እንኳን ደስ ያለዎት ተብለው ጉንጫቸው በእስረኞች ተሳመ ፣ ትከሻቸው ተተመተመ ። በተከታዩ ደብዳቤ "ሴሎ" ማለትም ትደንቂያለሽ የሚል ስም የወጣላት መሆኑ ተገለጸላቸው።

ከሽርሽር መልስ ከመቀየጃ ክፍሉ እንደገባ የዘብ አለቃው በሌላ ቀን አምሐ ገብርኤልን እስጠራው ፣ እንዲት ቁራጭ ደብዳቤ በእጁ እንደያዘ ። በእውድ ቀን ከቤተሰብ ደብዳቤ ስለማይመጣ ሁኔታው እስገርሞት ሰውነቱ ንንገን ብሎ ነበር ወደዘቡ ኃላፊ የሄደው ። "የምስራች ባለቤትዎ በደህና ተገላግለዋል" ሲለው ነው መንፈሱ የተረጋጋውና በመውለጃዋ ጊዜ ባለቤቱ ምን ችግር ያጋጥማት ይሆን የሚለው ጭንቀት ጥሎት

የሄደው ። ደብዳቤውን ገልጦ ሲመለከት በጥር 17 ቀን 1967 ዓ·ም በደህና ወንድ ልጅ ለመገላገልዋ የምስራቹን ያበሰሩለት ለባለቤታቸው ስንቅ ለማቅረብ የመጡት ወይዘሮ ሮዛ አበበ መሆናቸውን ተረዳ ። እርሱም በፋንታው በደስታ ተፍነከነከ ። ወደ ክፍሉ እንደገባ ለምን ተጠራ ብለው በሥጋት ይጠባበቁት ለነበሩት የእስር ጓደኞቹ መልካሙን ዜና ገለጸላቸው። ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ ደብዳቤና ልዩ ምግብ የያዘ ቴርሙስ ደረሰው ። በደብዳቤውም ባለቤቱ የገለጸችለት አዲስ ለተወለደው ሁለተኛ ልጁ ኑርልኝ የሚል የመጠሪያ ስም ያወጣችለት መሆኑንና ከባልንጀሮቹ ጋር እንዲቃመስ ገንፎ የላከችለት መሆኑን ነበር ። ልጁን ኑርልኝ ያለችበት ምክንያት የአምሐ ገብርኤል የአያቱ ስም በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ፣ ከእርሱ ጋር ታስረው ከነበሩት አርባ ሰባቱ ከሁለት ወራት በፊት በደርግ በግፍ በመገደላቸው ከድርጊቱ ጋር በማያያዝ ባለቤትዋን "ኑር ልኝ" ስትል መልካም ምኞቷን ለመግለጽም ታሪካዊ ምሥጢር ባለው ምክንያት ጭምር ነበር ።

በአምሐ ገብርኤል ቤተሰብ የልጅን ስም ከታሪካዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ማውጣት ይህ የመጀመሪያው አልነበረም ። በ1962 ዓ·ም አምሐ ገብርኤል ለስብሰባ ወደ ጂኔቫ ሔዶ ሳለ ከባለቤቱ ደብዳቤ ሳይደርሰው ከሁለት ሳምንት በላይ ስለሆነው የቤተሰቡን ወሬ በማጣቱ አሳብ ገብቶት ነበር ። ከዚያም በቁርክ አገር በቁስጥንጥንያ /ስታምቡል/ ከተማ በሚደረገው የቀይ መስቀል የማዕከለ-በሐውርት ጉባኤ/ኢንተርና ሽናል ኮንፍረንስ/ ላይ በኢትዮጵያ መንግሥትና ቀይ መስቀል ማኅበር መልእክተኞች መሪነት የተባኤው ተካፋይ ለመሆን ጉዞ መቀጠል ስለነበረበት የቤተሰቡን ደህንነት ለመስማት ሲጓጓ ፣ እንደንገ ከጂኔቫ ሊንሳ እንደዛፊ ነበር ከባለቤቱ በጉጉት የጠበቀው አንድ ደብዳቤ የደረሰው ። በደብዳቤውም የእርሷንና የቤተሰቡን ደህንነት ከገለጸችለት በኋላ የግል ሐኪሟ ዶክተር ሶኮሎፍ ምርመራ አድርጎ እርግዘኛል ማለቱንና ይኸውም በፖስተር ኢንስቲቱት በተደረገው ልዩ ምርመራ መረጋገጡን፣ ለዘመናት ሲጠባበቀው የነበረውም ልጅ የማግኘቱ ተስፋ ከመቼውም የበለጠ የሚያስተማምን ሁኖ መገኘቱን እበሰረችለት ። አምሐ ገብርኤል ደብዳቤውን በሲታ ደጋግሞ ካነበበው በኋላ "ተመስገን" ብሎ በደብዳቤው ላይ ጽፎ እኖረው ። ተመስገን ካለበት ምክንያት አንዱ የባለቤቱን ደህንነት በማወቁ ሲሆን ፣ ዋንኛው ምክንያት

ከተጋቡ ጊዜ ጀምሮ ለአስራ ሦስት ዓመታት አልፎ አልፎ ባለቤቱ አርግዛለች ተብሎ ከተገመተ በኋላ እንደታሰበው ሳይሆን እየቀረ ይሳቀቁ ስለነበር ፣ አሁን ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ፈቃዱ ሁኖ በጣም ይመኙት እንደነበረው ሁሉ የባለቤቱን በእርግጥ የማርገዝ መልካም ዜና በመስማቱ ይህን ላሰማው አምላክ ምስጋና ለማቅረብ ነበር ። በባዕድ አገር ሳለ የሰማው የተስፋ ቃል እሙን ሁኖ ወንድ ልጅ በመወለዱ ለአምላክ ምስጋና ሲያቀርብ ነበር አምሐ ገብርኤል የበኩር ልጁን ስመ ተጸውኦ "ተመስገን" ያለው ።

በእስር ቤት የሚሰማው የምሥራች ብቻ ሳይሆን መርዶም ጭምር ነው ። ከእስረኞቹ ጥቂቶቹ የዘመድ ሞት ተረድተዋል ፣ ሀዘን ተቀምጠዋል። ከነዚሁም በቀብር ሥነ ሥርዕት ላይ የመገኘት ዕድል የተሰጣቸው በጣም ጥቂቶቹ ነበሩ ። ሄደው ለመቅበር ያልቻሉት ከመሪሩ ሀዘናቸው በቀላሉ ለመፅናናት አልቻሉም ።

ሀዘን ከቤት ብቻ አልነበረም የሚመጣው ፣ በእስር ቤትም ሞት ጉራ ያለበት ጊዜ ነበር ። የታደሉት ጥቂት ሰዎች ሲፈቱ እርሳቸው ሳይፈቱ በመቅረታቸውና ለመፈታት የነበራቸው የተስፋ ፍንጭ እውን ሳይሆን በመቅረቱ እርር ኩምትር በማለታቸው በልብ ሕመም ከእስር ቤት ሬሳቸው በመጀመሪያ የወጣው ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ ነበሩ ። በአፋጣኝ ሕክምና ሳያገኙ በሞት አልጋ ላይ ሲሰቃዩ ቆይተው ለሞት ሲቃረቡ ወደ ሆስፒታል ተወስደው የሞቱት ደግሞ አቶ ይልማ ዴሬሳ ፣ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልና ብ/ጄኔራል ጌታቸው ሀብተ ወልድ ናቸው ። በስትሮክ በመፀዳጃ ቤት ውስጥ ዘፍ ብለው በመውደቅ የፈታውራሪ አላሚን እንድሪስ ሕይወትም አልፏል ።

የሞቱትን ነፍስ ይማርና ዘፀኑ ሕምም የሚሰቃዩትና በቂ የተፈጥሮ ብርሃን በማጣትም የማየት ኃይላቸው የተቀነሰው ሰዎች ብዙዎች ነበሩ ። በዋሻው ቀዝቃዛነትና የታፈነ መሆን ምክንያት የአስም ሕመም ያለባቸው ሰዎች በየጊዜው የሚያጋጥማቸው ስቃይ እጅግ የሚያሳዝን ነበር ። ከስኳር በሽታቸው መፅናት ወይም በሌላ ሕመም የተነሳ ሕሊናቸውን ከመሳት የሚደርሱና በጓደኞቻቸው ጉትጎታ ብዛት ወደ ሆስፒታል ተወስደው ሕይወታችው ሊተርፍ የቻሉም ነበሩ ።

ሌሊት ታመው የተፈጥሮ ግዳጃቸውን ለመወጣት ወደ መታጠቢያ ቤት ለመሔድ በር እንዲከፈትላቸው እስረኞች ዘቡን እጥብቀው ሲጠይቁ

ወይም የመጣራት አቅም አንሷቸው በሌላ ሲያስጠይቁ ጠባቂዎቹ እየሰሙ እንዳልሰሙ እየሆኑ ሁሉንም ተጨናቂ የሚያደርጉበትም ጊዜ ጥቂት አልነበሬም ። የዚህ ዓይነቱ ችግር ከደረሰባቸው አንዱ በውድቅት ሌሊት ወደ በሩ ሔደው "ዘበኛ ፣ ዘበኛ" እያሉ ቢጣሩ እንዳልሰማ ሲሆንባቸው ጊዜ ቢራራልኝ ብለው "ክቡር ዘብ" በማለት ተጣሩ ከጭንቀታቸው የተነሳ ። አሁንም ደግም ክፉም አልመለሰላቸውም። በድምፁ መረዋነት የሚተማመነው ሌላው እስረኛ ጭንቀታቸው ተሰምቶት "ወንድም! ፣ ወንድም ሆዳቸውን በጣም ታመዋል እባክህ ወደ መታጠቢያ ቤት መሔድ እንዲችሉ በሩን ክፈትላቸው" ብሎ ለመነው ክቡርን ወንድም በሚል ቃል ለውጦ ። ውትወታው አሰልችቶት ይሁን ወይም የሚራራ ልቡና ሰጥቶት ወደ በሩ ሲመጣ "እኔ ዘብ እንጂ ዘበኛ አይደለሁም ፣ ዘበኛችሁን ከቤታችሁ ፈልጉ" ብሎ በሩን ከፈተ ፣ ሌሊት በመጠራቱ እያጉተመተመ ።

በቁስል ላይ ጥዝጣዜ እንዲሉ ፣ በሕመምና በእስራት ከሚሰቃዩት እስረኞች መካከል እንዳንዶቹን በልዩ ልዩ ምክንያት እየጠሩ ጠባቂዎቹ ስለሚዘልፋአቸው የሚያደርስባቸው ብስጭትና የመንፈስ ጭንቀት የማይረሳ መጥፎ ትዝታ ነበር ።

የሌሊት ልብስ ፣ የቀን ጉርስ የሌላቸውን ሠርቶ አዳሪዎች ሳይቀር ከየፋብሪካው እያመጡ ከፖለቲካ እስረኞች ጋር ሲደባልቁዋቸው ማየቱ ሌላው መንፈስን የሚያውክ ጉዳይ ነበር ። በሰራተኛ ማኅበር ሹማምንት ምርጫ ላይ መንግሥት የሚፈልገውን ሰው ተቃውማችኋል ተብለው ከታሰሩት ሰዎች አንዱ የሳምሶን ዳቦ ቤት ሠራተኛ የሆነው ነበር ። ይህ ወጣት ማንም የሚጠይቀው ዘመድ ስለአልነበረው የእስር ቤት ጓደኞቹ በሚያካፍሉት ድርጐ እየተረዳ ነበር ለቀናት የቆየው ። "ትልቅ ሰው ሁኜ ከከፍተኛ ባለስልጣኖች ጋር በመታሰሬ ኩራት ይሰማኛል" ሲል ነበር ወጣቱ የዘበተው ፣ እንደፖለቲካ እስረኛ ተቆጥሮ ከፖለቲካ ሰዎች ጋር በመታሰሩ በመገረም ።

ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ ራሳቸው በሰፉት ነጭ ኮት ላይ በእስር ቤቱ የሚገኙት እንዲፈርሙላቸው ጠይቀው ያስፈረሙት ለእስር ቤቱ ሕይወት ትውስት ጥሩ መታሰቢያ ይሆናል ። ሊወጣ በተቻለው መጠንም ፊርማዎቹን ከሚከተሉት ገጾች ይመለከቷል ።



ዛሰቃ አድማሴ ዘለቀ ራሳቸው የሰፋትንና እስረኞችን ያስፈረሙበትን ኮት እንደለበሱ



የእስረኞች ፊርማ በኮቱ በስተጓላ

፲፫

ቶማስ ወልድ

ቶማስ ወልድ የኢትዮጵያዊ ስም ነው ወይስ የሌላ አገር ሰው? ያልተለመደ የስም አውጣጥ!! "ቶማስ" የኢትዮጵያም የሌላም አገር ሰው ስም ሊሆን ይችላል። ሥር መሠረቱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለዚህም ነው በየትኛውም አገር ሊወጣ የሚችል ሰም የሚሆነው። " ወልድ" ግን ጥሬ ዘሩ ኢትዮጵያዊ ነው። እርሱም በግዕዝና በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ ነው። በሃይማኖት ትምህርት " ወልድ" ማለት ልጅ ማለት ሲሆን፣ ከሶስቱ ሥላሴዎች የአንደኛው፣ ሰው የሆነው አምላክ፣ የወልድ የመጠሪያ አምላካዊ ስም ነው። ለሰብዓዊ ፍጡር ግን ይህ ስም የሚሰጠው ከአናባቢ ጋር ብቻ ነው። ለምሳሌ አካለ ወልድ፣ ቃለ ወልድ፣ ሀብተ ወልድ ተሰኝቶ እንጂ ብቻውን አይደለም። ስለዚህ " ቶማስ ወልድ" የፈጠራ እንጂ እውነተኛ ስም አይመስልም፣ በተለይ ለኢትዮጵያዊ። ታዲያ ለኢትዮያዊነቱ አስተማማኝነት የሌለው ስም በተለይ ስለኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የእስር ቤት አበሳ በሚያዘክር መጽሐፍ ውስጥ ምን አግባብ ነት አለው? የሚል ጥያቄ ይቀርብ ይሆናል።

ስም ስያሜው አግባብነት ይኑረውም፣ አይኑረውም በዚህ ስም ለተወሰነ ጊዜ ይታወቁ ወይም ይጠሩ የነበሩ ሰው በዚህ መጽሐፍ ማዕቀፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ሚና እንደነበራቸው የሕይወት ታሪካቸው ስለሚገልጽ፣ ፍጻሜያቸውን ከሥራቸው ጋር ያገናዝቧል።

በኢትዮጵያ፣ በግብጽና በፈረንሳይ አገር የተማሩ፣ የሕግና የፖለቲካል ሳይንስ ምሩቅ ናቸው ቶማስ ወልድ። በ1928 ዓ.ም ነበር ለኢትዮጵያ ሕልውና ጠበቃ ሁነው በፓሪስ የፖለቲካ መድረክ ለይ ብቅ ያሉት። የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ሆርና የፈረንሳዩ የውጭ

ጉዳይ ሚኒስትር ሙሴ ላቫል ላደረጉት የሆር—ላቫል ስምምነት የመቃወሚያ መግለጫ በማውጣት ነበር በፓሪስ የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን በፕሬስ አታሼነት መንግሥታዊ ግልጋሎትን በክፉው ጊዜ የጀመሩት ። እኒህ ሰው ለኢትዮጵያ ሕልውና የሚታገሉ ሁለት ኮሚቴዎችን በፈረንሳይ አገር በማቋቋም፣ በእነዚሁ በመታገዝ " የኢትዮጵያ ዜና" (ኑቬል ደ ኤትዮፒ) የሚል ጋዜጣ በመመሥረት የኢትዮጵያን አቋም ለዓለም አሳወቁ። በመንግሥታት ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሺንስ) የኢትዮጵያ የልውካን ቡድን ጸሐፊ በመሆን በፓሪስ የኢትየጵያ ሌጋሲዮን ሚኒስትር ከነበሩት ከፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ዋየህ ጋር ከፓሪስ ወደ ጂኔቫ እየተመላለሱ ስለኢትዮጵያ ተሟገቱ። በጋዜጣም በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጸመውን ደባ ለዓለም አጋለጡ። ከሚያዝያ ወር 1928 ዓ.ም ጀምሮ በፓሪስ የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን እንደኛ ፀሐፊ በመሆን፣ በግዚያቱ የኢትዮጵያ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ሲከጹ ደግሞ ከመስከረም 1929 ዓ.ም ጀምሮ በሌጋስዮኑ በጉዳይ ፈጻሚነት ሠሩ። በአምስቱ የወረራ ዓመታት ከእቶ መኩንን ሀብተ ወልድ ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ስደተኞች መረዳጃ ማኅበር በማቋቋም ስደተኞችን ሲረዱ ቆዩ። በናዚስት ጀርመን ጦር አሜሪነት የፈረንሳይ መንግሥት ወድቆ ከፓሪስ ወደ ቦርዶ ሲዛወር በብዙ ችግር በብስኪሌት ወደዚያው ሄደው ስለኢትዮጵያ ነፃነት ታገሉ። የጀርመን ጦር ወደዚያው ሲገሰግስ ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ተገደዱ።

የወጣቱ ዲፕሎማት መልክ የላቲን አሜሪካ አገሮች ሰው ያስመስላቸዋል። የላቲን አሜሪካ ሰው የሚያስመስላቸው ደም ግባታቸው፣ ቀለማቸው፣ ገጽታቸው፣ፀጉራቸውና የአፍንጫቸው ቅርጽ ነው። ለዚህም ነው ብዙዎች የሜክሲኮ ወይም የኩሎምቢያ ተወላጅ እንደሆኑ አድርገው የሚወስዱዋቸው የነበረው ።

ይህም ነበር በፈረንሳይ አገር በማርሴይ ከሚገኘው የኮሎምቢያ ቆንስል "ቶማስ ወልድ" በሚል ስም የኮሎምቢያ ለሴ ፓሴ (ፓስፖርት) ለማውጣት የረዳቸው ። የራሳቸውን ፓስፖርት በኪሳቸው ይዘው እንዳይገኙ በማሰብ በፓሪስ የአሜሪካን አምባሳደር በሌላ ዘዴ እንዲልክላቸው በእደራ ሰጥተው ፣ የትምህርት ቤት ጓደኛቸውን ፣ ፈረንሳይቱን ፍቅረኛቸውን ማጻም ኮሌትን ተሰናብተው ማንነታቸውን ላለማሳወቅ በሌላ አገር ፓስፖርት ወደ ፖርቱጋል ሹልክ አሉ ። የአሜሪካን አምባሳደር የላኩላቸውን

CONSULADO DE COLOMBIA
MARSELLA Francia

SAUF-CONDUIT POUR SE RENDRE E COLOMBIE.

SALVO-CONDUCTO PARA DIRIGIRSE A COLOMBIA.

A LAS AUTORIDADES PORTUARIAS DE LA REPUBLICA DE COLOMBIA.

El CONSUL DE LA REPUBLICA DE COLOMBIA, EN MARSELLA, FRANCIA,

CERTIFICA: Que el señor THOMAS WOLD, natural de San Andrés (Intendencia de San Andrés y Providencia) Repúblico de Colombia, de 28 años de edad, profesión comerciante, soltero, y cuya fotografía aparece en este documento, es CIUDADANO COLOMBIANO.----------

Y con el fin de que pueda hacerlo constar así ante las Autoridades de Colombia, y las autoridades Civiles y Militares de los paises por donde tenga que transitar para su viaje a Colombia, se le expide el Presente documento en Marsella, a lo. treinta días del mes de Agosto de mil novecientos cuarenta.----------

30 AOUT 1940

Cónsul de Colombia.



Nota:- El titular de este pasaporte será repatriado por el Consulado de Colombia en Lisboa, segdn instrucciones recibidas de nuestro Gobierno.-

Cónsul

የቶማስ ወልድ ለሴ ፓሴ (ፓስፖርት)

እውነተኛውን ፓዘፖርታቸውን ለማግኘት የቻሉት ሊዝቦን ከተማ ፣ (ፖርቱጋል) ሲደርሱ ነበር። ሊዝቦን ከደረሱ በኋላ የተንቀሳቀሱት በአሳ ሳቱ በሦኑ ፡ በኮሎምቢያ ፓስፖርት ሳይሆን ከፓሪስ በተላከላቸው በእውነተኛው ፓስፖርታቸው ነበር ።

ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እንደወጣች ከነበሩበት ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው በመርከብ የመሳፈር ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ለእንግሊዝ መንግሥት ጥያቄ አቀረቡ። ጥያቄአቸው ሲፈቀድላቸው በአፍሪካ ዞረው ሞምባሳ ደረሱ፣ ከዚያም በመነሳት በ1934 ዓ·ም አዲስ አበባ ገቡ።

በነፃነት ማግሥት ቶማስ ወልድ በጽሕፈት ሚኒስቴር ውስጥ እንዲሠሩ ተመደቡ። በዚህ ጊዜ ነበር የሕግ አሳብና ስለኢትዮጵያ አቋም ራፖር ማቅረብ የጀመሩት። በዚሁ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትርነት ሲሾሙ ነበር የሥልጣን እርካብ የረገጡት።

በአፍላ ዕድሜያቸውም በሎርድ ላንግ ፎርድ መሪነት የእንግሊዝ የልዑካን ቡድን ለድርድር አዲስ አበባ ሲመጣ በኢትዮጵያ ተዋዋይ ቡድን አፈ ጉባኤነት የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ እንዲቋቋም፣ በምሥራቅ አፍሪካ ሺሊንግ ፈንታ የኢትዮጵያ ብር የሀገሪቱ ሕጋዊ መገበያያ እንዲሆንና በማንኛውም ረገድ የኢትዮጵያ ጥቅም በሚገባ እንዲጠበቅ በሰፊው ተከራከሩ፣ የተሳካ ውጤትም ለማስገኘት ቻሉ።

ከ1936 ዓ·ም ጀምሮ እስከ 1952 ዓ·ም በመጀመሪያ በምክትል ሚኒስትርነት በኋላም በሚኒስትርነት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ሲመሩ የሥራ መመሪያቸው ያደረጉት ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ በመገምገም ወደፊት ማድረግ የሚገባትን መቀየስን ነበር። በዚያን ወቅት ኢትዮጵያን የሚያሳስቧትና ያልተቆጠበ ጥረት ልታደርግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ብዙዎች ነበሩ።

ከነዚህም ግምባር ቀደሙ ኢጣልያ ተሸንፋ ከኢትዮጵያ ብትወጣም፣ ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ጋር የጦር ማቆምም (አርሚስትስ) ሆነ የሰላም ውል ባለመፈራረምዋ በሕግ በጦርነት ላይ እንዳሉ ስለሚቆጠር ለጉዳዩ አንድ እልባት የመስጠቱ ጉዳይ ነበር። ስለዚህም ነበር በ1938 ዓ·ም ፓሪስ ላይ በሚደረገው የሰላም ጉባኤ ኢትዮጵያ ተካፋይ ትሆን ዘንድ ቀደም አድርገው በመንግሥታቸው ስም ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሳይና ከመስኮብ መንግሥታት ሹማምንት ጋር ንግግር የጀመሩት። ለእነዚህ

መንግሥታት ያቀረቡትም አሳብ፣—

ሀ· ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ጋር የጦርነት ማቆምም ሆነ የሰላም ውል ስለአልተፈራረመች በጦርነት ላይ እንዳለች ስለሚቆጠር፣

ለ· አርበኞች አምስቱን ዓመት መዋጋታቸውን ባይቀጥሉ ኑሮ ኢጣልያ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ወታደር አስፍራ፣ ኢትዮጵያን የጦር ሠፈር በማድረግ ሱዳንንና ግብጽን፣ እንደዚሁም ኬንያን በቀላሉ ትይዝ እንደበረና፣

ሐ· ኢጣልያ በ1932 ዓ·ም ከጀርመን ጋር ለመሰለፍ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ በመግባቷ ምክንያት ቁጥራቸው በተወሰነ የእንግሊዝ የቃል ኪዳን ወታደሮችና በኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያ ውስጥ ወዲያውኑ እጁን መስጠቱን፣

በማዘከር ፡ በ1932 ዓ·ም ለተጀመረው ጦርነት ኢትዮጵያ ወደ አውሮጳ ጦር ሜዳ ወታደር ልካ እንደተዋጋች መቆጠር አለባት የሚል ነበር። እንደዚህ ባለ አስቸጋሪና አሳሳቢ የሆነ ክርክር ነበር ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀያ መንግሥታት ጋር በመሆን ከኢጣልያ ጋር በተደረገው የሰላም ውል ድርድር ላይ ተካፋይ ለመሆንና የይገባኛል ጥያቄዋን ሁሉ ለማቅረብ የሞከረችው።

ለጉባኤው ቅድመ ዝግጅት፣—

ሀ· ኢጣልያ በቅኝ ግዛት አገሮችዋ ላይ ያላትን ይዞታ ሁሉ እንድትለቅ ለማስደረግ፣

ለ· በኤርትራና በሶማሊያ ላይ ኢትዮጵያ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ ፣

ሐ· ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰችውን ጥፋት ዘርዝሮ በማቅረብ የጦር ካሳ ለመጠየቅ ፣

የክርክር ሰነድ (ዶሴ) አሰናዳች። አስፈላጊው መሰናዶ ከተደረገ በኋላ ለሌሎቹ እንደተደረገው ሁሉ በፓሪስ በሚደረገው የሰላም ጉባኤ ኢትዮጵያ ተካፋይ እንድትሆን ከአራቱ ኃያላን መንግሥታት ጥሪ ደረሳት። በጥሪው መሠረት በቶማስ ወልድ መሪነት፣

1· አቶ ሎሬንሶ ታዕዛዝ*

*በኋላ ብላቴን ጌታ

2· አቶ* ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ
3· ብላታ** ኤፍሬም ተወልደ መድኅን
4· አቶ ተስፋዬ ተገኘ
5· ልጅ መንበረ ያየህ ይራድ
6· አቶ*** ዘውዴ ገብረ ሕይወት፣ • • •
7· ሼክ ሁመር አል አሣሪ
8· ሐጂ ፋራ
9·አቶ እምሩ ዘለቀ
የሚገኙበት የልዑካን ቡድን ላከች።

በየተራ የየአገሮቹ መልእክተኞች ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ አሳባቸውን በመግለጽ ንግግር ከአደረጉ በኋላ የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲኞር ጺ ጋስፔሪ የመናገር ዕድል እንዲሰጠው ጠይቆ ተፈቀደለት። በዚህ ጊዜ፦—

" እዚህ የተሰበሰብነው የውሉ ረቂቅ እንደሚያመለክተው እ·ኤ·አ በ1940 (በ1932) ለተጀመረው ጦርነት ፍጻሜ ለመስጠት ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት የተጀመረው እ·ኤ·አ· በ1935 ሆኖ፣ በ1936 ስላለቀ፣ ኢትዮጵያ እዚህ ምን ታደርጋለች? እዚህ ታላችሁት 90 በመቶ የምትሆኑትም ኢጣልያ ኢትዮጵያን መያዟን እውቃችኋል፣ በዚህ አኳኋን ተሆነ ጉባኤው የሚደረገው የቻይናንና የጃፓንን ጦርነት ለምን አያይም" ሲል በመናገሩ፣ በተወካይ አገሮች መልእክተኞች ላይ መቾገርና የመደናገጥ ሁኔታ ተፈጠረ።

" እኛ እዚህ የመጣነው ሰላምን ፈልገን ነበር። ከኢጣልያ ጋር በ1928 ዓ·ም (እ·ኤ·አ በ1935) ጦርነቱ ተጀምሮ እስካሁን በጦርነት ላይ ነን። አርሚስቲስም ሆነ የሰላም ውል አላደረግንም፣ ጣልያን ሰላም አልፈልግም፣ ጦርነቱን እቀጥላለሁ ካለች፣ ዛሬውኑ ወደ አዲስ አበባ ለጃንሆይ ቴሌግራም እደርጋለሁ ጦርነቱ እንዲቀጥል ። በዚህ አኳኋን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ወደ 300,000 የሚሆኑት ኢጣልያኖች ለሚደርስባቸው ሁሉ እኛ ኃላፊ እንሆንም" አሉ ጭማስ ወልድ መልስ

* በኋላ ጸሐፊ ትእዛዝ
** በኋላ ብላቴን ጌታ
*** በኋላ ቢትወደድ
**** ብቴሌግራም ታዘው ከስዊድን ሔደው በጉባኤ የተሳተፉ

ሲሰሙ፣ የጠበቃ ሙግታቸውን በማሳመር።

ከጥያቄው ይልቅ የተሰጠው መልስ መልእክተኞቹን ይበልጥ አስደነገጣቸው። ሁሉም በኢጣልያ መልእክተኛ ላይ ወረዱበት፣ በኢትዮጵያ የሚገኙት ጣልያኖች ያልቃሉ በማለት። ከዚህ በኋላ ነበር ኢትዮጵያ በሰላሙ ጉባኤ ተካፋይ በመሆኑዋ ተገቢነት ከስምምነት የተደረሰው።

" በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ትልቁ ጦርነት የተጀመረው በመስከረም 22 ቀን 1928 ዓ·ም (በእክቶበር 3 ቀን 1935) ስለሆነ፣ የሰላሙ ስምምነት የሚያካትተው ተዚያን ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት" በማለት በኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን በመጠየቁም ነበር በግጭባባት ኢጣልያ አንድትቀበል ተደርጉ፣ ይኸው በተፈረመው ውል ውስጥ በአንቀጽ 38 የተመለከተው።

ጉባኤው ሁለት ወር ያህል ሲነጋገር ከቆየ በኋላ በሰላሙ ውል ይዘት ላይ ከስምምነት ተደረሰ።

በዚህ ጉባኤ ላይ ሌላው ኢትዮጵያን በተመለከተ ያከራከረው ኢትዮጵያ የጠየቀችው የጦር ካሣ ጉዳይ ነበር። ጉባኤው በተከፈተ በማግሥቱ የጦር ካሣ ጠያቂ አገሮች ሁሉ በቅደም ተከተል እየተጠሩ በሉንዱን ቲቂቁሞ ለነበረው የጦር ወንጀለኞች ጉባኤ አቅረበውት የነበረውን ጥያቄ ከሚደግፉ ማስረጃዎች ጋር ለሰላም ጉባኤው እንዲያቀርቡ፣ ተጠየቁ። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ ላይ የደረሰባትን ጉዳት በመዘርዘር የካሣ ጥያቄውን አቀረበ።

የጦር ካሣ እንድትከፍል ኢጣልያ በብዙ አገሮች ጥያቄ ስለቀረበባት መልእክተኛዋ ከጉባኤው ፊት አንድ ጊዜ ቀርቦ የመናገር ዕድል እንዲሰጠው በድጋሚ ጠየቀ። ከብዙ ክርክር በኋላ የመናገር ዕድል ተሰጠው። በዚህን ጊዜ ሲኞር ጺ ጋስፔሪ ከጉባኤው ፊት በመቅረብ በመናገሪያው ሥፍራ ሲቆም ምን ይናገር ይሆን እያለ ሁሉም ሲያስብ፣ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ለማየት በሚችልበት ቦታ ላይ በነጭ ጨርቅ ተሸፍኑው ተሰቅለው የነበሩትን ሁለት ትልልቅ ሰሌዳዎች በመግለጥ በመጠቆሚያ ዘንጉ እያመለከተ፣ " ይህ የኢትዮጵያ ካርታ ነው። አንደኛው ሰሌዳ ከኢጣልያ ይዞታ በፊት የነበረውን፣ ሁለተኛው ደግሞ በኢጣልያ ይዞታ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ያመለክታል" በማለት ንግግሩን ጀመረ። ንግግሩንም በመቀጠል ኢትዮጵያ ከኢጣልያ ይዞታ በፊት

በሚለው ካርታ በያዘው ዘንግ እየጠቆመ "ምንም መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ የሕክምና መስጫ ሆስፒታል፣ የውሀ አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ መብራት አልነበራትም" ሲል እያንዳንዱን የአገልግሎት ዓይነት እየጠራ "ዜሮ" በማለት በአገሪቱ ምንም እንዳልተሠራ አድርጉ አቀረበ።

ኢትዮጵያ በኢጣልያ ይዞታ ጊዜ የሚለውን ካርታ በተመለከተ ደግሞ ከአዲስ አበባ— አሥመራ፣ ከአዲስ አበባ — ጂማ፣ ከአዲስ አበባ — ደብረ ማርቆስ፣ ከአዲስ አበባ — ጂቡቲ፣ ከጉንደር— አሥመራ፣ ከጉንደር — አድዋ የመኪና መንገድ ሠርተናል፣ በሌሎች አገልግሎቶች ረገድ ደግሞ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከፍላተ ሀገር ይህን ያህል ትምህርት ቤቶች፣ ይህን ያህል ሆስፒታሎች፣ ይህን ያህል የውሀ ቧንቧና የኤሌክትሪክ መስመሮች ዘርግተናል ሲል አገልግለቶቹ ተጀቁመዋል የሚባልባቸውን ቦታዎች በካርታው ላይ በመጠቆም እየጉተጉራደደ መናገሩ ፣ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን አባል የጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳን ወልድ ትውስታ ነበር ።

ሲኞር ጋስፔሪ ንግግሩን በመቀጠል "በድምሩ 760,000 ሰዎች በጦርነትና በሌላም በተለያዩ ጊዜያቶች ኢጣልያ ገድላብኛለች ስትል ኢትዮጲያ ላቀረበችው ደግሞ ይህ ፈጽሞ የማንቀበለው ቁጥር ነው። ምክንያቱም እንደኛ ኢትዮጵያ የዘመተውንና የሞተውን ወታደር ቁጥር ለማወቅ የምትችልበት ዘዴ ስላላት፣ ሁለተኛ የዘመቱት ሻለቆች(አገረ ገዥዎች) የዘመቱት ወታደራቸውንና ባላገሩን ሞምር እያግበሰበሱ ስለሆነ፣ የሞተውንና የዳነውን ለማወቅ ስለማይችሉ፣ ሶስተኛ የዘመተው ወታደርና ባላገር ከኢጣልያ ጦር እየሸሸ ሲሄድ ኢትዮጵያዊው ባላገር መሣሪያውንና የያዘውን ዕቃ ለመዝረፍ እርስ በርሱ ይጋደል ስለነበረ፣ በጦርነቱና በዚህ አኳኋን የሞተውን ለመለየት ስለማይቻል፣ የተባለውን ቁጥር አንቀበለውም። ኢትዮጵያ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በኢጣልያ ወታደሮች ተቃጥለውብኛል ብላ ያቀረበችውም ቁጥር የተጋነነ ስለሆነ፣ ሊታመን አይችልም። እዚህ ለምትነጉት ልዑካን ተታጠሉ የተባሉት አብያተ ክርስቲያናት እንደ ኖትረ ዳም የፓሪሱ፣ ወይም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ካቴድራል የሎንዶኑ መስሎአችሁ ምናልባት ሳትደናገጡ አልቀራችሁም ይመስለኛል። ነገር ግን የተባሉት አብያተ ክርስቲያናት ከሁለት መቶ ዶላር ባልበለጠ ገንዘብ የተሠሩ የእንጨትና የሙታ ቤቶች ናቸው" ብሎ በማፌዝ ተናገረ። ንግግሩንም ሲያጠቃልል፡—

"ሌላው የቀረበው የይገባኛል ጥያቄ (ክለይም) ሁሉ በዚህ መልክ የሚወሰድ ነው" አለ የኢጣልያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኢትዮጵያን ጥያቄ ሲያቃልል ።

የኢጣልያኑ መልእክተኛ ያደረገውን ንግግር ከሰሙ በኋላ የጉባኤው አባሎች ፡ ለኢትዮጵያ የመቆርቆር ስሜት (ሲምፓቲ) የነበራቸው ሳይቀሩ አጉተመተሙ ።

"እውን ከዚህ ታላቅ ጉባኤ ፊት ቀርበው የኢጣልያው መልክተኛ የተናገሩዋቸው ታላላት የእኛን የይገባናል ጥያቄ በጣም የሚጉዱና የጉባኤውንም አባሎች ግራ የሚያጋቡ መስሎ ስለታየን እንዳንድ ማብራሪያ ለመስጠት እንድንችል የመናገሪያ ቀጠሮ እንዲሰጠን እጠይቃለሁ" አሉ፣ ከኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን አባሎች አንዱ አቶ ሉሬንሶ ታዕዛዝ ።

"የኢትዮጵያ መልእክተኛ ጉዳዩን በሙሉ ዘርዝሮ ተናግሮ ለውሳኔ ተመዝግቦአል ፣ የኢጣልያ መልእክተኛ አንድ ጊዜ ብቻ ተናግሮ እንዲወጣ በተወሰነው መሠረት ፣ ተናግሮ ወጥቷል ። አሁን እርሰም እንደገና እንዲናገሩ ብፈቅድ ሌሎችም የርስዎን ምሳሌ በመውሰድ በድጋሚ ለመናገር መጠየቃቸው ስለማይቀር ፡ በዚህ ዓይነት የቀጠልን እንደሆነ ነገሩ መቆሚያ ላይኖረው ስለሚችል ጻግመኛ መናገር አይፈቀድም" አሉ አሜሪካዊው የጉባኤው ሊቀ መንበር ሚስተር በርንስ ።

"የኢጣልያኑ መልእክተኛ አንጋገር ጉዳያችንን ጉድቶብናልና ብዙ ጊዜ ሳንወስድ ላንጻንዶቹ ፡ ምላሽ ሳይሰጥባቸው ለማይታለፉት ነጥቦች ብቻ ማብራሪያ እንድሰጥ ይፈቀድልኝ" ሲሉ ጻግመኛ ጠየቁ በኃይለ ቃል፣ የሊቀ መንበሩን ከልከላ በመታወም ።

ሊቀ መንበሩ አሁንም እይፈቀድም ቢማለታቸው የኢትዮጵያ መልእክተኞች በሊቀ መንበሩ ውሳኔ በመገረም ተቸግረውበትና ተጨንቀው ሳለ፣ የሁለቱን ወገኖች ንግግር ያዳመጡት የሶቭዬት ኅብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፡ ሚስተር ሞሎቶቭ እጃቸውን በማንሳት የሊቀ መንበሩን ዓይናች ወደ እሳቸው እንዲያተኩሩ ካደረጉ በኋላ ፡—

"ክቡር ፕሬዚዳንት ! የዚህ ጉባኤ ሊቀ መንበር ሁነው የተቀመጡት በጉባኤው አባሎች ምርጫ ነው ። የተመረጡትም የማንኛውም አገር መልእክተኛ የሚያቀርበውን ጉዳይ ለመስማት ነው እንጂ ፣ በእምባገነን ነት (በዲክቴተርነት) ለመራት አይደለምና የኢጣልያኑ መልእክተኛ

የተናገረ። ጉዳያችንን አበላሽቶብናልና ማብራሪያ መስጠት ያስፈልገናል ብለው ሲያመልክቱ ፡ አያናገሩም ብሎ መከልከል አይችሉም ። ስለዚህ ለኢትዮጵያው መልእክተኛ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ይገባል፣ እኔም ስለኢጣልያ የምናገረው አለኝና ሰዓት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ" አሉ ቆጣ ብለው ።

"ሚስተር ሞሎቶቭ! የኢትዮጵያን መልእክተኛ ጥያቄ ያልፈቀድኩበት ምክንያት ላንኡ መልእክተኛ ከፈቀድኩ ፡ ለሌላውም መናቀድ ይኖርብኛል ፡ በዚህ አኳኋን ከሠራን ነገሩ መቆሚያ ስለማይኖረው ይህን ጉዳይ ጨርሰን ለልደት በዓል ወደቤታችን እንዳንገባ የሚያደርገን ይሆናል በማለት ነበር ። አሁን ግን እርስዎም እንደገና መናገር እፈልጋለሁ ስለእሱ ነገ ጧት በሶስት ሰዓት የኢትዮጵያው መልእክተኛ ፡ እርሳቸው እንደጨረሱ ደግሞ እርስዎ ሊናገሩ ይችላሉ" አሉ ሊቀ መንበሩ ተዝቀዝ ብለው ።

"ትናንት ጧት የኢጣልያኑ ተናጋሪ ስለተናገራቸው ቃሎች እንዳንድ ማብራሪያ እንድንሰጥ ስለተፈቀደልን ምስጋና አቀርባለሁ" በማለት ነበር እቶ ሎሬንሶ በማማስቱ ንግግራቸውን የጀመሩት ። በመቀጠልም ፡ "በኢትዮጵያ ውስጥ ኢጣልያ ሠርታለች የተባሉት መንገዶች የተሠሩት ለወታደራዊ አገልግሎት እንጂ ለሀገር ልማት ሥራ ምንም ጠቃሚነት የሌላቸው ናቸው ። የተሠሩትም በነተራጣው ክፍልና በየቆላው ነው ። ባለሙያ በደጋው አገር የሠራቸው መንገዶች በጣም ጥቂት ናቸው ። ከነዚህም እንዳንዶቹ በከፊል የተሠሩት በአስፋልት ሳይሆን የበጋ ጊዜ መንገዶች ናቸው ። ከተጠቀሱት መንገዶችም ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ያሠራቸው የእፈር መንገዶችም ይገኙባቸዋል ። ስለትምህርት ቤቶች ያህም የኢጣልያ ተናጋሪ እንዳለው ሳይሆን እንዳንድ ትምህርት ቤቶች ተደም ብሎም ተመርተዋል ። ለምሳሌ በአዲስ አበባ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ፡ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤቱ ፡ የእቴጌ መነን የሴቶች ልጆች ትምህርት ቤትና የሚሰዮናውያን ትምህርት ቤቶች ተመርተዋል ። በየጠቅላይ ግዛቶቹም የመንግሥትና የሚሰዮናውያን ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ ። በሆስፒታሎችም በኩል የመጀመሪያው የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ፡ ቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ፡ ጉለሌ የሚገኘው የተፈሪ መኮንን ሆስፒታል ፡ የንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታልና ሌሎችም የሚሲዮናውያን ሆስፒታሎች ተመርተዋል ። የውሃና የኤሌትሪክ አገልግ

ሎትም በብዛት አይሁን እንጂ በመጠኑ ነበር ። የኢጣልያኑ ተናጋሪ ኢትዮጵያ ምንም እንዳልሠራች አድርጉ ያቀረበው ፡ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸመችው የወራሪነት ጦርነትና በእደረሰችው ጉዳት የተጠየቀችውን የጦር ካሣ እንዳትከፍል የፈራጀችን አሳብ ለማደናገር እንደሆነ አድርገን እንገምታለን" አሉ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በዝርዝር ሲያስረዱ ።

"ሊቀ መንበር ሚስተር በርንስ ለልደት በዓል ወደ ቤታቸው ሄደው የልደት በዓልን ተርኪ ለመብላት የነበራቸውን አሳብ ትተው ዛሬ ጧት የኢትዮጵያው መልእክተኛና እኔም እንድንናገር ስለፈቀዱልን እያመሰገንሁ ፡ ስለኔ ሁነው ሚስተር ቪቪንስኪ እንዲናገሩ እጠይቃለሁ" ብለው ሚስተር ሞሎቶቭ ተቀመጡ ፡ ፈገግታ እያሳዩ ።

"ትናንትና ጧት የኢትዮጵያ መልእክተኛ እንዳንድ ነገር እንዳብራራ ይፈቀድልኝ ብለው ሲጠይቁ ሚስተር በርንስ ፈቃደኛ ያለመሆን ሁኔታ በግሳየታቸው እይገርመኝም ። ምክንያቱም አሜሪካና እንግሊዝ በመታደል አገራቸው በጠላት ኃይል ተይዞ ስለማያውቅ በጠላት መያዝ (አክዩፔሽን) ምን ማለት እንደሆነ ስለማያውቁ ችግሩ አይገባቸውም ። እኛና ኢትዮጵያውያን ግን ፡ ዛሬና እድርገን እናውቀዋለን ። በዚህ ጉባኤ አጻራሽ ለሚያከራክሩን ጉዳዮች ምክንያት በሆነው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ጀርመን ወታደሮች ከአገራችን እንዳንድ ክፍል ይዘው በነበረበት ወቅት ወታደሮቹ ወደ ሌላ ጦር ግምባር እንዲሄዱ ሲፈለጉ የጀርመርን የጦር አዛዦች በቁጥጥራቸው ስር አድርገውት የነበረውን መሬት የፋሽስት ኢጣልያ ወታደሮች እንዲጠብቁ ያደርጉ ስለነበረ ፡ እነዚህ ወታደሮች በሕዝቡ ላይ የሚፈጽሙት የጭቆናና ሕገ ወጥ ድርጊት ይህ ነው ተብሎ ሊነገር አይችልም ። በዚህ አኳኋን የፋሺስት ኢጣልያ ወታደሮች በሕዝባችን ላይ የሠሩት ግፍ እጅግ ብዙ ነው ። ይህን የግፍ ሥራቸውን የሚፈጽሙት እነርሱ ተዋግተው በያዙት አገር ላይ ቢሆን ምን ያድርጉ በተባለ ነበር ። ነገር ግን ይህን የሚያደርጉት በሌላ መንግሥት ወታደሮች የተያዘውን አገር በጥብቅነት እንዲያስተዳድሩ በተፈቀደላቸው ሕዝብ ላይ ነው" ብለው ተናገሩ ። ንግግራቸውንም ሲያጠቃልሉ "የኢጣልያ ጀኔራሎችና ወታደሮች ጀግንነት እዚያ ላይ ነው እንጂ በጦርነት ላይ አይደለም ። ስለዚህ መፍራት የሚገባው ውጊያቸውን ሳይሆን ፡ አክዩፔሽናቸውን ነው ። የኢጣልያ ጀኔራሎች

የአምበሳ ቆዳ የለበሱ አህዮች ናቸው" በማለት ተናግረው ሲቀመጡ ነበር ረጅም ሳቅና ሁካታ በአዳራሹ ያስተጋባው ።

በመጨረሻ ኢጣልያ ኢትዮጵያን በጣሩ ስለወረራች የመር ውንጀላኛ በመሆን ተፈርዶባት ካሣ ከፍላለች ተብሎ እንዲመዘገብ ያህል ብቻ ነበር ሀያ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ካሣ እንድትከፍል ኢጣልያ የተወሰነባት ። በዚህ የሰላም ጉባኤ ሂደት ኢትዮጵያ ለደረሰባት ጉዳት የተጠበቀውን ያህል ካሣ ባታገኝም ኢጣልያ የቅኝ ግዛቷን እንድትለቅ ለማስደረግ ችላለች ።

ሌላው በዚያን ወቅት ለኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ የነበረው ጉዳይ በጥር 23 ቀን 1934 ዓ/ም ከብሪታንያ ጋር የተደረገው የመር ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲሻሻል ማድረጉ ነበር።

ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በሎርድ ደ፡ላ፡ዋር ከሚመራው የእንግሊዝ የልዑካን ቡድን ጋር በተደረገው ድርድር በብዙ ጉዳዮች ከስምምነት ለመድረስ ሲቻል ፡ በሶስት ጉዳዮች አለመግባባት ተፈጠረ ።

ከነዚህም የመጀመሪያው የእጋያን መለቀቅ ጉዳይ ሲሆን ፡ እንግሊዝ ላለመልቀቅ የሰጠችውን ምክንያት በመቃወም ብርቱ ፕሮቴስት ለእንግሊዝ ልዑካን ቡድን በጽሑፍ ሲቀርብ ፡ ኮሚው ለአሜሪካ ፡ ለፈረንሳይና ለመስኮብ መንግሥታት እንዲደርስ በመደረጉ እንግሊዞች ተቃውሞው ካልተነሳ ንግግሩን እንቀጥልም በማለታቸው ድርድሩ ለሶስት ቀናት ከተቋረጠ በኋላ ከኢጣልያኖች ጋር በመርነት ላይ ስለሆንን ለጦሩ እንዲረዳ ሙርነቱ እስከሚያልቅበት ጊዜ ድረስ የኢትዮጵያ የገዥነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ እጋያን በእንግሊዝ የመር አስተዳደር ስር እንዲቆይ የእንግሊዝ ልዑካን ቡድን አሳብ በማቅረቡ በመጨረሻ በዚሁ ቃለ መስማሚያ (ፎርሙላ) ከስምምነት ተደረሰ ።

ሁለተኛው አከራካሪ ጉዳይ የአዲስ አበባ — ጂቡቲ የምድር ባቡር ጉዳይ ነበር ። ባቡሩን በተመለከተ ከብዙ ውዝግብ በኋላ መርነት ላይ ስላለንና እናንተም ባቡሩን ለማካሄድ ችሎታና የሰው ኃይሉ ስለሌላችሁ ለማካሄድ ችሎታ እስከሚኖራችሁ ድረስ ባቡሩን ማካሄዱን እንለቅም በማለታቸውና ፈረንሳይም በጀርመን በመያዟ ለጊዜው ባቡሩ በእንግሊዞች እጅ እንዲቆይ መስማማቱ የግድ ሆነ ።

የአሳብ ልዩነት የታየበት ሶስተኛ ጉዳይ ከእንግሊዝ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት መቋቋሚያ የሚሰጠው ዕርዳታ አጠቃቀምን የተመለከተ ነበር ። ከጦርነቱ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት የተቋቋመው የእንግሊዝ መንግሥት በሰጠው 12 ሚሊዮን ፓውንድ እርዳታ ነበር ። በ1936 ዓ·ም እንግሊዞች "ወደፊት የምንሰጠውን 5 ሚሊዮን ፓውንድ የምታወጡበትንና የምትሰሩበትን ሁሉ እንግሊዞች የሚገኙበት አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ በእርሱ አማካይነት እየተቆጣጠርን ነው ፡ ያለበለዚያ እርዳታውን አንሰጥም" በማለታቸው ፡ ይህ አሰራር ኢትዮጵያን የእንግሊዝ ጥገኛ (ፕሮቴክተሬት) ስለሚያደርጋት ፡ ኢትዮጵያ ነፃ አገር ሁና ይህን አትቀበልም በማለት ክርክር ተደርጉ ከስምምነት ባለመደረሱ ከገንዘብ ክብር ይበልጣል በማለት እርዳታው እንዲቀር ተደረገ ።

ከዚህ ዓይነት አሰቸጋሪ ክርክር በኋላ የአንግሎ-ኢትዮጵያን የ1934 ዓ·ም ስምምነትና የወታደራዊ ቃል ኪዳን በታህሳስ 10 ቀን 1936 በተፈረመው የኢትዮጵያን መብት በሚጠብቅ ስምምነት እንዲተካ ተደረገ ።

በዚያ ፈታኝ ወቅት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከብር በአካባቢ የቅኝ ግዛት ያላቸው አገሮች የያዙባትን ግዛቶች ለማስመለስና ከጉረቤት አገሮች ጋር ያለው ወሰን በመሬት ላይ ምልክት ያልተደረገበት ምልክት እንዲደረግበት ከስምምነት ለመድረስ የሚደረገው ጥረት ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነበር ። በዚህም ውስጥ የሚካተተው ፈረንሳይ የወለደቻውን አፋምቦንና እንግሊዝ የያዘችውን ጋምቤላን ፡ እጋዴንና ባቡሩን ለማስመለስ ከሚመለከታቸው መንግሥታት ጋር መደራደርና ወሰንን መካለል ናቸው ።

ያለማቋረጥ በተደረገው ዲፕሎማሲያዊ ትግል በተለያየ ጊዜ እጋዴን ፡ አፋምቦና ጋምቤላ እንደዚሁም የአዲስ አበባ—ጅቡቲ ባቡር ተመልሰዋል። በኢጣልያ ሱማሌ ግዛት በኩል ያለው ድንበር እ·ኤ·አ በ1908 በኢጣልያና ኢትዮጵያ የወሰን ስምምነት መሠረት ወሰኑ በመሬት ላይ እንዲለይና ምልክት እንዲደረግበት ግዛቱን ታስተዳድር ከነበረችው ከኢጣሊያና በኋላም ከነፃይቷ ሱማሊያ መንግሥት ጋር ለብዙ ዘመናት ድርድር ቢደረግም ፡ ጉዳዩ ውሳኔ ሳያገኝ ሊቆይ የቻለው ከላይ ከተጠቀሱት መንግሥታት በጉ ፈቃድ መጓደል ነበር ።

እርቆ በመመልከት በዓለም አቀፍ መድረክ ተገቢ ቦታ ለማግኘት

ነበር ሌላው የተደረገው ጥረት ። በዓለም መንግሥታት ማኅበር ፈንታ ሌላ ማኅበር ለማቋቋም መታሰቡ እንደተሰማ እንደቀድሞው በልመና ከመጣ ባት መሥራች አባል ለመሆን በቅድሚያ መጣጣሩ እንደሚጠቅም በመረዳት ነበር በ1937 ዓ·ም ፕሬዚዲንት ሩዝቬልት አንድ አውሮፕላን ልከውላቸው እንዲገናኙ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጠየቁት መሠረት ስለተላከላቸው ስዊዝ ካናል በመርከብ ላይ በምስጢር ከፕሬዚዳንቱ ጋር ተነጋግረው ወደፊት ለሚቋቋመው ማኅበር ኢትዮጵያ መሥራች እንድትሆን የጠየቁት ። በዚህም በመስማማት ፕሬዚዲንቱ ቃል ስለሰጡ ኢትዮጵያ ሳንፍራንሲስኮ ላይ በተደረገው መሥራች ጉባኤ ላይ እንድትገኝ እንደሌሎቹ ነፃ መንግሥታት ሁሉ ጥሪ ደርሷት የስብሰባው ተካፋይ ሆነች ። በሳንፍራንሲስኮ ጉባኤ ተካፋይ የሆኑት የኢትዮጵያ ልዑካን፡-

1/ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው*
2· ቶማስ ወልድ
3/ ብላታ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን
4/ አቶ ተሰፋዬ ተገኝ
5/ አቶ አማኑኤል አብርሃም
6/ አቶ ምናሴ ለማ
7/ ዶክተር አምባዬ ወልደ ማርያም
8/ አቶ ጴጥሮስ ማሀሉ ነበሩ ።

በዚህም ጉባኤ ላይ የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ሲረቀቅ የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን ብዙ የማሻሻያ አሳቦች በማቅረብ አስተዋፅኦ አድርጓል ። ለምሳሌ "አንድ መንግሥት አንድ ሌላ መንግሥት ሊያጠቃኝ ይሰናዳል ብሎ ለድርጅቱ አቤት ባለ ጊዜ አቤቱታውን ለመስማት የፀጥታ ምክር ቤቱ መሰብሰብ አለበት" የሚለውን አሳብ ያቀረቡት ቶማስ ወልድ ናቸው ።

"በሆነ ባልሆነው ነገር እውነቱ ሳይረጋገጥ ጥያቄ በቀረበ ቁጥር ምክር ቤቱ መሰብሰብ የለበትም" በማለት ነበር የአሜሪካው መልእክተኛ በብርቱ የተቃወሙት ።

"ሰባት ወር ሙሉ ኢጣልያ ልትወረን ነው እያልን ደጋግመን ስናመለክት በጀኔቫ አቤቱታችንን የሚሰማ ጠፍቶ ፣ በዚሁ ጊዜ ውስጥ

*ጉባኤው ሳያልቅ ነበር ወደ አገራቸው የተመለሱት ።



ቶማስ ወልድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ቻርተር ሲፈርሙ

ሙሶሊኒ ጦሩን ፣ መድፉንና ታንኩን በቀይ ባሕር ለማጓጓዝ ጊዜ ተሰጥቶት ሰላሳ ኪሎ ሜትር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ከገባ በኋላ ነበር አቤቱታችንን ለማየት ማጎበሩ ጥያቄአችንን የተቀበለው ። ይህ በመሆኑ ነበር በከርከሩ ጊዜ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር የቻለችው ። ስለዚህ ይህ ዳግመኛ እንዳይደርስ አንድ መንግሥት አቤቱታ ሲያቀርብ የፀጥ ታው ምክር ቤት በአስቸኳይ ተሰብስቦ ጉዳዩን ማየት አለበት" የሚል ክርክር የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን በማቅረቡና የብዙ መንግሥታት መልእክተኞችን አሳብ በመማረኩ ማሻሻያው ተቀባይነትን ለማግኘት ቻለ ። የቻርተሩ ረቂቅ እንደተጠናቀቀ ቻርተሩን ከፈረሙት የአምሳ ሁለት አባሎች መልክተኞች አንዱ ቶማስ ወልድ ናቸው ። ቶማስ ወልድ ከሳንፍራንሲስኮ ሲመለሱ ወደ ዋሽንግተን ሄደው የአየር መንገድ ስለማቋቋም ከአሜሪካን መንግሥት ባለስልጣኖች ጋር ተነጋገሩ ። በመጨረሻም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1939 ዓ·ም ሊቋቋም በቃ ።

በነፃነት ማግሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በጣም አንገብጋቢው ጉዳይ ኤርትራንና በናዲርን ለማስመለስ የሚደረገው የዲፕሎማቲክ ጥረት የሚሳካበትን ማቀድ ነበር ። እነዚህ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የነበሩት ሁለት ግዛቶች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በእንግሊዝ መንግሥት ተይዘው ነበር ።

ከእንግሊዝ እጅ እነዚህን ግዛቶች ማውጣት ከእንበሳ መንጋጋ ሥጋ እንደማስለቀቅ በሚቆጠርበት ወቅት ኢትዮጵያ ትግሉዋን ጀመረች ።

ኢትዮጵያ በኤርትራና በበናዲር ላይ ያላትን የአለኝታ ጥያቄ እና ከኢጣልያ የምትጠይቀውን ሁሉ የሚዘረዝረው ማስታወሻ ለፕሬዚዳንት ሩዝቬልት የቀረበው ስዊዝ ካናል ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በተገናኙበት ጊዜ ነበር ። ከፕሬዚዳንት ሩዝቬልት ጋር ንጉሠ ነገሥቱ መገናኘታቸውን ሲሰሙ ሚስተር ቸርችል ከያልታ ጉባኤ ሲመለሱ በፕሬዚዳንቱ በኩል ከጃንሆይ ጋር ለመገናኘት ጠየቁ ። ንጉሠ ነገሥቱም እርሳቸውንና ሚስተር ኤደንን ተቀብለው አነጋገሩዋቸው ። በንግግሩም ወቅት በኤርትራና በበናዲር ላይ ኢትዮጵያ ያላትን ጥያቄ የሚገልጽ ማስታወሻ ለፕሬዚዳንት ሩዝቬልት በቀረበው ዓይነት ለሚስተር ቸርችልም ተሰጣቸው ። በዚህ ጊዜ ነበር ኤርትራን ለማስመለስ ጥረቱ የተጀመረው ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማለቂያ በኋላ በ1938 ዓ·ም በፓሪስ በተፈረመው የሰላም ስምምነት በአንቀጽ 23፡-

"ሀ/ ኢጣልያ በቅኝ አገሮች ላይ ያላትን መብት ሁሉ ለቃለች ፣

ለ/ የእነኝህ አገሮች እጣ ፈንታ (ፈት) በታላላቆቹ አራቱ ኃያላን መንግሥታት (በእሜሪካ ፣ በመስኮብ ፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይ) ይወሰናል ፣

ሐ/ ሲወሰንም የሕዝቡን ፍላጐት ፣ የሰላምና የፀጥታውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩ የሚያገባቸውን (ኢንተረስት ያላቸውን) መንግሥታት ሀሳብ በመስማት ይሆናል ፣

መ/ አራቱ መንግሥታት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከስምምነት ሳይደርሱ የቀሩ እንደሆነ ጉዳዩ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይቀርባል"

ተብሏል ። ኢትዮጵያ የተወረረችው በኤርትራና በሶማሌ ቅኝ ግዛት በኩል በመሆኑ በዚህ ስምምነት ውስጥ "ሰላምና ሴኩሪቲን" መሠረት በማድረግ የሚለው ሐረግ እንዲገባ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ስብሰባ ላይ እየቀረበች አሳብ ለማቅረብ እንድትችል "ኢንተረስት ያላቸውን መንግሥታት ሀሳብ በማዳመጥ" የሚለው ሀረግ በስምምነቱ ውስጥ እንዲገባ ያደረገው በቶማስ ወልድ የተመራው በፓሪስ የሰላም ጉባኤ የተሳተፈው የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን ነው ።

በዚሁ መሠረት ነበር ታሪክና ማስረጃን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያ በኤርትራና በብናዲር (በኢጣልያን ሶማሌ) ያላትን ጥያቄ ያቀረበችውና ኢጣልያም በቅኝ ግዛቶቿ ላይ ያላትንም ይዞታ እንድትተው ያላሰበችው ። በዚህ ጊዜ ነበር የግብጽ መልእክተኛ ድሮ ምዕዋን ይዘን ነበርና ኤርትራ ለእኛ ልትሰጥ ይገባናል ሲል ጥያቄ ያቀረበው ።

"የቱርክ ተገዥዎች ስለነበራችሁ ፣ የቱርክ ሠራዊት ወደዚያ የመጣው ለአሞር ጊዜ ሁኖ ትንሽ ስፍራ ይዞ ወዲያው በእነራስ አሉላ በጉንጻጉንጻ ተዋርዳችሁ የተጨረሳችሁበትን አስታውስ" የሚሬ መልስ ስለተሰጠው በጥያቄው መሣፋቱን ተወው ።

በሌላ ጊዜ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት ልዑካን በሎንዶን ተሰብስበ በን የኢትዮጵያን ሀሳብ ስለምንሰማ እንድትገኙ ሲሉ ስብሰባው ሰኖ ሲከፈት አርብ ለኢትዮጵያ አስታወቁ ።

በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ አውሮፕላን አልነበራትም ። ቢ·አ·ኤ·ሲ (B.O.A.C) ወደ አዲስ አበባ የሚመጣው በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር ። ስለዚህ የትራንስፖርት ችግር በመኖሩ ለአራትና ለአምስት ቀን

አስተላልፉልን በማለት ኢትዮጵያ ብትጠይቅ የሚቀ፡ላት ስለእማች ብርቱ ችግር ተፈጠረ ። የኢትዮጵያ አሳብ ሳይሰማ እንፈይቀር በማለት ከእንግሊዝ መንግሥት ለንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠችውን ያልተመዘገበች አነስተኛ አውሮፕላን ይዘው በሱዳን ፣ በግብጽ ፣ በግሪክና በፈረንሳይ አገሮች እያረፈች ቤንዚን በመቅዳት መንገዝ ስላለባት ከእነዚህ አገሮች ሌጋስዮኖች የተጻፈ ወረቀት ይዘው ቶማስ ወልድ ቅዳሜ ከአዲስ አበባ ተነሱ ።

ሱዳን ተቀብላ ስታሳልፍ ሱክሰር ሲደርሱ ወረቀቱን ቢያሳዩም የግብጽ ባለስልጣናች ከእሥራኤል ጋር ጦርነት ላይ ስለሆን ይህን ወረቀት እንቀበልም አሉ ። የሰጡትም ምክንያት "ፓይለቱ ነጭ ስለሆን አስራኤላዊ ሊሆን ስለሚችል ፣ በጦርነትም ላይ ስለምገኝ ከቀኑ ከአስር ሰዓት በኋላ በግብጽ አየር ላይ መብረር ክልክል ነው" የሚል ሲሆን ፣ "በቀጥታ ወደ ካይሮ ሄጻችሁ ትመረመራላችሁ ፣ በአውሮፕላን እንከተላ ችኋለን" በማለት ሞገዱ ።

"እሺ ወደ ካይሮ እንሄጻለን" ብለው ከተነሱ በኋላ ካይሮ ቢሄዱ የሰኞ ቀጠሮ ሊሰናከል ስለሚችል የአገር ጉዳይ እንዳይበላሽ ቀይ ባሕርን እየተከተለ ወደ ግሪክ አገር እንዲበር ቶማስ ወልድ ለፓይለቱ ትእዛዝ ሰጡ፡ ከሕይወታቸው የአገራቸውን ጉዳይ በማስበለጥ ። በዚሁ መሠረት ተጉዘው ሚዲትራንያን ባሕር ሲደርሱ ነበር እፎይ ያሉት ። ከማታው በሶስት ሰዓት ሳይኘረስ (ቆጵሮስ) ደርሰው ቤንዚን ለመቅዳት ሲወርዱ መብራት ስለሌላቸው የካሚዎን መብራት አብርተውላቸው ነበር ለመቅ ዳት የቻሉት ። እዚያው አድረው በማግስቱ እሑድ ግሪክ ደርሰው በደህና ስለተቀበሉዋቸው ወዲያው ወደ ፈረንሳይ አገር በረው ማርሴይ አረፉ ። ያልታወቀ አውሮፕላን ነው በማለት እጅ በእጅ ካልከፈላችሁ ቤንዚን አንሞላም ብለው ቢያስቸግሩዋቸውም እንደምንም ብለው በማስሞላት ሎንዶን ከቀጠሮው በፊት ደረሱ ። ሕይወት ለአደጋ የተጋለጠበት (ሪስክ የተወሰደበት) ጉዞ በፈቃደ እግዚአብሔር ተቃና ።

ቶማስ ወልድ ሎንዶን እንደደረሱም የአራቱን መንግሥታት መኪኖች በየአረፉበት ሆቴል እየተዘዋወሩ አነጋገሩዋቸው ። ጉባኤው ሲከፈትም 60 ገጽ የሆነውን ዲስኩራቸውን አባዝተው ለአራቱም ልዑካን ከመስጠታቸውም በላይ ለአቀራረቡ ሕይወት ለመስጠት ማን በብ ጀመሩ። ወሩ ነሐሴ ስለነበረና በጣም ስለሚሞቅ "ይህንን ሁሉ

እስቲያነቡ እዚህ ልንቆይ ነው እንዴ? ንግግሩ በጽሑፍ ስለታደለን ለምን ያንቡታል" አለ የፈረንሳይ መልእክተኛ ።

"በብዙ ችግር ቦስት ሺህ ኪሎ ሜትር አቋርጬ የመጣሁት ሁለት ሰዓት ትሰሙኛላችሁ ብዬ ተስፋ በማድረግ ስለሆነ ፣ በንባብ ለማሰማት ይፈቀድልኝ" አሉ ቶማስ ወልድ በትህትና ።

"እውነት ነው ፣ የኢትዮጵያን መልክተኛ መስማት አለብን" ብሉ ወሰነ ሚስተር ግሌክ መስኮባዊው የጉባኤው ሊቀ መንበር ።

ንግግሩ ተሰምቶ እንዳለቀ አንዳንድ ጥያቄዎች ቀርበው መልስ በሚሰጡበት ጊዜ "ስለ ኤርትራ ጥያቄ ስንኳ ይሁን ፣ ደግሞ ስለሱማሌ ምን መብት አላችሁ?" ሲል የፈረንሳይ መልእክተኛ ሙሴ ግሊግሊ ተቃወመ ።

"ታሪክ እንደሚያስረዳው የፈረንሳይ ሶማሌም የእኛ ነበር ፣ ይህን እያውቁምን?" በማለት ቶማስ ወልድ ተሳለቁበት ።

"ያውልህ መልሱ" አሉት መስኮባዊው ደስ ብሏቸው ።

ከዚህ በኋላ የአራቱ መንግሥታት ጉባኤ ወደ ኤርትራና ሱማሊያ አጣሪ (ኢንኳይሪ) ኮሚሽን ለመላክ ወሰን ። በኮሚሽኑ አባልነት ከተላኩትም የእንግሊዝ ልዑካን መሪ ቀድሞ በኢትዮጵያ የነንዘብ ጉዳይ አማካሪ የነበሩት ኮሎኔል ፍራንክ ስታፎርድ ሲሆኑ ፣ የአሜሪካኑ ደግሞ በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚከታተሉት ሚስተር ጆን አ ተር ነበሩ ። የፈረንሳዩ ደግሞ ሙሴ ቡረን ዴ ሮዜርስ ፣ የመስኮቡ ሚስተር ኤ·ፍሬልዶሮቭ ነበሩ ።

የኮሚሽኑ አባሎች ወደ ኤርትራ መጥተው ዋና መሥሪያ ቤታቸውን አሥመራ አድርገው የማጣራቱን ተግባር አካሄዱ ። የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን መሪ ቶማስ ወልድ በቻዎ ሆቴል በያንዳንዱ አባል ክፍል እየሄዱ ለብቻ ፣ በኋላም በእንድነት በማነጋገር የኢትዮጵያን አሳብ አሳወቁ ። በዚህም ጉዳይ በኤርትራ የእንግሊዝ አስተዳደር (አድሚኒስትሬሽን) ብዙ የደባ ሥራ (ሳቦታዥ) እንደሚያደርግ በመረዳታቸው ለእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተገቢውን ተቃውሞ ቶማስ ወልድ አስተላለፉ ።

የኮሚሽኑ አባሎች ለሁለት ወራት በመላው ኤርትራ እየተዘዋወሩ የሕዝቡን ተጠሪዎች በማነጋገር ፣ በሕዝባዊ ስብሰባዎችም የሕዝቡን አሳብ በማዳመጥ ፍላጐቱ ምን እንደሆነ አጣሩ ።

የአራቱ መንግሥታት ልዑካን ግን በእንድ አሳ፣ ለመስማማት አልቻሉም ። የአሳብ ልዩነታቸውም ፦

ሀ/ <u>የእሜሪካን ሀሳብ</u>፦ ከአሥመራ ከተማና ከምፅዋ በቀር አሰብና ሌላው የክርስቲያኑ አገር (አካለ ጉዛይ ፣ ሀማሴን - ሠራዬ) ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ ።

ለ/ <u>የእንግሊዝ አሳብ</u> ፦ ኢትዮጵያ ለአሥር ዓመታት ኤርትራን በሞግዚትነት አስተዳድራ ከዚያ በኋላ ኤርትራ ነፃ አገር እንድትሆን ፣

ሐ/ <u>የፈረንሳይና የመስኮብ አሳብ</u>፦ ከፊሉ አገር ለኢትዮጵያ ተሰጥቶ ሌላው ለኢጣልያን በሞግዚትነት እንዲሰጥ የሚሉ ነበሩ ።

ስለዚህ ነበር ጉዳዩ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ለውሳኔ የቀረበው ።

ጉዳዩ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ከመታየቱ በፊት የአራቱ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በ1940 ዓ·ም በፓሪስ በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ለመሳተፍ ወደ ፓሪስ መጥተው ሳለ ቶማስ ውልድ እያንዳንዳቸውን በየተራ አነጋገሩዋቸው ። በመጀመሪያም የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጄኔራል ማርሻልን አግኝተው ፦

"አሥመራንና ምፅዋን ኢትዮጵያ እንዳታገኝ የአሜሪካን መንግሥት የከለከለው ለማስተዳደር አትችሉም በማለት እንደሆነ ፣ ከአሥመራ አምስት ጊዜ የሚበልጥ ሕዝብ ያለበትን አዲስ አበባን ስናስተዳድር እንዴት አሥመራን ማስተዳደር አትችሉም ትላላችሁ? ምፅዋም በገቢው የሚተዳደር ወደብ በመሆኑ እንዴት ማስተዳደር ይሳናል? አሜሪካ የትንንሽ አገሮች ተከራካሪ (ሻምፒዮን) ሁና ሳለ መጀመሪዋ ተጠቂ (ቪክትም) ለሆነችው ኢትዮጵያ በየጊዜው የወረራ በር የሆነው ወደብና ግዛት ፣ ይልቁንም የኢትዮጵያ ዋና ታሪኳ የተጀመረበትን አዶሊስን እንዴት ትከለክሉናላችሁ? እኛ መቼም ወገን የሌለን ትንሽ አገር ነን ፣ የምንጠይቀው ፍትህ (ጀስቲስ) ነው ። ፀረ ቅኝ አገዛዝ (እንቲኮሎኒያሊስት) የሆናችሁት አሜሪካኖች ተከለከላችሁን በጣም እናዝናለን ።

ለሁሉም ይህን እጭር ማስታወሻ ራስም እንዲያነቡት እለምናለሁ" ብለው ቶማስ ወልድ በሚያራራ አኳኋን አስረዱ ። በመቅጠልም "ማስታወሻው የያዘው ሐቅ (ፋክት) ብቻ ነው ። እንድም ነገር ውሸት ሁኖ ቢገኝ የጠየቅነው ይቅርብን" አሉ ፍትህን በሐቅ ሲጠይቁ ።

ሁሉንም ነገር በትካዜ ከአዳመጡ በኋላ ማስታወሻውን ተቀብለው "በጥሞና አነበዋለሁ ፡ ከፕሬዚዴንት ትሩማን ጋርም ተመካክሬ መልሱን እስክ 15 ቀን እሰጣለሁ" አሉ ፡ ወታደራዊው ጂፕሎማት ጀኔራል ማርሻል ። ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ፡ —

"ከፕሬዚዳንት ትሩማን ጋር ተመካክረን ተአቆርጻት በቀር ሌላው የኤርትራ ክፍል አሥመራ ፡ ምፅዋና አሰብ ጭምር — ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ አሜሪካ ትስማማለች" በማለት ድጋፋቸውን ጀኔራሉ ገለጹ ።

ከእንግሊዞች ጋር በተገናኙበት ወቅት ደግሞ "ኢችዮጵያውያን የሆኑ ወንድሞቻችንን እንዴት በሞግዚትነት አስተዳድሩ ትሉናላችሁ? ወዳጆቻችን ስትሆኑ አሥመራና ምፅዋ ለኢትዮጵያ አይሰጥም እንዴት ትላላችሁ?" ሲሉ ቶማስ ወልድ እጥብቀው በመጠየቃቸው ነበር "እሜሪካኖች ከደገፉዋችሁ ከአቆርጻት በቀር ሌላው ክፍል ለኢትዮጵያ እንዲመለስ እንስማማለን" የሚል የተሰሩ ቃል የሰጡት ።

መስኮብና ፈረንሣይ ከኤርትራ ከፊሉ ለኢጣልያ እንዲሰጥ አሳብ ያቀረቡበት የየራሳቸው ምክንያት ነበራቸው ። መስኮብ ኤርትራ በከፊል ለኢጣልያ እንድትሰጥ የምትደግፈው በኢጣልያ አገር ጠንካራ የኮሚኒስት ፓርቲ ስለነበር መስኮብ ኢጣልያን ሪድታለች ተብሎ የኮሚኒስት ፓርቲ በምርጫ እሸንፎ መንግሥቱን እንዲይዝ ይረጻዋል በሚል አስተሳሰብ ነበር ። ፈረንሳይ ደግሞ የኤርትራ ሁሉም ክፍል አለበለዚያም ከፊሉ ለኢጣልያን ይመለስ የምትለው ሲቢያ ነፃ መንግሥት ስትሆን አልጄሪያና ቱኒስያ ተመሳሳይ ጥያቄ እንደሚያቀርቡ በመስጋትና ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ ብቻ ተጠቃሚ ሁና እንድትኖር ለማድረግ ነበር ። ስለዚህ የነዚህ ሁለት አገሮችን አቋም በመጀመሪያ ለማስለወጥ አልተቻለም ነበር ።

የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ በ1940 ዓ·ም የመጀመሪያው ክፍል ስብሰባ ፓሪስ ውስጥ ፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ኒውዮርክ ላይ ተደረገ ። በዚህ በሁለተኛው ስብሰባ ኤርትራን በተመለከተ የአራቱ መንግሥታት ሪፖርት ቀርቦ ንግግር ተደረገበት ። በዚህም ወቅት የኢትዮጵያን አቋም

ቶማስ ወልድ ካሰሙ በኋላ ጉዳዩ በ1941 ዓ·ም በሚደረገው ጉባኤ እንደገና እንዲታይ ተወሰነ ።

ተከታዩ የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ከመከፈቱ በፊት ለኢትዮጵያ ዓይን የሆነው ኤርትራንና የባሕር በሮቹን የማግኘት ጉዳይ እንዳይበላሽ ቶማስ ወልድ በፓሪስ የኢትዮጵያ ሚኒስትር የሆኑትን አቶ ተሰፋዬ ተገኝንና የቅርብ ረዳታቸውን አቶ እምሩ ዘለቀን ይዘው ወደ ግብጽ ፡ ፈረንሳይ ፡ እንግሊዝ ፡ ብራዚል ፡ እርጀንቲና ፡ ፔሩ ፡ ዘንዝዌላ ፡ ሜክሲኮና አሜሪካን አገር በመሄድ የኢትዮጵያን የይገባኛል ጥያቄ በግሰረጃ በግስደገፍ አስረዱ ።የተባበሩት መንግሥታት የ1941 ዓ/ም ጉባኤ ከመጀመሩ በፊት የቪቢንና የሳፎርሳ ፕላን የሚባለው ብቅ አለ ። የእንግሊዝና የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በመንግሥታቸውና በደጋፊዎቻቸው ስም ያቀረቡት ሃሳብ ፡—

ሀ) ሊቢያን እንግሊዝ ፡ ፈረንሳይና ጣልያን ተከፋፍለው በሞግዚትነት ለአስር ዓመት እንዲያስተዳድሩ ፡

ለ) ሶማሌን ኢጣልያ በሞግዚትነት ለአስር ዓመታት እንድታስተዳድር ፡

የሚል ነበር ።

በፖለቲካ ኮሚሽኑ ክርክር ላይ አቆርጻትም ከሌላው የኤርትራ ክፍል ጋር ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ ፈረንሳይ አሳብ ብታቀርብም አሜሪካ ፡ እንግሊዝና ተከታዮቻቸው ስለተቃወሙት አሳቡ በድምፅ በመውደቁ የቀረበው ድምፅ ብልጫ አገኘ ። ከዚህ በኋላ የኮሚሽኑ ውሳኔ (ሬዞሊዩሽን) ለጠቅላላው ጉባኤ ቀርቦ እንቀጽ በእንቀጽ ድምፅ እንዲሰጠበት ተጠየቀ ። በተሰጠው ድምፅ የኤርትራ ግዛት በሙሉ ለኢትዮጵያ እንዲመለስ የሚለው አሳብ ከተፈላጊው ድምፅ ማለትም ከጠቅላላው 2/3 በላይ ድምፅ አገኘ ። ሊቢያ ለፈረንሳይና ለእንግሊዝ ትከፋፈል የሚለውም 2/3 ድምፅ ሲያገኝ ፡ ኢጣልያም በሶማሌ ተፈላጊውን ድምፅ ስታገኝ በሊቢያ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ድምፅ ሳታገኝ ቀረች ። ከዚህ በኋላ በውሳኔ ረቂቁ በጠቅላላው ድምፅ ሲሰጥ ኢጣልያ ካላገኘች የተያያዘ ጉዳይ ስለሆነ ግንም አያገኝም በሚል "በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ዖት ባንሰጥም እርሷ ከሚያስፈልገው በላይ ድምፅ አግኝታለች ፡ ግን ሬዞልዩሽኑ የተያያዘና አንድ አካል ስመሆኑ እናዝናለን" በማለት የፈረንሳይ መልእክተኛ መግለጫ (ዴክላራሲዮን) ከሰጠ በኋላ ጣልያንን በመደገፍ ድምፅ

በመስጠቱ ፡ የላቲን አሜሪካ አገሮች ልዑካንም በፈረንሳይ በመመራት የተቃውሞ ድምፅ በመስጠታቸው ውሳኔው የድምፅ ብልጫ (ማጆርቲ) እንጂ 2/3 ድምፅ ባለማግኘቱ ፕላኑ ወደቀ ። የኤርትራም ጉዳይ በዚህ ወቅት ሳያልቅ ቀረ ።

ስለዚህም ጉዳዩ ወደ ኮሚሽኑ ተመልሶ ክርክሩ እንደገና ቀጠለ ። የኤርትራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችም ተጠርተው አስተያየታቸውን በግንባር ቀርበው እንዲገልጹ ተደረገ ። የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ማኅበር ለውህደተ ያለውን አቋም በመቃወም የቀረቡት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊበራል ፕሮግሬሲቭ ፓርቲ ፡ ራቢጣ ኤል ኢስላሚያና የተለያዩ የጣልያን አፍቃሪ (ፕሮ—ኢታሊያ) ድርጅቶች ነበሩ ። ኢትዮጵያን የሚቃወሙት ፓርቲዎች ዲስኩራቸውን ያደረጉት ከኢጣልያ የልዑካን ቡድን ጐን ተቀምጠው ነበር ። እነርሱም ዲስኩራቸውን ማሰማት እንደጨረቡ ቶማስ ወልድ ልዩ ልዩ ጥያቄ እያቀረቡ ንግግራቸውን ዋጋ ቢስ ስላደረጉት በኮሚሽኑ አባሎችም ላይ ልዩ ስሜት (ኢምፕሬሽን) ሳሳደሩ ።

በዚህ ወቅት የመስኮብ ልዑካን ቡድን አንድ ሬዞሉዩሽን አቀረበ ። ያቀረበውም አሰብ ብቻ ለኢትዮጵያ ተሰጥቶ ሌላው የኤርትራ ክፍል ነፃ ይሆኑ የሚል ነበር ። ይህም የኢትዮጵያን ጥያቄ የሚያዳክም በመሆኑ ቶማስ ወልድ ብዙ የልዑካን ቡድኖችን ለየብቻ በማነጋገር አቅጣጫ ለማስለወጥ ሞከሩ ።

ክርክሩ ቀጥሎ ስለነበር አንድ ሌላ የውሳኔ ረቂቅ (ሬዞሉዩሽን) ቀረበ። ይኸውም የአምስት መንግሥታት መልእክተኞች በተባበሩት መንግሥታት ስም ወደ ኤርትራ ሄደው የሕዝቡን አሳብ ይጠይቁ የሚል ነበር ። ይህ አሳብ በመቅረቡ መስኮብ አሳቡን እንዲያነሳ የግብጽ የልዑካን ቡድን ጠየቀው ። የመስኮብ መልእክተኛ ግን አላነሳም በማለቱ ድምፅ ሲሰጥ መስኮብን የደገፈው 3 ድምፅ ብቻ ሆነና አሳቡ ወደቀ ። የልዑካን ቡድን የመላኩ አሳብ ሲፀድቅ ምንም ስንኳን ኢትዮጵያ ?ኮሚሽኑ አባል እንዲሆኑ ከታሰቡት አገሮች አንዳንዶቹን ባቋማቸው ምክንያት ብትቃወምም ፡ በቀረበው አሳብ መሠረት የተመረጡት ደቡብ አፍሪካ ፡ ፖኪስታን ፡ ጓተማላ ፡ በርማና ኖርወይ ነበሩ ።

የኮሚሽኑ አባሎችም ኤርትራን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሶማሊያንና ግብጽን የጎበኙ ሲሆኑ ፡ አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ስብሰባ ላይ በመገኘት

የኤርትራን ታሪክ ፡ የኢትዮጵያም አካል መሆኑዋን ፡ ከጊዜ በኋላ ኢጣልያ እንደያዘቻትና ብዙ ጊዜ ለኢትዮጵያ መወረሪያ እንደሆነች ፡ አሁንም በእንግሊዝ አስተዳደር ስር እያለች ሕዝቡ እውነተኛውን አሳቡን ለማሰማት የሚቸገር መሆኑን በመዘርዘር ቶማስ ወልድ አስረዱ ።

ቶማስ ወልድ ይህን ሁሉ በሚያደርጉበት ጊዜ በድካም ብዛት በየጊዜው ስለሚታመሙ ስብሰባው በሚደረግበት በራስ ሆቴል ውስጥ ሐኪም እየመጣ ያክማቸው ነበር ።

ከጉብኝቱና ማስረጃ ካሰባሰበ በኋላ ኮሚሽኑ ራፖሩን ለተባበሩት መንግሥታት አቀረበ ። የኮሚሽኑ አባሎች በአንድ ሃሳብ ለመስማማት ባለመቻላቸው፡—

ሀ) <u>ደቡብ አፍሪካና በርማ</u> ፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሀድ ፡

ለ) <u>ፖኪስታንና ጓተማላ</u> ኤርትራ ነፃ እንድትሆን ፡

ሐ) <u>ኖርወይ</u> ፡ ኤርትራ ያለምንም ገደብ (ኮንዴሽን) ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ።

ሲሉ የተለያየ አሳብ አቀረቡ ። ይኸውም አሳብ ትንሹ (ሚኒ) ጉባኤ በተባለው የየመንግሥታቱ ሁሉ ተወካዮች በተገኙበት አካል ሲጠና ቆይቶ በመጨረሻ በ1942 ዓ.ም ለሚደረገው ለድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ተወሰነ ።

በትንሹ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ወደ ኒው ዮርክ ሲሄዱ ቶማስ ወልድ ፓሪስ ላይ ጤንነታቸውን ተመርምረው ፡ ሐኪሙ "ታመዋልና ሆስፒታል ገብተው ኦፔራሲዮን መደረግ አለብዎ" አላቸው ።

"ያገር ጉዳይ ስላለብኝ አልችልም " ነበር ያሉት ለሐኪሙ ።

"በአውሮፕላን ላይ አደጋ ሊደርስብዎ ይችላል" አለ ሐኪሙ ቁርጥ ባለ አነጋገር ። እርሳቸው ግን ዝም ብለው ወደ ኒውዮርክ ሄደው የኤርትራን ጉዳይ ጨርሰው ሲመለሱ ነበር ኦፔራሲዮን የተደረገላቸው ። በዚህም ጉዞ እግረ መንገዳቸውንም በፓሪስ ፡ በሎንዶንና በዋሽንግተን በመገኘት ከየመንግሥታቱ ባለሥልጣኖች ጋር ተገናኝተው "አንድነት እንጂ ፌዴሬሽንን አንቀበልም" በማለት የመንግሥታቸውን አቋም ዘርዝረው አስረዱ ። የአገራቸውን አቋም ለማስረዳትና በኤርትራ ጉዳይ ሲከራከሩ ለሰባት ወር ኒውዮርክ ቆዩ ።

ከብዙ ክርክር በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ የሚያሳልፈ

ውን የውህደት አገር አዋጅ (የፈዴራል ሕገት) የሚያሰናዳ አነብራዚል የሚገኙበት አንድ ኮሚቴ ተቋቋመ። አጣልያኖችና አጋሮቻቸው የኮሚቴውን ጥያቄ ሲደግፉ፣ አሜሪካኖችና እንግሊዞች ደግሞ የኢትዮጵያን ጠንካራ አጽም ስላዩ ኢትዮጵያ ልትቀበለው የምትችለው እንዲሆን ለማድረግ በመጣጣር የሬዞሊዩሽኑን አሳብ አሰናድተው ለ1942 ዓ/ም ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ አደረጉ።

ጉባኤው እንደተከፈተ ኢጣልያኖች ጥያቄአቸው የማይፈጸም መሆኑን ሲያውቁ የአቀራረብ ሥልታቸውን (ታክቲካቸውን) ለውጠው፣ የነፃነት አቀንቃኝ (ሻምፒዮን) በመሆን ለኢጣልያ ቅኝ ግዛት (ኮሎኒ) ሁሉ ነፃነት ይሰጥ የሚል አሳብ አቀረቡ። ከሰፊ ክርክር በኋላ በሀዳር 22 ቀን 1942 ዓ.ም የፈዴራል አክቱን የያዘው የውሳኔ ሀሳብ በከፍተኛ ድምፅ አለፈ።

ከዚሁ ሁሉ ዲፕሎማቲካዊ ጥረት በኋላ ነበር በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤርትራ ኮሚሽነር ተብለው ከተሾሙት፣ የቦሊቪያ ተወላጅ ከሆኑት፣ ሚስተር አቴብ ግቴንሶ ከተባሉት ሰው ጋር ሌላ የክርክር ግንባር የተከፈተው። ከብዙ ክርክር በኋላ የኤርትራ የውስጥ አስተዳደር በፈዴራል አክቱ መንፈስ ተሠራ። የኤርትራም ሕዝብ የባይቶውን (የአሴምብሊውን) መማክርት መርጠ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፈዴሬሽን መቀላቀሏንና በዚሁ መሠረት ከሕዝብ በተሰጠው ውክልና ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥቱን አፀደቀ። ንጉሠ ነገሥቱም በመስከረም 1 ቀን 945 ዓ.ም በፈዴራል አክቱና በኤርትራ የውስጥ አስተዳደር ሕግ ተስማምተው ውሀደቱ እውን ሆነ። በመጨረሻም በኤርትራ ሕገ መንግሥት መሠረት ባይቶው በሀዳር 5 ቀን 1955 ዓ.ም ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ፈዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ የኢትዮጵያ አንዲቱ ክፍለ ሀገር ሆነች።

ከዚህም ሌላ በቶማስ ወልድ በዲፕሎማቲኩና በሌላውም መስክ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል። በታሪክ ልዩ ስፍራ ከሚሰጣቸው አበይት ተግባሮች አንዱ የካዛ ብላንካና የሞንሮቪያ በመባል የሚታወቁትን ቡድኖች በማቀራረብ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ለማቋቋም በአፍሪካ መድረክ የተደረገው ከፍተኛ ጥረት ነው። በ1955 ዓ.ም በሌጐስ በተደረገው

የአፍሪካ መንግሥታት የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ አንድ ድርጅት ለመመሰረት በአዲስ አበባ የመሪዎች ስብሰባ እንዲደረግ በብዙ ድካም ከስምምነት ተደረሰ። በአህጉራዊ ድርጅት አመሰራረትና አሰራር ልምድ ያለው ሰው ከላቲንአሜሪካ ተቀጥሮ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ክፍል ተሰጥቶት በቶማስ ወልድ የቅርብ ክትትልና ምክር የአፍሪካ አንድነት ቻርተር ረቂቅ እንዲዘጋጅና የአፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ በቅድሚያ እንዲመክርበት ተደረገ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ ከስምንት ቀን በኋላ መሪዎቹ ሲሰበሰቡ ቀርቦላቸው እንዲያጠኑትና አሳብ እንዲሰጥበት ለሚመጣው ዓመት እንዲተላለፍ ነበር ያሰቡት። ቶማስ ወልድ ግን ዋና ዋናዎቹን በየተራ ቢሮአቸው እየጠሩ "ቻርተሩን እውኑ መፈረም አለብን" እያሉ በግንጋገር ስለአግባቡዋቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ በረቂቁ ተስማምተውበት የመሪዎች ጉባኤ ተከፈተ። ንጉሠ ነገሥቱም "ቻርተሩን ሳንፈርም መለያየት የለብንም" ብለው በመክፈቻ ንግግራቸው ስላሳሰቡና ሌሎቹም ተመሳሳይ አሳብ በማስከተላቸው መሪዎቹ ዲስኩራቸውን በሚያደርጉበት ጊዜ ጉን ለጉን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ ከመሪዎቹ በሚነገረው መንፈስ የቻርተሩን የመጨረሻ ረቂቅ እንዲያሰናዱ ተደረገ። በመጨረሻም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ ጉባኤ ራፖር ለርዕሳነ ብሔራቱና ለመንግሥታት መሪዎቹ ከፍተኛ ጉባኤ ቀርቦ አንቀጽ በአንቀጽ ውይይት ተደረገበት። እውን መፈራረም አይቻልም ያሉትን በማግባባት፣ በግንቦት 17 ቀን 1956 ዓ.ም ከሌሊቱ በአሥራ አንድ ሰዓት የቻርተሩ መፈረም በመሪዎች ተከናወነ። የተፈረመው በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ሲሆን፣ የቻርተሩን ረቂቅ ከስር ከስሩ በመቀበል ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በመተርጐም ለፈርማ ያደረሱት አቶ አብተው ገብረ ኢየሱስና አምሐ ገብርኤል ናቸው። በዚህ ሌሊት ነበር የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተወለደው። የመጀመሪያው የድርጅቱ የመሪዎች ጉባኤ በ1957 ዓ.ም ካይሮ እንዲደረግ በተወሰነው መሰረት በካይሮ ሰብሰባ ላይ የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ እንዲሆን ቶማስ ወልድ ያቀረቡትን አሳብ መሪዎቹ በጭብጨባ ስለተቀበሉት አዲስ አበባ የድርጅቱ መዲናም ለመሆን በቃች። በዚሁ የካይሮ ጉባኤ ላይ የአፍሪካ አገሮች ወሰን ነፃ በወጡበት ጊዜያት ባለው እንዲረጋ አቢይ ውሳኔ ተላለፈ።

በሌላው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ከፍተኛ ጉባኤ ላይ

የሶማሊያ ፕሬዚዳንት የሶማሊያን ግዛት ከያዙት መንግሥታት እንደ ኢትዮጵያ ናት በማለት ለአደረጉት የክስ ንግግር ቶማስ ወልድ "ኢትዮጵያ ታሪኳ የታወቀና ለሦስት ሺህ ዘመን ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች መሆኑዋን በመግለጽ የሶማሊያ መንግሥት የሚባል በታሪክ እንደሌለና የአገር መስፋፊያ ጥያቄ ማንሳት ከተፈለገ ኢትዮጵያ ሶማሊያን ራሷን ከግዛቷ እንደ አንዱ መጠየቅ በቻለችም ነበር" ሲሉ የሰጡት ቅጽበታዊ መልስ ነበር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፈላቸው ።

ቶማስ ወልድ ለመሆኑ ማናቸው? ይህን ሁሉ ያደረጉት በ1953 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር ተብለው የተሾሙት ኢትዮጵያዊው አሐፈ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ናቸው ።

እንደነዚህ ያሉትን የአገር ተከራካሪና አገልጋዮች ነበር ደርግ ለጥይት የዳረጋቸው ። ሕያው ሥራ የሠሩትን ሰዎች ነበር የአገር በዳይ በማስመሰል ጥላሸት ሊቀባቸው የሞከረው ።



ጸሐፈ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ለሶማሊያ ፕሬዚዳንት ክስ መልስ ሲሰጡ

፲፬

ረቶ መታሰር

ዘመኑ መታሰር ቀርቶ መገደልም ልዩ ክስተት ያልሆነበት ፣ ከወንጀል አስረኛው ይልቅ የፖለቲካ አስረኛው ቁጥር የበረከተበት ነበር። ለመታሰር ፣ ግፉ ሲልም በፖለቲካ ውሳኔ ፣ በቀይሽብር ፣ በነፃ እርምጃ በሌላም ፣ በሌላም ስያሜ ለሚፈጸም ርሽና መከሰስና መረታት ቅድመ ሁኔታ የሆነበት አልነበረም ። ምክንያቱም የሰው ደም እንደ ደመ ከልብ የተቆጠረበት ፣ የሰው ሬሳ በየመንገዱ የሚጣልበት ፣ ክቡሩ ፍጡር የሰው ልጅ እንደ ኢምንት የታየበት ፣ ሰብዓዊ መብት የማይከበርበት ፣ ሕግና ፍትህ ዋጋ ያጣበት ዘመን ነበርና ።

በ1967 ዓ·ም ነበር "ከመካከላችሁ የሚከሰስ ቢኖር ለፍርድ ቤት ይቀርባል ፣ የማትከሰሱት ደግሞ ትፈታላችሁ ፣ ስለዚህ ፍርድ ቤት ብትቀርቡ የምትለብሱት ልብስ ከቤታችሁ እንዲመጣላችሁ ጠይቁ" ተብሎ በታላቁ ቤተ መንግሥት ለሚገኙ የፖለቲካ አስረኞች በደርግ አባሎች የተነገረው።

"ምናልባት ብከሰስ ሰው መስዬ (ዲሰንት ሆኜ) ፍርድ ቤት ለመቅረብ እንድችል የምለብሰውን ላኩልኝ" በማለት ጽፎ በአስር ቤት ዘወትር ከሚለብሰው እጅግ ከነተበውና ከተጨማደደው የተሻለ ልብስ ሁሉም ከየቤቱ አስመጣ ። ፍትህ አገኛለሁ በሚል ተስፋ መከሰስን ሁሉም በጉጉት ይጠባበቅ ነበር ። መከሰስ የሚናፈቅበት ጊዜ በመሆኑ መረቀት ብጤ ይዞ የሚመጣ የአስር ቤት ጠባቂ ክሩቅ ባየ ቁጥር ክስ መጣ በማለት አቆብቁቦ ጠባቂው ብዙ ነበር ። ክስ ሳይሆን ሌላ መረቀት መሆኑን ሲያውቅ የሚበሽቅም ነበር ። ከንቱ ጉጉት ፣ የፍትህ ጥማት ፣ የመለቀቅ ረሀብ!

ልዩ ፫ር ፍርድ ቤት ይቋቋም ፡ ዳኞች ይሰየሙ ፡ ልዩ አቃቤ ሕግ ይሾም እንጂ ክስ ሊቀርብ አልቻለም ። ክስ በማስረጃ ላይ እንጂ በአሉባልታ ፡ በመግለጫ ጋጋታ ላይ እይመሰረትምና ። በብዙ አቅጣጫ ምርመራ ቢያረግም ፡ በየመስሪያ ቤቱ ማስታወቂያ ተለጥፎ ከሳሽ ቢጋበዝም ለመከሰስ የሚያበቃ ማስረጃ በብዙዎች ላይ ለማግኘት አልተቻለም ።

ለፍትህ ቆሚያለሁ ፡ ንፁሐን ከጥፋተኞች ተለይተው ይፈታሉ እያለ ደርግ እንደልፋፈ ጽድቅ ያለማቋረጥ የደገመው ሁላ በአየር ላይ የተሰ ራጨ እስትንፋስ ሁኖ ቀረ ። ከእንደበቱ (ከልሳኑ) የወጣውን ቃል ደርግ መልሶ ዋጠው ።

ለወጉ ያህል ግን ከረጂም ጊዜ እስራት በኋላ በ12 ሰዎች ላይ በልዩ የጦር ፍርድ ቤት በተለያየ ጊዜ ክስ መሠረተ ። መጥሪያ ለተከሳሾቹ ተላከ ። ጠበቃ ቅጠሩ ፡ መከላከያችሁን አቅርቡ ተባሉ ። የሞት ፡ ሽረት ጉዳይ ስለሆነ ቤተሰብ ተንቀሳቃሽ ንብረት ሽጠ ወይም ተለቅቶ ጠበቃ ለመቅጠር ተሯሯጠ ። ለእንዳንዶችም ጠበቆች ያለከፍያ በልጨኛነት ጥብትና ቆሙ ። ጠበቃ ለማቆም ላልቻሉት ደግሞ ፍርድ ቤቱ በነፃ የሚቆሙላቸው ጠበቆች አዘዘ ። የእምነት ፡ ክህደት ቃል መስጠቱ ፡ ክስና መልስ መለዋወጡ ፡ እሰጥ አገባው ፡ ጠቅላላውም ሙግቱ ቀጠለ ። ከምድር ቤት ወደ ፎቅ ወጥቶ መሚገቱ ፡ የስነሥርዓት ጥያቄ በማቅረብ ፍርድ ቤቱን መፈታተኑ ፡ አቃቤ ሕጉ የሚለውን በማስተባበል ማስቆጣቱ ፡ የሥነ ሥርዓት አስከባሪዎችን ዓይን ማስፈጠጡ እንድ ተከሳሽ ፍርድ ቤት በቀረበ ቁጥር የሚታይ ጉዳይ ሆነ ።

ፍርድ ቤቱ ብያኔ እንዲሰጥባቸው ከቀረቡት የሥነ ሥርዓት ጥያቄዎች አንዳንዶቹ "ሕግ ወደኋላ ተመልሶ እይሠራም ፡ እንድ መንግሥት በስልጣን ላይ ላልነበረበት ጊዜ የወንጀል ዓይነትና ቅጣት ለመወሰን ስልጣን አይኖረውም" የሚሉ ነበሩ ። ለቀረበው ሕገ መንግሥታዊ የሕግ ክርክር አቃቤ ሕጉ የበኩሉን አስተያየት እንዲያቀርብ ሲጠየቅ "እጼ ቴዎድሮስን በዘመኑ የነበሩት ሰዎች እንተ ማነህ? ሲሉ እንደተፈታተኑት ሁሉ አሁንም እናንተ በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት ያወጣውን ሕግ መቃወማችሁ ከዚህ ድርጊት የሚለይ አይሆንም" የሚል ሐተታ በማከል ነበር የተከሳሾቹ ጥያቄ ሙድቅ እንዲሆን ሽንጡን ገትሮ የተሟገተው ። በቀረበው የሥነ ሥርዓት ጥያቄ ላይ ፍርድ ቤቱ

የመሰለውን ብያኔ ከሰጠ በኋላ የፍሬ ነገር ክርክሩ ቀጠለ ።

ክስ የቀረበባቸው 12 ሲሆኑ ፡ ከነዚሁ መካከል ስድስቱ ሲረቱ* ሁለቱ ብቻ ናቸው በሁለት ዓመት ገደብ የተፈረደባቸው ። በአራቱ ላይ የቀረበው ክስ እንዳይቀጥል ተደረገ ። በመጀመሪያ ጊዜ የረቱት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት ይፈቱ ነበር ። በኋላ ግን ይህ አይሆንም ።

በመካከሉ ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ የቀድሞ ባለስልጣናች ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ተይዘው ለፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ረጂም ጊዜ መቆየታቸውን በመመልከት "ሕግ ከሚያዘው ውጭ ማንኛውም ሰው መታሰር አይገባውም" በማለት በፓርላማ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልነታቸው በአራተኛ ክፍለ ጦር ምድረ ግቢ ለተሰበሰበው ሠራዊት በሰኔ 20 ቀን 1966 ዓ.ም ንግግር በማድረጋቸው ፡ ጦሩን ለማነሳሳትና ለመከፋፈል ሞክረዋል በማለት ነበር የተከሰሱት ። ለፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር "የቀድሞ ባለሥልጣናች ያላግባብ ሰው ይበድላሉ ፡ ያስራሉ በማለት አብዮት ለማካሄድ የተነሳ ቡድን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰው አስሮ ማጉላላቱ አግባብ እይደለም ማለቴና በዋስ እንዲፈቱ መጠየቄ ጥፋተኛ እያስደርገኝም" የሚል ነበር ።

የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ፡ የተጠቀሰባቸውን የሕግ አንቀጽ ከእገናዘበ በኋላ "ከሕግ ውጭ ለምን ይታሰራሉ ማለት ጥፋት አይደለም ፡ በአገራችንም ባህል የታሰረ እንዲፈታ ማማለድ መልካም ምግባርና የተለመደ ስለሆነ ጥፋተኛ ባለመሆናቸው በነፃ ለቀናቸዋል" ሲል ነበር ፍርድ ቤቱ ጎሳር 23 ቀን 1968 የፈረደው ።

በአንድ በኩል ተከሳሹ ደስታ ስለፈነቀላቸው ፡ በሌላ በኩል አለአግባብ ለረጅም ጊዜ መታሰራቸው ስለአበሳጫቸው ነበር "በእ ላይ መንግሥት ባወጣው መግለጫ ሕዝብ ጥፋተኛ አድርጉ ሊገምት ስለሚችል የቀረበብኝ ክስ ተገቢ አለመሆኑን ወደ ሐረርጌ ሄጀ ለሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልነት ለመረጠኝ ሕዝብ ማሳወቅ ስለአለብኝ የፍርዱ ግልባጭ ዛሬውኑ ይሰጠኝ" ሲሉ በሲቃ ፍርድ ቤቱን ጠየቁ ። ፍርድ ቤቱም እንዲፈቱ የተለመደውን ትእዛዝ ሰጠ ።

ባለጉዳዩ የተናገሩት ንግግ ቃል ለደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣናች ጆሮ

---

* የረቱት ሌ/ኮሎኔል አደላ ቾጣው፡ ሜ/ጄኔራል ግርማ ሙላት ፡ ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ ፡ አቶ ተፎሙ ገብረ ማርያም ፡ አቶ ጉርሱ ገብረ መድህን ፡ አቶ አክሊሉ ቤተ መርያም ናቸው ።

ወዲያውኑ በመድረሱ እንደፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዳይፈቱ ለጠባቂዎቹ በደርግ ትእዛዝ በመሰጠቱ ሳይፈቱ እደሩ ። በማግሥቱም ባለመፈታታቸው ምክንያቱን ቢጠይቁ "አርፈህ ተቀመጥ" ተባሉ ። ደርግ ከሕግ ውጭ የሚፈጽመው ግፍ ከእደባባይ እንዳይወጣበት በመስጋትም እንደ ሆነ እንጂ ራሱ ባቋቋመው ልዩ የጦር ፍርድ ቤት የተሰጠውም ፍርድ ስንኳ እንዳይፈጸም እደረገ ። ይባስ ብሎም ከዚያ በኋላ የተፈረደላቸውም እስረኞች ሁሉ እንዳይፈቱ ወሰነ ።

ይህ ከሆነ መርታት ከመረታት በምን ይለያል? የረታ ከታሰረ ያውም ላልተወሰነ ጊዜ? ይህ ነበር እንግዲህ የዚያ ዘመን ፍትህ ፣ ረትቶ መታሰር!!

፲፭
ይቅር በሉኝ

ከልዳተ ክርስቶስ በኋላ በአራተኛው ምዕተ ዓመት ነበር ትምህርተ ክርስትና ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በቅሉ ያበበውና ቀስ በቀስም በመላ ኢትዮጵያ የተዳረሰው ። በትምህርተ አሪት ማኅ ላይ በመብቀሉ ክርስትና በምድረ ኢትዮጵያ በእጭር ጊዜ ውስጥ አብቦ አፈራ ፣ ማኅደረ ክርስቶስ በየኀጡ ታነፀ ። ሐዋርያተ ወንጌል ፣ ካህናተ ቤተ ክርስቲያን ተበራከቱ ። የሥዕል ቤት ፣ የቤተ መቅደስ ፣ የአድባራትና የገዳማት ቁጥር ዕልፍ እምአዕላፍ ሆነ ። ቤተ ክርስቲያን ሳሚው ፣ መብዓ አቅራቢው ፣ ሥዕለት ተሳዩ ፣ ጸሎት አድራሹ ሁልቆ መሳፍርት የሌለው ሊሆን ቻለ ። ኢትዮጵያ በሐዋርያዊው በፈልጶስ እጅ በተጠቀመው ጃንደረባ ብሥራተ ወንጌል የተበሰረባት ፣ ካሳቱ ብርሃን ሰላማ የሰበከባት ፣ ቅዱስ ያሬድ ንሴብሆ ያለባት ፣ ተሰዓቱ ቅዱሳን ያስተማሩባት ፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አኮቴት ያደረሱባት ፣ ክርስቶስ ሰምራ ሱባኤ የገባችባት አገር ሆነች ።

ይሁንና በ325 ዓ·ም የተመሠረተችው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሀዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት እስከያዝነው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው እኩሌታ ድረስ ይመራ የነበረው በግብጽ (ኮፕቲክ) አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ነበር ። ኢትዮጵያዊቱ ቤተ ክርስቲያን ትታይ የነበረችው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ልጅ እንጂ ፣ እህት ሁና አልነበረም ። በመካከላቸው የነበረው ግንኙነት ያቻነት ሳይሆን በበላይና በበታችነት መልክ ስለነበረ ፣ ለዘመናት መንፈሳዊ አባት የሚመጣው ከምድረ ግብጽ ነበር ። የወንጌላዊው የቅዱስ ማርቆስ መንበር ከሆነችው ከእስክንድርያ የሚመጣላት አባት ሕዝቡን በቋንቋው ቃለ እግዚአብሔር

የሚያስተምሩና የሚያናዝዙ አልነበሩም ፡ በስማበለው የሚናገሩ እንጂ ።

ይህን የበላይነት የፀና ሁኖ ለማቆየት በኒቅያ ጉባኤ ባደረጉት በሰለስቱ ምዕት/በ318 የቤተክርስቲያን አባቶች/ተጻፈ ተብሎ በሚነገር ለት በፍትሐ ነገሥት ውስጥ "ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው መካከል መርጠው ፓትርያርካቸውን አይሹሙ" ተብሎ ከጊዜ በኋላ በክፍል 4 በምዕራፍ 27 ሥረ ዋፅ ሐረግ ታክሎበታል ።

ከዚህ ወጥመድ ውስጥ ለመውጣት ለአንድ ምዕተ ዓመት እኩሌታ ለተቃረበ ጊዜ ያልተቋረጠ መንፈሳዊ ትግል ተደረገ ። የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለማስቻል ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱና የቤተ ክህነት ሊቃውንት ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተከታታይ ድርድር አደረጉ ። በዚህ ድርድር የፖትርያርክነት ሹመት ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያ ዊው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ·ም ተሰጠ ። ይሁን እንጂ ሢመቱ የተፈጸመው በምድረ ግብጽ ፡ በካይሮ ከተማ በኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እጅ ነበር ።

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ፓትርያርክ በመሾም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ነፃነቷን አግኝታ ራሷን ለመቻልዋ የማረጋገጫ ማኅተሙ የታተመው ፡ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የመሆን ሢመት በአምስት የተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች ፡ እንደዚሁም በኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት አንብሮተ እድ በተፈጸመበት በግንቦት 1 ቀን 1963 ዓ·ም ነበር ።

በ1935 ዓ·ም ነበር መምህር መልእክቱ ወልደ ማርያም በአዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አውደ ስብከት ብቅ ያሉትና ልብ የሚነካ ስብከት በመስበክ ሐዋርያዊ ተልእኮ የጀመሩት ። በተሟላ ሙያቸውም በመጀመሪያ የጥንቱም የአዲሱም ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ፡ በኋላም ደብሩ የመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ገዳም የሚል ስያሜ ሲሰጠው የመጀመሪያው ሊቀ ሥልጣናት ተባሉ ። አቡነ ቴዎፍሎስ በሚል ስመ ሢመት በ1940 ዓ·ም የሐረርጌ ጳጳስ ፡ በ1942 ዓ·ም ደግሞ በዚሁ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳሳት ፡ በኋላም የፓትርያርኩ እንደራሴ ተብለው ተሾሙ ። ሁለተኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርኩ በመሆን ለመጨረሻው ማዕረገ ክህነት በበቁበት በ1963 ዓ·ም ነበር የእጩጌነት ማዕረግ በተደራቢ የተሰጣቸው ።



ንጉሠ ነገሥቱና ፓትርያርኩ ለብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ሸኑዳ የእስክንድሪያ ፓፕና ፓትርያርክ በተደረገ አቀባበል ላይ ፡
(ከግራ ወደ ቀኝ ጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ፡ ብፅዕ ወቅዱስ ሸኑዳ ፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ)

ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስ መቻልና ሐዋርያዊና ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ፣ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለመቀራረብና ለክርስቲያናዊ ልማት ፣ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ዕናት ይጥሩ የነበሩትን እኒህን መንፈሳዊ አባት ደርግ በየካቲት 9 ቀን 1968 ዓ.ም ከመንበረ ፓትርያርክ በጨለማ አፍኖ ወሰዳቸው ። በኢ.ዮ.ቤ.ልዩ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻቸውን አሰራቸው ። "ሲጠበቅ የቆየው ፍርድ" በሚል ርዕስ መግለጫ አወጣባቸው ። በዚህ መግለጫ የተዘረዘረው ውንጀላ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም "ሰማዕቱ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ" በሚል ርዕስ ቤተ ክርስቲያን ባወጣችው መጽሔት እንድ በእንድ ተስተባብልዋል ። በእንዛሩም ፓትርያርኩን ከመንበራቸው ለማውረድ ያበቁት ምክንያቶች ፣ የፓትርያርኩ አቋም ከደርግ ፖሊሲ ጋር የማይስማማ መሆኑና የቤተ ክርስቲያንንም መብት ለማስከበር ለወታደራዊ መንግሥት የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ንዴለ ቃል እንደነበሩ ማስረጃ በመጥቀስ በዚሁ መጽሔት ተገልጸዋል ። እኒህ መንፈሳዊ አባት በመጽሔቱ እንደተዘረዘረው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅን በመምራት ዘመናዊ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲዳረስ ፣ የስብከተ ወንጌል ድርጅት በማቋቋምና በማስተማር የምዕመናን ቁጥርና ዕውቀት እንዲዳብር ማድረጋቸው ፣ የወጣቶች ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት በመመስረት በየደብሩ ወጣቶች በመንፈሳዊ ተግባር በይበልጥ እንዲጐለብቱና ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲቀራረቡ በማድረግ የሐዋርያዊነት ተግባር መፈጸማቸው ተመስክሮላቸዋል ። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር እየተላኩ ልዩ ልዩ እውቀት እንዲቀስሙ ማድረጋቸው ፣ በሀገረ ስብከታቸው በሐረርጌ የቀላውስትና የዲያቆናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች እንዲሠሩ ፣ በዘመን ብዛት ያረጁና የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ በማድረግ የሕዝቡን የትምህርትና የመንፈሳዊ ሕይወት የሚያሟሉ ታላላቅ ሥራዎች መሥራታቸው የትሩፋታቸው ሌላው ዘርፍ ሁኖ ቀርቦላቸዋል ። በውጭ ግንኙነትም ረገድ በ1940 ዓ.ም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሆላንድ ፣ አምስተርዳም ላይ ሲቋቋም ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዑካንን በመምራት በስብሰባው ላይ ከመገኘታቸውም በላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጉባኤው መሥራች አባል እንድትሆን ማድረጋቸው ለቀረበባቸው ውንጀላ

ሌላው አፍራሽ ምክንያት ሁኖ ማስረጃ ቀርቦበታል ። በተከታታይም በ1946 ዓ·ም በእንግሊዝ አገር በቼትሰተር ፡ በ1949 ዓ·ም በአሜሪካ ኤቫንስተን ፡ በ1954 ዓ·ም በሕንድ በኒው ደልሂ ፡ በ1960 ዓ·ም በስዊድን ኡፕሳላ ፡ እንደዚሁም በ1963 ዓ·ም በአዲስ አበባ በተደረጉት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤዎችና የማዕከላዊ ኮሚቴ ሰብሰባዎች መካፈላቸው ፡ በተለይም በ1954 ዓ·ም በኒው ዴልሂ በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እንዲሆኑ ተመርጠው እስከ 1960 ዓ·ም ድረስ ማገልገላቸው በዓለም አቀፍ መድረክ ከፍተኛ ግምት ስለአስገኘላ ቸው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤም ከሶስቱ የጠቅላላው ጉባኤ ፕሬዚዳንቶች አንዱ እንዲሆኑ ሁለት ጊዜ በተከታታይ መመረጣቸ ውና በ1961 ዓ·ም ኮትዲቧር ፡ አቢጃን ላይ የተደረገውን ጉባኤ በተለይ በፕሬዚዳንትነት የመሩ መሆናቸው በዚሁ መጽሔት ተዘክርዋል ።

ከዚህም ሁሉ በላይ ቅዱስነታቸው ከአስራ ስድስት ምዕተ ዓመታት በኋላ የምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ከፍተኛ የመሪዎች ጉባኤ ሲያደርጉ ፡ ጉባኤው የተሳካ እንዲሆን የአደራጁን ኮሚቴ በበላይነት ከመምራታቸውም በላይ ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን መሪ በመሆን በጉባኤው ተሳትፈ ዋል። በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ አገሮች የሥራ ጉብኝት ከማድረጋቸ ውም ሌላ በአሜሪካ ፡ በትሪንዳድና ቶቤጎ ፡ በጋያና ፡ ፡ በሱዳን ፡ በኢየሩሳሌም የተመሰረቱትን የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ጉብኝ ተው መንፈሳዊ አመራር ሰጥተዋል ።

እንደዚህ ያለ አስተዋጽኦ ያበረከቱትን መንፈሳዊ አባት የኮሚኒስ ታዊ ሥርዓት አራማጅ የነበረው ደርግ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በማይፈቅ ደው አኳኋን ከፓትርያርክነት መንበራቸው በማውረድ አሰራቸው ። ደርግ በመጀመሪያ አስሮ ከአስቀመጣቸው ቦታ ሲያመልጡ ወደ አሠሩት የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነበር የሄዱት ። ቅዱስነታቸው ከታሰሩበት ቦታ መጋቢት 2 ቀን 1968 ዓ·ም ከወጡ በኋላ ሊሄዱ ያሰቡት በምሥራቅ ሐረርጌ ወደሚገኘው ወደ ደብረ ወገግ አሰቦት ገዳም ነበር ። ከጐፋ ገብርኤል የደረሱት ጀምበር ከጠለቀች በኋላ ሲሆን ፡ ያሉበትን ጠቁሞ ያስያዛቸው ያሳደጉት ፈድአቸው ነው ። በማግሥቱ ጧት በአምስት ሰዓት በርካታ ወታደሮች መጥተው እያንገላቱ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት አስገቡዋቸው ። በሶስት ቁጥር ክፍል ውስጥ



ብፅዕ ወቅዱስ አቡን ቴዎፍሎስ

ለሰባት ቀናት በፅኑ እሥራት እሠሩዋቸው ።

በታላቁ ቤተ መንግሥት ከታሰሩበት ከመጋቢት 3 ቀን 1968 ዓ·ም ጀምሮ ለእርባ አምስት ቀናት እህል የሚባል ነገር አልቀመሱም ። የመንፈስና የአካል ጥንካሬአቸውን ያረጋገጡትም በዚሁ ነው ። ከእስረ ኞቹ መካከል በዕድሜ ገፋ ያሉት እንጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳን ወልድ ፣ ቢትወድድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ፣ ደጃዝማች ሐረጉት አባይ ፣ ፊታውራሪ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋርያት ፣ ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ፣ አቶ ንጉሤ ሀብተ ወልድና ሌሎችም እጥብቀውና አስጨንቀው በየጊዜው ስለ ለመኑዋቸው በትንሣኤ ማግሥት ሚያዝያ 18 ቀን 1968 ዓ·ም እህል ሊበሉ ቻሉ ።

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ደርግ ለያንዳንዱ እስረኛ ለስንቅ ግቅረቢያ ብሎ 120 ብር ይከፍል ነበርና ምግብ መብላታቸውን ሲያውቅ ለቤተሰባቸው ይኸው ገንዘብ እንዲሰጣቸው ወኪል እንዲወክሉ የጥበቃው ኃሌፊዎች ጠየቁዋቸው ።

"ምንም ገንዘብ አልቀበልም ፣ ወኪልም አልወክልም ፣ ድሮም በልመና እንጀራ ነው የተማርኩት ፣ አሁንም እየለመን ቁራሽ እንጀራ የሚልክልኝ ሰው ካለ ይላክልኝ ፣ ያለበለዚያ የእናንተን ገንዘብ አልቀበልም" የሚል ነበር መልሳቸው ። በሌላ ጊዜ ደግሞ "የሚፈልጉት ምንድነው?" ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ ፣ "ከናንተ የምፈልገው ፣ ካሰራችሁኝ ገዳም ወስዳችሁ እንድታስሩኝ ብቻ ነው ። ከተቻለ አሰቦት ገዳም ወስዳችሁ እሰሩኝ ፣ ካልተቻለም በፈለጋችሁት ገዳም እሰሩኝ" የሚል ነበር ። ልብስ ከቤት እንዲላክላቸው ለቤተሰብ በጻፉት ደብዳቤ ላይ "አባ ቴዎፍሎስ" ብለው በመፈረማቸው "ስምህ አባ መልእክቱ ስለሆነ አባ መልእክቱ ብለህ ፈርም" ሲል ሻምበል ስሜ ወልደ ጊዮርጊስ የተባለው የዘብ ኃላፊ ከዛቻ ጋር ሲጠይቃቸው ፣ "እኔ አሁን አባ ቴዎፍሎስ እንጂ አባ መልእክቱ አይደለሁም ፣ አባ መልእክቱ ድሮ ጳጳስ ከመሆኔ በፊት እጠራበት የነበረው የዓለም ስሜ ቢሆንም ፣ የፈለከውን ብታደርግም አባ መልእክቱ ብዬ አልፈርምም" በማለት በድፍረት መለሱለት ። ከዚህ በኋላ ፓትርያርክ ሲሆኑ የቆጵሮስ ፕሬዚዳንት ብፁዕ አባ መቃርዮስ የሸለሙዋቸውን ከወርቅ የተሰራ የእጅ መስቀል ቀምቶ ወሰደባቸው ። ከሚተኙበት ትንሽ ክፍል ውስጥ ሰቅለውት የነበረውንም

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥዕልም አውርዶ ወሰደው ።

በእስር ቤት ኑሮአቸው የቅዱስነታቸው አብዛኛው ጊዜያቸው በጸም በጸሎት ፣ በማስተማር የተጠመደ ነበር ። ሌሊት ለተወሰነ ጊዜ ሲፀልዩ ያድራሉ ። ጧትና ማታ በማኅበር ጸሎት ይካፈላሉ ። አንዳንድ ጊዜም አጠር ያለ የማዕናኛ ምክር ይሰጣሉ ። እሑድ ፣ እሑድ በንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ረዳትነት ሥርዓተ ቅዳሴ ያደርሳሉ ። በፍልሰታ ሁለቱ ሳምንት በየቀኑ ምሀላ ስለሚያዝ የውዳሴ ማርያምና የወንጌል ትርጉም ያሰማሉ ። ከሥርዓተ ቅዳሴ በኋላ ነበር አንድ ቀን ባሉበት ክፍል የሚገኙትን እስረኞች ሰብስበው "በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደልካችሁ ካላችሁ ይቅር በሉኝ" ብለው ቅዱስነታቸው ሁሉንም ይቅርታ የጠየቁትና ማንኛውንም ቅሬታ በትህትና በማስወገድ እውነተኛ መንፈሳዊ አባት መሆናቸውን ያስመሰከሩት ።

፲፮
ሰሙነ ሕማት

የዕልመት ቅዳሚት መጥፎ ትዝታ በየምክንያቱ ከአእምሮ ውስጥ ድንገት ብልጭ ማለቱ ባይቀርም ፣ በ"እንፈታለን" ተስፋ ከተተካ አምስት ዓመት አልፎታል ። ከቤተሰብ የሚመጣው ደብዳቤ ሁሉ ተስፋ ሰጭ እየሆነ በመሄዱ ለመፈታት መንፈስ ሁሉ አቆብቁቧል ። በር በር ማየት ፣ ለጠባቂዎች ፈገግታ ማሳየት ፣ የአጸፋ መልስ ማግኘት ተዘውትሮአል ። ከቤተሰቢ የሚገኘውን ማንኛውንም ጭምጭምታ ፣ የጠባቂዎችንም ፈገግታ በአስተማማኝ የመፍታት ዜና መተርጉም የልጅ የአዋቂው በጉ ምኞት ሁኖአል ። መቼስ እስረኛ የሚመኘው ፣ የሚያስበው ፣ የሚያልመው መፈታትን ፣ ከቤተሰብ ጋር መቀላቀልን ፣ ሰርቶ ማደርን ፣ በእስራቱ ዘመን ለረዱት ሁሉ ምስጋና ማቅረብን ነው ። ስለዚህ ነው ሌሊት የሚያየውን ሕልም ወይም ቅዠት ሁሉ በበጉ የሚፈታው ።

እጣ ፈንታውን በምኞቱ ላይ ጥሎ ነበር እስረኛው ሁሉ እንዳይወድቅ እየተሽመደመደ ጉስቋላ ሕይወቱን ረጋ ብሎ የሚመራው ። እስረኛነት ታሳሪ የሚያደርገው አካልን ብቻ አይደለም ፤ መንፈስንም ይቀይዳል ፤ ይሰቃያል፣ ያብሰለስላል ፣ ያብከነክናል ፣ ያሳዝናል ፣ የትዝታ ባሪያ ፣ የአሳብ ቁራኛ ፣ የመልካም ዜና ረሀብተኛ ያደርጋል ። የቆየ ፍቅርን፣ የተረሳ ሀዘንን ይቀሰቅላል ። ያውም ስሞ ለማይወጡት ፣ አልቅሶ ላይከፍሉት ። ለዛ ያለው የልጅ ልምምጥ ፣ በፍቅር ማር የተለወሰው የቤት ጭውውት ሲታወስማ ፣ ረቂቁ መንፈስ ከግዙፉ አካል ልይት ይላል ። ቤት፣ ቀዬው ፣ ገበታና መኝታ ቤት ፣ የመዝናኛ አልፍኝ ወይም እፍንፍኒትዋ ጉጀው ስትታወሰው የጉረቤት ሰላምታ ልውውጡ ሲዘነረው በአሳብ ፣ በትካዜ የማይባዝን አልነበረም ። በውጄታ ሳይሆን በግዴታ የተሰጠውን ውሱን ሕይወት የሚኖር በመሆኑ ግን ሊያደርገው የሚችለው ምንም ነገር የለም ።

ቢጨነቅ ፣ ቢጠበብ ፣ ቢያዝን ፣ ቢተክዝ ከዚያች ባለአራት ግድግዳ ዋሻ ሊያወጣው የሚችል ብልሀት አልተከሰተለትም ። ከአሳሪዎቹም ርህሩህ ልቡና ፣ መልካም ስብዕና ማግኘት ሕልም ሆኖበታል ። ሕልሙም ከቶ እውን ሊሆን አልቻለም ። ተስፋ ባለመቁረጥ ግን እምላኩን በጸሎት ይማፀናል ። መንታ የሚወርድ እንባ በማፍሰስና ጥጥር ልቡናውን በመስበር ፈጣሪውን የሙጥኝ ብሎታል ። ከተመዘዘ ሰይፍ ፣ ከበራሪ ጥይት ፣ ከወገን ጠላት እድነኝ ይላል ።

የኢትዮጵያን ምድር በምሀረት ዝናብህ እንጂ በደም እትጠባት ፣ ለፀሎት ወደ አንተ የተዘረጋ የኢትዮጵያን እጅ መና አታስቀረው ይላል ሁሉም ፣ በጋቢ ፊቱን ሸፍኖ እንዳይሰማ ድምፁን ዋጥ አድርጉ ። ከሙጭ የሚሰማው ተባራሪ ወሬ ፣ በጋዜጣ የሚነበበው ጽሑፍ እበስኩ ፣ ገበርኩ! ያሰኛል ፣ በዚያን ዘመን ክፉ እንጂ መቼም በጉ ነገር አይሰማምና ። እስረኛው ራዲዮ የሰማው የገጠር ርስቱን ፣ የከተማ ቤቱን መወረሱን እንዲሰማ በተደረገበት በየካቲትና በሐምሌ ወር 1967 ዓ.ም ሁለት ቀናት ብቻ ነበር ። ከዕለተ ሰኑይ በቀር በየዕለቱ ዜና የሚያገኘው በግል ወይም በማኅበር ከሚገዛው ጋዜጣ ብቻ ስለሆነ ወሬ ከሚያጋሩት ከሌሎቹ የመገናኛ ብዙሃን ጋር ከተቆራረጠ ዓመታት አልፎታል። ቢሰማቸውስ ከዘለፋ ፣ ከወቀሳ ፣ ከፍየል ወጠጤ መደለቅ ሌላ ከጋዜጣው የተለየ ነገር ስለማይገኝባቸው ጀሮውን ላለማደንቆር እምብዛም አይጓጓላቸውም ። ጋዜጣውን ግን የሚያነበው ከገጽ ገጽ ፣ የፍርድ ቤት ወይም የጨረታ ማስታወቂያውንም ጭምር ነበር ። የፍርድ ቤት ማስታወቂያው መነበቡስ ይሁን ባቦ ፣ ምናልባት ከቤተ ዘመድ ሰው ሙቶ መርዶው ያልተነገረው ቢኖር ከውርስ ማስታወቂያ የወጻጅ ፡ ዘመድን ወይም የሚያውቁትን ሰው ዜና ዕረፍት ለማወቅ ስለሚያስችል ይሁን ። የጨረታ ማስታወቂያ ማንበቡ ትርጉም አይኖረውም ፡ ለመጫረት በማይችሉበት ቦታ እያሉ ያሰኝ ይሆናል ። ግና ሥራ ከመፍታት ልጇን ላፋታት እንዲሉ ፡ ይህንም ዓይነት ማስታወቂያ ማንበብ ግዜን ለመግደል ሲባል የሚደረግ ነው ።

የእስር ቤቱ ሕይወት በጋ ተክረምት የቀዘተዘ ፡ ማጠፊያው ያጠረ ፡ እቅጣጫው የማይታወቅ በመሆኑ ለፀሐይ ብቅ ከሚባልበት ጊዜ በቀር እስረኛው ሁሉ በጉሮኖው ታጉሮ ነው የሚውለው ። ጠባቂው እንዳልራራለት ክብት ያችንም በቁንጢጥ ተለክታ ፡ የምትሰጥ የፀሐይ መሞቂያና የእግር ማፍታቻ ጊዜ የሐምሌ ዝናብ እየተሻማት ሁሉም ተቸግሮአል ።

ዝናቡስ የተፈጥሮ ሕግን ተከትሎ ነው የመጣው ፡ ለሕግ የማይገዛው ፡ ሰብዓዊ መብትን የሚጻፈረው የሰው ጭካኔ ግን ይገርማል ። ዝናቡስ ይዝንብ እብቅሎ ሊያበላ ነው ፡ ሰው ግን ፋታ ፡ እረፍት ፡ ፀጥታ ለመንሳት ነው የሚያሸብረው ።

በ1971 ዓ.ም የሐምሌ በፀታ እለት ነበር ከምሳ በኋላ በማሸለቢያ ሰዓት የጥበቃው ኃላፊ የሁለት ቁጥር ክፍልን ኃላፊ ከሙጭ አስጠርቶ "ጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነወልድንና አቶ ሠይፉ ማኅተመ ሥላሴን ጥራ" ሲል ትእዛዝ የሰጠው ። ተዋከበው ሲወጡ ሳንጃ የወደሩ ፡ ጠበንጃ የደገኑ ወታደሮች እየነጹ ቁልቁለቱን ይዘዋቸው ወረዱ ፡ ደብዛቸው እየጠፋ ሄደ ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ የፕሮስቴት (የሽንት መከልከል) ሕመም ታመው ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻው በጦር ኃይሎች ሆስፒታል አፕራሲዮን ተደርጉላቸው ወደ እስር ቤት በተመለሱ ሳምንት ባልሞላው ፡ ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት ጠይቀው ከእስር ቤት ከተፈቱት ባለቤታቸው ጋር ተገናኝተዋቸው በተመለሱ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ነበር የተጠሩት ። በሽሚዝ ላይ ነጠላ ጣል እንዳደረጉ በድንገተኛ ጥሪ ወጥተው ሄዱ ።

አቶ ሠይፉ ደግሞ ጋደም እንዳሉ በተደጋጋሚ ጥሪ ያላበውን ፈታቸውን ስንኳ ሳይታጠቡ ተነስተው ወጡ ። አቶ ሠይፉ ከጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ጋር የጋብቻ ዝምድና ስላላቸው ሁለቱንም በእንድነት ሲጠሩዋቸው ከጋራ ቤተሰቦቻቸው ጋር ያገናኙዋቸው ነበር እስረኛው የመሰለው ። ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘ ከተለመደው ጊዜ በላይ ሲቆዩም ፡ ሰፊ ጊዜ ተሰጣቸው በማለት እስረኛው ቀናባቸው ። ጀንበር ስትጠልቅ ሳይመለሱ ሲቀሩ ግን የሰቆቃ ጓደኞቻቸው ሥጋት እደረባ ቸው። በር በር መመልከቱን ተያያዙት ። የክፍሉ ኃላፊ ዘቦችን እንዲጠይቅ ሌሎቹ ገፋፉት ። ሲጠይቅም ይመጣሉ የሚል መልስ ተሰጠው ። እንደተባለው ግን አልተመለሱም ። ሌሊቱ በጭንቀት ታለፈ። በነጋታው ረቡዕም ብቅ አላሉም ። ሁለት ቀን አለፈ ምንም ፍንጭ ሳይሰማ ። ይህም እስረኛውን ሁሉ እጅግ አሳሰበው ፡ አስጨነቀው ። ሰጉዳዩም ትርጉም አጣለት ።

የማክሰኞው ጥሪ ሠሙስ ከእኩለ ቀን በኋላ ተደገመ ። አሁንም ጉንድ እስረኞች ነበሩ ከሁለት ቁጥር ክፍል የተጠሩት ። ከሁለት ቀን

በፊት እስረኞቹን ያስጠሩት በክፍሉ ኃላፊ አማካይነት ነበር ። እውን ግን የጠሩትም ፣ ያስጠሩትም የክፍሉን ኃላፊና ምክትል ኃላፊ አቶ አበበ ከበደንና አቶ አሰፋ ድፋዱን ነበር ። ይህም እስረኛውን ይበልጥ እስደነገጠው ። ጠባቂዎቹ ግን ወደ ሌላ ሰፍራ እንደማዛወሩ ለማስመሰል "እንድብርድልብስና የመዐጻጃ ወረቀት ያዙ" አሉ ።

ከዚህ በኋላ ነበር እስረኛው ተስፋ ቆርጦ ተራፊ ቢናር በማለት ጉሳዜ እየተናዘዘ አንዱ ለሌላው የሰጠውና ሞትን እንደ መልካም እንግዳ ለመቀበል ተዘጋጅቶ ተራውን መጠበቅ የጀመረው ። ማንም ራሱን ከነዚህ የተለየ አድርጉ ባለመቁጠሩም ነበር የእም ተራ ይመጣል በሚል የሚጠባበቀውና ቀን ከሌት እንቅልፍ ያጣው ፡ መንፈሱ የበረገገው ። በአሳብ ፡ በጭንቀት የሰለሰለው የሕይወቱ ክር መበጠሻዋ የተቃረበ መስሎ ታየው ። አንዱ ብቻ አለኝታው የሆነውን ፈጣሪውን ሌት ተቀን መንዝነዙን አጠናከረው ።

ሐምሌ 5 ቀን 1971 ዓ.ም የተወሰዱትም እንደፈተኛዎቹ አልተመለሱም ። የት እንዳደረሱዋቸው አልታወቀም ። ሁለት ቁጥር ክፍል በዚህ ወቅት ያጣው የክፍሉን ኃላፊና ምክትል ብቻ ሳይሆን ከሶስት ቀን በፊት የተመረጡት የሶስተኛውን ሹም አቶ ሠይፉንም ጭምር ነበር ። ስለዚህ ጊዜያዊ ኃላፊ መረጠ ፡ በክፍሉ የነበረው እስረኛ ሕይወት እስካለ ለውስጥ አስተዳደሩ ኃላፊ መተካት ነበረበትና ።

ጥረው ግን ፋታ አልሰጠም ። ቅዳሚት ደግሞ ሁለት ጥንድ እስረኞች ተጠሩ ፡ ከእንድ ቁጥር ሶስት ፡ ከሁለት ቁጥር ክፍል ደግሞ አንድ ። ከሁለት ቁጥር አቶ ዮሐንስ ኪዳነ ማርያም የተጠሩት ከቤት ከመጣላቸው ምግብ አንድ ጉርሻ ጉርሰው ፡ ሁለተኛውን እንደቆረሱ ነበር። ፊታቸው ከስም እንዳለ ፡ አንደበታቸው ምሬት እየተናገረ ነበር ከግዕድ ላይ ተነስተው የወጡት ። በዚያን ወቅት ምግብ ቢመገቡትም ከሰውነት አይጠጋም ። አካል እኮ በምግብ የሚደገፈው የመንፈስ መረጋጋት ሲኖር ነው ። በዚያ ወቅት እህል የሚጉረሰው ለቁመተ ሥጋ እንጂ የመመገብ ፍላጉት ኑሮ አልነበረም ።

ከእንድ ቁጥር በመጀመሪያ የተጠሩት ደጃዝማች ካሣ ወልደ ግርያምና ብ/ጄኔራል ሣሙኤል በየነ ነበሩ ። ስለዚህም ነበር ደጃዝማች ካሣ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘንድ ቀርበው "ይፍቱኝ" ቢሉ የጠየቁት ፡ "እግዚአብሔር ይፍታ" የምትለውን ቃለ ሥርየት እግኝተ

ውና መስቀል ተሳልመው ወጡ ። እፍታ ሳይቆይ ብፁዕነታቸውም ተጠሩ። ለቀሪዎቹ በመስቀላቸው እያማተቡ መርቀው በግርማ ወጡ ።

የዚህ ዕለት ሁኔታ ከአለፉት ሁለቱ ቀናት ለየት ያለ ነበር ። የሥጋቱ ትኩሳት የተሰማቸው እስረኞቹ ብቻ አልነበሩም ፡ ጠባቂዎቹም ጭምር እንጂ ። ስለዚህ ግርግሩ በዛ ፡ ጠበንጃ ድገናው ተጠናከረ ፡ የዕልመተ ቅዳሚት ሁኔታ እንደገና ተደገመ ።

ፓትርያርኩ በሶስት መንፈሳዊ ልጆቻቸው ግራና ቀኝ ታጅበው ፡ ጥቁር ቀሚሳቸውን ለብሰው ፡ ካባቸውን ደርበው ፡ እክሊል እንደደፉ አርዌ ብርት እንደያዙ ፡ ነጠላ ጫማ እንደተጫሙ ሲሄዱ ጽዋ ሰማዕትነትን ለመቀበልና ሕይወታቸውን ለቆሙለት ዓላማ አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጁ እንጂ ፡ ምንም ዓይነት ሥጋት የሚታይባቸው አልነበሩም ።

የቀሪዎቹ እስረኞች ጭንቀት ግን በዚያች ቀውጢ ሰዓት በእጅጉ ጨመረ ። የመኖር ተስፋቸውም እከተመ ። ሰቆቃውን በጣም የከበደ ያደረገው እያሰለሱ ስለሚወሰዱ በነጋ በጠባ ቀጣዩ የኔ ተራ ይሆን የሚለው ቁጥጥን ያለማወቅ ነበር ። ጭንቀቱን ሲያራዝሙም እሁድና ሰኞን ምንም እስረኛ ሳይጠሩ ውለውና እድረው ማክሰኞ ሐምሌ 10 ቀን 1971 ዓ.ም ለምሽት መስተንግዶ ደጃዝማች ሐረጉት ዓባይን ጠሩ ። ይህ በሁለት ቀን ልዩነት የተደረገ ጥሪ የሥጋቱን ትኩሳት በመለኪያው (በቴርሞሜትሩ) ላይ ጥቂት ማዘትዘት የታየበትን ሁኔታ ከመቅጽበት ከሰማይ ሰቀለው ። ትካዜው ቀጠለ ። መራበሹ ተባባሰ ። በዕልመቲቱ ቅዳሚት ዕለት እርሳቸው የሉበትም የተባሉት ሰው መጠራት የሚቀር ሰው የለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ነበር ሁሉም የደረሰው ።

በሶስተኛው ቀን ነበር የታሰሩትን ሰዎች ዕቃ ጠቅልላችሁ አውጡ የተባለው ።

ፓትርያርኩንና ሌሎቹን እስረኞች የት እንዳደረሳችኋቸው ግለፁልን በማለት ነበር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፡ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ፡ የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ድርጅቶች ደጋግመው የጠየቁት ። ደርግ ግን የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ነበር ያለው ።

፲፮

መማቀቅ

በሐምሌ 27 ቀን 1971 ዓ.ም የተወሰኑ እስረኞች ስም ተጠራ። ሁሉም እንደነና ተደናገጠ። ለሁለት ሳምንት ያህል ምን ይመጣ ይሆን? የማንኛችን ተራ ይሆን? እያለ ሲባንን የቆየው እስረኛ ሁሉ ከፉኛ ተሸበረ። ያለፈው ጥሪ ለጥሩ ስለእልነበረ ፣ "እባብ ያየ በልጥ በረየ" እንደሚባለው ሆነ። የጠባቂዎችን ዓይን መመልከቱም ምንም ምልክት አልሰጠም። የጥሪው ምክንያት ከበር እስከሚወጣ ድረስ ስለማይገለጥ ግራ መጋባት ፣ መጠራጠር ሰፈነ ፣ ያለፈው ተመክሮ የተሻለ ነገር እያዘከርምና። ጥሪው ሲቪልም ወታደርም ያቀላቅላል ፣ አዛውንትም ፣ ወጣትም ይደባልቃል።

ለተጠሩት ሰዎች ያልሰጋ አልነበረም። እነርሱም ለብሰው ሲወጡ በጉ ነገር አልታያቸውም። አሸልቦ የነበረው ሲቀሰቀስግ ከመባነን አልፎ መበርገግ ነበር የታየበት። የክፍል ኃላፊው ስማቸውን ሲጠራ እንደተሳሳተ አድርገው የገመቱም አልታጡም።

መቼስ ተጠርቶ አልወጣም ማለት አይቻልምና የተጠሩት ዘጠኝ ሰዎች ከበር ሲወጡ ግን የተነገራቸው ከጠበቁት የተለየ ሆነ። ጀሮአቸው ንም አላመኑትም። መድኃኔ ዓለም በዕለተ ቀኑ የፈጸመው ታምራት አድርገው ቆጠሩት። ዕቃቸውን እስናዱ ተብለው ወደ ዋሻው ሲመለሱ መፈታታቸውን ለጓደኞቻቸው ገለጹላቸው። የእስረኛውን መገንገን ለማረጋጋት ነበር በተወሰጹት እስረኞች ልክ ዘጠኝ እስረኞች የፈቱት። ይህም በሥጋት የሰነበተውን እስረኛ ጭንቀት ለማስተንፈስ ተብሎ የተደረገ ስለሆነ ፣ የተጠበቀውን ውጤት ማስገኘቱ አያጠራጥርም። ይሁን እንጂ መፈታታቸውን ቀሪው እስረኛ በእውን የተቀበለው ከቤተ

ሰብ "የነእገሌ ዕድል ሳይደርሳችሁ በመቅረቱ እናዝናለን" በማለት የጸፉት መሳቀቃቸውን የገለጹበት ደብዳቤ ሲደርሳቸው ነው።

ጥቂት እስረኞች የሚፈቱት ብዙ ጊዜ ተምጦ ከረጂም ጊዜ በኋላ እንጂ ነበር። ነገ ፣ ተነገወዲያ እንፈታለን በማለት እስረኛው ሁሉ በተስፋና በጉጉት ይጠብቃል። ስለዚህ ነው ሌሎች ሲፈቱ ቀሪው ራስ ምታት የሚያድበት ፣ ሌላ ረጅም ጊዜ መቆየት እንዳለበት እያሰበ የሚቆዝመውና የእስር ሕይወቱ ከብደት ይበልጥ የሚሰማው። እንደቤተ ሰቦቹ ሁሉ እስረኛውም ይሳቀቃል። የመፈቻው ጊዜ ነገ ይሆናል በሚል ተስፋ ይጠብቅ የነበረው ቀርቶ ከቀናው ለከርሞ ፣ ያለበለዚያም እስከናካቴው የማይፈታ መስሎ ይታየዋል። የደርግ የመፍታት ቁጥ ፣ ቁጥ ምሥጢር ለማንም ግልጽ አልነበረም። ሲገድል በገፍ ፣ ሲፈታ ግን በቁጥር መሆኑ ምን ዓይነት ሕዝባዊ አስተያየት እንደሚያስጠው ደርግ ያውቅ ነበር ይሆን? ደርግ ይወቅም አይወቅ ፣ የቀሩት እስረኞች እድል ፈንታ ከመቆራመድ አልዘለለም። ከቤተሰባቸው ለረጂም ጊዜ ተለይተ ዋል። ችግር ቤታቸውን ፈቶታል። ልጆቻቸው የመማር ዕድላቸው ሳይቀር ተታውሶባቸዋል። የእድሀሪ ልጅ ተብሎ መሳለቂያ መሆን እንገፍግፎአቸዋል። ያንዳንዶች ትዳር ፈርሷል። ከቤተሰብ በቀር ጎብረተሰቡ እየረሳቸው ሄዷል። ንብረት አትሸጡ ፣ ስም አታዛውሩ ፣ ግብር ገብሩ ፣ ንብረት አስረክቡ በተደራራቢ ለቤተሰብ የሚሰጥ ትእዛዝ ነበር። ምግብ ይዘው ሲመጡ የሚደርስባቸው መገልመጥ ፣ እምጡን እንጂ በቃኝን የማያውቁ ሕፃናት የሚያቀቡትን ጥያቄ ለማስተናገድ ባለመቻል መቸገር ፣ የቤተሰብ ሌላው ዕጻ ነበር። ለወር ጨው ስንኳ ምንም የማይደግፍ እስረኛ ግድ ሁኖበት እንዲህ ያለ ነገር ላኩልኝ ሲል መሳቀቁ የእርሱ ብቻ ሳይሆን ፣ ለመላክ ያልተቻለው የቤተሰቡም ጭምር ነበር። ስለዚህ በፍላጉትም ፣ ባንጋገርም ፣ በእርምጃም መቆራመድ የታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት ምርጫ የሌለው ሕይወት ነበር። እካል ከመቆራመድ እዝ ስር ሲውል የእስር ቤት በር አልፎ ፣ እጥር ጥሶ ተዘብ ተሰውሮ ወደ አሻው ሰፍራ ሂዶ የሚመለስ እሳብ ብቻ ነበር።

እሳብ ፣ ጥሩ ትዛታ ፣ መልካም ምኞት ፣ በጎ ሁኔታ ፣ ከሕሊና ፊት አምጥቶ ስለሚይቅን ፣ ለብቻ ስለሚያነጋግር ይወደዳል። ጻሩ ግን ምን ያረጋል ፣ የዚህን አፀፋ አምጥቶ ስለሚያውክ የወደዱትን ያህል ይጠሉ ታል። ሰው በአሳቡ የሚፈጥረው ነገር ምነው ሁለት ገጽታ ባልኖረው!

ደግ ደጉን ብቻ ቢያመለክት የሚቆራኙት ፣ በቁረባን የሚጋቡት የሕይወት ባልንጀራ በሆነም ነበር ። "ዓለም ዘጠኝ ናት" ተብሏል ፣ መቸም እትሞላም ። በእርሷ ላይ የተፈጠረው ተጓዥ አሳብም የእርሷው አለመሟላት የተጋባበት በመሆኑ ፍጹም ውኖ አይገኝም ። እንዳንዱ የተቃና ፣ ሌላ ጊዜ የተሰናከለ ይሆናል ።

በእስር ቤት ሕይወት አሳብን እንደአካል መቀየድ አለመቻሉ ነው አንዱ ችግር ። ተሰብስቦ ባለመቀመጡ ነው መጥፎ ስሜት እያሳደረ እስረኛውን የሚፈታተነውና ለአፍታ ልየት ያለውን ጭንቀት መልሶ የሚያመጣበት ። ሲካበድም ከንዝህላልነት ፣ ከነጭናጫነት ፣ በመጨረሻም ሕይወትን እስከመጥላት ያደርሳል ። በገፋኸኝ ፣ በገላመጥከኝ ፣ በጉንጥከኝ ፣ በተራ ቀደምከኝ ከመከራ ጓደኛ ያጣላል ፣ ያነዛንዛል ። ደግነቱ ጠብ ሲፈጠር ሽማግሌዎች ስለሚያስታርቁ ነገሮች ሲበርዱ መቻላቸው ነው ። የመንፈስ ፀጥታ በሌለበት መቀያየም መቼም ያለ ነው ።

በዚህ ላይ የተጠመደ መትረየስ ፣ የተደገነ ጠበንጃ በአፈጠጠበት ፣ መላወስ ከስጋት እጥር የማይወጣበት ሁኔታ ውኖ ይገኛል ። ፀሐይ በመሞት እስረኞቹ በመንከላወስ ላይ ሳሉ ነበር ከእስረኞቹ አንዱ አቶ አብተው ገብረ ኪየሱስ በባረቀች ጥይት እግራቸው ላይ የቆሰሉት ። በዋሻ ውስጥ መቀየድ ፣ በችግር መቆራመድ እንሶ በጥይት መቁሰል ፣ በሕመም መማቀቅ እያድርስ!

ሐኪም ቤት ለሕክምና እንደዚሁም ቀድሞ መሥሪያ ቤት ተጠርቶ ሲኬድ ከኋላና ከፊት መትረየስ በተጠመደበት ጂፕ (በአራዳ አጠራር በቋሚ ተጠሪ) መታጀብ የመንፈስ ጭንቀት ይፈጥራል ። ሰንድ ታስረከባላችሁ ተብሎ ወደ ቀድሞ መሥሪያ ቤቱ ከዶክተር ሥዩም ሐረጉት እና ከአቶ አብተው ገብረ ኪየሱስ ጋር ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በአጃቢ በጥር 19 ቀን 1967 ዓ.ም ሲወሰድ ነበር አምሐ ገብርኤል ብርቱ ሥጋት ያደረበት ። በዚህ ዕለት ከእኩለ ቀን በፊት ነበር ለመጀመሪያና ለመጨረሻም ጊዜ በደርግ የምርመራ ክፍል ልዩ ልዩ ጥያቄ ቀርቦለት መልስ የሰጠውና ቃሉም በሰፈረበት ሰንድ ላይ የፈረመው ። ከእኩለ ቀን በኋላ ድንገት ተጠርቶ ሲሄድ እስረኛው ከባለሥልጣኖች በሚሰጠው ቃል እምነት ያጣበት ጊዜ ስለነበረ ለሥጋቱ ምክንያት ነበረው ። ምንም ስንኳ የጉዞው አትጣጫ ወደ ቀድሞ መሥሪያ ቤቱ ቢሆንም ከስፍራው

እስኪደርስ የጉዞውን መድረሻና የጥሪውን ትክክለኛ ምክንያት ማወቅ ካለመቻሉም በላይ የእጀቡ ጋጋታ ለጥርጣሬ ጻረገው ። ከመሥሪያ ቤቱ ሕንፃ መግቢያ ላይ ሲደርሱ እምሳ አለቃ ፍቅሬ ዘርጋው የተባለው የበታች ሹም ተቀበላቸው ። የበታች ሹሙ የደርግ የመጀመሪያው ሊቀ መንበር የሌ/ጂኔራል አማን አንዶም ልዩ ጠባቂ ሁኖ ኡዚውን ጨብጦ ከጽሕፈት ቤታቸው በራፍ ላይ ተቀምጦ የሚጠብቅ ነበር ። ጂኔራሉ ከተገደሉ በኋላ ነበር የደርግ ሊቀመንበር ጽሕፈት ቤት በተባለው በቀድሞው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት የለውጥ ሐዋርያ ተብሎ የተመደበው ።

አምሐ ገብርኤል የተፈለገው ይሠራበት የነበረውን ጠረጴዛ ከፍቶ እንዲያስረክብ መሆኑ ሲነገረው ፣ የጠረጴዛውን መሳቢያ የሚከፍተውን ቁልፍ አለመያዙንና ከሁለት ቀን በፊት ባለቤቱ ወልዳ ሆስፒታል ስለምትገኝ እሷ ወደ ቤት እስክትመለስ ድረስ ቁልፉን ፈልጉ የሚልክለት አለመኖሩን ከገለጸለት በኋላ አምሳ አለቃ ፍቅሬ "በሌላ ጊዜ ቁልፉን ይዘው እንዲመጡ" ብሎ ከሌሎቹ ጋር መለሰው ። እርሱም የሚፈለገውን ቁልፍ እንድትልክለት ለባለቤቱ ሲጽፍ ሁለት ቁልፎች ብትልክለትም ሁለቱም የጠረጴዛው መክፈቻ አልነበሩም ። ከተቂት ቀናት በኋላ ነበር አውንም በአጃቢ ወደ ቀድሞ መሥሪያ ቤቱ ከጓደኞቹ ጋር እንደገና የተወሰደው ። ሌሎቹ የተጠየቁትን ሁሉ ያለምንም ማሰረጃ ሲያስረክቡ አምሐ ገብርኤል የመጣለት ቁልፍ የተሳሳተ መሆኑን በመግለጽ ስልክ ወደቤቱ ደውሎ እንዲያመጡለት ለመጠየቅ እንዲፈቀድለት ጠይቆ ሲደውል ፣ ባለቤቱ ስለቀረበችለት የቁልፍ መያዣውን እንዳለ በአስቸኳይ እንድትልክለት ጠየቃት ። ጊዜ አልወሰደችም በወለደች በሳምንቱ ከአራስ አልጋዋ ላይ መንተፍ ብላ ከንደኛዋ ከወይዘሮ ሙሉ ቦጋለ ጋር በመሆን ቁልፉን ይዛለት ስትመጣ ። መኪናዋን በመስኮት እንደተመለከተ የለውጥ ሐዋርያውን ጠቅቶ ቁልፉን ተቀብሎ እንዲያመጣ እንዲፈቅድለት ጠየቀው ። "አይቻልም" ነበር የተሰጠው መልስ ። መልሱ ከእንደበቱ እንደወጣ ተንደርድሮ ሂዶ ቁልፉን ከባለቤቱ እጅ ነጥቆ አመጣው ። ቁልፉን እንዳመጣ "ከፍተው ይሂዱ" አለ ቆጣ ብሎ ።

"በመሥሪያ ጠረጴዛዬ ውስጥ የመንግሥትም የራሴም ሰነዶች ስለሚገኙ የራሴን መርጬ እንድወስድና የመንግሥቱን በደረሰኝ እንዳስረ ክብ ይደረግልኝ" ሲል ጠየቀ አምሐ ገብርኤል ሥርዓት ጠብቆ ።

"ጠረጴዛው ለሌላ ሥራ ስለሚፈለግ ከፍተው መተው እንጂ ለርክክብ ጊዜ የለም" የሚል መልስ ተሰጠው ።

"የራሴንና የመንግሥቱን ሰነድ ለይቶ ለመረካከብ ካልተቻለ እሁን ጠረጴዛውን ከሌላ ክፍል ያዛወራችሁት ቢሆንም ፣ በቀድሞው ቢርዩ ውስጥ የሰነድ ማስቀመጫ ካቢኔት ስለለለ ከጠረጴዛው ውስጥ ሰነዶቹን አውጥቼ ከዚያ በማዛወር አሽጌበት የምትፈልጉትን ጠረጴዛ ላጋባላችሁ" ሲል ጠየቀው አምሐ ገብርኤል በትህትና ።

የሰነድ ማስቀመጫው ካቢኔት ከቦታው እንዳለ ለማረጋገጥ ቀድሞ ይሠራበት ወደነበረው ቀጥሎ ወደለለው ክፍል ሲሄድ በክፍሉ ሶስት መኰንኖች ተቀምጠው ፣ ካቢኔቱ ከክፍሉ እንዳለ በማግኘቱ በዚህ ካቢኔት ውስጥ ሰነዶቹን አዛውሮ እንዲያሽግ ባእነዚህ መኰንኖች ፊት በድጋሚ ጠየቀው ። በዚህም የበታች ሹሙ ይበልጥ ተቆጣ ። በዚህ ጊዜ ነበር አቶ ኃይሉ ዘርይሁን የተባለው የዚሁ መሥሪያ ቤት ባልደረባ "ጠረጴዛው ከተለቀቀ በካቢኔቱ ውስጥ ሰነዶቹ ቢታሸግባቸው ምን አለበት?" በማለት አሳብ ያቀረበለት ።

"እሽገውበት ከሄዱ ካቢኔቱ ሲፈለግ ደግሞ እርሳቸውን ልናመላልስ ነው እንዴ! ማሸግ የለባቸውም" ብሎ ሞገተው አምሳ አለቃው ።

እንዲህ ያመረረው ሰነድ ያለርክክብ ይዝረከረክ ፣ የምትሠራበት ጠረጴዛ ተከፍቶ ይቀመጥ ማለት ሌላ ጽሑፍ በጠረጴዛው ውስጥ ከቶ ለመወንጀል መንገድ ማመቻቸት ይሆናል በሚል ጥርጣሬ አምሐ ገብርኤል ቁልፉ የተወሰደው በማስገደድ ለመሆኑም ምስክር ለመቁጠር ሲል የሚያደርገው መሆኑ ገብቶት ይሁን ወይም በመኰንኖች ፊት ለምን እንደአላዋቂ አደረገኝ በማለት እንደሆነ አይታወቅም ። የአምሐ ገብርኤልን ሕጋዊ ጥያቄ ለመገንዘብ ካልቻለ ሐዋርያነቱ እምኑ ላይ ነው?

የለውጥ ሐዋርያው እየተመናጨቀ ወጣ ሲል አቶ ኃይሉ ዘርይሁን አምሐ ገብርኤልን ወደ ጉን ወሰድ በማድረግ "ለምን ማንኛውንም ነገር ግድረግ ከሚችል የደርግ አባል ጋር እንዲህ ትከራከራለህ! ባይሆን ለጥንቃቄው ያህል እኛ ፈርመንበት ቢታሸግ ይሻላል" ሲል አስታራቂ አሳቡን አቀረበለት ። ምንም ስንኳ ጥያቄው ሕጋዊ መሆኑን ቢያውቅም ፣ አምሐ ገብርኤል ከባለጊዜ ጋር መከራከሩ ዋጋ እንደሌለው ተረድቶ ምስክር ለመቁጠር በመቻሉ በመተማመንና የቀረበለትን የማስታረቂያ አሳብ በመቀበል ፣ አቶ ኃይሉና ሌሎቹ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች

በማሸጊያው ወረቀት ላይ ፈርመውበት ሰነዶቹ በካቢኔት ውስጥ ተቆልፈው ታሸገ ። አምሐ ገብርኤልም እንደበሽቀ ወደ መቀየጃ ስፍራው ተመለሰ ።

የደርግ አባሎች የሚቀይዱት እኳልን ብቻ አልነበረም ፣ አሳብንም ጭምር ነበር ። ስለዚህም ነበር የእስረኞን ሰነድ ለማግኘት የሚያነፈንፉትና በድንገት ከክፍሉ ውስጥ ዘው ብለው በመግባት እስረኞቹን አስወጥተው ጽሑፍ የሚበረብሩት ። ከዚህም የተነሳ በዕለት ተዕለት የተደረጉትን ነገሮች የሚያሰፍሩበት የማስታወሻ ደብተር አንዳንዶቹ እስረኞች ተወስዶባቸው አልተመለሰላቸውም ። ከፍተኛ ቀኖቹ በአንደኛው ቀን አምሐ ገብርኤል "ሕይወት" በሚል ርዕስ የሚጽፈውን መጽሐፍ ረቂቅ በመጻፊያ ገበታው ላይ ትቶ ነበር በድንገት ከክፍሉ የወጣው ። ዓይናቸውን ምን እንደያዘው አይታወቅም ጽሑፉን አልወሰዱበትም ። ተደብቆ የተቀመጠን ሲጐረጉሩ ይሆናል ሜዳ ላይ ጣል የተደረገውን ያላስተዋሉት ። ቢያገኙትስ የቀደመ ታሪክን እንጂ አምሐ ገብርኤል ምኑ ሞኝ ነው የሚጨመሩ ሁኔታ በዚያን ጊዜ የሚጽፈው!

የሚሰማውን በጽሑፍ ለማቆየት ፣ "የተጠየቅ ሙግትን" ሥርዓት ከሚያውቁ ከፊታውራሪ አበበ ገብረና ከሌሎች እየጠየቀ ሌት ተቀን ሲጫጭር የተመለከቱት ሌ/ጀኔራል ዓቢይ አበበ "ሊወጣ መቻል አለመቻሉ ለማይታወቅ ጽሑፍ ለምን ዓይንህን ታጠፋለህ!" ሲሉ በጽሑፍ ላይ ማቀርቀሩን እንዲቀንስ አምሐ ገብርኤልን ይመክሩት ነበር።

"ጊዜ እንዳይባክንብኝ ልጻፈውና ይቀመጥ ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እኔም ጽሑፉም አብረን እንወጣለን ፣ ይህ ባይሆንም ከሁለት እንዳችን እንወጣ ይሆናል ፣ ማን ያውቃል?" በማለት ያለተፈጥሮ ብርሃን ሲጽፍ ዓይኑን እንዳያጣ በመሳሳታቸው እያመሰገነ አምሐ ገብርኤል መለሰላቸው ።

እንዳሉትም ቅጭጭ ያለ (ረቂቅ) ጽሑፍ ስንኳ ማንበብ የሚችለው፣ የአነባበብ ጥራትና ፍጥነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፍተኛ አድናቆት ያስገኘለትን ዓይኑን ፈጽሞ ባያጣውም ፣ እጅግ እደከመው ። መች ይህ ብቻ ፣ በጽሕፈት ዳሩ አምሐ ገብርኤል ወንበር ስለማይገባ በእልጋ ጠርዝ ላይ ተቀምጦ ፣ በትንሽ ጠረጴዛ ላይ አቀርቅሮ ሲጽፍ ሳይታወቀው ከእልጋው ብረት ቅዝቃዜ የተነሳ በታፋው ላይ የስር መሽማቀቅ ሕመም አደረበት ። ከክሊኒክ እየተመላለሰ መታሻ (ካንፉር) ቢሰጠውም አላዳነ

ውም ። ስሩ በመሸማቀቁ ቀጥ ያለው ቁመናው የቀድሞ ሁኔታውን አላጥቶ አስነከሰው ። በእግሩ ላይ የእግር ብረት አልቦ ያልጠለቀበት ቢሆንም ፣ በቅዝቃዜ ብዛት እግሩን ሸመቀቀው ። የጭንቀት ማህደር ሆነ ። በልጅነቱ በወባ ሕመም ምክንያት ደርሶበት የነበረው ቁሞ የመሄድ ችግር ተደገመ በማለት በሥጋት ሰነበተ ። ዶክተር ዮሐንስ ወርቅነህ ለእስረኞች የሕክምና እርዳታ ለመስጠት ወደ ክሊኒኩ የሚመጡበት ዕለት ደርሶ ሄዶ ተመረመረ ። እምሐ ገብርኤል የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጉ አድራጉት ድርጅትና ሆስፒታል አስተዳዳሪ በነበረበት ዘመን ዶክተር ዮሐንስ በዚሁ ሆስፒታል ሐኪም ሁነው እብረው ይሠሩ ስለነበረ በቅርብ የሚተዋወቁና በእድሜም እኞች ሲሆኑ ፣ እንዳማያውቁት ሁነው እርስዎ እያሉ ነበር ሲመረምሩት ጮክ ብለው የሚጠይቁት ። በምክንያቱ ሁለቱም ስለተግ ባቡ እርሱም እርስዎ እያለ ነበር የሚመልስላቸው ።

ከተመረመረ በኋላ ሐኪሙ መድኃኒት ያዘዙበት ወረቀት በጠባቂ ዎች አማካይነት ለቤተሰብ ተሰጥቶ ፣ ተገዝቶ እንዲመጣለት ተደረገ ። መድኃኒቱ በማግስቱ ይመጣል ብሎ ሲጠባበቅ ሳይመጣለት ቀረ ። ውድ መድኃኒት ውኖ ቤተሰቤ የመግዛት አቅሙ ሳይፈቅድለት ቢቀር ነው ያልተላከልኝ በማለት በልቡ አዘነ ። በሚቀጥለውም ቀን ሳይመጣለት ቀረ። ፈውስን ለማግኘት ቸኩሎ "የዛሬን እንዴት አድሬ" እንዳለው ዓይነ ስውር ሆነ ። ግና ምን ያደርጋል ፣ እንቆቅልሹ ያልታወቀ ጉዳይ ሆነበት ። ቢቸግረው "መድኃኒት ተገዝቶ እንዲላክልኝ ሐኪሙ ያዘዙበት ወረቀት ሰሞኑን ተልኮ ነበር ፣ መድኃኒቱ ገበያ ላይ ታጥቶ ነው ወይስ መግዣ ገንዘብ አጥተሽ ነው ያልላክሽልኝ?" ሲል ለባለቤቱ ጻፈላት ፣ ጭንቀቱ ገፋፍቶት ።

ይህን ደብዳቤ እንዳነበበች ነበር "የሐኪሙ ወረቀት የታለ ?" ብላ የክሊኒኩን ሠራተኛ የጠየቀችው ። እኪሱ ውስጥ ረስቶት ኑሮ በሶስተ ኛው ቀን ሰጣት ። በማግሥቱ በእጥር ላይ አስጠርቶ በጥፋቱ ይቅርታ በመጠየቅ የክሊኒኩ ሠራተኛ አንድ ባኮ ቤዝሮል ሰጠው ።

"ይህ የጉንፋን እንጂ የስር መኮማተር መድኃኒት አይደለም ፣ ተሳስቷል ፣ የሐኪሙ መኪናቸው ስለሚታየኝ የሄዱ ስለማይመስለኝ ያዘዙልኝ ይህ መድኃኒት እንደሆነ እባክህ እማራልኝ" ሲል ጠየቀው ፣ እምሐ ገብርኤል ቅሬታውን ውጠ ።

"ሐኪሙ ከክሊኒኩ ኃላፊ ጋር ወደክበብ ስለሄዱ እዚያው ድረስ

ሄጂ አጣራልዎታለሁ" ብሎት ሄደ የሕክምና ረዳቱ ፣ በእርሱ ዝንጋታ መድኃኒቱ ውሎ በማደሩ ሊከሰው ፈልጉ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሶ ፦

"ዶክተር ዮሐንስ ያዘዝኩልዎት መድኃኒት ይሽው ስለሆነ ይውሰዱት ብለዋል" ብሎ ያመጣውን ቤዝሮል ሰጠው ።

ከሌላው የጉንፋን መድኃኒት ቀለል ያለ ነው እያለች ጉንፋን በያዛት ቁጥር ባለቤቱ ትወስደው የነበረው መድኃኒት ለነርቭ በሽታ ፈውስ ይሰጣል ብሎ ባለማመኑ እምሐ ገብርኤል በጣም አዘነ ። ወዳጁ የሆነውም ሐኪም እንደሚያዮፍበት አድርጉ ቆጠረው ። ይህንን ከሆነ ያዘዘልኝ ይህን ያህል ቀን መቼ እጠብቅ ነበር ፣ ከሌሎች እስረኞች ለምኜ እሞክረው አልነበረ ብሎ አማረረ ። በሌላ በኩል ደግሞ እግሩን ሽምቅቆት መታመሙን ቤተሰቦቹ አውቀው እንዳይሰጉ ደብቆ ስለነበረ ፣ ግድ ሁኖበት መድኃኒት ሲጠይቅ ቤዝሮል በመታዘዙ ያመመው ጉንፋን ነው ብለው ስለሚገምቱ እንደማይሰጉ በመተማመኑ ተጽናና ።

መድኃኒቱን እንደተቀበለ ነበር የጤና አጠባበቅ ትምህርት ወደ አለው የመከራ ጓደኛው ዘንድ ሄዶ ፣

"እግሬን ይሽመቅቀኛል ብዬ ለሐኪሙ ሕመሜን ብገልጽለት ይህንን የጉንፋን መድኃኒት በማዘዝ ተሜወተብኝ ፣ ምን ባደርግ ይሻል ይመስልሀል ?" ብሎ የጠየቀው ።

"ይህ መድኃኒት ሁለገብ ስለሆነ ሊያድንህ ይችላል ፣ ለሁሉም ሞክረውና በኋላ ሁኔታውን ለሐኪሙ ትገልጽለታለህ ፣ ገና ሳትሞክረው አያድንኝም ብለህ አታስብ" አለው አቶ ኃይሉ ሰብስቤ ሲያግባባው ።

"ቢያድነኝም ፣ ባያድነኝም እስኪ ዛሬ ግታ እሞክረዋለሁ" ብሎት ተለያዩ ። በመድኃኒቱ ብቻ እምነት ስለአልነበረው ግታ በካንቶር እግርና ወገቡን በአቶ ሀብተ ሥላሴ ታፈሰ ታሽቶ ፣ የሱፍ የላይና የታች ሹራብ (ሱንጊ) ለብሶ ፣ ትኩስ ሻይ ጠጥቶ ፣ ቤዝሮሉን ውጦ ተሸፋፍኖ ተኛ ። ሌሊት በላብ ተደፈቀ ። ሲገላበጥ የአልጋ ልብሱን በላብ ተዘፍቆ አገኘው ። ብርድ እንዳይገባው እንደገና ተሸፋፍኖ ሲተኛ የገዛ ገላው ላቦት አጠለቀው ። የካንቶሩም መጥፎ ሽታ አፍንጫውን ሰፈነገው ። እንዳይነጋ የለምና ነግቶ ከመኝታው ብድግ ሲል የእግሩ ስር በመጠኑ ተፍታትቶለት አራመደው ። ጥሩ ምልክት በማየቱ በማግሥቱም ፣ በሳልስቱም ደጋገመው ። ለአምላክ ክብር ምሥጋና ለሐኪሙ ደግሞ ወሮታ ይድረሰው ና ቆሞ እንደልቡ ለመሄድ በቃ ። ያጻነው ግን የአቶ ሀብተ ሥላሴ

እፍተልትሉ ማሽት ፣ በውሎ አገር በረዶ በሚጥልበት ጊዜ ከውስጥ የሚለበሰው የሱፍ ሱሪና የላይ ሹራብና ፣ የሻዩ ሙቀት ፣ የካንፉሩ ሥራውን መሥራት ወይም የቢዝሮሉ ፍቱንነት እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ አልቻለም ። የመጨረሻ ግምጋሜው ግን የሁሉም አስተዋጽኦ ሳይሆን አይቀርም የሚል ነበር ።

ይህ ሁሉ ሲቃይና መማቀቅ ግን ለጽሑፍ ሥራ ያለውን ፍቅርና ከመጽሐፍ ጋር ያዳበረውን ወዳጅነት ከቶ አልቀነሰበትም ። ተቆራምዶ ሳለም ቢሆን ስንኳ ከሰው የማያጣላውን ሥነ ጽሑፍን የጊዜ ማሳለፊያ ፣ የአእምሮ ማዝናኛ አድርጉ ያዘ ። ይህም በእስር ቤት መማቀቅ እጅግ የሚከብድ ቢሆንም ፣ የሚቻል ነገር አደረገለት ። በእስር ቤት እንደዚህ ያለ የማይክድ ባልንጀራ ማግኘት መታደል ነው ።

የታላቁ ቤተ መንግሥት የፖለቲካ እስረኞች መማቀቅ በአካላዊ ሕመም ፣ በመንፈስ ጭንቀትና በችግርም በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተካበደ ነበር የሄደው ። መከሰስ እንደጥሩ ነገር የተመረጠው ቢፈረድ ስንኳ የእስራቱ ጊዜ ልክ ስለሚታወቅ ከመማቀቅ የሚገላገሉበት ቀን ይመጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ ነው ። ለታወቀ ጊዜ መታሰር ነገ እፈታለሁ የሚልን ተስፋ ለጊዜው የሚያሳጣ በመሆኑ በመጀመሪያ የሚያስደንግጥ ቢሆንም ፣ ቀን ባለፈ ቁጥር ጊዜው ስለሚቀንስ ከዕለት ዕለት የመፈታት ዕድል ርቆም ቢሆን በእርግጠኝነት ይታያል ። ላልተወሰነ ጊዜ መታሰር ግን በረዘመ ቁጥር ከቀቢፀ ተስፋ ላይ ያደርሳል ። ስለዚህም ነበር ለአንድ አሠርት ዓመት ለተቃረበ ዘመን መታሰር በእስረኞቹ ላይ በአነሰልም ፣ በመንፈስም መማቀቅን ከማይቻልበት ደረጃ በላይ ያከበደባቸው ።

የእሥር ቤት ሕይወት እጅግ ስለከበዳቸው ነበር ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ መልደ መስቀል 74ኛውን የልደት በዓላቸው በጥቅምት 19 ቀን 1971 ዓ·ም የሚከበር ሲሆን ጥቅምት 6 ቀን 1971 ዓ·ም የሚከተለውን ግጥም ጽፈው ከመኝታቸው እራስጌ የለጠፉት ። ይህን በጻፉ በሁለተኛው ቀን ነበር በጸና ታመው ሆስፒታል ተወስደው ያረፉት፣ የተመኙትን ያገኙት ።



ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ መልደ መስቀል

እቀርገለሁ=ላምላክ=ልገዊ=ምስጋና:
አድርሶቶል=ገዚህ=ስጥቃ=መሉ=ጠና=
ያደረገሁት=ጉዞ=የረዘመ=ነው=
ደክሞኛል ሃክቃኛል=ቢበቃ=ምነው!
ከእንግዲህስ=መዲያ=ልረፍ=እገክህ=
ደሁን=ብለህ=እዘዝ=ገለሠልግን=ነህ::

ጥቅምት. 19/19.71

ለ74 ዓመቴ=
ፍጻሜ=ላይ=

፲፰

ዕድል ፈንታ

አንድ የታሪክ ዘመን እንደከንውኑ በክፉው ዘመን ወይም በደጉ ዘመን እንዲህ ተደረገ እየተባለ ይዘከራል ። የደርግ ዘመነ መንግሥት ከኋለኛው ወይም ከፊተኛው በየትኛው እንደሚጻፍ የሚወስነው በዘመኑ በተፈጸሙት ድርጊቶች አመዛኝ ክብደት ነው ።

አንድ ነገር ግን ግልጽ ነበር ። በዚያን ዘመን በከፍተኛ ቁጥር የሚገመት ሕዝብ ታሪክ በማይረሳው ሁኔታ ታሰሯል ፣ በግፍ ተገድሏል ። ንጉሠ ነገሥቱና መኳንንቱ ፣ ፓትርያርኩና ካህናቱ ብቻ ሳይሆኑ ፣ ተራውም ሕዝብ ጭምር ለእስራትና ለሞት ተዳርጓል ።

ስለዚህ በታላቁ ቤተ መንግሥት ከታጐሩት የፖለቲካ እስረኞች መካከል የከፊሎች ዕድል ፈንታ ሞት ሲሆን ፣ የሌሎቹ ደግሞ እስከመቼው በማይታወቅ እስራት መማቀቅ ሁኖ ነበር ። ነፃነትን ያህል ፀጋ በመነፈጋቸው ፣ የሠሩት እንዳልነበረ ሲሆን ፣ የገነቡት ሲፈርስ ፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ወደማያዋጣ አቅጣጫ ሲያመራ ፣ ሰብዓዊ መብት ሲደፈር ፣ ስብዕና ሲገሰስ ፣ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ያገኘችውን የክብር ስፍራ ስታጣ ፣ በብርቱ ጥረትና በረጂም ጊዜ ያፈራቻቸው ወዳጆች ሲርቋት በማየታቸው በሕይወት ያሉት ቆሽታቸው እርር ፣ ኩምትር ብሏል ። የእስራታቸውም ጊዜ ማለቂያ በማጣቱ ለቤተሰብ ስቃይ ከመሆን ሞትን የሚመርጡበትም ጊዜ አልታጣም ። በእንደዚህ ያለ መሪር ሁኔታ ላይ ሳሉ ነበር አንድ ታምር የተፈጠረው ።

በተለምዶ ደርግ አብዛኛውን ጊዜ እስረኛ የሚፈታው ለአዲስ ዓመት ዋዜማ በመሆኑ በዚያን ዕለት የተጠራ ባለመኖሩ ሁሉም ተስፋ ቆረጠ ። ስለዚህ በእስር ቤት በተገኘ ቁሳቁስ የተሠራ ፣ በውበቱ ሳይሆን

በልቦናዊነቱ ዋጋ የሚሰጠው "የእንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ" ካርድ ሁሉም በዋዜማው ለቤተሰቡ ልኮ የዘመን መለወጫን በዓል በእስር ቤት ለማክበር አቀደ ።

በ1975 ዓ.ም መባቻ ማለዳ በአንድና በሁለት ቁጥር ክፍሎች ቅዳሴው ተፈጽሞ እሜን እንደተባለ ግን የእስር ቤቱ ጠባቂዎች አለቃ የሁለቱን ክፍል ኃላፊዎች አቶ ከተማ አበበንና አቶ አብተው ገብረ ኪየሱስን አስጠራቸው ። ዛሬ ደግሞ ምን እንሰማ ይሆን ? ማን ይወሰድ ይሆን ? እያለ እስረኛው ሁሉ በሃሳቡ ሲታመስ ፣ ሲጨነቅ ተወካዮቹ እየተንደረደሩ ተመልሰው ከክፍሉ በራፍ እስከሚደርሱ አላስችል ብሏቸው "ሁላችሁም ተዘጋጁ ተብላችኋል" በማለት የእስረኛውን ያረረ ቆሽት ፣ የእዘን ልቡና ፣ በጭንቀት የታወከ አእምሮ የሚያሽረውን የምሥራች ከፍ ባለ ድምፅ አበሰሩት !

የመፈቻው ጊዜ አልፎ ሁሉም ተስፋ በቆረጠበት ፣ ይልቁንም ሁላችንም በአንድ ጊዜ እንፈታለን የሚል አሳብ በማንም ሕሊና ባልዞረበትና ባልተጠበቀበት ወቅት "ሁላችሁም ተፈታችኋል" በመባሉ የተነገረውን መልካም ዜና ለማመን ያዳገተው ጥቂት አልነበረም ፣ የማይታሰብ ነገር ነበርና ። ስለዚህም ሁሉም ቸደናገጠ ። ከድንጋጤውም የተነሳ የሚይዝ የሚጥለውን አጣ ። ለዓመት በዓሉ ስንኳ የዘወትር ልብሱን ያለወጠው የተሻለ ልብስ ለመልበስ ሲጣደፍ እጁ ተርበተበተ ። እንደበቱ የሚናገረው ያሰበውን ሳይሆን እንዳመጣ ሆነ ፣ ያውም ባልተስተካከለ አኳኋን ። ቢሆንም በዚያች የተቀደሰች ዕለት በቅዳሴ ማሳረጊያ ላይ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀበተ ማርያም ወርቅነህ የሰበኩትን "ፈጣሪ ነው ያናገራቸው" ከሚል ድምጻሜ ላይ ከመቅጽበት የደረሰውና ሁሉን ለማድረግ ለማይሳነውም አምላክ ልባዊ ምስጋና ያቀረበው በደስታ ነው ። የሰበኩትም ጌታ ኢየሱስ በሊሳያስ ምዕራፍ 61 በቁጥር 1–2 የተጻፈውን በማንበብ "ለታሰሩት መፈታትን ፣ ለታወሩት ማየትን እንዳውጅና የተጨቆኑትን ነፃ እንዳወጣ ልኮኛል ... እነሆ ይህ አሁን ሲነበብ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ" የሚለውን ጥቅስ በመተንተን ነበር ።

*ሉቃስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 16–20

በእስር ቤት ኑሮ ስንኳ ሳይቀር እድሐሪ ፣ ተራማጅ ይባባል የነበረው ሁሉ በአንድ ላይ ነበር የእስር ቤትን በር አብሮ ለመውጣት የተሰለፈው ። ለዚህ ዕድል ፈንታ ያልታደሉት የእስር ቤት ጓደኞቻቸው ትዝታ በዚህ የደስታ ወቅት መጥቶ በመደቀኑ ሀዘንና ደስታ በአንድነት ብዙዎችን ተናነቃቸው ።

ስም መጥራት ዕቃ አሰናዱ ማለት አልነበረም ። በዚህ ዕለት "ለብላችሁ ውጡ ፣ በአቅራቢያ በተኮለኩሉት አውቶቡሶች ተሳፈሩ" ነበር የዕለቱ ትእዛዝ ። ግንም ጨርቄን ፣ ማቄን ፣ የደከምኩበትን ጽሑፌን አላለም ዕቃውን ጠቅልሎ አስቀምጦ ተፈትልኮ ሲወጣ ፣ ከአውቶቡሶቹ በአንደኛው ላይ ፈጢኖ ሲል ፣ አሳብ ተለውጦ ያስቀሩኛል የሚል ፍራቻ ያደረበት ይመስል በመቻኮል ። አውቶቡሶቹ 55 እስረኞች ይዘው ቲኪታትለው ያመሩት ጃንሜዳ ወደሚገኘው የቀድሞው የክብር ዘበኛ (አንደኛ ክፍለ ጦር) ጠቅላይ መምሪያ ነበር ።

ቤት ያፈራውን የዓመት በዓል መዋያ ምግብ ይዘው የመጡት ቤተሰቦች በግሰፈተሻው ስፍራ ተኩልኩለው ሳለ ነበር አውቶቡሶቹ እየተግትለተሉ ከግቢው ሲወጡ የተመለከቱትና ዘግየት ብለው ለመጡትም "ሲፈቱ ወደ ጃንሜዳ ተወስደዋል" የሚል ወሬ በአካባቢው በነበሩ ወጣቶች የተነገራቸው ። ያመጡትን ምግብ እንዲያዙ ቤተሰቦች ወደ ጃንሜዳ ከነፉ ። እንደወቅቱ አጠራር የንቃት ትምህርት የሚሰጥበትን አዳራሽ ዙሪያውን ከበቡት ። በጥር ወር የተምቀት በዓል የሚከበርበትን ጃንሜዳን በመስከረም ወር ሌላ የጥምቀት በዓል የሚከበርበት አስመሰሉት ። ሕፃን እዋቂው ለአዲስ ዓመት የለበሰውን የክት ልብሱን እንደለበሰ ነበር ብቅ ያለው ።

ያች ሰናይ የመስከረም 1 ቀን 1975 ቀዳሚት ሰንበት ለእስረኞቹ ርዕሰ እውደ ዓመት ብቻ አልነበረችም ፣ ዳግማዊ ልደት ፣ ዕለተ ትንሣኤም እንጂ ። ያችን ዕለት ቤተሰቦቻቸው እንደገና እንደተፈጠሩባት ፣ እነርሱ ደግሞ የነፃነት ትንሣኤ እንደአገኙባት ዕለት ነበር የቆጠሩዋት ። የዘመናት ጸሎት ፣ እኩቴት ፣ ስለት በእምላክ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ከግጎበረሰቡ ጋር የመቀላቀሉ ትልቅ ታምራት የተፈጸመባት ዕለት ነበረችና ።

የታላቁ ቤተ መንግሥት የፖለቲካ እስረኞችን ጨምሮ በዚያች ዕለት የተፈቱት 716 እስረኞች ነቡሩ ። ያ የጅምላ መፈታት እስረኞችም

ሆን ቤተሰቦቻቸው ፣ ኀብረተሰቡም ያልጠበቀው አፀብ ድንቅ የሚባል የፈጣሪ ሥራ ነበር ። በታላቁ ቤተ መንግሥት የዙፋን አዳራሽ ምድር ቤት ቁሻ ውስጥ ታስረው ለነበሩት የፖለቲካ እስረኞች በጊዜያዊ መታደራዊ መንግሥት ስም ባደረጉት ንግግር ፦

"ሁኔታው አሰቸጋሪ በነበረበት ወቅት አብዮታችን የሰፈውን ሕዝብ ጥቅም ለመጠበቅና ራሱንም ለመከላከል በልዩ ልዩ ምክንያትና ሁኔታ ሰዎችን በጥበቃ ስር ለማቆየት ተገዶ ነበር ። ሆኖም የሶሻሊስት አብዮት ዓላማ መበቀል ሳይሆን ወደትክክለኛ አቅጣጫ በመመለስ በአገር ግንባታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማብቃት ስለሆነ ፣ አብዮታችን አስተማማኝ የዕድገት ደረጃ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ጊዜ ተለቃችኋል" ሲሉ ነበር ሌ/ኩሎኔል ወልደ መስቀል ጉንጤ እስረኞቹ መፈታታቸውን ያስታወቁት ።

እስረኞች ነፃነታቸውን አግኝተው ከስብሰባው አዳራሽ ሲወጡ ቤተሰብ እልልታውን አቀለጠው ። ሁሉም ቤተሰቡን እየፈለገ ተሳሳመ። በዚያን ወቅት ነበር አምሐ ገብርኤል ሲወጣ ይጠባበቅ የነበረው ልጁ ኑርልኝ "ያው ሹሉ ጫማው ታየኝ" ያለው ፣ በብዙዎች መካከል ተንጠራርቶ ፊቱን ለማየት ባለመቻሉ እግር ሲመለከት ቀደም ብሎ ለአባቱ ሲላክለት ልብ ያለውን ጫማ በማየቱ የአባቱ ለመሆኑ እርግጠኛ ሁኖ ። ከዚያ በኋላ ሁሉም በየፊናው ተበታተነ ። አምሐ ገብርኤልም ወደ መኖሪያ ቤቱ ከመሄዱ በፊት ከቤተሰቡ ጋር ወደ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ለፈጣሪው ምሥጋና አቀረበ ።

የአምላክ ፈቃድ ሁኖ የታላቁ ቤተ መንግሥት የመጨረሻዎቹ የፖለቲካእስረኞች ተፈተው ከቤተሰባቸው ጋር ለመቀላቀል በቁ ። ፈጣሪ ይክበር ፣ ይመስገን ።

የዕድል ፈንታ ጉዳይ ሆኖ 55 እስረኞች ለዓመታት በእስራት ላይ ቆይተው ከታላቁ ቤተ መንግሥት ሲፈቱ በተሰጣቸው የምስክር ወረቀት ላይ የታሰሩበት ምክንያት በሚለው ርዕስ "አብዮቱን ያደናቅፋሉ ብሎ በመጠርጠር" ተብሎ ሲመለክት ፣ የተፈቱበት ሁኔታ በሚለው ርዕስ ደግሞ "በምሕረት" ተብሎ ተሞልቷል ። ይህ አባባል የተምታታ መሆኑ ግልጽ ነው ። ደርግ በጥርጣሬ ለዓመታት እስሮ ከእሲቃየ በኋላ ሲፈታ ያለአግባብ በማሠሩ ይቅርታ መጠየቅና በታሳሪው ውኑ በቤተሰቡ ላይ ላደረሰው ጉዳት ካሣ በመክፈል ፈንታ ምሬአለሁን

ምን አመጣው! መቼስ ደርግ ለፍትህ መጠበቅ ደንታ ስለሌለው የአድራጎቱ ውጤት አልገባው እንደሆን እንጂ በጥርጣሬ ሰውን ማሰሩ ራሱ ሕጋዊና ሰብዓዊም አልነበረም ።

ሌላው አሳዛኙ የደርግ ድርጊት በጥርጣሬ እስሮ ባለኘው ጊዜ የፈታቸው የፖለቲካ እስረኞችን ወንጀል መፈጸሙ እንደተረጋገጠበት ወንጀለኛ ከግዕከላዊ ወንጀል ምርመራ መሥሪያ ቤት ወስዶ እስር ጣታቸውን ጥቁር ቀለም በመቀባት አሻራቸውን ማስነሳቱ ነው ። በታሪክ ፊት እጁ አድፎ የሚታየው መክረኛው እስረኛ ሳይሆን ይህን የመሰለውን ድርጊት የፈጸመው ወገን መሆኑ አያጠያይቅም ።


ሰማዕስክ ተቁ ሁሉ፣

በማዕከር ሥር የደቀው ስለሚከተዩ ገለሰቦች የሚከተዩ የምስክር ወረቀት፣

1/ ሙሉ ስም ወይም ስም ወይም ስም ኤቶ ሳህሉ ፊንሰሉ ጉራፊን

2/ ሞኝ/ረስተ ሥ/ነገ ጋ/ሰ/ሰ ጊ/ሰ

3/ የመረስተ ሥ/ቤትና ደረጃ ጀኖሳይን ይሲናሰሳት ሳተላይ ጠበቃ ከተባለ ጠቅ

4/ የተፈጠተ ሥ/ ነገ ሰዲኒሲ ሰ/ቤት ነጋሪ

5/ የተፈጠተ ሥ/ ሁኔታ ሰዳዕከሪ

6/ ለሁነ የሚገኝበት ሥ/ቤት/ ጃ/ሳ ከፍተኛ 18

ተበለ 24 የቤት ቁጥር 209 የሰፈሰ ቁጥር 15 48 49

ማ ስ ታ ወ ሻ ፣ ፣

ወደ ሥራው/ሥ/ቤታቸው ወይም አለመሆኑን ንፃፍ ከናሱ ማለት የሚፈው = / ሰነ ባለው የሰውነ ደንብ መሠረት ሰወሰነ ተገቢው ማስረጃ ከተገኘ አገንዘባለን ።

የክሥስክ ማዕከ ዩዛግል
በተገሳኘነ አናሸገፈለት//

፲፱

የማይታወቅ የተሰወረ የለም

መልካም ምኞት የሚለዋወጡበት ወቅት ነው ። "እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ" የሚባልበት ። በእንዳንዶች ቤት ተጨማሪ መልካም ምኞትም እየተገለጸ ነው ። በመስከረም 1 ቀን 1975 ዓ·ም የተፈቱት እስረኞች "እንኳን ለቤታችሁ አበቃችሁ" እያሉ መልካም ምኞት ለሚያቀርቡላቸው "ሁሉ ለማይሳነው አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው" እያሉ ይመልሳሉ ። ቤተሰቦቻቸውም "እንኳን ደስ አላችሁ" ሲባሉ "እንኳን አብሮ ደስ አለን" በማለት በፍሥሕ ገጽታ ደስታቸውን ይገልጻሉ ። ተፈቺውና ቤተሰቡ በዚያች የድርብ ደስታ ሰሞን የሚተያየው በናፍቶት ፣ በሰቀቀን ፣ በመሳሳት ነበር ።

ለዚህ ዕድል ባልበቁት የሥራና የመከራ ጓደኞቻቸው ቤት ግን ተረስቶ የነበረው ሀዘን እንደገና ተቀስቅሷል ። ከፊሎቹ ያዘኑት የቤተሰባቸው አስተዳዳሪ የነበሩትን አባወራዎቻቸውን ደርግ በግፍ ስለገደለባቸው ሲሆን ፣ ከፊሎቹ ደግሞ የት እንዳደረሱዋቸው ስንኳ ሳያውቁ በመቅረታቸው ነበር ። የእጪቸውን መልሶ የማግኘት ተስፋ ባይኖራቸውም አፅማቸው የወደቀበትን ለማወቅ ፣ ከተጣለበት አውጥቶ በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ለመቅበር ባለመቻላቸው ሀዘናቸው እጥፍ ድርብ ሁኖ ነበር ። በይፋ ተላቅሶ እርም የማውጣት መብት ስንኳ ስለአልነበራቸው ሀዘኑ ከእንጀት የማይወጣ ሆኖባቸዋል ።

በደርግ በግፍ የተገደሉት የኢትዮጵያ ሰማዕታት አፅም የተጣለበትን ስፍራ በውል ማወቅ ሳይቻል ፣ ብርቱ ምሥጢር ሁኖ ለዘመናት ቆይቷል ። በቅዱስ መጽሐፍ "የማይገለጥ የተከደነ ፣ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለም" እንደተባለው ጊዜው ሲፈቅድ ግን የተሰወረው ተገለጠ ። የተደበቀው ይፋ ወጣ ። ለሰማዕታቱ አፅም ፍለጋ ሁኔታዎች ተመቻቹ ፣ ጠቋሚ ተገኘ ።

በ1967 ዓ·ም በህዳር 14 ቀን ምሽት በአዲስ አበባ ወሀኒ ቤት ቅጥር ግቢ በጥይት ተደብድበው የተገደሉት የቀድሞ ባለሥልጣኖች ፣ ጀኔራልና መስመራዊ መኰንኖች ፣ የበታች ሹማምንት ሬሳ በወሀኒ ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኘው ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሠራተኞች ምልክታ ለመሰመር ሲባል በዕለተ ሰንበት ሌሊት በባውዛ ብርሃን በእንድ ረግረግ ፣ ፍራ በወሀኒ ቤቱ እስረኞች የተቀበሩበት በጠቋሚ ታወቀ ። ጉድጓዱ ሲቆፈር የሚችቹ አፅም አንዱ በሌላው ላይ እንደተደራረበ ቀብረዋቸው ተገኘ ። ቁፋሮው በጥንቃቄ የተከናወነ ቢሆንም ኖራ አፍሰውባቸው ስለነበር ከአሥራ ሰባት ዓመታት በኋላ አፅሙ ሲወጣ እንደኛውን ከሌላው ለመለየት የሚያስችል ምልክት ለማግኘት አልተቻለም ። የጣት ቀለበታቸው ፣ የእንገት ሀብላቸው ወይም የእጅ ሰዓታቸው ከአፅሙ ጋር አልተገኘም ። በየካቲት 9 ቀን 1984 ዓ·ም ነበር የእነዚህ ሰማዕታት አፅም ከተጣለበት አልባሌ ስፍራ ወጥቶ በመንበረ ፅባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው ከቆየ በኋላ በሐምሌ 20 ቀን 1984 ዓ·ም በአፀደ ቤተ ክርስቲያኑ በተዘጋጀለት መካነ መቃብር በክብር ያረፈው ።

የ1967 ዓመተ ምሕረቱ የመቃብር ምሥጢር በዚህ አላበቃም ። በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች በ1967 ዓ·ም ግብቂያ ላይ ለማሳሳቺያ ጥቂት ጉድጓዶች ተቆፍረው ነበር ። ግን በየትኛው ጉድጓድ እንደተቀበረ የሚያውቁት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ ። ከነዚህም አንዱ የሬሳ ሳጥኑን እሸጌአለሁ ያለው የቤተ መንግሥቱ የጥገና መሐንዲስ አቶ ጥላሁን ኪዳኔ ነው ። በእርሱም ጠቋሚነት ከአሥራ ስድስት ዓመት በኋላ በታላቁ ቤተ መንግሥት ቀድሞ የንጉሠ ነገሥቱ በኋላ የደርግ ሊቀ መንበር ጽሕፈት ቤት ከነበረው ሕንፃ ስር አፅም ለማውጣት ቁፋሮ ተጀመረ ። የሁለት ቀን ቁፋሮ በዚሁ ስፍራ ተካሒዶ ምንም አፅም ሳይገኝ ቀረ ። ስለዚህ ትክክለኛውን ስፍራ የሚያመለክት ሌላ ጠቋሚ አስፈለገ ። በወቅቱ የታላቁ ቤተ መንግሥት የጥበቃ ኃላፊ የነበረው ሻምበል ስለሺ መኩሪያ ከአስር ቤት በእጀቢ ተወስዶ በአመለከተው ፣ ከፊተኛው እምብዛም በማይርቅ ስፍራ ቁፋሮው ቀጠለ ። አሁንም የተፈለገው አፅም አልተገኘም ። ምሥጢሩ በተላለ ባለመገለጹ በስፍ

ራው የተገኘው ቤተሰብ ፡ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጀግኖች ማኅበር ሹማምንት፣ እምባላደሮችና የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጠኞች ተሰፋ ከመቁረጥ ደረሱ ። ለመጨረሻ ሙከራ የደርግ ልዩ ብርጌድ ጦር አዛዥ የሆነው ብ/ጄኔራል ገረመው በቀለ ክእስር ቤት መጥቶ ትክክለኛውን ስፍራ እንዲያመለክት እንዲደረግ የሽግግር መንግሥቱ ተጠየቀ ። ጄኔራሉ በእጃቢ መጥቶ በአመለከተበት ፡ ቀደም ብሎ ሁለቱ ካሳዩበት ባልራቀ ስፍራ ሲቆፈር ምንም የሳጥን ቅሪት ላይኖር የተፈለገው አፅም ተገኘ ። በራስ ቅልና በፊት ቅርፅ ፣ እንደዚሁም በእግር ቅልጥም የግርግዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ነው ተብሎ የታመነ አፅም በታላቁ ቤተ መንግሥት ከሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጽሕፈት ቤት ጋር በተያያዘ ፣ ከልዩ ረዳቱ መሥሪያ ክፍል ስር ከርቀቱ የሽንት ፍሳሽ ከሚወርድበት ስፍራ ከጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ተቆፍሮ ወጣ ። ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት ላሉ ባሠሩት ፣ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚገኘው መካነ መቃብር በክብር እስኪያርፍ ድረስ አፅሙ ዕለቱኑ የካቲት 9 ቀን 1984 ዓ·ም በታዕካ ነገሥት በዓታ ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው እንዲቆይ ተደረገ ።

ሌላው ተጻፍኖ የቆየው ምሥጢር የፓትርያርኩ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና በ1971 ዓ·ም በሐምሌ ወር አብረዋቸው የተወሰዱት ፣ መገደላቸው በይፋ ያልተገለጸው ስምንት እስረኞች ጉዳይ ነው ። የእነዚህን ሰዎች መሞት ወይም በሕይወት መኖር ለማወቅ ቤተሰቦቻቸውና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የሰብዓዊ መብት አስከባሪ ድርጅቶች ለዘመናት ወትውተዋል ። የተጻፈን ምሥጢር ነበርና ሊገልጽላቸው የደፈረ ግን አልነበረም ። ከአሥራ ሦስት ዓመታት በኋላ ነበር ስለአሟሟታቸው ሁኔታ አቶ ቀነኒ አብሳ ፍንጭ የሰጡትና ድርጊቱ ሲፈጸም የነበረ ሌላ ሰውም የመቃብሩን ስፍራ ያመለከተው ።

የዓይን ምስክሮቹ እንደገለጹት 33 ሰዎች ነበሩ ደርግ ለገጸይነት ባሠለጠናቸው ኮማንዶዎች በተለያየ ጊዜ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ተገድለው በልውል ራስ አሥራተ ካሣ ማቢ ውስጥ የተጣሉት ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና ሌሎቹ እስረኞች ወደ ልውሉ መኖሪያ ቤት እየተወሰዱ በእንድ ክፍል ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ በሰዋራ ስፍራ የተደበቁ ኮማንዶች በገመድ እያነቁ እንደገደሉዋቸውና ሕይወታቸው

ሲያልፍ ሌሎች ሬሳቸውን ወስደው በአጥሩ ካብ ስር በእርድ መልክ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ወርውረው እንደ ጣሉዋቸውና ቀባሪዎች አፈር እንዳለበሱዋቸው ነበር በዓይን ምስክር የተረጋገጠው ። አጽም ለማውጣት በዚያን ስፍራ ቁፋሮ ተጀምሮ ከአራት ቀናት ያላሰለሰ ማፈላለግ በኋላ ነበር የብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ፓትርያርክ አፅም በሚያዝያ 23 ቀን 1984 ዓ·ም ተቆፍሮ ወጥቶ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው እንዲያርፍ የተደረገው ። በሐምሌ 3 ቀን 1984 ዓ·ም ደግሞ አፅሙ ወደ መንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ፍትሐተ ጸሎት ሲደረስበት አደረ ። በማኅሥቱ ከውጭ አገር ለበዓሉ የመጡ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ልዑካን ፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የልዩ ልዩ የሃይማኖት መሪዎችና ካህናት ፣ ብዙ ምዕመናንም በተገኙበት በአውደ ምሕረቱ በተደረገው ልዩ ሥነ ሥርዓት ላይ ነበር የቅዱስነታቸው ትሩፋትና ገድል የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተወካይ ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ በእደረጉት ንግግር ከተገለጸ በኋላ "ቴዎፍሎስ ቅዱስ ሰማዕት" ተብለው እንዲጠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ መወሰኑ የታወጀውና በሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኙት ሁሉ "ይደልዎ" በማለት መንፈሳዊ እወጃውን የተቀበሉት ። የቅዱስነታቸው አፅም ዕለቱኑ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ·ም በክብር ያረፈው በጉፋ ሰፈር ራሳቸው ባሳነጹት በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በእሥሩት መካነ መቃብር ነው ። እለቃ አያሌው ታምሩ ስለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ሲገልጹ ነበር፦

"ቅዱስነታቸው ምዕመናን ሊገለገሉበት ለኢትዮጵያ መጠበቂያ ጸሎት ፡ ምጽዋት ፡ መስዋዕት ሊቀርብበት ፡ እግዚአብሔር ሊመሰገንበት ለቅዱሳኑ በተፈቀደላቸው የእግዚአብሔር ፀጋ መሠረት በነቢዩ ኤልያስና በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ስም ይህን የመካነ ሕያዋን ቤተ ክርስቲያን አሠሩ" ያሉት ።

"ዛሬ ደግሞ ደሀርትን ከቀደምት ማስተካከል፣ ቀደምትን ከደሀርት ማስተባበር የሚቻለው አምላክ ስማቸውን ከቅዱሳኑ ስም ጋር አንድ አድርጎ መታሰቢያቸውን ከመታሰቢያቸው አዋህዶ አፅማቸው ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ፡ ስማቸው ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን እንዲጠራ አደረገ" በማለት ነበር ስለቅዱስነታቸው ብቃትም የመሰከሩት ።

ከታላቁ ቤተ መንግሥት በሐምሌ ወር 1971 ዓ·ም የተወሰዱት ሌሎች ስምንት እስረኞች አፅም ፍለጋ የቅዱስነታቸው አፅም በተገኘበት ስፍራ ተጠለ ፣ የሁሉንም አፅም ለማግኘት ቁፋሮው 35ቀን ፈጀ ። ተስፋ ባለመቁረጥ ቤተሰባቸው ባካሔደው ቁፋሮ ከቡር አፅማቸው ተገኘ። በእንጦጦ ገነት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አርፎ ከቆየ በኋላ ከደጃዝማች ሐረጎት አባይ በቀር የሌሎቹ* ከስድሳዎቹ ባለሥልጣናት አፅም ጋር በሐምሌ 20 ቀን 1984 ዓ·ም በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ አፀደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተዘጋጀው መካነ መቃብር እንዲያርፍ ተደረገ ። በቤተሰቡ ፍላጎት የደጃዝማች ሐረጎት አባይ አፅም ግን ወደ አሥመራ ተወስዶ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀብሮአል ።

የሞቱትን ነፍስ ይማርና በታላቁ ቤተ መንግሥት የታሰሩትን ፣ ከነዚሁም መካከል የሞቱትን ፣ ወደ ሌላ እስር ቤት የተዛወሩትንና የተፈቱትን እስረኞች ዝርዝር ከሚከተሉት ገጾች ይመለከቷል ።

---

* ከአራተኛ ክፍለ ጦር ተወስደው በዚሁ ስፍራ የተገደሉት የፌታውራሪ እንቁ ሥላሴ አጽም ጭምር ፣

፳

አዘክሮት

ይህ አንስተኛ መጽሐፍ በታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት በነበሩት የፖለቲካ እስረኞች ላይ የደረሰውን ሰቆቃ ፣ የመንፈስ ስቃይና የሕልፈተ ሕይወት ሁኔታ በሚገባና በተሟላ አኳኋን ለማስረዳት ለመቻሉ ደራሲው ሙሉ እምነት የለውም ። የዕለት ተዕለት ድርጊትን በማስታወሻ መያዝ ባለመቻሉ ምክንያት የእስር ቤቱን ሙሉ ታሪክ ለማቅረብ ሳይቻል ቢቀርም ፣ ለስምንት ዓመታት በጭንቀት ተወጥሮ የቆየው አእምሮ ለመዘከር በቻለው መጠን ለማቅረብ ተሞክሯል ።

ይህ የታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት የእስረኞች አበላ በእጭሩም ቢሆን የቀረበበት ዓላማ ያለፈው ሁኔታ ትምህርት ሁኖ አሁንም ሆነ ወደፊት እንደዚህ ያለው ሰቆቃ እንዳይደገም የሕሊና ግሳሰቢያ እንደሚሆን በማሰብ ነው ። ከሌሎች ስህተት ብልሆች ይማራሉና ከሥልጣን ኮርቻ ላይ የሚወጡ ሁሉ ያለሕግ እግባብ ሕልፈተ ሕይወት እንዳይደርስ ፣ ሰብዓዊ መብት እንዳይገሰስ ፣ የዜጋ ስብዕና እንዳይደፈር ፣ ቤተሰብም እንዳይፈታ በማድረግ የሕግን ልዕልና በምድረ ኢትዮጵያ የማስፈን ግዴታ እንዳለበት መዘከር ይኖርበታል ።

1 በጥቅምት 1967 ዓ.ም ከአራተኛ ክፍለ ጦር ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት የተዛወሩ እስረኞች ዝርዝር

ተ.ቁ	ስም	በመጨረሻ የነበራቸው የሥራ መደብ	የታሰሩበት
1	ሬር አድሚራል		
	አስክንድር ደሴታ	የባሕር ኃይል ጠቅላይ አዛዥ	2/1/1967
2	ፅሐፊ ትእዛዝ		
	አክሊሉ ሀብተ ወልድ	ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር	18/8/1966
*3	ሌ/ጄኔራል አዚዮ አበበ	የአገር መከላከያ ሚኒስትር	9/11/1966
4	ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ	የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት	23/10/1966
5	ራስ መስፍን ስለሺ	የጀኖ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	5/11/1966
*6	ልጅ እንዳልካቸው መኩንን	ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽሕፈት ሚኒስትር	24/11/66
7	ጸሐፊ ትእዛዝ		
	ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ	የዘውድ ምክር ቤት አባል	19/8/1996
8	አቶ ይልማ ደሬሳ	የዘውድ ምክር ቤት አባል	22/10/1966
9	አቶ አበበ ረታ	የዘውድ ምክር ቤት አባል	25/11/66
10	አቶ ጌታሁን ተሰማ	የአገር ግዛት ሚኒስትር	18/8/1966
11	አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ	የፍርድ ሚኒስትር	18/8/1966
12	ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል	የዘውድ ምክር ቤት አባል	24/10/1966
13	አቶ አማኑኤል አብርሃም	የግዕድን ሚኒስትር	22/8/1966
14	ደጃዝማች ክፍሌ እርገፅ	አስቀድሞ የአገር ግዛት ሚ/ር ሚኒስትር ዶሌታ በኋላ በሙሪታኒያ የነበሩ	18/8/1966
15	ቢትወደድ ፀሙዬ ንብረ ሕይወት	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት	24/10/1966
16	ደጃዝማች ክፍሌ ጻፂ	የዘውድ ምክር ቤት አባል	1/11/1966
17	ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ	የዘውድ ምክር ቤት አባል	1/11/1966
18	ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት	የዘውድ ምክር ቤት አባል	26/11/1966
19	ቢትወደድ አስፍሐ ወልደ ሚካኤል	የዘውድ ምክር ቤት አባል	2/13/1966
20	ሌ/ጄኔራል ከበደ ንብረ	የአገር መከላከያ ሚኒስትር	18/8/1966
21	አቶ ምናሴ ለማ	የብሔራዊ ባንክ ገዥ	19/8/1966
22	አቶ ማሞ ታደሰ	የንገዘብ ሚኒስትር	18/8/1966
23	አቶ ክተማ ይፍሩ	የገግድ ፣ ኢንዱስትሪና ቅሪዝም ሚኒስትር	18/8/1966

* ከለውጡ በኋላ

24	አቶ ታደሰ ያዕቆብ	በሚኒስትር ማዕረግ የመንግሥት ሠራተኛ ማስተዳዳሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የሙሪታ ንባኤ የበላይ ኮሚሽነር	18/8/1966
25	አቶ ሠይፉ ማኅተመ ሥላሴ	የትምህርትና ሥነ ተበብ ሚኒስትር	18/8/1966
26	ፊታውራሪ አበበ ንብረ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	28/10/1966
27	ዶክተር ምናሴ ኃይሉ	የውጭ ንዳይ ሚኒስትር	20/10/1966
28	ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ	የእዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ	18/8/1966
29	ንዑረ ፅድ ጂሚፕሮስ ንብረ ማርያም	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ም/ፕሬዚዳንት	3/13/1966
30 *	ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም	የእርሻ ሚኒስትር	1/11/1966
31	አቶ ክተማ አበበ	የሕዝብ ጤና ተበታ ሚኒስትር	18/8/1966
32	አቶ ግሰሀ ሒኒት	የሥራና የውፃ ልማት ሚኒስትር	18/8/1966
33	አቶ በላይ አባይ	የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስትር	18/8/1966
34	አቶ ሙላቱ ደበበ	የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና የመራተኛ ንዳይ ሚኒስትር	18/8/1966
35	ዶክተር ሥዩም ሐረጉት	በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ሚኒስትር	18/8/1966
36	ሌ/ጄኔራል አሰፋ አየነ	የመጓናኛና ትራንስፖርት ሚኒስትር	23/8/1966
37	ሌ/ጄኔራል ኢሳያስ ንብረ ሥላሴ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	3/11/1966
*38	ደጃዝማች ተሰፋ ዮሐንስ በረሌ	የማዕድን ሚኒስትር	18/12/1966
39	ሌ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለ	የምድር ጦር ጠቅላይ አዛዥ	18/8/1966
40	ሌ/ጄኔራል በለጠ አበበ	የብሔራዊ ጦር ኤታማዦር ሹም	12/12/66
41	ሌ/ጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም	የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	29/11/1966
42	ሌ/ጄኔራል ኃይሉ ባይከሳኝ	የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም	18/8/1966
43	ሌ/ጄኔራል አበበ ንጦሳ	አስቀድሞ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ	19/8/1966
44	ሌ/ጄኔራል ይልማ ጂበሂ	የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ	18/8/1966
45	ሌ/ጄኔራል አሰፋ ደምሴ	ዋና የአልፍኝ አስከልካይ	13/12/1966
46	ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	25/10/1966
47	ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ	የጉሙ ጉፋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	18/11/1966
48	ደጃዝማች ግሀሉ ድፋዬ	የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	5/11/1966
49	ደጃዝማች ወርቁ እንቶ ሥላሴ	የኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	5/11/1966
50	ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃ	ተደም ብሉ የወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	18/8/1966
51	ደጃዝማች ልነሙ በዙ	የወሎ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ	24/10/1966
52	ደጃዝማች ሐረጉት አባይ	የአሥመራ ክተማ ከንቲባ	5/12/1966
53	ንዑረ ፅድ ኦርዎያስ ከበደ	የቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ	22/10/1966
54	ንዑረ ፅድ ንብረ ሥላሴ ፊልፆ	የአክሱም ንዑረ ፅድ	18/1/1967

* ከለውጡ በኋላ

55	ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ	የመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ገዳም አስተዳዳሪ	23/10/1966
56	አፈ ንጉሥ አበጀ ደባልቅ	የዙፋን ችሎት የፍርድ አጣሪ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት	2/11/1966
57	ኰሎኔል ሰሎሞን ከድር	በአገር ግዛት ሚ/ር የሕዝብ ፀጥታ ተበቃ ሚኒስትር ደኤታ	1/11/1966
58	ብላታ አድማሱ ረታ	በግቢ ሚ/ር ሚኒስትር ደኤታ	7/11/1966
59	አቶ ዮሐንስ ኪዳነ ማርያም	በጽሕፈት ሚ/ር ሚኒስትር ደኤታ	29/12/1966
60	ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ወልድ ሥላሴ	በግቢ ሚ/ር ሚኒስትር ደኤታ	18/12/1966
61	አቶ መክብብ ዳምጤ	በመገናኛ ሚ/ር ሚኒስትር ደኤታ	5/11/1966
62	አቶ እሸቴ መኩንን	በሕዝብ ጤና ተበቃ ሚ/ር ሚኒስትር ደኤታ	5/11/1966
63	አቶ አብተው ገብረ ኢየሱስ	በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ሚኒስትር ደኤታ	28/1/1967
64	አቶ አበራ ጀምበሬ (አምሐ ገብርኤል)	በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ሚኒስትር ደኤታ	27/1/1967
65	አቶ ሀብተ ሥላሴ ታፈሰ	በሚኒስትር ደኤታ ማዕረግ የቀሪስት ኮሚሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ	1/11/1966
66	አቶ አሰፋ ደምሴ	የአርዳና ኢንዱስትሪ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ	1/11/1966
67	አቶ ጉርፉ ገብረ መድህን	ዋና ኦዲተር	28/11/1966
68	ደጃዝማች ከበደ አሊ ወሌ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	5/12/1966
69	ሜ/ጀኔራል አበራ ወልደ ማርያም	በአገር መከላከያ ሚ/ር ዋና ኢንስፔክተር	25/11/1966
70	ሜ/ጀኔራል ሥዩም ገድለ ጊዮርጊስ	የሁለተኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ	26/11/1966
71	ሜ/ጀኔራል ታደሰ መልኬ	የአራተኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ	15/11/1966
72	ሜ/ጀኔራል ታፈሰ ለማ	የአንደኛ ክፍለ ጦር (የክቡር ዘበኛ) ዋና አዛዥ	12/11/1966
73	ሜ/ጀኔራል ግርማ ሙላት	የፈናንስ ፖሊስ ዋና አዛዥ	13/11/1966
74	ሜ/ጀኔራል ጽጌ ገዝሙ	በአገር መከላከያ ሜ/ር አማካሪ	1/11/1966
75	ሜ/ጀኔራል ጋሻው ከበደ	የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ዋና አዛዥ	5/12/1966
76	ሜ/ጀኔራል አበበ ወልደ ሥላሴ	የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ዋና አዛዥ	29/12/1966
77	ሜ/ጀኔራል ቀልቤላ ቤካ	የሸዋ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ዋና አዛዥ	14/11/1966
78	አቶ ኃይሉ ሰብስቤ	የአዲስ አበባ ከተማ ም/ከንቲባ	4/11/1966
79	አቶ ነቢየ ልዑል ክፍሌ	በግርማዊነታቸው ልዩ ካቢኔ ም/ሚኒስትር	1/11/1966

80	አቶ መርዕድ መንገሻ	በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ም/ሚኒስትር	4/13/1966
81	አቶ ሰሎሞን ገብረ ማርያም	በጽሕፈት ሚ/ር ም/ሚኒስትር	4/11/1966
82	አቶ አሰፋ ድፋቶ	በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ የአዋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ	23/9/1966
83	አቶ ሀብቱ እሸቴ	በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ እስታስቲክ ጽ/ቤት ሹም	1/11/1966
84	አቶ ንጉሤ ሀብተ ወልድ	በማስታወቂያ ሚ/ር ም/ሚኒስትር	1/11/1966
85	አቶ ተገኝ የተሻ ወርቅ	በማስታወቂያ ሚ/ር ም/ሚኒስትር	1/11/1966
86	አቶ አሸናፊ ሽፈራው	በገንዘብ ሚ/ር ም/ሚኒስትር	14/11/1966
87	አቶ ወርቁ መካሻ	በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ የወተት ሀብት ልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ	25/11/1966
88	የመቶ አለቃ ሚካኤል አመዴ	በሕዝባዊ ኑር ዕድገትና ሠራተኛ ጉዳይ ሚ/ር ም/ሚኒስትር	28/1/1967
89	አቶ አባሻውል ወልደ ማርያም	የአውራ ጉዳና ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ	23/10/1966
90	አቶ በትሩ አድማሴ	የቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድ ዋና ሥራ አስኪያጅ	23/10/1966
91	አቶ አበበ ከበደ	የቀ·ኃ·ሥ· በጉ አድራጉት ድርጅት ዋና አስተዳዳሪ	22/10/1966
92	አቶ አስናቀ ጌታቸው	የቡና ቦርድ ዋና ሥራ አስኪያጅ	5/2/1967
93	አቶ አክሊሉ ቤተ ማርያም	የአህል ቦርድ ዋና ሥራ አስኪያጅ	25/11/1966
94	አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ	የብሔራዊ ሀብት ልማት አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ	7/11/1966
95	አቶ መኩሪያ ወርቁ	የጡረታ ጉባኤ ኮሚሽነር	26/11/1966
96	ፊታውራሪ ከበደ ደስታ	የቤጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ም/አንደራሴ	6/11/1966
97	ፊታውራሪ አላሚን እንድሪስ	የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ም/አንደራሴ	12/12/1966
98	ፊታውራሪ አምዴ አበራ	ቀድሞ አውራጃ ገዥ በኋላ በግል ሥራ የተሰማሩ	11/12/1966
99	ብ/ጀኔራል ሳሙኤል በየነ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	26/10/1966
100	ብ/ጀኔራል ግርማ መንግሥቱ	በፖሊስ ሠራዊት የአስተዳደርና የችምህርት ረዳት ጠቅላይ አዛዥ	20/12/1966
101	ብ/ጀኔራል ዓለማየሁ ደግፌ	በፖሊስ ሠራዊት የንብረት ረዳት ጠቅላይ አዛዥ	4/11/1966
102	ብ/ጀኔራል ሌንጫ መለስ	በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት የኦፔሬሽን አማካሪ	5/11/1966

103	ብ/ጀኔራል ግርማ ፈለቀ	የፖስተኛ ክፍለ ጦር ም/አዛዥ	12/11/1966
104	ብ/ጀኔራል ሙላቱ ታምሩ	የአራተኛ ክፍለ ጦር ም/አዛዥ	12/11/1966
105	ብ/ጀኔራል ታፈሰ አበበ	የምድር ጦር ስንቅና ትጥቅ ማደራጃ መምሪያ አዛዥ	12/11/1966
106	ብ/ጀኔራል ግርማ ዮሐንስ	የፖሊስ ሠራዊት የወንጀል መከላከልና ምርመራ ረዳት ጠቅላይ አዛዥ	4/11/1966
107	ብ/ጀኔራል ሙሉጌታ ወልደ ዮሐንስ	የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አዛዥ	5/11/1966
108	ብ/ጀኔራልመስፍን አምባዬ	የባሌ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ዋና አዛዥ	1/11/1966
109	ብ/ጀኔራል ወንድሙ አበበ	የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ዋና አዛዥ	2/11/1966
110	ብ/ጀኔራል ሉሉ እንግሪዳ	የቤተ መንግሥት የተሽከርካሪና ሠረገላ ክፍል አዛዥ	26/1/1967
111	ልጅ ኃይሉ ደስታ	በአገር መከላከያ ሚ/ር ረዳት ሚኒስትር	1/11/1966
112	ኩሎኔል ከበደ እሸቴ	በአገር መከላከያ ሚ/ር ረዳት ሚኒስትር	30/10/1966
113	አቶ አባተ መንግሥቴ	በአገር መከላከያ ሚ/ር ረዳት ሚኒስትር	5/11/1966
114	አቶ አምደ ሥላሴ ጀምበሬ	በትምህርትና ሥነ ተበብ ሚ ር ረዳት ሚኒስትር	1/13/1966
115	አቶ አበበ ወንድሜነህ	የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት	28/1/1967
116	ጃንጥራር ሙሉጌታ ገብረ እግዚአብሔር	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	28/1/1967
117	ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ	የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል	23/10/1966
118	አቶ ዘውዴ በዳዳ	የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል	28/1/1967
119	አቶ ሲሜንሶ ዴንጋ	የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል	23/11/1967
120	አቶ መድኃኔ ዮሴፍ	የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ረዳት አንደራሴ	12/12/1966
121	ፊታውራሪ ኃይሉ ቪበቪ	የከፋ ጠቅላይ ግዛት ረዳት አንደራሴ	24/11/1966
122	ቀኛዝማች ይልማ አቦዬ	በእልፍኝ አስከልካይ ጽ/ቤት የአቤቱታ ክፍል ሹም	29/10/1966
123	ዶክተር አያሌው አሳዬ	በአገር መከላከያ ሚ ር የመምሪያ ኃላፊ	4/11/1966
124	ዶክተር እሸቱ ሙሌ	በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር	28/1/1967
125	አቶ ሳሙኤል ዓለማየሁ	በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የፖለቲካ ክፍል ሹም	28/1/1967

126	ፊታውራሪ ደምስ አላምረው	በከፋ ጠቅላይ ግዛት የአውራጃ ገዥ	24/11/1966
127	ቀኛዝማች አመኑ ገብረ ሐና	የግርማዊነታቸው ልዩ ግምጃ ቤት ም/ሹም	4/1/1967
128	አቶ ሠይፈ ሥላሴ ሊበን	የልዑል መኰንን ንብረት አስተዳዳሪ	20/11/1966
129	ኩሎኔል ግሰው ሞጀ	የከብር ዘበኛ መኰንን (አንጋች)	21/11/1966
130	ኩሎኔል ዓለም ዘውድ ተሰማ	የአየር ወለድ ሻለቃ ጦር አዛዥ	24/1/1966
131	ሌ/ኩሎኔል አደላ ቅጣው	የከብር ዘበኛ መኰንን	1/2/1967
132	ሌ/ኩሎኔል ይገዙ ዘለቀ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	29/12/1966
133	ሌ/ኩሎኔል ጉሌ ዘውዱ	በወህኒ ቤቶች የአስረኞች አስተዳደር ሹም	28/1/1967
134	ሌ/ኩሎኔል ማሩ ኃረድ	የከብር ዘበኛ መኰንን (ሊጋባ ጽ/ቤት)	28/1/1967
135	ሌ/ኩሎኔል እምሩ ወንዴ	የቀድሞ የከብር ዘበኛ መኰንን በግል ሥራ የተሰማሩ	28/1/1967
136	ቀኛዝማች ገብረ ክርስቶስ መኰንን	የደብረ ዘይት ወረዳ ገዥ	19/12/1966
137	ግራዝማች ሰሎሞን መብራቴ *	የጅማ ማዘጋጃ ቤት ሹም	19/11/1966
138	አቶ ታደሰ ወልደ ኪዳን	በቀ.ኃ.ሥ. በጉ አድራጉት ድርጅት የክፍል ሹም	1/11/1966
139	አቶ ገብረ ጻድቅ ኃይሉ ማርያም	በቀ.ኃ.ሥ. በጉ አድራጉት ድርጅት የቅርንጫፍ ኃላፊ	30/11/1966
140	ሻለቃ ተፈራ ተከለ አብ	የጦር ሠራዊት መኰንን	10/12/1966
141	ሻለቃ ብርሃኑ ሜጫ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	1/11/1966
142	ሻምበል ደምሴ ሽፈራው	የከብር ዘበኛ ንዑስ ደርግ ሰብሳቢ	1/2/1967
143	አቶ ሽፈራው ቁፋ	በግል የሚተዳደሩ	29/12/1966
144	ባላምባራስ ዘርፉ ዳምጤ	በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት የወረዳ ገዥ	1/13/1966
145	ባላምባራስ ወርቁ ደስታ **	በሲዳሞ ነጋዴ	29/12/1966
146	አቶ መለስ መኰንን	የወህኒ ቤት አስተዳደር ባልደረባ	5/11/1966

* ጅማ ተወስደው የተሰቀሉ ።

** ሲዳሞ ተወስደው የተሰቀሉ ።





2. ከህዳር መጀመሪያ 1967 እስከ 1974 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በተለያየ ጊዜ በተጨማሪ የታሰሩ ሰዎች ዝርዝር

ቁ.ቁ	ስም	በመጨረሻ የነበራቸው የሥ መደብ	የታሠሩበት ቀን
1	ክቡዕ ወቅዱስ አቡነ ቄምፍሎስ	ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ	9 6 1968
2	ብፁዕ አቡነ ሉቃስ	የአሩሲ ሊቀ ጳጳስ	10 8 1969
3	ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ	የፓትርያርኩ እንደራሴ	9 6 1966
4	ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ	አዲስ የተሾሙ ጳጳስ	9 6 1966
5	ልዑል ወሰን ሰገድ መኰንን	የሐረር መስፍን	16 9 1967
6	ልዑል ሚካኤል መኰንን	የልዑል መኰንን ልጅ	16 9 1967
7	ልዑል በእደ ማርያም መኰንን	የልዑል መኰንን ልጅ (ተማሪ)	16 9 1967
8	አቶ በለጠ ገብረ ጻዲቅ	የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስትር	10 3 1967
9	አቶ ጌታቸው በቀለ	የሥራ ፣ የማዕድንና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስትር	10 3 1967
10	ብ ጀኔራል መኰንን ደነቀ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	6 3 1968
11	አቶ አሐዱ ባቡሬ	የሐረር ክፍለ ዘገር ዋና አስተዳዳሪ	17 12 1967
12	አቶ ተሾመ ገብረ ማርያም	የማዕድን ሚ ር ሚኒስትር ደኤታ	13 3 1967
13	አቶ ፋንታዬ ወልደ ዮሐንስ	በገንዘብ ሚ ር ሚኒስትር ደኤታ	10 10 1967
14	አቶ ታደሰ ዋገሴ	በንግድ ኢንዱስትሪና ቁሬዝም ሚ ር ሚኒስትር ደኤታ	28 5 1967
15	አቶ ሜንያለው ተሾመ	በሜክሲኮ የኢትዮጵያ አምባሳደ	28 9 1967
16	አቶ አብርሃም ወርቅነህ	በመገናኛ ሚ ር ም ሚኒስትር	10 10 1967
17	አቶ ተስፋዬ ታደሰ	የማስታወቂያ ሚ ር ቋሚ ተ[illegible]	26 5 69
18	አቶ ተፈራ ሻውል	በውጭ ጉዳይ ሚ ር የመም ያ ኃላፊ	26 5 69
19	ደጃዝማች ዝናህብዙ መሳይ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	4 7 1968
20	ደጃዝማች አያሌው መንገሻ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	1 7 1968
21	ደጃዝማች ታደሰ አየለ	በጉጂም ጠቅላይ ግዛት ረአውራጃ ገዥ	23 3 1967
22	ብ ጀኔራል ሻውል ዘለቀ	የፖሊስ ሠራዊት ረዳት ጠቅላይ አዛዥ	7 11 1967
23	ብ ጀኔራል ዳንኤል መንግሥቴ	በግርማዊነታቸው ልዩ ካቢኔ የመምሪያ ኃላፊ	2 7 1969
24	ብ ጀኔራል ጌታቸው ዘ ወልድ	የገሙ ጉፋ ጠ ግዛት ፖ ዋ አዛዥ	2 11 1966
25	ብ ጀኔራል ደምመላሽ ተገኘ	አስቀድሞ የፖ ሠራዊት መኰንን በኋላ በጡረታ ላይ የነበሩ	7 11 1967
26	ብ ጀኔራል ታደሰ ብሩ *	በጡረታ ላይ የነበሩ	3 7 1967
27	ዋግሹም ጌታዑን አድማሱ	አስቀድሞ የአውራጃ ገዥ በኋላ በጡረታ ላይ የነበሩ	1 6 1968

* በፍርድ የተገደሉ

28	ቀኛዝማች ኃይሉ መሳይ	የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል	20 6 1966
29	አቶ አስፋ በሱ ፈቃድ	ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚ ር የመምሪያ ኃላፊ	23 9 1968
30	ደጃዝማች ይልማ ጂበጂ *	በጡረታ ላይ የነበሩ	17 10 1967
31	ፈታውራሪ ማሞ በጀ	በቤጌምድርና ሰሜን ጠ ግ አ ገዥ	29 6 1967
32	ፈታውራሪ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋርያት	የልዕልት ተናኘ ወርቅ ገብረት አስተዳዳሪ	10 3 1967
33	ቀኛዝማች ኃይሌ ሮባ	በአዲስ አበባ ከተማ የክፍል ማዘጋጃ ቤትሹም	1 7 1968
34	ኩሎኔል እንጋጋው ኃይሌ	የክብር ዘበኛ መኰንን	30 6 1968
35	ኩሎኔል ዘጋዬ መሸሻ	የአየር ኃይል መኰንን	27 9 1967
36	ኩሎኔል አሰፋ እሸቴ	የአየር ኃይል መኰንን	27 9 1967
37	ኩሎኔል ታደሰ ተሊላ	የአየር ኃይል መኰንን	27 9 1967
38	ኩሎኔል ወልደ ሥላሴ ካሳ	የአየር ኃይል መኰንን	22 6 1967
39	ሌ ኩሎኔል ዋቂ በቀለ	በጡረታ ላይ የነበሩ	4 7 1968
40	ኩሎኔል ተድላ ደስታ	የፖሊስ ሠራዊት መገናኛ ኃላፊ	7 11 1967
41	ኩሎኔል እንግዳ ጥላሁን	የፖሊስ ሠራዊት	7 11 1967
42	ኩሎኔል ማንያዘዋል ዳኜ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	10 11 1967
43	ኩሎኔል ኃይሉ ደገፈ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	7 11 1967
44	ኩሎኔል መሸሻ ወልደ ጻዲቅ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	17 11 67
45	ሌ ኩ እምሩ ወንዴ	ቀድሞ የክብር ዘበኛ መኰንን በኋላ በጡረታ ላይ የነበሩ	28 1 1968
46	ሌ ኩሎኔል ኃይሉ ረጋሳ *	የልዩ ወር ፍርድ ቤት ዳኛ	3 7 1967
47	ባላምበራስ ጀቤሳ ኢጀታ	የአውራጃ ፍ ቤት ዳኛ	30 7 1968
48	ሻለቃ ለሜሳ ሔይ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	7 11 1967
48	ሻለቃ ከበደ ደሳለኝ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	8 11 1967
50	ሻለቃ አሰፋ በላይ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	8 11 1967
51	ሻለቃ አሰፋ በቀለ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	7 11 1967
52	ሻለቃ ከፍያለው አድገህ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	8 11 1967
53	ሻለቃ ንጉሤ ረታ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	12 11 1967
54	ሻለቃ ከፈላ ኃይለ ሚካኤል	የአየር ኃይል መኰንን	22 6 1967
55	ሻምበል ጌታቸው መንግሥቴ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	8 11 1967
56	ሻምበል ፍቅሬ መኰንን	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	9 11 1967
57	ሻምበል መንግሥተ አብ ባሕሩ	የፖሊስ ሠራዊት መኰንን	26 5 69

* በፍርድ የተገደሉ

58	ኻምበል አጥናፉ መኩንን	የብሔራዊ ቁአትር ዋና ሥራ አስኪያጅ	6 6 1967
59	አቶ አሰፋ ወልደ ጊዮርጊስ	የሥጋ በርጅ ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ	28 5 1967
60	አቶ ጌታቸው ሀብተሥላሴ	የአዞል ቦርድ ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ	27 5 1967
61	አቶ ሙሉጌታ አሥራት	የማስታወቂያ ሚ ር ባልደረባ	16 9 1967
62	መጣት ይሙጹ አሥራት	የልውል አሥራቱ ካሳ ልጅ (ተማሪ)	16 9 1967
63	ወጣት የወንድ መሰን አሥራት	የልውል ራስ አሥራቱ ካሳ ልጅ (ተማሪ)	16 9 1967
64	ቀኛዝማች ጉልላት ወልደ ፅዮሐንስ	በአዲስ አበባ ኒጋዴ	4 7 1968
65	አቶ አባተ ወልዴ	በአዲስ አበባ ኒጋዴ	12 7 1968
66	አቶ ታደሰ ሚጫ	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የክፍል ኃላፊ	7 7 1968
67	አቶ አሰፋ ደስታ	በአዲስ አበባ ኒጋዴ	5 7 1968
68	አቶ ሠይፉ የተሻወርቅ	የአውራ ጉዳና ባለሥልጣን ባልደረባ	8 7 1968
69	አቶ ደበበ አጅናፍር	በንግድና ኢንዱስትሪ ሚ ር የሞጋ ቀናት ኮሚቴ ሰብሳቢ	28 5 1967
70	አቶ ሙድነህ ታደሰ	የእዞል ማህበር ሥራ አስኪያጅ	27 5 1967
71	አቶ ለገሠ ገብረሐና	የማኅበራዊና ሠራተኛ ጉዳይ ሚ ር ባልደረባ	26 5 69
72	አቶ አባተ ተፈራ	የማኅበራዊና ሠራተኛ ጉዳይ ሚ ር ባልደረባ	23 9 1968
73	አቶ ገመቹ ወልደ ሚካኤል	የናርድ አስፈጻሚ ጽ ቤት ባልደረባ	1 7 1968
74	አቶ አስፋው መኩንን	የሠራተኛ ድርጅት መሪ	23 9 1968
75	አቶ ያረጋል ደምሰ	የሠራተኛ ድርጅት መሪ	23 9 1968
76	ም ሙቶ አለታ መሰሰ ኒጋቱ	የፖሊስ ሠራዊት መኩንን	8 11 1967
77	ም ሙቶ አሰቻ ኃይሉ አጥናፈ	የፖሊስ ሠራዊት ኒጋቱ	9 11 1967
78	ኻሰቱ ባሻ መዝሙር ይሙኑ	የፖሊስ ሠራዊት አባል	10 11 1967
79	መታደር ኃይሉ እሸቱ	የጦር ሠራዊት አባል	30 5 1969
80	ግራዝማች ደባሱ ብየነ	በሲዳሞ የሕዝብ ፀ ጥበቃ ኣረተኛ	27 6 1967
81	አቶ ብርሃኑ ዘጊዮርጊስ	አስቀድሞ አድአ የገበሬ ማኅበር አባል ሆነበሩ በኋላ ወዘአደር	30 9 1969
82	አቶ ግርማ ፈሰቀ	የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ	17 6 1969
83	አቶ ጥላሁን ይትባረክ	የአየር ኃይል ባልደረባ (ጸሐፊ)	27 9 1967
84	አቶ ተድላ ፋንታየ	የሠራተኛ ማኅበር አባል	23 9 1968

85	አቶ ግርማ ጭብሳ	የድሬ ዳዋ ተ ፋብሪካ ሠራተኛ	30 5 1969
86	የመቶ አለቃ ታምራት ወልደ ማርያም	የሕዝባዊ ድርጅት ባልደረባ	26 5 69
87	ወጣት የማይን እሸት ተፈራ	የብ ጄኔራል ተፈራ በንቲ ልጅ	26 5 69
88	ከብ ጄኔራል ታደሰ ብሩ ጋር የተያዙ አምስት አስረኞች		3 7 1967
89	ስማቸው ያልታወቀ ሁለት መምህራን		
90	ስማቸው ያልታወቀ አምስት ተማሪዎች		
91	አንድ የሳምሶን ጓዮ ቤት ሠራተኛ		

3/ በሀዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም በግፍ የተገደሉ አስረኞች ዝርዝር

ሀ/ ከታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት

1/ ሬር አድሚራል አስክንድር ደስታ
2/ ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ
3/ ሌ/ ጄኔራል አቢይ አበበ
4 ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ
5/ ራስ መስፍን ስለሺ
6/ ልጅ እንዳልካቸው መኰንን
7/ አቶ አበበ ረታ
8/ አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ
9/ ደጃዝማች ከፍሌ እርገቱ
10/ ሌ/ ኰሎኔል ታምራት ይገዙ
11/ ሌ/ ጄኔራል ከበደ ገብሬ
12/ ሌ/ ጄኔራል አሰፋ አየነ
13/ አቶ ሙላቱ ደበበ
14/ ሌ/ ጄኔራል ድረሴ ጹባለ
15/ ሌ/ ጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም
16/ ሌ/ ጄኔራል አሰፋ ደምሴ
17/ ሌ/ ጄኔራል አበበ ገመዳ
18/ ሌ/ ጄኔራል ይልማ ሽበሺ
19/ ሌ/ ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ
20/ ሌ/ ጄኔራል በለጠ አበበ
21/ ደጃዝማች ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል
22/ ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ
23/ ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃ
24/ ደጃዝማች ማህሉ ድፋዬ
25/ ደጃዝማች ወርቁ እንቆ ሥላሴ
26 ደጃዝማች ለገሠ በዙ
27 አፈ ንጉሥ አበጀ ደባልቅ
28 ኰሎኔል ሰሎሞን ከድር

29/ ብላታ አድማሱ ረታ
30/ ደጃዝማች ከበደ አሊ ወሌ
31/ አቶ ነቢየ ልዑል ከፍሌ
32/ አቶ ሰሎሞን ገብረ ማርያም
33/ አቶ ተገኘ የተሻወርቅ
34/ ሜ/ጄኔራል ጋሻው ከበደ
35/ ሜ/ጄኔራል ሥዩም ገድለ ጊዮርጊስ
36/ ሜ/ ጄኔራል ታፈሰ ለማ
37/ ልጅ ኃይሉ ደስታ
38/ ፊታውራሪ አምዴ አበራ
39/ ፊታውራሪ ደምስ አላምረው
40 ቀኛዝማች ይልማ አቦዬ
41/ ብ/ጄኔራል ግርማ ዮሐንስ
42/ ብ/ጄኔራል ወንድሙ አበበ
43 ብ/ ጄኔራል ሙሉጌታ ወልደ ዮሐንስ
44/ ኰሎኔል የዓለም ዘውድ ተሰማ
45/ ኰሎኔል ጣሰው ሞጄ
46/ ሻለቃ ብርሃኑ ሚጫ
47/ ሻምበል ደምሴ ሽፈራው

ለ/ ከሆስፒታል

1/ ሌ/ጄኔራል ኢሳያስ ገብረ ሥላሴ
2/ ዶክተር ተስፋዬ ገብረ እግዚዕ

ሐ/ ከልዩ ልዩ ስፍራ

1/ ሌ/ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም
2/ ኰሎኔል ይገዙ ይመኔ
3/ ፊታውራሪ ታደሰ እንቆ ሥላሴ
4/ አቶ ኃይሉ ተክሉ
5/ ሻምበል በላይ ፀጋዬ
6/ ሻምበል ወልደ ዮሐንስ ዘርጋው
7/ ሻምበል ሞላ ዋከኔ
8/ የመቶ አለቃ ተስፋዬ ተክሉ
9/ ጁኔየር ኢክማን ዮሐንስ ፍትዊ
10/ ም/ አስር አለቃ ተክሉ ኃይሉ
11/ ወታደር በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ

8· ከጥር 1967 እስከ 1974 ዓ·ም መጨረሻ ከታላቁ ቤተ መንግሥት አስር ቤት በየጊዜው የተፈቱ አስረኞች ዝርዝር

1· ብፁዕ አቡነ ሉቃስ
2· አቶ ጌታሁን ተሰማ
3· አቶ አማኑኤል አብርሃም
4· ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት
5· ቢትወደድ አስፍሐ ወልደ ሚካኤል
6· ፊታውራሪ አበበ ገብሬ
7· ዶክተር ምናሴ ኃይሌ
8· ንቡረ ዕድ ዲሚጥሮስ ገብረ ማርያም
9· ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ
10· ንቡረ ዕድ ገብረ ሥላሴ ፀሐዬ
11· አቶ በለጠ ገብረ ጻዲቅ
12· አቶ ማለህ ሒኒት
13· አቶ በላይ አባይ
14· አቶ ጌታቸው በቀለ
15· አቶ መክብብ ዳምጤ
16· ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ወልደ ሥላሴ
17· አቶ እሸቴ መኰንን
18· አቶ ሀብተ ሥላሴ ታፈሰ
19· አቶ ታደሰ ሞገሴ
20· አቶ ሜንያለዉ ተሾመ
21· ደጃዝማች ዝናህብዙ መሳይ
22· ሜ/ጄኔራል ግርማ ሙላት
23· ሜ/ጄኔራል ጽጌ ገዝሙ
24· ሜ/ጄኔራል አበበ ወልደ ሥላሴ
25· ሜ/ጄኔራል ቀልቤሳ ቤካ
26· አቶ መርዕድ መንገሻ
27· አቶ ሀብቱ እሸቴ
28· አቶ በትሩ አድማሴ

29· ፊታውራሪ ከበደ ደስታ
30· አቶ መኩሪያ ወርቁ
31· ብ/ጄኔራል ሻውል ዘለቀ
32· ብ/ጄኔራል ሴንጫ መለሰ
33· ኩሎኔል ከበደ እሸቴ
34· አቶ አባተ መንግሥቴ
35· አቶ እምደ ሥላሴ ጀምበሬ
36· ጃን ጥራር ሙሉጌታ ገብረ እግዚአብሔር
37· ደጃዝማች አያሌው መንገሻ
38· ደጃዝማች ታደሰ አየለ
39· አቶ ተስፋዬ ታደሰ
40· አቶ ተፈራ ሻውል
41· ኩሎኔል ፀጋዬ መሸሻ
42· ኩሎኔል አሰፋ እሸቴ
43· ኩሎኔል ታደሰ ተሊላ
44· ኩሎኔል ወልደ ሥላሴ ካሣ
45· ኩሎኔል መሸሻ ወልደ ጻዲቅ
46· ኩሎኔል ዋቄ በቀለ
47· ኩሎኔል እንግዳ ጥላሁን
48· ኩሎኔል ማሩ ጋረድ
49· ኩሎኔል ኃይሉ ደገፈ
50· ዶክተር አያሌው አሳዬ
51· ዶክተር እሸቱ ጮሌ
52· አቶ ሳሙኤል ዓለማየሁ
53· ሌ/ኩሎኔል አደላ ቅጣው
54· ሌ/ኩሎኔል ተስፋዬ መንገሻ
55· ሌ/ኩሎኔል እምሩ ወንዴ
56· ሻለቃ ለሚሳ ሔይ
57· ሻለቃ ከፈላ ኃይለ ሚካኤል
58· ሻለቃ አሰፋ ጦይ
59· ሻለቃ ከፍያለው አድገህ
60· ፊታውራሪ ኃይሉ ሺበሺ

4/ በሐምሌ 1971 ዓ.ም ከእስር ቤት ተወስደው በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉ እስረኞች ዝርዝር

1/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ
2/ ጸሐፌ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ኪዳነ ወልድ
3/ አቶ ሠይፉ ማኅተመ ሥላሴ
4/ ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም
5/ አቶ ዮሐንስ ኪዳነ ማርያም
6/ ደጃዝማች ሐረጉት አባይ
7/ አቶ አሰፋ ድፋዬ
8/ አቶ አበበ ከበደ
9/ ብ/ጄኔራል ኅሙኤል በየነ

5/ በታላቁ ቤተ መንግሥት በሦስት ክፍል ለጥቂት ጊዜ ቆይተው የተገደሉ

1/ ደጃዝማች ይልማ በቪ
2/ ብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ *
3/ ሌ/ኩሎኔል ኃይሉ ረጋሳ *
4/ ወይዘሮ ዳሮ ነጋሽ
5/ አቶ ግርማ ጭብሳ
6/ የመቶ አለቃ ታምራት ወልደ ማርያም
7/ ወጣት የዓይን እሸት ተፈሪ
8/ ስማቸው ያልታወቀ ከብ/ጄኔራል ታደሰ ብሩ ጋር የተያዙ አምስት ሰዎች
9/ ስማቸው ያልታወቀ ሁለት መምህራን
10 ስማቸው ያልታወቀ አምስት*** ተማሪዎች

* ተፈረደባቸው ተብሎ የተገደሉ
** በዘብ ሰንተርያ ያደሩ
*** እንዱ ከሁለቱ መምህራን ጋር የመጣ

6/ በእስራት ላይ እያሉ በሕመም የሞቱ

1/ ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ *
2/ አቶ ይልማ ዴሬሳ **
3/ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል **
4/ ፊታውራሪ አላሚን እንድሪስ *
5/ ብ/ ጄኔራል ጌታቸው ሀብተ ወልድ * *

* በእስር ቤቱ ውስጥ የሞቱ ።
** በእስር ቤት በሕመም ብዙ ከተሰቃዩ በኋላ ወደ ሆስፒታል ተወስደው በሕክምና ላይ እንዳሉ የሞቱ ።

7/ ከታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት ወደ ሌላ እስር ቤት የተዛወሩ እስረኞች ዝርዝር

ሀ/ ወደ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት

1/ ልዑል ወሰን ሰገድ መኩንን
2/ ልዑል ሚካኤል መኩንን
3/ ልዑል በእደ ማርያም መኩንን
4/ አቶ ሙሉጌታ አሥራት
5/ ወጣት ዘውዱ አሥራት
6/ ወጣት የወንድወሰን አሥራት
7/ አቶ አሰፋ በሱፈቃድ *
8 አቶ አስፋው መኩንን
*9 አቶ ለገሠ ገብረ ሐና
* 10/ አቶ አባተ ተፈራ
* 11/ አቶ ያረጋል ደምስ
*12 ኦቶ ተድላ ፋንታዬ

እነርሱ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ 5 ዓመት ተፈረደባቸው ተብሎ ።

ለ/ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር

1/ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ
2/ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ
* 3/ ብ/ጄኔራል መስፍን አምባዬ
* 4/ ሻለቃ ንጉሤ ረታ
* 5/ ሻምበል ጌታቸው መንግሥቱ

* በራሳቸው ጥያቄ የተዛወሩ

61· አቶ መድኃኔ ዮሴፍ
62· አቶ ሠይፉ የተሻ ወርቅ
63· አቶ ሲሜንሶ ዴንጋ
64· አቶ ዘውዴ በዳዳ
65· ሻምበል ፍቅሬ መኰንን
66· ሻምበል አጥናፉ መኰንን
67· ቀኛዝማች ገብረ ክርስቶስ መኰንን
68· አቶ አሰፋ ወልደ ጊዮርጊስ
69· አቶ ውድነህ ታደሰ
70· አቶ ደበበ አጕናፍር
71· አቶ ጌታቸው ሀብተ ሥላሴ
72· አቶ ታደሰ ወልደ ኪዳን
73· አቶ ገብረ ጻዲቅ ኃይለ ማርያም
74· አቶ ገመቹ ወልደ ሚካኤል
75· አቶ ተሾመ ገብረ ወልድ
76· አቶ ታደሰ ሜጫ
77· ግራዝማች ደባሱ በየነ
78· ም መቶ አለቃ መለሰ ንጋቱ
79· ም/መቶ አለቃ ኃይሉ አጥናፌ
80· አቶ ጥላሁን ይትባረክ
81· አቶ ሽፈራው ቱፋ
82· አቶ መለሰ መኰንን
83· ሻምበል ባሻ መዝሙር ይመኑ
84· ወታደር ኃይሉ እሸቴ
85· አንድ የሳምሶን ዳቦ ቤት ሠራተኛ የሆነ ወጣት

፱· በመስከረም 1 ቀን 1975 ዓ·ም
ከታላቁ ቤተ መንግሥት
በአንድ ላይ የተፈቱ እስረኞች ዝርዝር

1· ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት
2· አቶ ምናሴ ለማ
3· አቶ ግሞ ታደሰ
4· አቶ ከተማ ይፍሩ
5· አቶ ታደሰ ያዕቆብ
6· አቶ ከተማ አበበ
7· ዶክተር ሥዩም ሐረጉት
8· ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ
9· ደጃዝማች ተስፋ ዮሐንስ ዘረሔ
10· አቶ አሐዱ ሳቡሬ
11· አቶ አብተው ገብረ ኢየሱስ
12· አ·· አበራ ጀምበሬ (አምሐ ገብርኤል)
13· አቶ ፈንታዬ ወልደ ዮሐንስ
14· አቶ ተሾመ ገብረ ማርያም
15· ለቃ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ
16· ብ/ጄኔራል መኰንን ደነቀ
17· ማ.ጄኔራል አበራ ወልደ ማርያም
18· ኔ/ጄኔራል ታደሰ መልኬ
19· አቶ አሰፋ ደምሴ
20· አቶ ጕርፋ ገብረ መድህን
21· አቶ ኃይሉ ሰብስቤ
22· አቶ ንጉሤ ሀብተ ወልድ
23· አቶ አሸናፊ ሽፈራው
24· አቶ ወርቁ መካሻ
25· የመቶ አለቃ ሚካኤል አመዴ
26· አቶ አብርሃም ወርቅነህ
27· አቶ አባሻውል ወልደ ማርያም
28· አቶ አስናቀ ጌታቸው

29· አቶ አክሊሉ ቤተ ማርያም
30· አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ
31· ብ/ጄኔራል ግርማ ፈለቀ
32· ብ/ጄኔራል ታፈሰ አበበ
33· ብ/ጄኔራል ግርማ መንግሥቱ
34· ብ/ጄኔራል ሙላቱ ታምሩ
35· ብ/ጄኔራል ዳንኤል መንግሥቱ
36· ብ/ጄኔራል ሉሉ እንግሪዳ
37· ፊታውራሪ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋርያት
38· ፊታውራሪ ማሞ በሺ
39· ቀኛዝማች ኃይሉ መሳይ
40· ዋግሹም ጌታሁን አድማሱ
41· አቶ አበበ ወንድሜነህ
42· ፥ኛዝማች አመኑ ገብረ ሐና
43· አቶ ሠይፈ ሥላሴ ሊበን
44· ኩሎኔል እንጋጋው ኃይሌ
45· ኩሎኔል ይገዙ ዘለቀ
46· ኩሎኔል ማንያዘዋል ዳኘ
47· ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ
48· ሻለቃ ከበደ ደሳለኝ
48· ሻለቃ አሰፋ በቀለ
50· ሻለቃ ተፈራ ተክለ አብ
51· ባላምባራስ ጀቤላ ኤጀታ
52· ቀኛዝማች ጉልላት ወልደ ዮሐንስ
53· አቶ አሰፋ ደስታ
54· ባላምባራስ ዘርፉ ዳምጤ
55· ሻምበል መንግሥተ አብ ባሕሩ

የደራሲው ሌሎች ሥራዎች

ሀ) የታተሙ

1. ስለጋብቻችሁ (1948)
2. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጐ አድራጎት ድርጅት መመሥረት (1952)
3. ኢትዮጵያ ሀገረ ተስፋ (1953)
4. አባኮስትር (1983)

ለ) ለህትመት የተዘጋጁ

1. ብቸኛው ሰው
2. አባገስጥ
3. ሕይወት
4. An Introduction to Ethiopian Law:
   Sources of Law and the Administration of Justice
   (1434 - 1974)

ሐ ትርጉም

የ1928 ዓ.ም. የማዕከለ በሐውርት (ኢንተርናሽናል) ምርምር፡
ኢጣልያና ኢትዮጵያ

በፕሮፌሰር አርኖልድ ቶይንቢ.
የተጻፈ ታሪክ

መ <u>ትያትር</u> (ወደፊት የሚታይ)

በላይ ዘለቀ - አባኮስትር

ታሪካዊ ድራማ

ዋጋ6.50ብር